# ከመጋቢት እስከ መስከረም



መስከረም ፳፻፲፬ ዓ.ም
ቅጽ 4 VOL 4

የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አህመድ(ዶ/ር) ከመጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ መስከረም 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

# ከመጋቢት እስከ መስከረም

የኢ.ፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ ከመጋቢት 2014 ዓ.ም. እስከ መስከረም 2015 ዓ.ም. ያደረጓቸው ንግግሮችና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ቅንብር፣ አርትዖትና ዝግጅት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት

**የዚህ መጽሐፍ ገቢ ለበጎ
አድራጎት የሚውል ነው።**

ISBN 978-99944-3-777-1
Copyright©2022 FDRE Office of the Prime Minister
ኅዳር ፳፻፲፭ ዓ.ም. ታተመ

# ማውጫ


## ቀዳሚ ሀሳብ ! i

## ክፍል አንድ – የአማርኛ ንግግሮች

1. አየር መንገዳችን - የመላው ኢትዮጵያዊያን የኩራት ምንጭ 1
2. ስኬታማ ዝናብ የማዝነብ ሙከራ 6
3. ምስጋና ለኢትዮጵያዊያን የጥበብ ባለሙያዎች 14
4. የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነትአስተዳደር(ኢመደአ) - የታላቅ ራዕይ ውጤት 21
5. ለኢትዮጵያ ዐርበኞች ቀን እንኳን በሰላም አደረሳችሁ! 30
6. የሞጆ ባቱ መንገድ አገራዊ ትስስርን ለማጠናከር 33
7. ለኢትዮጵያ አሸናፊነት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ 40
8. እንኳን ለ1442ኛው ዒድ አል ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ! 54
9. የሰመራ ኢንዱስትሪ ፓርክ ፈር ቀዳጅነት የተንጸባረቀበት ሥራ 58
10. የኢትዮጵያን ክብር እና ዝናዋን የምናጎናጽፍበት - ሳምንት 62
11. የአማራ ልማት ማህበር ወቅት የተደረገ ንግግር 64
12. ኢትዮጵያን እናልብስ! 67
13. ኢትዮጵያን የማልበስ የአርጓዴ አሻራ መርሃ ግብር - በደብረ ማርቆስ 76
14. መሃል አርማጭሆ ጀግናን አድናቂ 79
15. ጉራጌ የህብረት ተምሳሌት 83
16. አሻራ መጽሐፍ የ“አሻራ ማንጸሪያ 94
17. መስቀል አደባባይ የድንቅ ሥራ ማሳያ 96
18. የኢትዮጵያ አሸናፊነት መሰረት! 102
19. በክረምት የአቅመ ደካሞችን ቤት የማደስ ተግባር 106
20. የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ - ለአፍሪካውያን 110
21. የትግራይ ክልል ወቅታዊ ሁኔታ 114
22. የሲቪክ ማኅበራት ደርጅቶች ምክር ቤት የምስጋና ምሽት 121
23. በምርጫው ውጤት እንኳን ደስ አላችሁ! 124
24. ጁንታው የኢትዮጵያ ህልውና ቀንደኛ ጠላት 131
25. ዒድ ሙባረክ! 133
26. የውሸት ፀሐይ ሲጠልቅ የሤረኞች ወጥመድ ይበጠሳል! 136
27. የአረንጓዴ አሻራ የስኬት ጉዞ ማሳያ 141

28. አዲስ ዓመትን በማይፀብሪ 144
29. የሤረኞች ምንቸት ወጥቶ፣ የኢትዮጵያዊነት ምንቸት እየገባ ነው 147
30. የኢሬቻ አስተምህሮት - በዕርቅ፣ በይቅርታና በሰላም መሻገር 150

## Kutaa Lama – Haasaawwan Afaan Oromoo

31. Jimma 156

32. የእሬቻ መልእክት Irreechi Irree dha! 168

## Part Three - English Speeches

33. An Open Letter to President Joseph R. Biden Jr. 176
34. Ethio-Telecom Licensing Speech 182

## ኣርባዕተ ክፍሊ - መግለጺ ትግርኛ

35. ጁንታ ፀረ-ህዝቢ ትግራይ ምኧኑ ብዕሊ እናንዳዕደዐ ይርከብ። 188

# ቀዳሚ ሀሳብ !

የአገር መሪዎች በታላላቅ አገራዊ ጉዳዮችና በልዩ ልዩ መረሃ ግብሮች ላይ ተገኝተው የሚያደርጉት ንግግርና የሚያስተላልፉት መልዕክት ፋይዳው ከፍተኛ ነው። አገራዊ አቅጣጫን ያመለክታል፣ የህዝብ ንቅናቄን ይፈጥራል፤ ባለሙያ ያተጋል፤ ወጣቶች ተስፋ እንዲሰንቁ ያደርጋል።።

መሪዎች በልዩ ልዩ መርሃ ግብር ላይ የሚያስተላልፉት ጠንካራ ሀሳብ የዝግጅቱን መሰረታዊ ጉዳይ ከመዳሰስ ባሻገር በአገር ደረጃ የሚጨምረውን እሴት አጉልቶ ማሳየት ይችላል። መዳረሻውን ያመላክታል። ከዚህም ባሻገር ለታሪክ ተመራማሪዎችና መጪው ትውልድ “ትናንት ምን ተብሏል?” ብሎ ለሚያነሳው ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚያስችል ሰነድ ለማዘጋጀት ያስችላል።

በመሪዎች የሚተላለፉት ንግግሮችና መልዕክቶች አገራቸው ከዓመታት በኋላ ሊኖራት የሚችለውን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚያመላክቱበት የተግባቦት መሳሪያዎች ናቸው። የመሪዎች ንግግሮች ህብረተሰቡን የማንቃትና ለልማት የማነሳሳት ትልቅ አቅም አላቸው። በአገር ውስጥ የሚካሄዱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን በመዳሰስ አንድምታቸውን ይገልጹባቸዋል፤ ይተነትኑባቸዋል። ከጎረቤትም ሆነ ከሌሎች አገሮች ጋር የሚኖር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የሚመራበትን መርህ ለዜጎች ያመላክቱበታል። በዚህ ምክንያት የመሪዎች ንግግርና መልዕክት በእጅጉ ተፈላጊ ነው። በአንድ ተሰናድቶ የመቅረቡ አስፈላጊነትም የጎላ የሚሆነውም ለዚህ ነው።

ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዶክተር ዐብይ አህመድ በልዩ ልዩ ቦታዎች በተካሄዱ መርሃግብሮች ላይ ተገኝተው ያደረጓቸው ንግግሮች፣ በህዝብ በዓላትና አገራዊ ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መልዕክቶችና ከተለያዩ አካላት ጋር በተካሄዱ ውይይቶች ላይ ያስተላለፏዋቸው ሀሳቦችን “ከመጋቢት እስከ መጋቢት” በሚል ርዕስ በመጽሀፍ ምልክ በመሰነድ አራተኛ ዕትም ላይ ደርሰናል።

አራተኛው ዕትም “የኢትዮጵያ አሸናፊነት” የተበሰረበትን ምርጫ ሂደት አስመልክቶ የተደረጉ ውይይቶች ላይ ያስቀመጧቸው አቅጣጫዎች፣ “ኢትዮጵያን እናልብስ” በሚል በተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር፣ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን ለማስገንባት መሰረት ድንጋይ ሲቀመጥና የተጠናቀቁት ሲመረቁ ያደረጓቸው ንግግሮች፣ ያስተላለፏቸው መልዕክቶች ተካተዋል። በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያነሷቸው አንኳር ነጥቦች፣ የምርጫው ውጤትንና የትግራይ ክልል ወቅታዊ ሁኔታን የሚዳስሱ ንግግሮቻቸው በመጽሀፉ ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል። የኢትዮጵያዊያን ሃይማኖት በዓላትን አስመልክተው ለአማኞቹ “እንኳን አደረሳችሁ” በማለት ያስተላለፉቸው መልዕክቶች የመጽሀፉ አንድ ማዕዘን ናቸው።

በዚህ መጽሀፍ ላይ የቀረቡት ንግግሮች የት ተላለፉ? እነማን ነበሩ? መቼ ተላለፉ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በየመሃሉ በሚያቀርቧቸው ምስጋናዎች፣ አጽንኦት በሚሰጧቸው ጉዳዮች፣ ትኩረት በሚደረግባቸው ነጥቦች አማካኝነት በግልጽ ተላልፈዋል።

**መልካም ንባብ!**

**ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት**



# ከመጋቢት እስከ መስከረም

ንግግሮች ፡ አማርኛ

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# አየር መንገዳችን - የመላው ኢትዮጵያዊያን የኩራት ምንጭ

ዛሬ እዚህ የተገኘነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አስፋፍቶ በአዲስ መልክ የገነባውን ተርሚናል ለማየት ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለአገራችን ኩራት ተብለው ከሚጠሩት ኩባንያዎች መካከል የመጀመሪያውን ስፍራ ይይዛል። በበርካታ መመዘኛዎች በአፍሪካ የተሻለ ስም ያለውና በሥራዎቹ ውጤት ያስመዘገበ እድሜ ጠገብ ተቋም ነው። ይህ ተቋም ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ እንዳይፈርስና ወደ ኋላ እንዳይመለስ ከፍተኛ ድጋፍ ያስፈልገዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ አራት ታላላቅ ሥራዎችን ያከናውናል። አንደኛው፤ የካርጎ አገልግሎት ሲሆን ይህም እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ወደብ አልባ አገሮች በጣም ትልቅ ትርጉም ያለው ተግባር ነው። ብዙውን ጊዜ የተለያዩ እቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትና ለማስወጣት ቅድሚያ ለምንሰጣቸው ነገሮች እንጠቀምበታለን። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከካርጎ አገልግሎት አኳያ አንድ ሚሊዮን ቶን ሊያመላልስ ይችላል። በጣም ትልቅ አቅም ነው። በአፍሪካ ደረጃ ተመሳሳይ አቅም ያላቸው አየር መንገዶች ብዙም አይደሉም። ለእኛ ከአበባ፣ ከስጋ ምርትና ወደፊትም ሌሎች ምርቶችን ወደ ውጭ ገበያ ከመላክ አኳያ የካርጎ አገልግሎት አቅማችን ማደጉ በጣም ጥሩ ነው። በቀላሉ የሚበላሹ ዕቃዎችንም በፍጥነት ለማመላለስ እንጠቀምበታለን።

በካርጎ አገልግሎት የማቀዝቀዣ አቅሙ ከፍተኛ ነው። ይህም እቃዎች በቀላሉ እንዳይበላሹ ለማድረግ ያስችላል። በተለይ በመላው ዓለም የኮሮና ክትባትን ከማሰራጨት አኳያ የታየው እንቅስቃሴ በጣም አስደማሚ ነው። ለዚህም በቂ ዝግጅት አድርጓል። ዘመናዊ የሚባሉ መሳሪያዎችን ታጥቋል። እጅግ የሚያኮራ ተግባር ነው።

ሁለተኛው፤ የጥገና አቅም ነው። አየር መንገዱ የራሱን አውሮፕላኖች ሙሉ በሙሉ የመጠገን አቅም አለው። ከሌሎች አገሮችም ተረክቦ ይጠግናል። አየር መንገዱ የሚጠግናቸውን

አውሮፕላኖችን አይተናል፤ ከጥገና አኳያ በቂ አቅም አለን። ይሄ ለወደፊቱ የመገጣጠምና የመፍጠር አቅማችንን ለማሳደግም ጠንካራ መሰረት ይሆናል።

ሶስተኛው፤ የአካዳሚው አቅም ነው። አካዳሚው በሆስተስነት፣ በቴክኒሺያንነትና በአውሮፕላን አብራሪነት ከአራት ሺ በላይ ሰዎችን የማሰልጠን አቅም አለው። ከበርካታ የአፍሪካ አገሮች አየር መንገዶች መጥተው ይሰለጥናሉ። የተቋሙ የማሰልጠን አቅም የተሟላ መሆኑን ተመልክተናል።

አራተኛውና ዋነኛው አየር መንገዱ ራሱ ነው። ይህ አየር መንገድ ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ አስር ሚሊዮን ያህል ተሳፋሪዎች የማስተናገድ አቅም ነበረው። አሁን ሃያ አራት ሚሊዮን ገደማ ማስተናገድ ይችላል። በዓመት ሃያ አራት ሚሊዮን ተሳፋሪ ማስተናገድ የሚችል አየር መንገድ ያላቸው ጥቂት ናቸው። ምን አልባት ደቡብ አፍሪካ ወይም ግብጽ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ሃያ አራት ሚሊዮን ተሳፋሪዎች ማስተናገድ ብቻ ሳይሆን ከጥራት አኳያ ኤምሬትስ ወይም የኳታር አየር መንገድ ካልሆኑ በስተቀረ ሊወዳደረው የሚችል አገልግሎት የሚሰጥ ያለ አይመስለኝም። በተለይ ላውንጁን እንዳያችሁት በጣም ሰፊ ነው። በአንድ ጊዜ ሶስት ሺ ሰው ማስተናገድ ይችላል። እጅግ በጣም የሚያምር የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ቅርጽ፣ ባህል የሚያሳይ ውብ ሆኖ የተሰራ ነው። የዚህ ዓይነት አገልግሎት በበርካታ ሆቴሎች ውስጥ እንኳን አይገኝም።

አየር መንገዱ ሃያ አራት ሚሊዮን ተሳፋሪዎች የማስተናገድ አቅም ብቻ ሳይሆን ከ132 በላይ አውሮፕላኖች አሉት። በዓለም ላይ ኮረና በተከሰተበት ወቅት ድጋፍ ሳይደረግለት የጀመረውን ሥራ ያስቀጠለ ተቋም ነው። በተለይ ሙሉ በሙሉ ሠራተኛ ሳያባርር፣ ደመወዝ ሳይቀንስ ሥራውን ያስቀጠለ ብቸኛው አየር መንገድ ነው።

አየር መንገዱ በዓመት አራት ቢሊዮን ዶላር ጥቅል ትርፍ የሚያገኝ፤ በዓለም ተወዳዳሪ፣ እጅግ በመልካም ሥነ ምግባራቸው የሚታወቁ፣ በጥራት የሚሰሩና አገራቸውን የሚወዱ ከአስራ ሰባት ሺ በላይ ቋሚ ሠራተኞች አሉት። በአሁኑ ወቅት ኩባንያው እየፈጠረ ያለው አቅም ለአገራችን ታላቅ ኩራት ነው። ማንኛውም ሰው ወደ አገራችን ሲመጣ በቅድሚያ

የሚያየው አየር መንገዳችንን ነው።

አየር መንገዱ የእኛን ማንነት ለማሳየት በሚችል መልኩ ሳቢና ንጹህ ከሆነ፣ በየመንገዱ መትከል የጀመርናቸው ዛፎች ካሉ፣ አበባ ኖሮ በጸዳ መንገድ ላይ ከተጓዝን አገራችን ተስፋ እንዳላት ያመላክታል። ሆቴሎቻችን እንግዳ ከተቀበሉ፣ ካስተናገዱ፣ ንጽህና ካላቸው የኢትዮጵያ ብልጽግና እውን እንደሚሆን፣ አጀማመራችን ተስፋ እንዳለው ያሳያል። ይሄ ተጠናክሮ ከቀጠለ ኢትዮጵያን እንደምናልመው፣ እንደምናስበውና እንደምንሻው የተሻለች አገር ለማድረግ ተስፋ እንዳለን ያረጋግጣል።

እንግዲህ ጋዜጠኞች ዛሬ አየር መንገዱን አይታችኋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ ወደ መስቀል አደባባይ በመሄድ እዚያ የሚሠራውን ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያ (Parking) ተመልከቱ። ከአንድ ሺ አምስት መቶ በላይ ተሽከርካሪዎች ይይዛል። ዋናው ጉዳይ እርሱ አይደለም፤ ኢትዮጵያዊያን ብዙ አገሮች ስንሄድ የምንመኘውን እጅግ ያማረ ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መገንባቱ ነው። አውቶሜትድ የሆነ፣ ካሜራ ያለው፣ ምድሩ ኢፖክሲ (epoxy) የተቀባ፣ እጅግ ንጹህ የሆነ፣ አሜሪካ ውስጥም አልፎ አልፎ ብቻ የሚታይ ብዙ አካባቢ የማይገኝ በጣም አስደማሚ ነው። ከተሽከርካሪ ማቆሚያው ወጥታችሁ ዙሪያውን ስትመለከቱት አንድ ሚሊዮን ሰው በአንዴ መያዝና ማስተናገድ የሚችል አደባባይ አለ። ከአደባባዩ ትይዩ ቸርችል ጎዳና አለ። የጎዳናው ግራ እና ቀኝ እየሰፋ፣ ዛፍ እየተተከለ ይገኛል። ይህም ዋና ጎዳና በመሆን ሰዎች በዝግታ የሚንሸራሸሩበት ይሆናል።

ዋናውን መንገድ ጨርሳችሁ የአዲስ አበባ ከንቲባ ጽህፈት ቤት ስትገቡ በጣም በሚያምር ሁኔታ እየተሰራ መሆኑን ታያላችሁ። አሁን እየተገነባ ያለበት ደረጃው ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት እጅጉን የተሻለ ነው። ከእርሱ ፊት ለፊት ደግሞ አድዋ ፓርክ አለ፤ ከአድዋ በአራት ኪሎ መንገድ ይዛችሁ ከሄዳችሁ "ሸገር ፊዝ ዋን" ሥራ እና ቤተ መጻሕፍቱ ይገኛሉ። የሸገርና የአንድነት ፓርኮች የተሽከርካሪ ማቆሚያ አላቸው። ከእንጦጦ ፓርክ የሚመጣውን ወንዝ ካገናኘን አዲስ አበባ ላይ በጣም የሚሸጥ፣ የሚታይ፣ ተነግሮ የማይጠገብ ነገር ይኖራል። አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ የማስመሰል ተግባር በስኬት እየሄደ መሆኑን ያሳያል። የኢትዮጵያ ተቋማት እየተለወጡ መሆኑን ያመላክታል።

ይሄ ብቻ አይደለም። በቅርቡ የሚመረቁትን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ ወይም ኢንሳ) እና የደህንነት ዋና መሥሪያ ቤቶችን ከተመለከታችሁ ተቋማት እየተለወጡ መሆኑን ታስተውላላችሁ። በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት የሚመረቀው የመከላከያ ዋና መሥሪያ ቤት በዓለም ላይ እጅግ ግዙፍ፣ ውብ ከሆኑና ብዙ ነገር ካሟሉ ቦታዎች አንዱ ነው። ይህ ካለምንም ጥርጥር የኢትዮጵያን አቅም ከፍ ያደርጋል። ኢመደአ እንዲሁ እጅግ ዘመናዊ የሆነ ውስብስብ የዳታ ማይኒንግ አቅም ያለው፣ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች የሚስተናገዱበት ነው። የአገር መረጃን መጠበቅ፣ ቴክኖሎጂን ማሳደግ የሚያስችል፤ የተሟላ ነገር ያለው ነው። ሁሉንም ተቋማት ይሄንን መልክ እያስያዝን፣ እያሻሻልን፣ ጥራት ያለው ነገር እየሰራን፣ እያገናኘን፣ እያስተሳሰርን ትርፋማ እያደረግን ከሄድን ሌሎች አገሮች ላይ የምንመኛቸውን፣ የምንቆጭባቸውን ነገሮች ኢትዮጵያ ውስጥ የማየት እድል መኖሩን ያመለክታል።

ከእኛ የሚጠበቀው መትጋት ነው። በምኞት ብቻ የሚሆን ነገር የለም። ተግተን መሥራት ይኖርብናል። መመኘት ጥሩ ነገር ነው። ነገር ግን ተግተን ሠርተን ውጤት እያመጣን አገራችንን የመቀየር፣ ከልመና የማውጣት ተግባር ከሁላችን ይጠበቃል።

ዛሬ በአየር መንገድ ያየነው ሥራ ተስፋ እንዳለን፣ ልንወዳደር እንደምንችል አመላክቷል። ኢትዮጵያዊያን የሚያምር ነገር እንደምንሰራ፣ የሰውን ማድነቅ ብቻ ሳይሆን የሚደነቅ ነገር መስራት እንደምንችል አመላካች ነው። በዚህም እጅግ በጣም ደስ ብሎናል።

ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብና ከእናንተ የሚጠበቀው አየር መንገዱ ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከብሄር ነጻ የሆነ ንጹህ “የመላው ኢትዮጵያዊያን የኩራት ምንጭ” መሆኑን ተረድቶ ድጋፍ ማድረግ ነው። ሁላችንም ኩባንያውን እንደ ንግድ ተቋም ማየት ያስፈልገናል። የኩራት ምንጫችን መሆኑን በማስተዋል መደገፍ፣ ማገዝ ይጠበቅብናል። በሁሉም ጉዳይ ላይ ፖለቲካን ካስገባን ይበላሻል። ይሄንን ኩባንያ ሠርተውታል፤ እኛ አዘምነን፣ አሻሽለን፣ አልህቀን ለልጆቻችን ማስረከብ እንድንችል ልባችን የሰፋ፣ የኩባንያውን ጠቀሜታ የምንገነዘብና የምንደግፍ እንድንሆን “አደራ” እላለሁ። ይሄንኑ ሥራ ማስፋት፣ ማስቀጠል ይገባል።

ኢትዮጵያ ለማንም ማራኪና ሳቢ እንድትሆን አድካሚውን የብልጽግና ጉዞ በትክክለኛ መስመር ላይ (ትራክ) የጀመርን መሆኑን ያንጸባርቃል። ብልጽግና እንዲሁ በዋዛ አይመጣም፤ አድካሚ፣ አሰልቺ፣ አታካች ሥራ ይጠይቃል። ብልጽግና ዜጎች ተባብረው፣ ተደምረው ከሠሩ ሊያሳኩት የሚችሉት ጉዳይ ነው። ይሄንን ለማሳካት ሁላችንም በቁርጠኝነት እንድንተጋ አደራ እላለሁ።

እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል!

**አመሰግናለሁ!**

**መጋቢት 21፣ 2013 ዓ.ም**

# ስኬታማ ዝናብ የማዝነብ ሙከራ

በዓለም ላይ ባለፉት ሰላሳ እና አርባ ዓመታት ደመናን የማዝነብ ቴክኖሎጂ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ሲነገር ነበር። ላለፉት 15 ዓመታት ደግሞ የተሳካ ሙከራ ማድረግ ተችሏል። በአሁኑ ወቅት ከሃምሳ አገሮች በላይ ዳመናን የማዝነብ፣ የበረዶ ክምር በቀለለ መንገድ እንዲወርድና በእርሻ ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የማድረግ፣ ደመናን የማከማቸት መሰል ተግባራት ያከናውናሉ።

ሁላችሁም እንደምታስታውሱት የቻይና መንግሥት እ.ኤ.አ በ2008 የቤጂንግ ኦሎምፒክ መክፈቻ ሥነ ስርዓት ከመካሄዱ በፊት የነበረውን የደመና ክምችት በማዝነብ የዕለቱ መርሃ ግብር በዝናብ እንዳይታወክ አድርጓል። በዕለቱም ሁሉም ሰው በስታዲየም እንዲታደም የተሳካ ሙከራ ማድረጉ ይታወሳል። ከዚያ ውጪ በካናዳ፣ በሌሎች አገሮች የተሳካ ሙከራ ተደርጓል። የዚህ ፕሮጀክት ዋነኛ ዓላማና አስፈላጊነት እንደየአገሮቹ ፍላጎት እና ትልም የሚመሰረት ቢሆንም፤ ለኢትዮጵያ ግን እጅግ አስፈላጊ ልዩ ፕሮጀክት ነው።

እንደእኛ ግድብ ገንብተው ኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጩና የመስኖ እርሻን የሚያስፋፉ አገሮች ከምንም በላይ የዳመናን ክምችት ወደ ዝናብ ለመቀየር ይሠራሉ። እኛ በርካታ ግድቦችን ለኤሌክትሪክ ኃይልና ለመስኖ እየገነባን ብዙ ሀብት እያፈሰስን ስለሆነ ከዚህ ዓይነቱ ቴክኖሎጂ ከራቅን የተሳካ ሥራ ልናከናውን አንችልም።

ግድቦቻችን ሲጎድሉ ለመሙላት፣ መስኮቻችን ሲደርቁ በለምለም ለመሸፈን እጅግ አስፈላጊ የሆነ የእውቀት ዘርፍ መሆኑን ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል። ዳመናን ማዝነብ ከፈጣሪ ጋር የሚያጋጭ ያልተገባ ተግባር አድርገው የሚያስቡ ሰዎች አሉ። እኔ ልጠይቃችሁ የምፈልገው ነገር ዳመናን ማዝነብ ከፈጣሪ ጋር የሚያቀያይመን ከሆነ ለምን ተሽከርካሪ እንጠቀማለን? እያንዳንዳችን እንሄድበት፣ እንሮጥበት ዘንድ እግር ተሰጥቶን ሲያበቃ እግራችንን መጠቀም ትተን ተሽከርካሪ መጠቀማችን ከፈጣሪ ጋር ለምን አላጣላንም? የተሰጠን እግር እያለ

ተሽከርካሪ ለመጠቀም ለምን ተገደድን? ብለን መጠየቅ ያስፈልገናል። ውሃም ራሱ ቢሆን ህዳሴ ግድቡን ጨምሮ መገደብ ስህተት ይሆናል፤ ውሃ መንገዱን ጠብቆ እንዳይሄድ በየመሃሉ እያቆሙ፣ ከዋናው የተፈጥሮ መንገዱ እያወጡ ለእርሻ ማዋል፣ ለኤሌክትሪክ ኃይልነት ማዋል ከተፈጥሮ ጋር መጋጨት ነውን? ለመሬት ማዳበሪያ መጠቀም ከተፈጥሮ ጋር የሚያጋጭ ነውን? እያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን ቤት መስራትንም ጨምሮ ከተፈጥሮ ጋር የሚያጋጨን ነውን? ከሁሉ በላይ ግን ለምን ጥላ ትይዛላችሁ? ፀሃይ እኮ ተፈጥሯዊ ነው፤ የተፈቀደን ፀሃይ እንዳያቃጥለን እያልን ጥላ መያዝ ሊያጋጨን ነውን?

በመሰረቱ ተፈጥሮን ለሰው ልጅ ምቹ አድርጎ መጠቀም ከፈጣሪ ጋር አያጣላም። ፈጣሪ የእያንዳንዱን ሰው አእምሮ እንዲበለጽግ አድርጎ ፈጥሮታል። ለዚህም ነው በዘመናት መካከል የሰው ልጅ የአኗኗር ዘዬውን እያሻሻለ፣ እያሳደገ የመጣው። ዳመናን ማዝነብ ከፈጣሪ ጋር የሚያጋጨን ሳይሆን የተሰጠንን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ መጠቀም ነው። የተሰጠንን የተፈጥሮ ሃብት ከከርሰ ምድር ማዕድን ቆፍረን በማውጣት እንደምንጠቀመው፣ ውሃ እንደምንገድበው ማለትም ሁሉ ዳመናን በማዝነብ ለእርሻችን፣ ለግድቦቻችን ለምንተክላት ተክሎችና ለአረንጓዴ አሻራችን በጣም ጠቃሚ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከፈጣሪ ጋር የሚያጋጭ ነገር ተደርጎ መወሰድ የለበትም። የአእምሮ አብርሆት የተፈጠረው እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን መጠቀም እንድንችል ነው።

ፕሮጀክቱን በፋይናንስ ያገዙን የተባበሩት ዐረብ ኢሚሬትስ ወይንም ዱባይ ተብሎ የሚታወቀው የዛሬ ሃምሳ፣ ስድሳ ወይንም ሰባ ዓመት ነዳጅ ማውጣት ባልቻሉበት፣ የእውቀት ባለቤት ባልሆኑበት ወቅት በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ይኖሩ ነበሩ። ነገር ግን ከምድር በታች ያለን ሃብት አውቀው፣ አውጥተው መጠቀም ሲችሉ ግን ያንን በረሃ አገር ለም አድርገዋል። ከዚህም በላይ እንደኛ ያሉ አገሮችን ለማገዝ ተጠቅመውበታል። እውቀት ተፈጥሮን ከማገዝ ጋር እጅግ የተቆራኘ ነው። ከሰማይም፣ ከምድርም፣ ከምድር በታችም ያሉ ሃብቶችን መጠቀምና አገርን ማዘመን፣ ማሻሻል ከሁላችን የሚጠበቅ ነው።

ለአገራችን ሳተላይት ብናመጥቅ፣ ዝናብ ብናዘንብ፣ የግድቦችን ግንባታ ብናሳካ የሰላምና ወንድማማችነት ስሜት መጠበቅ እስካልቻልን ድረስ ሁሉም ከንቱ ይሆናል። መላው

የኢትዮጵያ ህዝብ፣ እዚህ ያላችሁ ወገኖችና በሩቅ ያሉ ኢትዮጵያዊያን እንድትገነዘቡ የምፈልገው ነገር "አትችሉም፣ ስለዝናብ፣ ስለግድብ አታስቡ፣ እናንተ በበሬ እያረሳችሁ የጎደላችሁን ስንዴ እኛ እየረዳናችሁ መኖር ብቻ ነው የተፈቀደላችሁ" የሚሉ ኃይሎችና ከውስጥ የተገዙ ሽፍቶች ኢትዮጵያዊያንን እርስ በእርስ ለማባላት ለመከፋፈል ቀን ከለሊት እየሰሩ ይገኛሉ። እነዚህን ተባባሪ ሽፍቶችና አሽባሪ ሃይሎች ጠርገን ስናጠፋ የዋናው የላኪውን ሃይል ፍላጎት የምንገነዘብበት ጊዜ ሩቅ አይደለም።

በአሁኑ ወቅት የአገር መከላከያና የፌዴራል ሠራዊት በስምንት ግንባሮች በሰሜን፣ በምዕራብ ተሰልፈው እየተፋለሙ ይገኛሉ። ኢትዮጵያዊያንን ሊያባሉ (ጸረ አርሶ አደር፣ ጸረ ንጹሃን ዜጎች የሆኑ) ከተነሱ ኃይሎች ጋር ከፍተኛ ፍልሚያ እያደረጉና መስዋዕትነት እየከፈሉ ናቸው። የኦሮሞ ወዳጅ፣ የአማራ ጠላት፣ የአማራ ወዳጅ የኦሮሞ ጠላት እየተደረገ የሚሳለው ኢትዮጵያዊያንን ለመከፋፈል ካልሆነ በስተቀረ የእያንዳንዱ አርሶ አደር ሞት የኢትዮጵያ ሞት ነው። የእያንዳንዱ የአርሶ አደር ጠላት የኦሮሞ፣ የአማራ ጠላት ነው።

በከተማ ውስጥ የምትኖሩ፣ ፌስቡክ ያላችሁ ጉዳዩን በቅርበት የማትገነዘቡ ሰዎች ትላልቅ አፋቸውን የከፈቱ ጅቦች፣ ትናንሽ አይጦች ልከው ካጫረሱን በኋላ ሊውጡን መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። እነርሱ በቀደዱልን ቦይ መፍሰስና መባላት ሳይሆን፤ እኛ አንድ ሆነን ህልማቸውን ማክሸፍ ይጠበቅብናል። ዋናው ነገር "አማራ እና ኦሮሞን፣ ጉራጌ እና ስልጤን ካባላን በኋላ" የሚሉትን ቅዠት በቀላሉ ማስቀም ይቻላል። ነገር ግን "ወደነበሩበት ድህነት እንዲመለሱ፣ከዚያ በላይ መመኘት እንዳይችሉ እናደርጋቸዋለን" ለሚሉ ኃይሎች ሳናውቅ ተባባሪ እንዳንሆን መጠንቀቅ ይገባል።

የመከላከያ ሠራዊታችንን በቅርበት በማገዝ፣ በመረጃ በመደገፍ ቅዠታቸውን ማስቀም ያስፈልጋል። እነዚህ እንደጀግና ከወታደርና ከፖሊስ ጋር የማይገጥሙ ናቸው። ለዚህም ነው ፖሊስና ወታደር እያንዳንዱን ተራራና መንደር ማሰስ ግድ የሆነበት፣ የሚታይ ጠላት ሳይሆን ተደብቀው፣ ተሸፍነውና ተመሳስለው የሚከፋፍሉን ኃይሎች መሆናቸውን መገንዘብ ተገቢ ነው። ይህ ደግሞ እኛ ከምንገነዘበው በተለየ እጅግ አድካሚና አታካች ወታደራዊ ግዳጅ የሚጠይቅ ነው።

ከጁንታው ጋር የነበረን የመጀመሪያው ወታደራዊ ግዳጅ የፈጀው ከፍተኛ ጊዜ ሦስት ሳምንት ነው። ወታደራዊ የደንብ ልብስ አለው፤ ቦታው ይታወቃል፤ በሁሉም ዓይነት ተኩሶች ይፋለማል። በሶስት ሳምንት ያስወገድነው ጁንታ ወደ ሽምቅ ገብቶ ከአርሶ አደር ጋር ተመሳስሎ መሹለክለክ ሲጀምር ግን በሶስት ወርም ልናጠፋው አልቻልንም። በግልጽ የሚታይን ጠላት መደምሰስና ተመሳስሎ የተደበቀን ጠላት ማጥፋት ተመሳሳይ አይደሉም። አስቸጋሪና አታካች ናቸው። ባለፉት ሶስት ቀናት እጅግ አታካች እርምጃዎች ወስውደን የህዝቦቻችንን ጠላቶች የማዳከም ሥራ ሠርተናል። እነዚህ እርምጃዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

ከተማ ውስጥ የምትከፋፈሉ ሰዎች ዓይኖቻችን ዝናብ ከማዝነብ፣ በምግብ ራሳችንን ከመቻል፣ ግድቦቻችንን ከመሙላት፣ ከድህነት እና ልመና ከመውጣት አታንሱ። ከተከፋፈልን የእነዚህ ኃይሎችን ፍላጎት በቀላሉ እናሳካላቸዋለን። እኛን በቀላል ገንዘብ ገዝተውን እንዳያባሉን መጠንቀቅ ይገባል። የራሳችን ህልሞችና ፍላጎቶች ተገንዝበን የእነርሱን በማክሸፍ የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ከዜጎች ይጠበቃል። ስለሆነም ይህን ተገንዝበን በትብብር፣ በስምምነት፣ በመደማመጥ መንፈስ አገራችንን ወደሚገባት ስፍራ ማድረስ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ካልተቀየረችና ካልበለጸገች አፍሪካ እንደማትቀየር መገንዘብ ተገቢ ነው። አገራችንን በመቀየር ከመለመን ወደ መርዳት የማሸጋገር ጉዞን ብዙዎች ሊያደናቅፉ ቢጥሩም ሊቆም እንደማይችል በተግባር ማሳየት ተገቢ ነው። ፈተናዎች ያሉብን፣ መስዋዕትነት የምንከፍል ብንሆንም የኢትዮጵያን ብልጽግናና የግዛት አንድነት የማረጋገጥ ጉዳይ በፍጹም የማይቀር ነገር መሆኑን መገንዘብ አለብን። ይቺን ታላቅ አገር እንደስሟ ታላቅ አድርጎ ከስንዴ እርዳታና ልመና ነጻ ለማውጣት መስዋዕት ለመሆን መዘጋጀት ይጠበቅብናል። በአህጉሪቷ ፈር ቀዳጅ ሆኖ መገኘትም ያስፈልጋል።

አገራችንን ከልመና ነጻ ለማውጣት መሬታችንን በኩታ ገጠም ማስተሳሰር፣ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት ግድ ይለናል። ይህ ቴክኖሎጂ በምግብ ራሳችንን ለመቻልና ሁሉም የኢትዮጵያ ጎጆዎች መብራት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል ነው። በተለይም የጠላቶቻችንን

ህልም የሚያጨነግፍ፣ የእኛን ብልጽግናን የሚያረጋግጥ በመሆኑ በረባው ባልረባው ሳንከፋፈልና የጠላትን ፍላጎት ሳናሳካ በአንድ መንፈስ ኢትዮጵያን ወደሚገባት ታላቅ ስፍራ ለመውሰድ በትብብር መስራት ይኖርብናል። ጠላቶቻችን በብዙ መንገድ "አይሳካም" ብለው እንዳሳካነው ሁሉ ሌሎች እቅዶቻችንን ባስቀመጥነው ትልም መሰረት ማሳካት ይጠበቅብናል። በቴክኖሎጂው፣ በግብርናው፣ በማዕድኑ፣ በቱሪዝሙ፣ እንደዚሁም በኢንዱስትሪው ትልሞቻችንን ከማሳካት በቀር ምንም ነገር እንደማይኖር አረጋግጥላችኋለሁ።

ይህ ስራ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተጠንስሶ የኢትዮጵያ ምሁራን በተለይም የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ኢመደአ እና ሌሎች ተቋማትን ሚትሮዎሎጂ በባለቤትነት ይዘው ላለፉት ስድስት እና ሰባት ወራት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። የተባበሩት ዐረብ ኢሚሬትስ በፋይናንስ፣ በእውቀት ከፍተኛ ድጋፍ አድርጓል። ለዚህም ጓደኛዬንና ወንድሜን ሼክ መሃመድ ቢን ዛይድን በከፍተኛ ደረጃ አመሰግናለሁ።

በዚህ ጉዳይ ላይ ከመንግሥት ውጪ በግል የተሳተፉ ወጣቶች አሉ፤ የነገዋ ኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ባለቤት የሆኑ ግለሰቦች ተሳትፎ አድርገዋል። ሁላችሁንም በኢትዮጵያ ህዝብ ስም አመሰግናለሁ።

ይሄ ጅምር ሥራ ነው፤ በጣም መስፋፋት አለበት። በብዙ መንገድ ከሰማይም ከምድርም ሙከራው ማደግ አለበት። የተሳካ ሙከራ ስላደረጋችሁ እንኳን ደስ አላችሁ። በሚቀጥሉት ወራት እስከ ክረምት ድረስ ሰፋፊ ሥራ በማከናወን ውጤቱን እያንዳንዱ ዜጋ እንዲገነዘበው ማድረግ ያስፈልጋል። አሁንም በተደመረ መንፈስ በጋራ እንድትሠሩ አደራ እላለሁ።

**እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ**
**እንኳን ደስ አላችሁ !**

**መጋቢት 23፣ 2013 ዓ.ም**






DANGER
GTRAILERS

# ምስጋና ለኢትዮጵያዊያን የጥበብ ባለሙያዎች

በአንድ ወቅት “ኢትዮጵያ ስትመሰረት ምሰሶ ያቀረቡ እነማን ናቸው?” የሚል ጥያቄ በአእምሮዬ ውስጥ እንዲነሳ የሚያደርግ አጋጣሚ ተፈጠረ። ጥያቄውን ለመመለስ ባደረኩት ጥረት እዚህ የተሰበሰባችሁና ያልመጣችሁ በሥነ ጥበብም ሆነ በሁሉም መስክ የምትሰሩ፣ የምታነቁ፣ የምታስተምሩ ሰዎች በእያንዳንዱ ዜጋ አእምሮ ውስጥ ኢትዮጵያን የሳላችሁ፣ የፈጠራችሁ “የኢትዮጵያ ምሰሶ እናንተ ናችሁ” የሚል እምነት በውስጤ አደረ።

ከአንድ ዓመት በፊት አንድ ምሽት ላይ መረጃ ደረሰኝ። መረጃው አንድ ኢትዮጵያ እንደ አገር እንዳትቆም፣ የኢትዮጵያዊያንን መዳከም፣ መባላት የምትፈልግ አገር “የኢትዮጵያ ድምጽ” በሚል ስም ፌስቡክ፣ ትዊተር . . . ከፍታ ዘመቻ መጀመሯን ያመላክታል። ዋና ዓላማው ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያዊያን፣ ኢትዮጵያዊያንን ደግሞ ከኢትዮጵያዊያን ጋር ማጣላት ነው። በርካታ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ኢትዮጵያዊያን ብቻ የሚጣሉ ይመስላቸዋል። አይደለም። ኢትዮጵያዊያንም ከኢትዮጵያ ጋር ይጣላሉ። ይሄንን መረጃ ሳገኝ በጣም ውስጤን ጨነቀው።

አንዳንዶቻችን ኢትዮጵያ ሲባል የሚነዝረን፣ የሚጨንቀን፣ እንባችን የሚቀድመን፤ ሌሎች ደግሞ በአነስተኛ ገንዘብ ኢትዮጵያን ለመሸጥ የሚዘጋጁት ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ በውስጤ ተመላለሰ። ውድ ውድ ነገሮች ሁሉ በገንዘብ ይሸጣሉ። ኢትዮጵያም እንደ ፈጣሪዋ በገንዘብ እንድትሸጥ ብዙ ውስጣቸው የተሰለበና የተሸጠ ሰዎች በመኖራቸው ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ለዚህች አገር ቅጥረኛ ሆኖ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያዊያን ጋር የሚያጣላ ሥራ ለመስራት እንዴት ለሽያጭ ራሱን ያዘጋጃል? የሚል አስጨናቂ ጥያቄ ተፈጠረብኝ። በዚሁ ሃሳብ ለሊቱን አጋመስኩ። ይህ በራሱ ኢትዮጵያ ማን ናት? ኢትዮጵያ ምንድን ናት? ኢትዮጵያ ለምን? ጥያቄ እንዲፈጠርብኝ አደረገ። ኢትዮጵያ ማን ናት? ለምንድን ነው ኢትዮጵያ ሲባል ብዙዎች ያለቀሱት? ብዙዎች ህይወታቸውን ለመስዋዕትነት ያዘጋጁት? ደማቸውን ያፈሰሱት? ለምንድን ነው አንዳንዶቹ ለትናንሽ ገንዘብ ኢትዮጵያን የሸጡት? ኢትዮጵያ ምንድን ናት?

አሁን እምነት፣ ክርስትና እና እስልምና የሚባል ነገር ባይኖር ኖሮ ኢትዮጵያ በግማሽ እንደምትቀንስ አታስቡም? እምነት ለካ አንዱ የኢትዮጵያዊነት ምሰሶ ነው። እምነትን እምነት ያደረገው እና ያጸናው ምንድን ነው? ኦርቶዶክስ ውስጥ ዜማ ባይኖር፣ በሙስሊም እምነት ሌላው ቀርቶ አዛን ሲወጣ ሃሳቡን ማወቅ ብቻ ሳይሆን የተሻለ ድምጽ ያለው ሰው ካልሆነ ጥሪ ማድረግ አይችልም። ያን "አብረን እንስገድ" የሚለውን ጥሪ የሚያቀርቡ ሰዎች ያንኑ ሃሳብ በተሻለ ድምጽና ዜማ ማቅረብ የሚችሉ ሰዎች ናቸው። የሚያሰግዱም በስብከት አካባቢ ያሉም ሰዎች ዜማ ከሌለው ለአንድ እና ለሁለት ሰዓት ተቀምጠው ስብከት ለመስማት ይቸገራሉ። ከዜማ አኳያ በሁሉም እምነት ውስጥ የጥበብ ሚና እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል። ከሥነ ጽሑፍ አኳያም መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቅዱስ ቁርአን ባይጻፉ ኖሮ ለሁለት ሺህ ዓመታት ባለው እውቀት ልክ ማዝለቅ ይቻል ነበር ወይ? ለሁለት ሺህ ዓመት እንኳን ሳይጻፍ ተጽፎም በጣም ይበረዛል። ጽሑፍ፣ ዜማ፣ የተለያዩ የጥበብ ስራዎች ባይኖሩ እምነትን ለሁለት ሺህ ዓመታት ማዝለቅ አይቻልም። እምነት ደግሞ አንዱ ምሰሶ ነው።

በመሰረቱ የእያንዳንዱ አገር የአመጋገብ፣ የአዘፋፈን፣ የአነጋገር ባህሎች ጎልተው እንዲወጡ የሚያደርገው ጥበብ ነው። ይህን የሚያስተዋውቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩ የሚያደርገውም ጥበብ ነው። በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ያለ ባህል አንድ ምሰሶ ነው። ባህልን በማሸጋገር ደረጃ የጥበብ ሚና ከፍተኛ ነው። ጥበብ ሲባል ስዕሉ ሳይሆን አጠቃላይ ማለቴ ነው። በካርታ ላይ የምናውቃት ኢትዮጵያ መሬት ላይ የለችም። ኢትዮጵያ በእያንዳንዳችን አእምሮ ውስጥ ተስላ እንድትቀይ ማድረግ የቻለው አንዱ የጥበብ ሙያ ነው። እዚያው አካባቢ ከተወለዱት ውጪ ጢስ ዓባይ የሚባለውን ቦታ የሚያውቀው ኢትዮጵያዊ ምናልባት አንድ በመቶ ይሆናል። በስዕል ካልሆነ በስተቀር ሁላችንም ጢስ አባይን አናውቅም፤ ሁላችንም የሰሜን ተራራን አናውቅም፤ ሁላችንም ህዳሴ ግድብን አናውቅም። ዜጎች ኢትዮጵያ ስላላት ሃብት እንዲያውቁ የሚደረገው በስዕል፣ በዘፈን፣ በፎቶግራፍና በተንቀሳቃሽ ምስል ነው። በስዕሉም፣ በዜማውም፣ በሥነ ጽሑፉም፣ በተውኔቱም፣ በፊልሙም በሁሉም ቦታ የሚሠራው ሥራ ባይኖር ኖሮ ኢትዮጵያም፣ እምነቷም፣ ቋንቋዋም፣ ባህሏም አሁን ያለውን ቅርጽ ስለማይዝ በአድዋ ጦርነት ከተት ሊባል

አይችልም። ቋንቋ ከሌለ፣ አዝማሪ ከሌለ ሊነቃቃ አይችልም። ማሸነፍ የተባለው በጥይት ብቻ ሳይሆን ሲጠራ የሚሰማ፣ ቋንቋ ያለው፣ "በማርያም" ሲባል እምነት ያለው፣ በአዝማሪ ሲነቃቃ የሚደፍር ሰው በመኖሩ ነው።

ኢትዮጵያ ስትመሰረት ምሰሶ ያቀበሉት የዜማ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የስዕል፣ በአጠቃላይ የጥበብ ሰዎች ናቸው። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በቪዲዮ ዘርፍና በተውኔት የሚሰሩ ባለሙያዎች ይጠቀሳሉ። ለኢትዮጵያ ምሰሶ የሚሆነው በእያንዳንዱ ዜጋ አእምሮ ውስጥ ኢትዮጵያ ተስላ፣ ተቀርጻ ስትኖር ነው። ኢትዮጵያ በሥነ ሥርዓት ሳትቀረጽ ስትቀር ግን በረባው ባልረባው እርሷን ማድማት የሚሻ ትውልድ ይፈጠራል።

በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አእምሮ ውስጥ ኢትዮጵያን የሳሉት የጥበብ ሰዎች ናቸው። ለምሳሌ ከ1990ዎቹ በፊት በ1980ዎቹ አካባቢ የነበረውን ብንወስድ የነአረጋኸኝ፣ የነንዋይ፣ የነፀጋዬ፣ የነጸሃዬ ቡድን በእኔ ትውልድ አእምሮ ውስጥ ኢትዮጵያን በመሳል በኩል ሚናው በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ኢትዮጵያ የቆመችው የጥበብ ሙያ ተሰጥኦ ያላችሁ ግለሰቦች በሠራችሁት ሥራ ነው። እናንተ ብዙ ጊዜ ዜጎች ሲገደሉ፣ ሲሰደዱ፣ ሲጎሳቆሉ "ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር መጣ" ብላችሁ እንደምታስቡ አውቃለሁ። ላሳሰባችሁ የምፈልገው ነገር የእናንተ ሙያ ባይኖር ኢትዮጵያ መኖር አትችልም። እናንተም ብዙ ኢትዮጵያዊያንም እንዲገነዘቡ የምፈልገው በእናንተ ጊዜ በአእምሯችን የተቀረጸችው ኢትዮጵያ ብዙዎች ጥያቄ ሳይጠይቁ፣ ክፍያ ሳይሹ ራሳቸውን በመስጠታቸው ዘልቃለች።

ብዙዎቻችሁ የከተማ ልጆች ትመስሉኛላችሁ። በገጠር ያደግን ልጆች ተሸከርካሪ ስንሳፈር ተሸከርካሪው ወደፊት ይሄዳል፤ ዛፉም ህንጻውም ነገሩ ሁሉ ወደኋላ ይሄዳል፤ ይዞርብናል። አሁን እየዞረብን ያለው ተሽከርካሪው ሳይሆን ዛፉ እየተንቀሳቀሰብን ያለ ስለመሰለን እንጂ! ብታምኑም ባታምኑም ኢትዮጵያዊነት እና ኢትዮጵያ እንደገና እያበቡ ናቸው።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት እያበቡ ያሉት በእናንተ ዘመን በአእምሯችን ውስጥ ስለአገር፣

ስለባህል፣ ስለማንነት፣ ስለቋንቋ፣ ስለመተባበር በተውኔት፣ በዜማ፣ በጽሑፍ፣ በዘፈን ያስተማራችኋቸው ኢትዮጵያን ለማቆየት ከፍተኛ ሚና በመጫወታቸው ነው። ከእናንተ በኋላ አንድ ወደፊት የመጣ ደግሞ መሳደብ፣ አሉታዊ ኃይል ያለው ስሜት ማንጸባረቅ (negative energy) ይበልጥ በገበያ የሚያዋጣ በመሆኑ እና የነበረው ሥርዓትም ያን ስለሚፈቅድ በመሃል ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን ማጉላት አልተቻለም። በዚህ ምክንያት የአንድ ትውልድ ክፍተት ተፈጥሯል። አሁን በየቦታው የምናየው ችግር ቢያጋጥምም ወረድ ብላችሁ በቤኒሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በትግራይ፣ በደቡብ ኢትጵያ በሁሉም አካባቢ ብትሄዱ እድሜያቸው ከአስር ዓመት በታች የሆኑ ትውልዶች "ኢትዮጵያ" እያሉ ናቸው። በእናንተ ሥራ በእኔና በመሰሎቼ አእምሮ ውስጥ ኢትዮጵያን መሳል እንደቻላችሁት ሁሉ ጥበብ አክላችሁበት አሁንም ሥራችሁን ብታከናውኑ ኢትዮጵያን የሚረከቡ ሰዎች ልኳን፣ ክብሯን፣ ምንነቷንና አስፈላጊነቷን አውቀው እንዲያድጉ ያደርጋል።

ኢትዮጵያ ስትመሰረት ምሰሶ ማቀበል ብቻ ሳይሆን በግንባታ ሂደት ውስጥ የሚያፈሱ አልፎ አልፎም ብርድ፣ ነፋስ የሚያስገቡ የተቀደዱ ቦታዎች ለመጠገን የጥበብን ሚና መልሶ ማነቃቃትና መቀስቀስ ይገባል። ዛሬ እንድንገናኝ የሆነው ይሄንን ተግባር የፈጸሙ ሰዎችን ማክበር ስለሚያስፈልግ ነው። እናንተም ይሄንን ሃሳብ ተጋርታችሁ ኢትዮጵያን በመሰብሰብ ውስጥ ያላችሁ ሚና ትልቅ መሆኑን እንድትረዱት ነው። የእናንተን ህብረትና አንድነት በጨለማ ውስጥ ተስፋንና የብርሃን ጭላንጭልን በማሳየት ኢትዮጵያ እንድትቀጥልና ከእናንተ በኋላ ያለው ትውልድም ትምህርት ወስዶ እንዲሰራ ለማድረግ ስለሚያስፈልግ ጭምር ነው።

አርሶ አደር እጅግ አስቸጋሪ በሆነ አየር ፀባይ ውስጥ በሐምሌ እና ነሃሴ ወጥቶ የሚያርሰውና የሚዘራው መስከረም እና ጥቅምትን እያሰበ ነው። ዝናቡ ማሳ ላይ ለማረስ ይቅርና ከብርድ ልብስ ውስጥ ወጥቶ ለመቀመጥም አይመችም። ነገር ግን አርሶ አደሩ ዝናቡ እየዘነበበት እየጨቀየ የሚያርሰው ዓመቱን ሙሉ የሚበላውን ነገር ማምረት እንደሚቻል ስለሚያውቅ ነው። ያንን መከራ እያሰበ ሳይሆን ከመከራ በኋላ የሚመጣውን መልካም ጊዜ በማሰብ ስለሚሰራ ነው። በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ የምትፈተን አልፎ አልፎም ዝናብ የሚያስገባ

ጣርያ ያላት እንጂ የማትፈርስ መሆኗን በእናንተ ሥራ ምክንያት በግሌ በሙሉ እምነት አረጋግጫለሁ። ይህ እንዲሆን ደግሞ እናንተ ስለሠራችሁ እጅግ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ። እንግዲህ እናንተ ስትባሉ ከእናንተ በፊት የነበረውን ትውልድ ታሳቢ ያደርጋል።

ኢትዮጵያ ፊደል ቀርጻ መጻፍ ከጀመረች የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ ሆኗታል። በድንጋይ ላይ መሳል መቅረጽ ከጀመረች ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመት በላይ አስቆጥራለች። ቀደም ባሉት ዘመናት ኢትዮጵያ ውስጥ ወጣቶች ከፍ ያለ ቦታ ላይ ሆነው ልጃገረዶችን በቡሄ ጨዋታ፣ በመስቀል በዓል የበርካታ ሰዎችን ቀልብ የሚይዝ ትዕይንት ለሺህ ዓመታት ሲያሳዩ ቆይተዋል። የእነዚህ ሁሉ ድምር ነው ዛሬ ኢትዮጵያ በእምነቷ፣ በባህሏ እንድትቆም ያደረጋት።

እንጦጦን እንኳን ብትወስዱ የጥበብ ውጤት ነው። ጫካው መንገድ ቢወጣለት እንደዚህ ዓይነት ስፍራ ቢሰራ “ያማረ ሊሆን ይችላል” የሚል እሳቤ በአእምሮ ውስጥ ባይፈጠር ኖሮ አሁን የምናየውን ነገር ልናይ አንችልም። ጥበብ ማለት መንገድም፣ ህንጻም፣ እንደዚህ ዓይነት መዝናኛ ስፍራም የሚገነባው በአእምሯቸው፣ በምናባቸው መሳል በሚችሉ ሰዎች ነው። ያን ደግሞ በእርሳስ ከሚያኖሩ ሰዎች በኋላ የተሳለውን ነገር ለብዙዎች ለማሳየት በርካታ ሙያተኞች ቢሳተፉም የመጀመሪያው ሃሳብ የሚወለደው አእምሮ ውስጥ ነው። ኪነ ጥበብ፣ ዕደ ጥበብ፣ ሁሉም ዓይነት የተፈጥሮ ፀጋዎች በእናንተ ውስጥ አሉ። በብዙ ሰዎች ውስጥ እንብዛም አይገኙም። ይቺን አገር ለማስቀጠልና አዲሱን ትውልድ ከብሽሽቅ፣ ከስድድብ ወጥቶ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ የሚያደርግ ሥራ እንዲሠራ የአርአያነት ሚናችሁን ለማስታወስም ነው። ይህም የኢትዮጵያዊያን ልምምድ እንዲሆን ለማድረግ ታስቦ የተጀመረ ሲሆን፤ ምናልባት አዲስ በመሆኑ የሚጎድሉ ነገሮች ካሉ እየታረመ እና እየተሻሻለ ይሄዳል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በዚህ በእንጦጦ ይህን አንፊ ቲያትር፣ ታች ዝቅ ብሎ ከአምስት ሺህ በላይ የሚይዝ አንፊ ቲያትር፣ በሸገር ያያችሁት አንፊ ቲያትር ተገንብቷል። አሁን ለመከላከያ ሚኒስቴር እየተገነባ ባለው ዋና መሥሪያ ቤትና በየቦታውም ለመገንባት ሙከራ እያደረግን ነው። መስቀል አደባባይም በተለየ መንገድ ቢያንስ እስከ አንድ ሚሊዮን ሰው መያዝ በሚችል መልኩ ተገንብቶ ተጠናቋል። በቅርቡ ይመረቃል። ይሄ ሁሉ እናንተን

የሚጠብቅ ነው። መሠረታዊ ጉዳዩ ለአርቲስቶች ሥራዎቻቸውን ለህዝቡ የሚያቀርቡበትን አውድ መፍጠር ስለሆነ የሚቀረን ነገር ቢኖርም፤ ልንሰራባቸው የሚገቡ በርካታ ነገሮች አሉ። ጅምሩ መልካም ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ የምናየው ያለንን ሳይሆን የሌለንን ነው፤ ያገኘነውን ሳይሆን ያጣነውን ነው፤ የሆነልንን ሳይሆን የሆነብንን ነው። በዚህ ምክንያት መልካም ነገሮች በስፋት እንዳይታዩ ቢሆንም፤ ብዙ ሊነገሩ፣ ብዙ ሊተላለፉ የሚገቡ ሥራዎች አሉ። እናንተ በዘመናችሁ እጅግ አነስተኛ ክፍያ ወይም ሳይከፈላችሁ ኢትዮጵያን ለማቆየት መሰረታዊ የሆነውን ሥራ አከናውናችሁ ለትውልድ አሸጋግራችኋል። “እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን” እላለሁ።

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ካደረግነው የምስጋና መርሀ ግብር በተጨማሪ በተለይ እድሜያቸው ከፍ ያሉትን ምናልባት ሊያመልጡን የሚችሉ የጥበብ ሰዎችን (የዛሬው መርሃ ግብር ከታቀደለት ጊዜ ለአንድ ዓመት በመዘግየቱ ብዙዎች አምልጠውናል።) ሳያመልጡን በታክሲ ቦታ በሰልፍ፣ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቦታዎች፣ በአየር መንገድ በአንዳንድ አካባቢ በአዋጅ ሳይሆን በፍቅር ቅድሚያ እየሰጠን ማክበር ይገባል። ለዚህ በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ደረጃ እንዲሆን ክብር የሚገባቸው ሳያተርፉ፣ ሳያገኙ፣ መጦሪያ ሳይቋጥሩ ኢትዮጵያን ለማቆየት ብዙ የደከሙ ስለሆኑ ሁሉም ዜጋ የሙያውን ክብደት እና ጠቃሚነት ተገንዝቦ በየአስፈላጊው ቦታ ክብር እንዲሰጣቸው አደራ እላለሁ።

በዚህ መርሀ ግብር መሸለም፣ ስማቸው መጠራት ሲገባቸው የተዘነጉ ሰዎች ካሉ ኃላፊነቱን እኔ የምወስድና በዚሁ መድረክ ይቅርታ የምጠይቅ ይሆናል። ነገር ግን ይህ መድረክ በዚህ መንገድ እንዲዘጋጅ በተቻለ መጠን ከሁሉም ሙያ ሰዎች ተዘንግተው ሳይጠሩ እንዳይቀሩ ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ ጥረት አድርገው መርሀ ግብሩን ያዘጋጁ፣ የመሩ ሰዎች ከመድረክ ጀርባ የሚታዩትን ሰዎች በሙሉ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

“እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን።” በሚቀጥለው ጊዜ መርሀ ግብሩ እንደዚህ መደበኛ መልክ ከመያዝ ባሻገር አልፎ አልፎ ታላላቆቻችን ለአምስት እና አስር ደቂቃ ልምዳቸውን

የሚያካፍሉበትና የምንማማርበት ማድረግ ሙሉ ቀንም ቢወስድ ችግር ስለማይኖረው ይህ ቢካሄድ ጥሩ ይሆናል።

**እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!**

**እንኳን ደስ አላችሁ!!**

**መጋቢት 30፣ 2013 ዓ.ም**

## የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነትአስተዳደር (ኢ.መደአ) - የታላቅ ራዕይ ውጤት

በመጀመሪያ ይህ ራዕይ እንዳይጨናገፍ የረዱ፣ የጣሩ፣ ያሳኩ ጥቂት ሰዎችን እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። የመጀመሪያው ተመስጋኝ የኢትዮ-ቴሌኮም የቀድሞ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አማረ አምሳሉ ናቸው። ለመጀመሪያ ጊዜ ሃሳቡን ካካፈልኳቸው በኋላ ቦታው ከቴሌ ቆርጠው የሰጡት እርሳቸው ስለሆኑ አመሰግናቸዋለሁ። ሁለተኛው ጄኔራል ሳሞራ የኑስ ናቸው። ሃሳቡ ከተጀመረ በኋላ በወቅቱ በነበረው ቢሮክራሲ በጣም አስቸጋሪ ጉዳዮች ቢገጥሙም ጅምሩ እንዲሳካ ከፍተኛ ጥረት ስላደረጉ እርሳቸውንም አመሰግናለሁ።

ሀሳቡ ፈር እየያዘ ከሄደ በኋላ በኢንጂነር መሰለ ኃይሌ፣ ኢንጂነር ሃይለመስቀል፣ ኢንጂነር ዘካርያስ እንደ ዲዛይን ኩባንያ ሳይሆን ራዕያችንን ተጋርተው ከመጀመሪያው እስካሁን ድረስ ላለው ሂደት አስተዋፅኦ አድርገዋል። የእነርሱን ሙያዊ ድጋፍ በመጠቀም መንግሥትን ለማሳመን ሠርተናል። ለዚህም ሦስቱን ሰዎች አመሰግናለሁ። በመጨረሻም ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል፣ ዶክተር ሹመቴ ግዛው፣ የኢመደአ ሠራተኞች በሙሉ “ደከመን፣ ሰለቸን” ሳትሉ በመስራታችሁ አመሰግናለሁ። ይሄንን ማሳካትና በገንዘባችሁ መደገፍ የቻላችሁ፣ በሃሳብ የደገፉችሁ ሰዎችን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ውስጥ የማየው ኢትዮጵያን ነው። ደቡብ አፍሪካ ለትምህርት በነበርኩበት ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ በሳይበር ስፔስ ላይ የሚሠራ ተቋም ማቋቋምን በሚመለከት ሃሳብ ያካፈልኩትና ያጋራሁት አሁን የሰላም ሚኒስትር ዲኤታ ለሆነው ሃይላይ ብርሃነ ነው። ሁለታችንም አንዲት ክፍል ውስጥ በጋራ ስለምንተኛ ናኖቴክን፣ ሲ.ኤስ.አርን፣ የተለያዩ ኩባንያዎችንና የምርምር ተቋማትን ስመለከት “እንደዚህ ዓይነት ተቋም መፍጠር ይቻላል። መፍጠር አለብን” የሚል ሃሳብ አጋራሁት። በመጀመሪያዎቹ ወራት ሞራሌን ጠብቆና ደግፎ በብቸኝነት ሃሳቡን ተቀበለ። ከእርሱም ጋር ጓደኞቻችን እነ አብረሃ ደስታ፣ ቴዎድሮስ በቀለ፣ እነተሾመ፣ እነሃይለአብ የሚባሉ

ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ሀሳቡ እንዲሳካ ከመጀመሪያውኑ ተጋሪና ደጋፊ ስለነበሩ ከፍ ያለ ምስጋናዬንና አድናቆቴን እገልጽላቸዋለሁ።

ከእነርሱ በመቀጠል ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ ይሄ ራዕይ ወደ መንግሥት ደርሶ እንዳይጨናገፍ ጀኔራል ሳሞራ የኑስ፣ አቶ አባዱላ ገመዳ እና አቶ ተፈራ ዋልዋ ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል። እነዚህ ሦስት ሰዎች ያጋራኋቸው ሃሳብ በወቅቱ ለነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር በጽሑፉ እንዲደርሳቸው ያመቻቹና ወደ ተግባር እንዲለወጥም ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው ናቸው።

አሁን በከፍተኛ አመራር ደረጃ ላይ ያሉ ሲሳይ ቶላ፣ አህመድ ሃምዛ፣ ከፍያለው ተፈራ፣ ተመስገን ጥሩነህ፣ ሙላት፣ ተክለብርሃን ወልደአረጋይ የኢመደአ ሃሳብ በመንግሥት ተቀባይነት እንዳገኘና ሊሳካ እንደሚችል በአንድ ቀን ሃሳቡን ያጋራኋቸው ጓደኞቼ ናቸው። ኢመደአን እኔ ባስበውም በተፈለገው ደረጃ እንዲሳካ ከፍተኛውን ሥራ የሠሩ የመጀመሪያ አባላት ናቸው። ለነዚህም ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

ኢመደአ ሲጀመር “አሁን ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች” እንደሚባለው ሁሉ የቅርብ ጓደኛን ጨምሮ ሁሉም ሰው እንደ እብድ ወይም በምድር ላይ ያለውን ሁኔታ መገንዘብ እንደሚሳነው ሰው የማየት ችግር ነበር። አፍሪካ ውስጥ ካሉ የሳይበር ስፔስ ተቋማት ጋር የሚመሳሰል ጠንካራ ተቋም ለመፍጠር ሀሳብ ስናነሳ ለመቀበል ተቸግረው ነበር። የዛሬ አስራ ሶስት ወይም አስራ አራት ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት የአይቲ ፖሊሲ፣ የኢንተርኔት ፖሊሲ ወይም ደግሞ ቴሌኮም ራሱ የነበረው የሴልፎን አገልግሎት ከኦዲዮ ወደ ዳታ ያልተሸጋገረበት፣ ኢንተርኔት የሚጠቀሙ ሰዎች እጅግ ቁጥራቸው ያነሰና በዋና ዋና ከተሞች ብቻ የተወሰነበት ጊዜ ስለነበረ ያንን ራዕይ መቀበል ለብዙዎች ያስቸግር ነበር። ራዕዩ ተሳክቶ ተቋም ከተፈጠረ በኋላ ኢመደአን ከመደመር ውጪ ስለማናስበው ሃያ ስድስት ብሄር ብሄረሰቦች በአባልነት እንዲታቀፉበት ለማድረግ ተጥሯል። በተቻለ መጠን ከእያንዳንዱ የተማሩ ሰዎች ለማግኘት እስካሉበት መንደር ድረስ በመሄድ ለመሰብሰብ ተሞክሯል። በወቅቱ የማስታውሰው ከኮንሶ አካባቢ አባል መጨመር አለብን “ኢመደአ ኢትዮጵያዊ ተቋም መሆን አለበት” ብለን ያገኘነው አንድ ሰው አሁን በከፍተኛ አመራር አባልነት ይገኛል።

በወቅቱ ሃያ ስድስት ብሄር ብሄረሰቦች ያሉበት ተቋም እንዲሆን የተፈለገበት ዋነኛው ምክንያት ዘመን መሻገር እንዲችል፣ ለትውልድ እንዲተላለፍ፣ ከመንግስታት ጋር እንዳይጠፋ ከነበረን ፍላጎት የመነጨ ነው። ይሁንና በርከት ብሎ መታየት፣ መብዛት የሚፈልጉ ኃይሎች በጥሩ መልኩ አልተቀበሉትም። ይህንንም ጅምር ወደ ኋላ ለመመለስ ጥረት ያደረጉበት ሁኔታ ነበር።

ቅድም ለመግለጽ እንደተሞከረው ራዕዩ በአፍሪካ ጠንከር ያለ ተቋም መፍጠር፣ ተለቅ ያለ ህልም ማለም ያን ለማሳካት መረባረብ ነበር። ህልሙ ትልቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በብዙዎች በቀላሉ ተቀባይነት የሚያገኝ ባለመሆኑ የነበረው ውጣ ውረድ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚታየው የሚተናነስ አልነበረም። ሽኩቻው፣ ሃሜቱ፣ መገፋፋቱ ጨምሮ በጣም በርካታ ችግሮች ነበሩ። ነገር ግን ሁለት ዓመት ተኩል ኢመደአ ከቆየ በኋላ በሶስተኛው ዓመት ላይ ለጀርመንና ለበርካታ አፍሪካ አገሮች ሶፍትዌር ሸጠን የውጪ ምንዛሬ ማስገባት ስንጀምር፣ የዛሬ አስራ አንድ ወይም አስራ ሁለት ዓመት አካባቢ የመጀመሪያዎቹን አራት ዩ.ኤ.ቪዎች ሰርተን ዲሞንስትሬት ማድረግ ስንችል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በፋክስ ብቻ የነበረው የቴክኖሎጂ ልውውጥ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አውቶሜት ማድረግ ስንችል፣ በወቅቱ የኢ-ገቨርንመንት አንድ አካል የሆነው ቢ.ፒ.አር.ፒ.ኤስ የተባለውና የመንግሥትን አሰራር ለማቀላጠፍ አብዛኛውን የመንግሥት ቢሮዎች አውቶሜት ስናደርግ፣ አዲስ አበባን ከፊሉን የካሜራ ሲስተም መትከል ስንችል፣ በኤምባሲዎቻችን ኢንክሪፕት የሆነ የኮሚኒኬሽን ሥርዓት ስንዘረጋ፣ በውጭ ጉዳይ ለመጀመሪያ ጊዜ ደህንነቱ የተረጋገጠ ኮሚኒኬሽን፣ በመከላከያ፣ በኢትዮ ቴሌኮም፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ በርካታ ስራዎች እየተሠሩ ሲሄዱ ትንሽ የማመንና የመደገፍ ዝንባሌ ተፈጠረ።

ኢመደአ ከመከላከያ ሚኒስቴር በተዋሳቸው በጣም ጥቂት ቦታ ሥራ የጀመረ ቢሆንም፤ በኋላ ግን ሰፋ ያለ በሺህ የሚቆጠር ሙያተኞች የሚይዝ "ህንጻ መገንባት አለብን" በሚል ግንባታውን አካሂዶ በማጠናቀቅ እንደማስመረቅ ቀላል ጉዳይ አልነበረም።

አንደኛ መንግሥት ከመሬት በታች ሶስት እና አራት ወለል ገንብቶ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ማሠራት የሚባል ነገር እንደእብደት የሚታይበት፣ በሺህ የሚቆጠሩ ባለሙያዎች ማቀፍ

መያዝ ማሰራት የሚችል ቦታ ሳይሆን ብቸኛ የዳታ ማዕከል ግንባታ፣ የፈጠራ ክህሎት ላላቸው ወጣቶች ቦታ የሚያመቻች፣ በኤግዚቢሽን መልክ ለሚጎበኙት ሰዎች ሃሳቡን በቀላሉ ማስተላለፍ የሚችል፣ ለመማሪያና ለእንግዶች የሚሆን አድርጎ ማሰብ በመንግሥት ተቀባይነት ያለው አልነበረም። የቅንጦትና አላስፈላጊ ተደርጎ የተወሰደ በመሆኑ በጣም ብዙ አታካች፣ አድካሚ ሂደቶችን ከተጓዝን በኋላ ግንባታው ተፈቅዶ፣ ሥራው ተጀመረ። አንድ ዓመት ሳይሞላው ኢመደአ ውስጥ የበለጡ ችግሮች እየተፈጠሩ ሄዱ። ኢመደአን መልቀቅ ግድ ከሆነ ከአምስት፣ ስድስት፣ ሰባት ዓመት በኋላ በዚህ መንገድ እየሄድኩ ህንጻውን ለማየት፣ ለማዘን አልፎ አልፎም ለማንባት ተገድጃለሁ። በጣም የሚያሳዝንና ልብ የሚሰብር ልብ አጨናጋፊ አድርጌ የወሰድኳቸውን ርምጃዎች በከፍተኛ ሃዘን ተመልክቻለሁ። ዋናው ህንጻ እንዳይሰራ ወይም እንዳይጠናቀቅ የተደረገው ከበጀት ወይም ከአቅም እጥረት ሳይሆን “ራዕዩ የአብይ ስለሆነ መጠናቀቅ የለበትም” ከሚል ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከዘመድ አዝማድ ሕንጻ በመከራየት በርከት ያለ ገንዘብ ማሸሽ ስለሚቻል ነበር።

ባለፉት አስራ አንድ ዓመታት ኢመደአ ለቤት ኪራይ አንድ ቢሊዮን ብር ገደማ አውጥቷል። የዚህ ፕሮጀክት በወቅቱ የነበረው አጠቃላይ በጀት ሶስት መቶ ሚሊዮን ነበር። አንድ ቢሊዮን አውጥቶ አሁን ባለቀበት ደረጃ እንኳን ሲታይ ሃምሳ በመቶ የፕሮጀክቱን ዋጋ ለኪራይ አውጥቷል። ለኪራይ ለማውጣት በነበረው ፍላጎት ሥራው እንዲጓተት የተደረገ ቢሆንም፤ ዛሬ ግንባታው ተጠናቆ ሲመረቅ ለማየት በመቻሌ ከፍተኛ ደስታና ክብር ተሰምቶኛል። ይህም ብቻ ሳይሆን ኢመደአ ትልቅ ህልም በመሆኑ ትላልቅ ተግዳሮቶች እንደገጠመው ሁሉ፤ የኢትዮጵያ ብልጽግና እውን ሆኖ ኢትዮጵያ ላቅ ያለችና ለአፍሪካ ተምሳሌት ሆና በጋራ የምናይበት ጊዜ እንደሚመጣ ሙሉ ተስፋ፣ ሙሉ እምነት፣ የይሆናል ደረጃውም ከፍ ያለ ሆኖ እንዳይ አድርጎኛል። ልክ እንደ ኢመደአ ስኬት ኢትዮጵያም በልጽጋ የምናይበትና ይሄን ቀን የምናስታውስበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ያለኝን ተስፋና እምነት እገልጽላችኋለሁ።

እንግዲህ ሁላችሁም እንደምታውቁት በመጀመሪያው፣ በሁለተኛውና በሦስተኛው ኢንዱስትሪ አብዮት የነበረው ዋናው መሠረት መሬት፣ ሰማይ እና ሐይቆች፣ ወንዞች፣ ውቅያኖሶች ናቸው። አጠቃላይ ስራዎች የሚከናወኑት መሬትና ሰማይ ላይ ነበር። አውሮፕላን

ሰማይ ላይ ይበራል፤ ተሽከርካሪ መሬት ላይ ይሄዳል፤ የእርሻ መሳርያዎች በመሬት ላይ ይሰራሉ። አብዛኛው ነገር ከሶስቱ የተፈጥሮ ስፔሶች የዘለለ አልነበረም። የሳይበር ስፔስ የምንለው እስካሁን ከነበሩት አብዮቶች የሚለየው "Fourth Industrial Revolution" ዋናው ልዩ የሚያደርገው የራሱ ስፔስ መፍጠሩ ነው። የፈጠረው ስፔስ ሰማይ፣ ምድር እና ውሃ ላይ ያልተወሰነ ግን በክላውድ ሲስተም (cloud system) ሰዎችን በርቀት የሚያገናኝ ሁሉንም የህይወት ነገሮች የሚነካ እስካሁን ከተሰሩት ሁሉ የላቀና በአጭር ጊዜ ውስጥም ከፍተኛ ሃብት የፈጠረ ነው።

በአሁን ወቅት የሳይበር ስፔስ በጥቅሉ በዓለም ላይ ካለው ህዝብ ከሃምሳ በመቶ በላይ ይጠቀምበታል። ከአንድ እና ከሁለት ዓመት በኋላ አሁን ባለው ሁኔታ በዓለም ላይ ካለው ሃብት አንድ አራተኛው የሚዘዋወረው በዚህኛው ኢንዱስትሪ ነው። ከተፈጠረ በጣም ጥቂት ጊዜ ቢሆንም አብዛኛውን ሃብት የያዘው ይህ የሳይበር ስፔስ የሚባለው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጨምሮ አጠቃላይ በዙሪያው ያሉ እንቅስቃሴዎች ናቸው። በአሁኑ ወቅት ዓለም ላይ ካሉ አስር ትላልቅ ኩባንያዎች ሰባት ወይም ስምንቱ በዚህ ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ዓለም ላይ ካሉ አስር ትላልቅ ሃብታሞች ቢያንስ ስድስቱ በዚህ አውድ ውስጥ የሚሰሩ ናቸው። ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም ሃብት የመጀመሪያውን ትሪሊዮን የተሻገረው አማዞን የዚህ ስፔስ ተጠቃሚ ነው።

ይህንን የቴክኖሎጂ አብዮት ከሌሎቹ የሚለየው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍ ያለ ሃብት መሰብሰብ የቻለ፣ የባንክ ኢንዱስትሪ፣ አጠቃላይ ፋይናንሻል ኢንዱስትሪ፣ እርሻ፣ የአየር ቴክኖሎጂዎችን፣ ተሽከርካሪዎችን፣ ቢሮዎች እያንዳንዱን እንቅስቃሴ መገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ መቆጣጠር በመቻሉ ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት የተመረተው የዳታ ክምችት ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ የተፈጠረውን ይበልጣል። አሁን ዓለም ላይ ያለው ዳታ ዘጠና በመቶ የሚሆነው ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ የተመረተ ነው። ይህ ወደፊት የዳታ፣ የኢንፎርሜሽን ዘመን ይመጣል የተባለው የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ፣ የሚታይ ይሆናል። ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያም ወደኋላ እንዳትቀር ተቋሙ ከፍተኛ ድርሻ ሊጫወት እንደሚችል አመላካች ነው።

እንደዚህ ዓይነት አዲስ እውቀት ከመተጋገዝ፣ ከመደጋገፍ፣ ከመተባበር ውጪ ሊሳካ አይችልም። እንደዚህ ዓይነት አዳዲስ ነገር የመፍጠር ሥራ ቅዳሜ እና እሁድን ካለመትጋት ማታ ቢሮ ካለማደር እንዲሁ በከንቱ ሊሳካ አይችልም። የኢመደአ አባላት መተባበርና መደጋገፍ አለባችሁ። የኢትዮጵያ የመጀመሪያው በከፍተኛ ሃብት የሚጠቀሱ ተቋማት ከኢመደአ ውስጥ የሚፈጠሩ መሆን አለባቸው። ኢመደአም ባለብሩህ አእምሮ ያላቸውን ሰዎች መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ብቃታቸውን አመንድጎ የራሳቸው ኩባንያ ኖሯቸው ሃብታም እንዲሆኑና ኢትዮጵያን እንዲረዱ የሚያመቻች ተቋም መሆን አለበት። በአፍሪካ ውስጥ እስካሁን ባለን እውቀት የነበርንበትን ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ የኢመደአን ተቋም የሚያክል ልዩ ልዩ ነገሮችን በአንድ አካባቢ ያካተተ (Compound)፣ በርካታ የተለያዩ መገልገያዎች መያዝ የሚችል ያለው ተቋም የለም።

ደቡብ አፍሪካ ያሉ ተቋማት በአራት አምስት ተቋማት የተበተኑ ናቸው። በዚህ ደረጃ ሰብሰብ ብሎ መስራት የሚችል በአፍሪካ ውስጥ የለም። ኢመደአ በዚህ ከተኩራራ እንዳረጁት ተቋሞቻችን ያረጃል። ሩጫው፣ ፍጥነቱ፣ ውድድሩ መቆም፣ መተኛት የማይፈልግ መሆኑ ገብቶት ከሠራ ግን በርካታ ሃብት ሊያመጣ ይችላል። እያንዳንዱን ሰው፣ እያንዳንዱን ቤት፣ እያንዳንዱን ኩባንያ እየፈተነ ያለውን የሳይበር ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል ብቃት መፍጠር ይችላል። በዚህ ዓመት ብቻ በዓለም ላይ ከሁለት ትሪሊዮን ዶላር በላይ ጥፋት ደርሷል። የሳይበር ጥቃት በዓለም ላይ የምንሰማው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ላይም ከፍተኛ ጥቃቶች ተደርገዋል።

ዛሬ "ከሳይበር ጥቃት ውጪ ነኝ" ብሎ የሚያስብ ግለሰብ የለም። ከዚህ ቀደም በርካታ ሶፍትዌሮችና ሃርድዌሮችን በመጫን የሚሠራው ምናባዊ ጠለፋ (Virtual Hacking) ወይም ጥቃት ሥርዓት ወደ ዜሮ ጠቅታ (Zero click) ተቀይሯል። ስልካችሁን አስቀምጣችሁ ምንም ነገር ሳትሰሩ፣ ምንም ነገር ሳታደርጉ ስልኩ ውስጥ ያለውን ዳታ መውሰድ የሚያስችል ጥበብ ላይ ተደርሷል። አሁን ላይ ስልካችሁን አንስታችሁ ሳትከፍቱትና ሳትነጋገሩበት ስፒከሩን በመክፈት ብቻ የምትነጋገሩትን መስማት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ተፈጥረዋል። እያንዳንዱ ሰው ከዚህ ጥቃት ነጻ መሆን የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ስለዚህ እንደግለሰብ፣ እንደ

ኩባንያ፣ እንደ አገር ከእንደዚህ ዓይነት ጥቃት መከላከል እንዲችል ተቋሙ ቀዳሚውን ሚና መጫወት አለበት። በተጨማሪም ከምርምር ተቋማት፣ ከዩኒቨርስቲ፣ የፈጠራ ክህሎት ካላቸው ግለሰቦች ጋር በመተባበር አዳዲስ እውቀቶችንና ቴክኖሎጂዎችን እንደሚፈጥር ያለኝን ሙሉ ተስፋ እገልጻለሁ።

ዛሬ ጠዋት አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ በኢንተርኮንቲኔንታል ባዘጋጀው ኤግዚቢሽን የራሱንና የሌሎች ወጣቶችን እጅግ አስደማሚ የሚባሉ ሥራዎች ለማየት እድል አግኝቻለሁ። ኤግዚቢሽኑ ነገም ስለሚቀጥል ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ምን እየሠሩ እንደሆነ ለማወቅ እዚህ ያላችሁ ሰዎች ኢንተርኮንቲኔንታል የአንድ ወይም የሁለት ሰዓት ቆይታ ብታደርጉ በርካታ እውቀት ታገኙበታላችሁ። አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ፣ ኢመደአም፣ ፋይናንሻል ኢንተሊጀንስ ሌሎችም የምርምር ሥራ ያላቸው ተቋማት ሳትበታተኑ ውስን ሃብታችንንና እውቀታችንን ደምራችሁ ኢትዮጵያን በዚህ ረገድ የምትወዳደር አገር እንድታደርጓት በታላቅ አክብሮትና ትህትና እጠይቃለሁ።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዘመን ተሻጋሪ ተቋም የመፍጠር፣ ለትውልድ የሚሻገር ተቋም የመሥራት ጅምር ዛሬ በኢመደአ ምርቃት ያየነውን በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ከአፍሪካ እጅግ ግዙፍና ማራኪ የሆነውን ለመላው ጥቁር ህዝቦች እንደ ኩራት የሚታየውን የመከላከያ ሚኒስቴር ዋና መሥሪያ ቤት የምናስመርቅ ይሆናል።

ይህ የመከላከያ ሚኒስቴር ዋና መሥሪያ ቤት በበርካታ አገሮች ካየናቸው በብዙ መልኩ የላቀ፣ የቴክኖሎጂ አቅም ያለው፣ ኢትዮጵያን ከየትኛውም ጠላት ለመከላከልና ለማስቀጠል የሚያስችል ዝግጅት ለማድረግ መሰረት የሚሆን እጅግ የሚያኮራ ሥራ ነው። ዛሬ ያላችሁ እንግዶች በምርቃቱ ቀን ወይም ከዚያ በኋላ በሚኖረው የጉብኝት ጊዜ በማየት በኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ በመከላከያ ሚኒስቴር እንዲሁም በከንቲባ ጽህፈት ቤት፣ ከዚያም ውጪ በሚሰሩ ፕሮጀክቶች ተቋማት የመገንባት ሥራ ፈር እየያዘ መሆኑን መገንዘብ ትችላላችሁ። ይህን ማስፋት፣ ማጠናከር፣ ማላቅ፤ በአእምሮ “አንችልም” ብሎ መታሰር ሳይሆን አርቆ እና አስፍቶ ማሰብ ይጋል። አርቀን ባሰብን ቁጥር ተግዳሮቱም የዚያኑ ያህል የሚሰፋና የሚጠነክር መሆኑን በመገንዘብ በትብብር መንፈስ

ጠንክሮ መሥራት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ልክ እንደ ኢመደአ ትልቅ ህልም አልማለች፣ መበልጸግ፣ መለወጥ ትፈልጋለች። ይሄንን ብልጽግና የሚገዳደሩ ሃይሎች ከሩቅ አይመጡም። ኢመደአ ብቃት ያላቸው ሰዎች እንዳይፈጥር፣ የተሻለ ብቃት ያላቸው ሀብት ፈጥረው ተባባሪ ኩባንያ እንዳይሆኑ ያደረጉት ሌሎች ሰዎች ሳይሆኑ በውስጡ የነበሩ አባላቱ ናቸው። ከውስጥ ሆነው "ይሄን ሃሳብ እንጋራለን፣ አብረን እናድጋለን" ያሉ ሰዎች ናቸው መጨረሻ ላይ በፖለቲካ ተበክለው ሃሳቡ እንዳይሳካ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ብዙ መንሳቆልና መገፋት ነበረበት። ያም ሆኖ ግን ኢመደአን ማዘግየት እንጂ እንዳይወለድ ማድረግ አልቻሉም። ዛሬም ኢትዮጵያ ውስጥ በየቦታው፣ በብሄር፣ በሃይማኖት፣ በማያገባን ነገር ሁሉ እየተጋጨን ለሌሎች ሲሳይ እንድንሆን የሚፈልጉ ሃይሎች በቀዳሚነት ኢትዮጵያዊያን ናቸው። የተገዙም ቢሆኑ፣ የሚደግፋቸው ኃይልም ቢኖር በቀዳሚነት ኢትዮጵያዊያን ናቸው።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች። ስትበለጽግ መስዋዕትነት እንከፍል ይሆናል፤ አልባሌ የሆኑ ግጭቶች ይፈጠሩ ይሆናል፣ ያልተዘጋጁ ሲቪሎችን፣ አርሶ አደሮችን፣ ንጹሃን ዜጎችን የሚገድሉ፣ ሽብር የሚፈጥሩ ኃይሎች ይኖሩ ይሆናል። እነዚህን ሁሉ አሸንፈን የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ብልጽግና እናረጋግጣለን።

የኢትዮጵያን ግዛት አንድነት ለማስቀጠል፣ ለማስጠበቅና ብልጽግናዋን እውን ለማድረግ ምንም ኃይል አያቆመንም። ይሄንን ነገር ለማቆም፣ እንዲዘገይ፣ ሃሳባችን እንዲበተን፣ በየጊዜው የሚረብሹ ኃይሎች ይኖራሉ። እናሸንፋቸዋለን። ኢትዮጵያን እናበለጽጋለን። ተቋሞች እንገነባለን። የነገይቱ ኢትዮጵያ ለትውልድ የምትመች፣ ለእኛም በስተርጅና የምንኮራና የምንኖርባት አገር ትሆናለች። ለብዙዎች መጠለያ አገር ትሆናለች። ይህ እንዲሆን እንተባበር፣ በጋራ እንስራ፣ ተቋም እንፍጠር። አንተኛ፣ ህልማችን ተሳክቶ ኢትዮጵያ ከልመና ተላቃ ረጂ እንድትሆን የሁላችሁንን ጥረት ስለሚጠይቅ በትብብርና በመደመር መንፈስ የኢትዮጵያን ብልጽግና በጋራ እናረጋግጥ።

**አመሰግናለሁ!**

**ሚያዚያ 9፣ 2013 ዓ.ም**


ዋና መስሪያ ቤት ምርቃት
ሚያዝያ 9 ቀን 2013
HEADQUARTERS INAUGURATION
APRIL 17, 2021
የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ
Information Network Security Agency

## ለኢትዮጵያ ዐርበኞች ቀን እንኳን በሰላም አደረሳችሁ !

ይህ ቀን ጀግኖች ዐርበኞቻችን ሀገራችንን ከአምስት ዓመቱ የኢጣልያ ወረራ ነጻ ያደረጉበት ቀን መታሰቢያ ነው። ይሄንን ቀን ስናስብ ከጀግኖች ዐርበኞቻቶን ሦስት ነገሮችን እየተማርን ነው።

የመጀመሪያው ከምንም ነገር በላይ ሀገርን ማስቀደም ነው። በወቅቱ የነበሩት ሁሉም ዐርበኞች በንጉሡ አገዛዝ የሚደሰቱ፣የሚስማሙና የሚደግፉ አልነበሩም። በመንግሥት አስተዳደር ቅሬታ የነበራቸው፣ የተገፉ፣ የተለያዩ አማራጭ የአስተዳደር ዘይቤዎችን የሚያቀርቡ ነበሩ። በንጉሡ ላይ ዐምጸው የሸፈቱም ነበሩ። በወቅቱ ጠላት እጁ ላይ ካለው አቅም ይልቅ አሸናፊ ያደርገኛል ብሎ ያሰበውን የኢትዮጵያውያንን ብሶትና ቅሬታ እንደ መሳሪያ ሊጠቀምበት ተንቀሳቅሶ ነበር። ከንጉሡ ጋር የማይዋደዱና በሆዳቸው ቅሬታ የያዙትን በስልጣንና በማባባያ ዝም አሰኝቶ ኢትዮጵያን የመጨበጥ ፍላጎቱ ለማሳካት ሞከሯል። ነገር ግን ዐርበኞች ሁሉም ለሀገራቸው ከብር፣ ፍቅር እና የጸና ዐቋም ነበራቸው። ቅሬታቸውና ልዩነታቸው ከመንግሥት አስተዳደር ጋር እንጂ ከሀገራቸው ጋር አልነበረም። በዚህም የተነሣ በሉዓላዊነታቸው ሳይደራደሩ፣ ለፋሽስት ጥቅም ሳያጎበድዱ፣ የሀገራቸውን ነጻነት ለማስከበር ዱር ቤቴ ብለው ዘመቱ።

ሁለተኛው ለሀገር ማንንም አለመጠበቅ ነው። ለሀገር ለሚከፈል ዋጋ ማንም እንዲጠይቅ፣ እንዲያስተባብር ወይም እንዲቀሰቅስ አይጠበቅበትም። ሁሉም ዜጋ የሚያውቀውን፣ የሚያምነውንና የሚችለውን ለማድረግ በራሱ መንፈስ መነሣት አለበት። ዐርበኞቻችን ያስተማሩን ይሄንን ነው። በወቅቱ ንጉሡ ከሀገር ወጥተዋል። ሊያስተባብሩ የሚችሉ ተቋማትና የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አልነበሩም። በዚያ ጊዜ ዜጎች ለሀገራቸው ራሳቸውን ነው ያስተባበሩት።
በጀት፣የሰው ኃይል፣ ቁሳቁስ አልጠየቁም። የሚሰጥ የለምና። ይዘው የወጡት የራሳቸውን መሣሪያ፣ የራሳቸውን ስንቅ እና ራሳቸውን ብቻ ነበር። ምናልባት ከስንቃቸው ጋር የሀገር ፍቅር በልባቸው ይዘው ስለወጡ እሱ ገመድ ሆኖ አስተሳስሯቸው እንደ አንድ ጦር ሆነው ጠላትን እንዲፋለሙ አድርጓቸው ይሆናል፤ ግን ለዚያ የሀገር ፍቅር የማንንም ቅስቀሳ ወይም የየትኛውንም ተቋም ውትወታ አላሻቸውም።

ሦስተኛው ትልቅ ቁም ነገር ሀገርን የሚታደገው የዜጎች አንድነት መሆኑ ነው። ዐርበኞች

በየአካባቢያቸው በጎበዝ አለቃ እየተመሩ በመዝመት ትግሉን ጀምረውታል። ትግላቸው ፍሬ ማፍራት የጀመረው ግን በየአቅጣጫው የነበረው የዐርበኞቻችን ተጋድሎ እየተቀናጀና እየተናበበ ሲመጣ ነው። የሚችሉት በአካል፣ ያልቻሉት በመልእክት እየተገናኙ አንድነታቸውን አጠናከሩ። የውስጥና የውጭ ዐርበኞች ተቀናጁ። ብሔር፣ ቋንቋና እምነት ገደብ ሳይሆንባቸው ሀገር አንድ አደረገቻቸው። ለአንዲት ሀገር በአንድነት ቆሙ። ይህም ፍሬውን በቶሎ እንዲለቅሙት አደረጋቸው። እኛ የእነዚህ ዕርበኞች ልጆች ነን። የእነዚህ ዐርበኞች ባለ ዕዳዎችም ነን። ሀገራችን በየዘመናቱ ዋጋ እየተከፈለባት እዚህ የደረሰች ናት። የምትቀጥለውም ዋጋ ስሚከፍሉ ልጆቿ ነው። እንደ ዐርበኞች እናትና አባቶቻችን ከምንም ነገር በላይ ሀገራችንን እናስቀድም።
ዐርበኞቻችንን ከባድ ዋጋ ያስከፈሏቸው ከለየላቸው ጠላቶቻቸው በላይ የሚመሳሰሏቸው ባንዳዎች ነበሩ። ዛሬም ዋጋ የሚያስከፍለን ባንዳነት ነው። ባንዳነት ሆገርን ለግል ጥቅም፣ ሕዝብን ለእለት እንጀራ፣ ሕሊናን ለተራ ቅያሜና ኩርፊያ ሲባል ያለ ማንገራገር መሸጥ ነው።

በሐሳብ፣ በአመለካከት፣ በርእዮት፣ በአሠራር ልዩነት ሊኖረን ይችላል። ብዝኃነት ስንል የሐሳብ ብዝኃነትንም ይጨምራልና።
የሐሳብ ብዝኃነት የሀገር ዕሴት እንጂ የሀገር ዕዳ መሆን ግን የለበትም። የምንቃወመው መንግሥት ይኖረን ይሆናል፤ የምንቃወማት ሀገር ልትኖረን ግን አትችልም። ሀገር እስይዘን ቁማር ልንጫወት የምንችለበት ምንም አማራጭ የለም። እኛ የዐርበኞቻችን እንጂ የባንዶች ልጆች አይደለንም።

ዜጋ በሀገሩ ጉዳይ ከማን ምን ይጠብቃል? ከማን ምን ይጠይቃል? ራሱን ለሀገሩ ለመስጠት እንጂ ሀገሩን ለራሱ ለመሠዋት ኢትዮጵያዊ የሆነ ማነው? በየትም ሀገር እንኑር፣ የትኛውም ሞያ ላይ እንሠማራ፣ ምንም ዓይነት ዐቅም ይኑረን፣ ግን ለኢትዮጵያ ጥቅም እስካላዋልነው ድረስ የዐርበኞች ልጅነታችን ትርጉም የለውም። ዐርበኞች ሞተውና ቆስለው ያወረሱንን ሀገር ባገኘነው አጋጣሚ አስውስንና አሳምረን ለልጆቻን ማሳለፍ ይገባናል። ያለን ጥቂት ዕቅም ሀገር ወዳድነት ሲጨመርበት ሚዛኑን ይደፋል። ያለን ውሱን ዕውቀት ኢትዮጵያዊ ወኔ ሲታከልበት ተአምር ይፈጥራል። ያለንበት ቦታና ኃላፊነት ቀላል መስሎ ቢታየንም፤ ለሀገር ለመሥራት አስበን ከተነሣን ትንሽዋም አስተዋጽኦችን ለኢትዮጵያ በትልቁ የምትመነዘር ናት።

## ውድ ኢትዮጵያውያን፣

ዐርበኞቻቸን እንደነበሩበት ዘመን ዛሬም ኢትዮጵያ በውስጥ ባንዳዎችና በውጭ ጠላቶች

መከራ እየተቃጣባት ነው። ይሄን ለሀገራችን የሚደገስ የመከራ ድግስ የምንቀለብሰው እና ወደ ጠላቶቻችን የምንመልሰው ከተቀናጀን፣ ከተባበርንና ከተናበብን ነው። በየዘርፉ የምናደርገው ሀገር የመታደግ ትግል ለአንዲት ኢትዮጵያ ትርፍ በሚያመጣ ዓላማ ካልተቀናጀ ሲሚንቶና ብረት እንዳጣ አሸዋ ይሆናል። የቆመ ቢመስልም ይወድቃል፤ ሕልውናችንም በቀላሉ አደጋ ያገኘዋል።
ስለዚህ በያለንበት፣ በምንችለውና በምናውቀው ነገር ሁሉ እንተባበር፤ ሊጋራ ሕልውናችን ተናብበን እንሥራ፤ ለአንዲት ሀገር አንድ እንሁን።

ሀገር የዐርበኝነት መንፈስ ትፈልጋለች። የዐርበኝነት መንፈስ ማለት ለሀገር የሚከፍሉት ዋጋ ከሀገር ከሚቀበሉት ነገር ሲበልጥ ነው። ዐርበኝነት የምንደኝነት ተቃራኒ ነው። ምንደኝነት ሀገርንም ጨምሮ ሁሉንም ነገር በጥቅም ብቻ መተመን ነው። ለመሆኑ ዐርበኞቻችን ለከፈሉት የሕይወት ዋጋ ምን ገንዘብ ይተመንለታል?

ለማንም ሳይሆን ለራሳችን ጥቅም ስንል ወደ ቀልባችን እንመለስ፤ የምንሠራው ሥራ ለነገ ስማችን፣ ለልጆቻችን፣ ለታሪካችን ምን ዓይነት መጥፎ ጠባሳ እንደሆነ ይግባን። ማንም ሰው ካላበደ በቀር የገዛ ቤቱን ለማፍረስ ከጠላቱ ጋር ኢያሴርም። ስለ ምንም ጉዳይ እንደራደር ይሆናል። ነገር ግን የመጨረሻ ምሽጋችንን አሳልፈን ለመስጠት፣ በሀገርና በቤታችን መደራደር የሞኞች ሁሉ ሞኝ አስመስሎ በጠላቶቻችን ፊት መሳቂያ መሳለቂያ እንደሚያደርገን ማወቅ አለብን። እንደ ብልሆቹ ዐርበኛ ወላጆቻችን በሴረኝነትና ባንዳነት ላይ ኮርተን "ጅሎች ነበሩ" በሚለው ፋንታ "ጀግኖች ናቸው" የሚል የከብር ስም እንያዝ። ከተሞኘን ሀገር ስለማይኖረን እንደ ተረት ንበሩ" መባላችን ጥርጥር የለውም፤ በተቃራኒው በጠላቶቻቸን ሴራ ሳንወድቅ ይሄን ከፉ ጊዜ በስኬት ካለፍን እንደ ዐርበኛ ወገኖቻችን "ጀግንነታችን" በመላው ዓለምእየተመሰከረለት፣ ትውልድ እያመሰገነን ይቀጥላል።

ክብር፣ ይህችን ሀገር በነጻነት ላቆዩልን ዐርበኞች እናቶቻችንና አባቶቻችን ይሁን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ሚያዚያ 26፣ 2013 ዓም**

## የሞጆ ባቱ መንገድ አገራዊ ትስስርን ለማጠናከር

ከሁሉ በላይ ዋናው የዕለቱ ሙሽራ ኢንጂነር ሀብታሙ አቦቲ ገዳ

Abbootii Gadaa, Haadholii Siinqee, qeerroof qarree, ummata Magaalaa Baatuu fi Magaalaa Maqii akkasumas naannoo kanarraa bakka kanatti kan argamtan hundaa, nageenyi Badhaadhinarraa isin haa gahu jechuun barbaada.[Harka rukutuu]

Wal makaan dubbadhaa, na ofkalchaa gaa.

ኢትዮጵያን መገንባትና በሚገባት ቁመና ላይ እንድትገኝ ማድረግ ቀላል ተግባር አይደለም። ፈታኝ ሥራ እንደሆነ እንገነዘባለን። አገር የሚገነባው በግራ እጅህ መጠበቅ፤ በቀኝ እጅህ ደግሞ መሥራት ስትችል ነው። አገርን በማላዘን ብቻ የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ መፍጠር አንችልም። ከዚህ በፊት እንዳልነው በግራ እጃችን እየጠበቅን፣ በቀኝ እጃችን እየሠራን ተስፋ ሳንቆርጥ፣ ጠላቶቻችንን ተስፋ እያስቆረጥንና ሪቫን እየቆረጥን የኢትዮጵያን ብልጽግናና አንድነት እውን እንደምናደርግ ዛሬም በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

ዛሬ በአገራችን በርካታ ፈተናዎች አሉ። በእነዚህ ፈተናዎች ምክንያት የሚባለው፣ የሚነገረው ለውጥ ይመጣ እንደሆን የሚሰጉና የሚጠራጠሩ ብዙ ዜጎች አሉ። ነገር ግን አንድም በዓለም ታሪክ ውስጥ ያለፈተና የመጣ ለውጥና እድገት የለም። የዓለም ህዝብ ቅዝቃዜ ሲያስቸግረው እሳትን፣ ሙቀትን ፈጠረ። ሙቀትን እንዲፈጥር ያነሳሳው የቅዝቃዜ ችግር ነው። ፍሬ እየለቀመ መመገብ ስላስቸገረው እርሻን፤ ከዚያም ዘመናዊ እርሻን ፈጠረ። ፍሬ እየለቀሙ መኖር አስቸጋሪ ባይሆን ኖሮ አሁን በምናየው ደረጃ በዘመናዊ እርሻ አብዝቶ ማምረት ባልተቻለ ነበር። እንስሳትን በየጫካው እያደኑ መብላት፣ ለማደን ሲሄዱ መሞት ሲያስቸግረው ማላመድ ጀመረ። ዛሬ በቀያችን የምናያቸው ያላመድናቸው የቤት እንስሳት አድኖ የመብላት ፈተና የወለደው የመፍጠር አቅም ውጤት። መገንዘብ ያስፈልጋል። በእጅ እየሠሩ በቂ ማምረት እንዳማይቻል የተገነዘበው ሰው የተለያዩ መሳሪያዎችን ፈጠረ።

ጉዞን ለማቅለል፣ ፈጣን ግንኙነት ለመፍጠር አውራ ጎዳናን ብቻ ሳይሆን እጅግ ቀልጣፋ፣ ምቹና በፍጥነት ለመጓዝ የሚያስችል መንገዶችን በየብስ ላይ ተገነቡ። ዛሬ የምናስመርቀው የፍጥነት መንገድም አንዱ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ድህነትና የሰላም እጦት አሉ። በአንጻሩ ደግሞ የታላቅነት ምስጢርን ያለመገንዘብ ችግር አለ። ታላቅነት ራስን ማሸነፍ፣ ታላቅነት ካለን ማካፈል፣ ታላቅነት የኢትዮጵያን ፀጋዎች ተገንዝቦ ማውጣት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። አሁን ያለንበት ፈተናና ችግር ያስተማረን የበለጸገችና ለልጆቿ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የምትተርፍ አገር መፍጠር እንደሚቻል ነው።

ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች። ነገር ግን ብልጽግና እውን የሚሆነው ዛሬ እንደምናስመርቀው ዓይነት ወሳኝ የሆነ መሰረተ ልማት ሲገነባ ነው። ሰው ያለ ደምስር ሟች ነው። አገርም ካለ መንገድ ግንባታ እንቅስቃሴና እድገት ሊኖራት አይቻልም። ለሰው ልጅ ደምስር ያለውን ዋጋ ልክ መንገድ ለአገር እድገትና ብልጽግና ከፍ ሲልም የአገር ሉዓላዊነት ለማስጠበቅና የግዛት አንድነትን ለማረጋገጥ በእጅጉ የሚያግዝ ነው።

ዛሬ የምናስመርቀው መንገድ ከአዲስ አበባ እስከ ኬንያ ያለውን የመንገድ ስራ የሚጎድለውን ክፍል የሚሸፍ ነው። በቅርቡ ከሞያሌ እስከ ሃዋሳ ያለውን እንዳስመረቅን ይታወሳል። ይህ ሲታከልበት በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል ኬንያዎች ደግሞ ዝቅ ብለው ከሌላ አገር ጋር የፈጠሩትን የመንገድ ትስስር በመጠቀም፣ ለመሸጥና ለመግዛት በእጅጉ የሚያግዝ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ከዚህ መንገድ ውጪ ከደቡብ ሱዳን፣ ከሶማሊያ፣ ከጅቡቲ፣ ከኤርትራ፣ ከሱዳን የሚያገናኟትን መንገዶች በመገንባት ላይ ትገኛለች። በተለይ በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት የምናስጀምረው የአዳማ – አዋሽ ቶል ሮድ በዚሁ ደረጃ የሚጀመርና በዓለም ባንክና በኢትዮጵያ መንግሥት ትብብር የሚሰራ ሲሆን፤ ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ያለውን የፍጥነት መንገድ በብዙ መልኩ ያሳድጋል። ይህም በሎጅስቲክስ ኮሪደር ያለውን መዘግየት ይቀንሳል። በምግብ ራሳችንን ለመቻል፣ ይበልጥ አምርተን ለመሸጥ፣ ከውጪ የሚገቡትን ለማስቀረት ያግዛል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያን ከምናስባት የእድገት ከፍታና ብልፅግና ለማድረስ የመንገድ

ልማት በእጅጉ ወሳኝ ነው።

Ulfaadhaa...! Ulfaadhaa...! Af-yaa'ii Taaggasaa Caafoo, Bakka Bu'aa Baankii Egziim kan Kooriyaafi Itiyoophiyatti Ambaasaaddara Kooriyaa Kaang, Itiyoophiyaatti Bakka Bu'aaBaankii Misooma Afrikaa Dr. Kaamaaraa, Itiyoophiyatti Bakka Bu'aa Baankii Addunyaa obbo Usmaan, Koomishiinii Diinagdee Afrikaatti Itti Gaafatamaa Itiyoophiyaa Veeraa Akkasumas, affeerraa Hayleetiin biyya obbolaa Keenyaarraa nu guddutti kan argame atileet Pooteel Gaat, akkasumas kabajamoo Pireezidaant Shimallis, kabajamoo Pireezidaant Ristuu, kabajamoo pireezidaant Abrahaam, kabamtuu Ministira Daagmaawit, Hundumaa olitti misirroo guyyaa kanaa kan ta'e Injinar Habtaamuu, Abbootii Gadaa, haadholii Siiqqee, Qeerroof Qarree, Ummata magaalaa Baatuufi Maqii akkasumas, naannoo kanarraa bakka kanatti argamtan hundaaf, nageenyi Badhaadhinarraa isin haa gahu jechuun barbaada.

Walmakaan dubbadhaa na ofkalchaakaa!

Biyya ijaaruun... Itiyoophiyaa ijaaruufi sadarkaa isheen malurra akka geettu gochuun hojii salphaa akka hin taane, hojii nama qoru ta'uu ni hubanna. Haata'u malee, biyyi kan ijaaramu, harka bitaan eegaa, harka mirgaan hojjachuu yoo dandeessedha. Biyyaa qooqifachaa(iyyaalaazzanni) qofa eegaa Itiyoophiyaa barbaannu uumuu hin dandeenyu waan ta'eef, akkuma duraan jenne harka bitaan eegaa, harka mirgaan hojjachaa abdii osoo hin kutin riivaani kunnee diinota keenya abdii kutachiisaa, badhaadhinaa fi tokkummaa kan mirkaneessinu ta'uu, har'as irra deebi'ee isiniif mirkaneessuun barbaada.

Biyya keenya keessa har'a qormaata baay'etu jira. Sababa qormaatota kanneeniin jijjiiramni jedhamu, kan dubbatamu dhufuu isaa lammiileen sodaataniifi shakkan heddu jiru. Haata'u malee, seenaa addunyaa keessatti jijjiiramni rakkoo malee dhufe tokkollee hin jiru. Ummanni addunyaa wayta qorri rakkisu ibidda(hoo'a) kalaqe. Rakkoo qorraati hoo'a akka uumu kan isa kakaase. Firii funaanee nyaachuun waan isa rakkiseef qonna achumaanis qonna ammayyaa jalqabe. Firii funaananii jiraachuun osoo rakkisaa ta'uu baatee, qonni ammayyaa amma agarru, baay'isanii oomishuun, kalaquun hin danda'mu ture. Bosona keessa jooranii bineesota adamsanii nyaachuun, yeroo adamsuuf deeman du'uun waan rakkiseef madaqsuu jalqabe. Har'ee keenyatti kan agarru beelladoonni madaqsine kunneen kanneen qormaanni

adamsanii nyaachuu dhale, bu'aa dandeetti kalaquu ta'uu hubachuun barbaachisaadha. Harka duuwwaan hojjachuun oomisha gahaa oomishuun akka hin danda'amne namni hubate maashina kalaqe. Imala salphisuuf, walqunnamtii ariifataa uumuuf, daandii guddaa qofa(awraa godaanaa) osoo hin taane, daandii daran si'ataa akka har'a eebbifnuu; kan imalaaf namatti tolu, saffisaan deemuu kan nama dandeessisan daandii saffisaa hojjate.

Itiyoophiyaa keessatti, hiyyummaa, nagaa dhabuu, rakkoo icciitii guddummaa hubachuu dhabuu jira. Guddummaan of injifachuu ta'uu, guddummaan kan qabnurraa qooduu ta'uu, guddummaa kennaa(tsaggaa) Itiyoophiyaan qabdu hubannee baasuu ta'uu, qormaannifi rakkoon amma keessa jirru yoo nu barsiise, biyya badhaate, ijoollee isheef qofa osoo hin taane, kanneen biroofis geessu uumuun ni danda'amaa, Itiyoophiyaan ni badhaati.

Haata'u malee, badhaadhini kan dhugoomu, bu'uuraaleen misoomaa daran murteessoo tan kan akka isa har'a eebbifnee kun yoo ijaaramaniidha. Namni hidda dhiigaa malee jiraachuu hin danda'u. Biyyis ijaarsa daandii malee guddinaa fi sochiin keessa jiraachuu hin danda'u. Daandiin gatii hiddi dhiigaa ilma namaaf qabu, guddina, badhaadhinaa fi guddina biyyaa kanarra darbees birmadummaa biyyaafi tokkummaa biyyaa eegsisuuf daran kan deeggaru waan ta'eef, daandiin har'a eebbifnu hojii daandii Finfinnee kaasee hanga Keeniyaa jiru keessatti hanqina jiru kan cufu. Yeroo dhiyoo dura kan Moyaalee hanga Hawaasaa jiru akka eebbifne ni yaadatamaa, kun gaafa itti dabalamu, walitti dhufeenya Itiyoophiyaafi keeniyaa, walitti hidhamiinsa warri Keeniyaa biyyoota biroo waliin uuman fayyadamuun, gurguruu, bitachuufi guddachuuf kan gargaaru yoo ta'u, Itiyoophiyaan kanaan ala Suudan Kibbaa waliin, Somaaliyaa waliin, Jibuutii waliin, Eritiriyaa waliin, Suudan waliin, daandii wal qunnamsiisa ijaaraa kan jirtu yoo ta'u, keessattuu torbee muraasa booda kan jalqabsiifnu daandii kaffaltii Adaamaa-Awaash sadarkaa kanaan kan jalqabamuu fi walta'iinsa Baankii Addunyaafi Mootummaa Itiyoophiyaatiin kan hojjatamu yoo ta'u, daandii guddaa Finfinnee hanga Jibuutii jiru hedduun kan guddisuufi harkifannaa Kooriidarii loojistii sanarra jiru kan hir'isu waan ta'eef, nyaataan of danda'uuf, caalatti oomishnee gurgurachuuf, kanneen alaa galan hambisuuf, walumaagalatti, badhaadhina yaannu Itiyoophiya olka'iinsa guddinaa yaannu biraan gahuuf, daran murteessaa kan ta'e misoomni daandii, caalumatti hojii daandii qofa osoo hin taane, miidhagina isaa kan eeggate akka ta'uuf, ummanni naannoo kanaa karoora ganna kanaaf qabnu biqiltuu dhaabuu keessatti naannoo daandii har'a eebbaafnqophaa'e kanaabiqiltuu dhaabudhaan magariisa gochuun yoo

danda'ame, naannoon kun akkuma hundi keessan beektan Itiyoophiyaa keessatti naannoo guddachuuf carraa guddaa qabuudhaa, bishaan qulqulluu baay'ee qabaa, qonni isaa ammayyaa'ee, bal'atee, oomishtummaan isaa guddachaa jira. Isaa olitti, pirojeektiin dirree xiyyaaraa haaraa ijaaramuuf deemu, naannoo kanaaf dhiyoo waan ta'eef, ummanni naannoo kanaa, keessattuu dargaggoonni, misoomni dhufaa akka jiru, misoomni kun jalqaba kan fayyadu ummata naannoo kanaa ta'uu hubattanii, naannoo keessan bareechuu, miidhagsuun isinirraa kan eegamu ta'uu hubattanii, mootummaa naannoo oromoyaa wajjiin walgargaaruudhaan, biqiltuu daandii kana bitaaf mirgaan dhaabudhaan bareechuufi miidhagsuun hojii keenya akka ta'e, amaanaa guddaan isinitti ibsuun barbaada.

Jalqabbiin keenya xumura akka argatuuf, ummata keenyarraa waan barbaannu; qonnaan bulaan biyya keenyaa, yoo qonnaaf waan qabu ishee xinnoo baase, biyyeerratti harcaasu, Waaqaa amanee, bokkaa amaneeti. Nus badhaadhini biyya kanaa ni dhufa ni mirkanaa'a gaafa jennu, hundaa ol ummata keenya abdanneeti. Ummanni keenya faaydaa badhaadhinarraa argannu, faaydaa tokkummaa irraa argannu hubatee, akka yeroo hunda dubbannu Ida'amuudha, misoomarratti xiyyeeffatee, naannoo isaa eeggataa, diina naannoo isaa dhufee nagaasaa balleessuuf adeemu irraa ofeeggachaa eeggachaa, misooma isaa babal'ifachuu akka danda'u, waliin dhaabbachuu akka danda'u, mootummaa naannoo gargaaruu akka danda'u, tokkommaa Itiyoophiyaa, wal jaalala sabaafi sab-lammii Itiyoophiyaaf akkuma kaleessaa waliin taanee dhaabachuu akka dandeennu, biyya kana akka ijaarru, biyya kana ceenees biyyoota ollaa waliin ta'uudhaan naannoo kana ijaaruu, nageenya bal'uu, misooma fiduu akka dandeenyuuf, ummanni keenya halkanii-guyyaa akka hojjatu, qulqullinaan akka hojjatu, baay'inarraa argachuu hubatee, baay'isuuf akka hojjatu, waan xiqqoon quufatee, na gaha jedhee dhiisuu akka hin dandeenye, imaanaa jechuun barbaada.

Ni jijjiiramna, ni misoomna, tokkummaan keenya ni eegama, tokkummaan biyya keenyaa ni eegama! Hin yaadda'inaa, jabaadhaa hojjadhaa jechuun barbaada.

Xumra irratti; Baankii Misooma Afrikaa, Baankii Egziim Kooriyaafi Abbaa Taaytaa Daandiwwanii Itiyoophiyaa akkasumas, Mootummaa Naannoo Oromiyaafi jiraattotta naannicha, waggoottan darbaniif tattaaffii pirojeektiin

akka milkaa'uuf taasiftaniif baay'ee isin galateeffadha! Daandii ijaaruu itti fufna. Qonnaan bulaan oomishtummaa isaa akka dabaluufi akka gurguratu gochuuf tattaaffiin itti fufa. Bona baranaa hektaara kuna 300 irratti qamadii oomishuuf karoorsinee, hojii haalan milkaa'aa ta'e hojjannee, oomishni kuntaala miiliyoona 15 ol ni argama jedhamee eegama. Bara dhufu kana dachaan dabaluu yoo dandeenye, nyaatan of danda'uu qofa osoo hin taane, kanneen biroofis gahuu waan dandeenyuuf, haa jabaannuu, haa hojjannuu, misoomaa fi tokkummaan Itiyoophiyaa itti fufa, diinota keenya harka bitaan eegaa, harka mirgaa keenyaa akka misoomsinu adaraa isiniin jedhaa, yeroo eebbaa gaarii isiniif haa ta'uu, Galatoomaa!

በመጨረሻም የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ የኮሪያ ኤግዚም ባንክ እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እንዲሁም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት እና የአካባቢው ነዋሪዎች ፕሮጀክቱ እንዲሳካ ባለፉት ዓመታት ላደረጋችሁት ጥረት እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። መንገድ መገንባት እንቀጥላለን፤ ምርታማ ለመሆን የሚደረገው ጥረትም እንዲሁ።

በዘንድሮ የበጋ ወቅት በሶስት ሺህ ሄክታር ላይ ስንዴ ለማምረት አቅደን የተሳካ ሥራ በመሥራት ከአስራ አምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚሰበሰብ ይጠበቃል። በሚቀጥለው ዓመት ይሄንን በእጥፍ ካሳደግን በምግብ ራስን መቻል ብቻ ሳይሆን ለሌሎች መትረፍን ስለሚያመጣ እንበርታ፣ እንስራ። የኢትዮጵያ አንድነትና ልማት ይቀጥላል። ጠላቶቻችንን በግራ እጃችን እየጠበቅን፤ በቀኝ እጆቻችን እንድናለማ አደራ እላለሁ።

**ሁላችሁም እንኳን ደስ አላችሁ!**
**አመሰግናለሁ!!**

ሚያዚያ 30፣ 2013 ዓ.ም



## ለኢትዮጵያ አሸናፊነት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ

ስድስተኛውን አገርዊ ምርጫ ለማሳካትና እስካሁን ከተካተቱ ምርጫዎች በተሻለ መንገድ ዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ተጠብቆ ሰላም እንዲላበስ፣ ፍፃሜው እንዲያምርና ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ምርጫ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት የምርጫውን ሂደቶች አፈፃፀም ገምግመን "ሊሰሩ ይገባቸዋል" ያልናቸው ተግባራት ከአንድ ሳምንት እድሜ አኳያ በብዙ መልኩ ከፍተኛ መሻሻልና አመርቂ ውጤት መመዝገቡን ተመልከተናል፡፡ ነገር ግን የምርጫው ጠቀሜታ፣ ያለንን ጊዜ፣ ያለንን ሀብት፣ የእኛ ቁርጠኝነትን በመጨመር ባለፈው ሳምንት ካከናወነው ሥራ በላይ ለመሥራት ጥረት ካላደረግን አሁንም በቂ አይደለም፡፡

በዚህ ሳምንት እያንዳንዱ ክልል፣ ዞንና ወረዳ ያደረገው ጥረት ከምርጫ ቦርድ ጋር የፈጠርነው ቅንጅት በሚቀጥለው ሳምንትም መስፋት ከቻለ ምርጫው በተሳካ መንገድ ይካሄዳል፡፡ ይሄን ተግባራዊ ማድረግ ከእያንዳንዱ ክልል ይጠበቃል፡፡ ይሄን መፈጸም የምንገደድበት ዋናው ምክንያት የዘንድሮ ምርጫ ለኢትዮጵያ ወሳኝ ስለሆነ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ረጅም ዘመን የሚቆጠር እድሜ ቢኖራትም በህዝብ ፈቃድና ይሁንታ የሚያስተዳድሯትን መሪዎች መርጣ ስልጣን የማስያዝ ልምምዷ በጣም አነስተኛ ነው፤ ወይንም አልነበረም፡፡ በዚህ ምክንያት ነው አሁንም ከምርጫ ይልቅ ሌሎች አማራጮች እንደ ጥሩ ነገር የሚታዩት፡፡ ልምምድ የለም፡፡ ሀሳብ አዘጋጅቶ፣ ተደራጅቶ፣ በምርጫ ሂደት የሚያስፈልገውን ዋጋ ከፍሎ፣ ህዝብ አሳምኖና ተመርጦ ስልጣን የመያዝ ልምምድ ባለመኖሩ በመንግሥትም ሆነ በሚፎካከሩ ኃይሎች ፈተናው ከፍተኛ ነው፡፡

ይህም ቢሆን በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያለን ኃይሎች ኢትዮጵያን አሸናፊ አድርገን ለመወጣት ሁለት ኃላፊነት አለብን። አንደኛ በተቻለ መጠን የምርጫ ሂደቱ በህዝቡ ተአማኒ እንዲሆን፣ ዴሞክራሲን ለማምጣት እንዲያግዝ፣ ለዴሞክራሲ ልምምድ መሰረት እንዲጥል

ትልቅ ኃላፊነት አለብን፡፡ በርግጥ ውስንነቶች አሉ። ተፎካካሪ ፓርቲዎች አልፎ አልፎ የሚያነሷቸውን ክሶችና ምርጫ ቦርድም የሚያቀርበውን ጉዳይ እኛ ማየት አለብን። ትናንሽ የሚባሉ ስህተቶችን ማረም አለብን። ትናንሽ የሚባል ጥፋት እያጠፉን የሚፎካከሩ ኃይሎች ተስፋ እንዲቆርጡ፣ ምርጫ ቦርድ “ድጋፍ አላገኘሁም” ብሎ እንዲያስብ ማድረግ የለብንም፡ ፡ በየቀኑ በዙም በምታደርጉት ውይይት ከተሰሩ መልካም ሥራዎች በላይ በየዕለቱ የተከሰቱ ስህተቶችን በመገምገም ማረም መቻል አለባችሁ፡፡ የመደጋገፍ አብሮ የመስራት ባህሉ ካደገ ከባድ አይደለም፡፡ ይሄ ካለፍንባቸው ፈተናዎች አኳያ ብዙ ከባድ አይደለም። እያንዳንዱ ክልል ወሳኝነቱን መረዳት ተገቢ ነው። አብዛኛው ኃላፊነትም እኛ ላይ የወደቀ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በትብብር መስራት በተቻለ መጠን ጥያቄዎቻቸውን ማድመጥ ይገባል። በተለይ ደግሞ ምርጫ ቦርድ የሚያነሳቸውን ድጋፎችና ከእናንተ የሚጠብቀውን ነገር ተጨማሪ ጥረት በማድረግ መስራት ይኖርባችኋል። ጉዳዩ “የምርጫ ቦርድ ነው” ብለን ዝም ልንል አንችልም። መንግሥት ነን። መንግሥት በመሆናችን የሚጠበቁብንን ሥራዎች ለማከናወን ትብብሩ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

እዚህ ላይ ያለው አንዱ ፈተና ከውጭ የምንበደራቸው ሀሳቦች ናቸው። አሁን ኢትዮጵያን እያመሰ ያለው የዛሬ ሃምሳና ስድሳ ዓመት ገደማ ከውጭ የመጣ ሀሳብ ነው። ይህ ከሸቀጦች ጋር በተለመደው መንገድ ከውጪ የገባው ሀሳብ የሆነ ቦታ ዲዛይን ተደርጎ በትምህርት ሥርዓት፤ በተለያየ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል። እዚያ ያለ ሰው በትክክል ሳያሰላስልና ሳያስብ እሳቤዎችን ወስዶ እውቀት አድርጎ በመቀበሉ በህዝባችን መካከል ከፍተኛ የሆነ ፍጅትና ደም መፋሰስ አስከትሏል፡፡

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያበበው የፖለቲካ እሳቤ የዛሬ ሃምሳ እና ስድሳ ዓመት ከውጭ የገባ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደ አይደለም፡፡ ዛሬ እያጫረሰን ያለው ከውጪ ዲዛይን ተደርጎና ተወልዶ የተላከልን ነው። እኛ ደግሞ እንደባለቤት ሆነን ከባለቤቶቹ በላይ እርስ በእርስ የተፋጀንበት ሀሳብ ነው። “እናውቃለን ተምረናል” የምንል ሰዎች የተሻለ ለማምጣት ደጋግመን መጠየቅ ሲገባን ያን ማድረግ አልቻልንም። በዚህም በቡድን ተከፋፍለን ለመባላትና እንደአገር ወደኋላ ለመመለስ አስገድዶናል፡፡ አሁንም ይሄ ችግር አለ።

ከአንድ ዓመት በፊት ኢትዮጵያ የጀመረችው አጠቃላይ የብልጽግና ጉዞና ያላትን ትላልቅ ራዕዮች የሚቀናቀኑ ኃይሎች በተቻለ መጠን ምርጫውን አጨናግፈውና እንዳይሳካ አድርገው ኢትዮጵያዊያንን እርስ በእርስ አባልተው “የሽግግር፣ የስብስብ፣ የድርድር” የሚባል ማህበር ፈጥረው መንግሥት ለማድረግ መስራት ከጀመሩ ውለው አድረዋል። እንደአንዳንድ ጎረቤት አገሮች ደካማ መንግሥት ብቻ ሳይሆን “የሚታዘዘውን የሚፈጽም መንግሥት እናደርጋለን” ብለው ሰነድ አዘጋጅተው ማሰራጨት ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ እንደ አዲስ እውቀት የገዙ ወንድሞቻችን በተለያየ አጋጣሚ ምርጫውን በማበላሸት እርስ በእርስ የማይደማመጥና የማይከባበር፣ በጋራ አገር ሊገነባ የማይችል የደካሞች ስብስብ ኃይል በመፍጠር በራሱ ውስጥ በአበልና በተሽከርካሪ ኪራይ የሚጨቃጨቅ መንግሥት እንዲመሰረት ይፈልጋሉ። ይሄ ሀሳብ የኢትዮጵያዊያን ሀሳብ አይደለም፡፡ ከውጭ የመጣ ነው፡፡ ወደ እኛ የላኩት ኃይሎች ፍላጎታቸው ደካማ ሆነን ህልሞቻችንን እንዳናሳካ ነው፡ ፡ የእኛ ህልም ስኬት ለአፍሪካ የሚፈጥረው ነገር አለ። በዚህ አጋጣሚ ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብም እዚህ ላላችሁ አመራር አባላትም መግለጽ የምፈልገው ኢትዮጵያ ውስጥ ከምርጫ በስተቀር የሚሸጋገር፣ የሚደራደር መንግሥት አይፈጠርም። ማንም ሰው ስልጣን መያዝ የሚችለው በምርጫ ብቻ ነው፡፡ ይሄን አውቆ የሚፎካከር ኃይል ሀሳብና አደረጃጀት ካለው ሀሳቡን ሽጦ ህዝብን አሳምኖ እንዲመረጥ መሥራት አለበት። እኛ ደግሞ ምርጫው ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን የምንፈልግ ኃይሎች በተቻለ መጠን አውዱ ለዚያ የሚመች መሆኑን አውቀን መስራት ግድ ይለናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በምርጫ የስልጣን ሽግግርና ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ጠንካራ መንግሥት መፍጠር ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉ ህልሞች እውን አይሆኑም። የጀመርነውን የዴሞክራሲ ጉዞ ያጨናግፉ ይሆናል እንጂ አይሳኩም፡፡ ዴሞክራሲ እንዳይጨናገፍ የጀመርናት ጭላንጭል እንዳትጠፋ፣ ጉዞው ወደኋላ እንዳይመለስ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም፣ ህዝብም፣ መንግሥትም በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት መስራት ይኖርባቸዋል። መንግሥት ከጀመረው መንገድ አውጥቶ ወደለመደው ወደአደገበት ነገር መመለስ ቀላል ነው፡፡ ያ ደም በማፍሰሱ የማንፈልገው የመንግሥት ሥርዓት ዓይነት እንዳይፈጠር ኢትዮጵያዊያን በትብብርና በመደጋገፍ መንፈስ በተቻለ መጠን ለዴሞክራሲ ጉዞ መሰረት የሚጥል

ምርጫ ማድረግ አለብን፡፡ ለዚህ በመንግሥት ኃላፊነት ላይ ያለን ሰዎች ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅብናል፡፡

ሁላችሁም እንደምታውቁት “ኢትዮጵያ ካርታ ላይ ነው ያለችው፤ ውስጧ ፈርሷል። በቀላሉ ልናባላት እንችላለን። ካባላናት በኋላ እንደ አገር መቀጠል ያለመቻል ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ላይ እየፈጠረች ያለውን ተጽዕኖ ማስቆም እንችላለን” ብለው ለሚያስቡ ህልመኞች እድል መስጠት የለብንም፡፡ ይህ እድል እንዳይሆን በጣም ወሳኝ ጊዜ ነው። ከፊታችን ያለው ክረምት በምርጫ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን መፃኢ ዕድል በመወሰን እጅግ ወሳኝ ጊዜ ነው፡፡ የጠላቶቻችንን ህልም በሚያከስም መንገድ ድርብ ኃላፊነት ወስደን ሠርተን ብናሳካው ኢትዮጵያ ታሸንፋለች፡፡ ኢትዮጵያ ካሸነፈች ኢትዮጵያዊያን ተጎጂ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ሩጫው ብልጽግና እንዲያሸንፍ ወይንም ሌላ “ኤክስ” የሚባል ፓርቲ እንዲያሸንፍ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ የሚያደርግ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ለማድረግ ድርብ ኃላፊነት አለብን።

ምርጫው ዴሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊ፣ በህዝብ ተአማኒ ከመሆንም በላይ ለሚቀጥለው የምርጫ ዘመን መሠረታዊ ነገሮችን ማሟላት መቻል አለበት። አሁን አንዳንድ ከምርጫ ቦርድ ጋር የሚነሱ ከሎጅስቲክስ ጋር ያሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ትምህርት ወስደን አምስት ዓመት ተዘጋጅተን፣ የተሻለ ነገርን የምንፈጥርበትን ነገር ማምጣት ይኖርብናል።

እንደምታውቁት በጣም ሰለጠነ በሚባለው አገረ አሜሪካ የተካሄደ ምርጫ ብዙ ችግሮች ነበሩበት። በየቀኑ ሰው ይገደላል። አሁንም እየሞተ ነው፡፡ “ምርጫ ተጭበርብሯል” የሚል ነገር ሳይጀመርም በምርጫው ሂደትም ከምርጫው በኋላም በስፋት ተዛምቷል። የተደራጁ ኃይሎች ባልተለመደ መንገድ ሽብር ለመፍጠር ሞክረዋል፡፡ በብዙ አገሮች የሚታይ በሽታ ነው። አሁን ባለ በማኅበራዊ ሚዲያ ዘመን “ምንም ዓይነት ፈተና አይገጥመንም” ብሎ ማሰብ ሥራን ካለማወቅ የሚነሳ ካልሆነ በስተቀረ ችግር ማጋጠሙ አይቀርም፡፡ በተቻለ መጠን ተግዳሮቱን በመተንበይና ዕቅድ በማውጣት በከፍተኛ ትጋት ከሠራን የተሻለ ነገር ማድረግ ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ የሚፎካከሩ ኃይሎች ደጋግሞ ማሰብ የሚጠበቅባቸው ነገር ስልጣን ለመያዝ ያለው መንገድ አንድ ብቻ መሆኑን ነው፤ እርሱም ምርጫ ነው፡፡ ከዚያ ውጪ ያሉ ህልሞች በሙሉ አይሳኩም። ይህ ብቸኛው መንገድ እንዳይበላሽ፣ እንዳይስተጓጎል በትብብርና በመደጋገፍ መንፈስ መስራት ጥሩ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን ለመያዝ የሚደረጉ ሁሉም ዓይነት የትግል ስልቶች ታግለንባቸዋል ወይንም አሸንፈናቸዋል። አዲስ የትግል ስልት የለም፡፡ እኛን የሚያስገርም፣ የሚያስደንቅ ነገር የለም፤ እናውቀዋለን፡፡ አሁን የሚደረገውን ጨዋታ እናውቀዋለን። የማይሰራ ስልት ነው። የሚሰራው ዴሞክራሲያዊ እና ሰላማዊ የምርጫ ስልት ብቻ ነው፡፡ በምርጫ ህዝብ ከወሰነ በተደጋጋሚ ቃል እንደገባነው ሳናንገራግር ስልጣን በመልቀቅ ኢትዮጵያን አሸናፊ እናደርጋለን፡፡ ከዚያ ውጪ ባለ መንገድ ብዙ ልምድ ስላለን ቅንጣት ታክል ጫና አይፈጥርም። ብቸኛው አማራጭ ምርጫ ነው። በዚህ አማራጭ ደግሞ ሁላችንም በትብብር መንፈስ መስራት ይኖርብናል። ለአገራችን ዴሞክራሲ ያስፈልጋል። ለአገራችን ሰላም ያስፈልጋል። እነዚህን ካላሟላን ብልጽግና አይመጣም። ብልጽግና ካልመጣ ደሃ አገር ደግሞ ስለሙብት ሊያወራ አይችልም። ከስንዴ ልመና ወጥተን በትብብር ለመሄድ ዋነኛው ነገር የወንድማማችነት ስሜት ነው። በህዝቦች መካከል፤ በግለሰቦች መካከል “በጋራ አድገን የጋራ አገር እንፈጥራለን” የሚል እሳቤ ካለ ሰላምም፣ ዴሞክራሲም፣ ብልጽግናም ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ለዚህ እንደ መሪም እንደ ዜጋም እያንዳንዱ በስልጣን ላይ ያለ ኃይል ዘጠና እና ዘጠና አምስት በመቶ ለዚህ ጉዳይ ስኬት ተጨማሪ ጥረት ማድረግ አለበት።

በርግጥ ዴሞክራሲ በመንግሥት ፍላጎት ብቻ ሊፈጠር የሚችል አይደለም። ማህበረሰቡ፣ የሚፎካከሩ ኃይሎች ዴሞክራሲያዊ ባህል ከሌላቸው መንግሥት ስለፈለገ ብቻ አይመጣም። ሁላችንም ስለሚያስፈልገን በትብብር መንፈስ ዴሞክራሲን ለማምጣትና ኢትዮጵያን አሸናፊ ለማድረግ መስራት በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ጸጥታን በሚመለከት የሚነሳው ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት የአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስ በየክልሎቹ ያሉ ልዩ ልዩ የጸጥታ ኃይሎች የዜጎቻቸውን ሕይወት ለመታደግና የኢትዮጵያን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በየቀኑ መስዋዕትነት እየከፈሉ

ናቸው። ህዝብን ለመታደግ በየቀኑ ወታደር ይሞታል። በየቀኑ ፖሊስ ይሞታል። ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ተግዳሮት መንግሥት ህዝብን የሚገድል የሚገፋ ነበር፡ ፡ ያን በትግላችን ቀይረነዋል። አሁን ያለብን ተግዳሮት ኢትዮጵያ እንደ አገር እንዳትቀጥል የሚፈልጉ የተገዙ ሽፍቶች በግራ በቀኝ ሾልከው መከላከያን፣ ፖሊስን አልፈው ንጹሐን ዜጎቻችንን የሚገሉ፣ የሚያፈናቅሉና የሚያጎሳቁሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ኃይሎች ለመከላከልና ለማስቆም መላው አገር ወዳድ ዜጋ ከመከላከያ፣ ከፖሊስ፣ ከመንግሥት ጋር በጋራ መቆም አለበት። በተደጋጋሚ ተጨማሪ የሰው ኃይል እንፈልጋለን። “ኑ እና መከላከያን አጠናክሩ፤ኑ እና ፖሊስን አጠናክሩ” ስንል ያልሰማ ጆሮ በፌስቡክ ቢጮህ ኢትዮጵያን አይታደጋትም፡ ፡ ኢትዮጵያን መታደግ የፈለገ ኃይል እነዚህን ተቋማት ማጠናከር አለበት። በፍቃደኝነት በሕግ፣ በሥርዓት እነዚህን ተቋማት ማጠናከር ያስፈልጋል።

በአንድ ጊዜ በየክልሉ በጣም በርከት ያሉ ቦታዎች ግጭት እንዲፈጠርና ኃይላችን እንዲበተን በዋናነት መከላከል በሚገባን አካባቢ ላይ መቆም እንዳንችል ለሚፈልጉ ኃይሎች ሲሳይ መሆን የለብንም፡፡ ግልጽ ነው፤ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያሰፈሰፈ ኃይል መኖሩ በግልጽ የሚነገር ነው። የሰው ሞትንና መፈናቀልን በትብብር መግታት አለብን። በውስጥ ያሉንን ችግሮች በተቻለ መጠን ቀንሰን ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ብናተኩር ይሻለናል፡፡ ህልማቸው በደቡብ፣ በሰሜን፣ በምዕራብ ጫፎች በትነውን በተስተካከለ ቁመና አገራችንን መታደግ እንዳንችል ማድረግ ነው። ትናንሽ ግጭት በመፍጠር ኃይል መበተን ነው፡፡ የአካባቢ ሚሊሺያ የአካባቢ ማህበረሰብ ግማሹ በመረጃ፣ ከፊሉ አብሮ በመቆም፣ በመከላከያና ፖሊስ በመሳተፍ በፍጥነት ይሔን ነገር ማቆም ካልቻልን በስተቀር የግጭት ፋቲክ ይሆናል፤ የግጭት ቀጣይነት ሁሉንም ያሰለቻል። ሰው በየቀኑ እየሞተ፤ መስዋዕትነት እየተከፈለ መሆኑን እውቅና ካልሰጠ ፋቲክ ይፈጥራል፡፡ ይሄ ሄዶ ሄዶ ልጆቻችንን አገር አልባ ስለሚያደርግ በትልቅ የኃላፊነት ስሜት የጸጥታ ተቋማትን ማጠናከርና አብሮ መቆም ያስፈልጋል። ይሄን በማድረግ በውስጥ ያለ ሰላምን እናረጋግጣለን። ከውጪ የሚቋምጠውን ኃይል እናስቆማለን። አገራዊ ህልሞቻችንን እናሳካለን። ይሄን ማድረግ ካልቻልን አገራዊ ህልሞቻችን ይጨናገፋሉ። አገራዊ ህልም ከተጨናገፈ ተጠቃሚ የሚሆን ኢትዮጵያዊ የለም። ተጎጂ የሚሆነው ቅጥረኛውም ጭምር ነው። አገር አልባ ስለሚሆን፡፡

አሁን ፈተናው ጥቂት ቅጥረኞች ሳይሆኑ “አገር እንወዳለን” የሚሉ ኃይሎች መሰብሰብ መደጋገፍ አለመቻላቸው ነው። “ና መከላከያ ግባ” መልስ የለም፤ “ና ፖሊስ ግባ” መልስ የለም። ቤት ተቀምጦ ሰላምን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ አገሩን የሚወድ ሁሉ በቀጥታ ተሳትፎ ሰላም ማምጣት አለበት። ያ ሰላም ለምርጫም ያግዛል። ከምርጫ በኋላም ለምናስባቸው ጉዳዮች ሰላም ያስፈልገናል። ለዚህም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በቀረው ጊዜ ውስጥ ህገ-መንግስታዊ የሆነ መብቱን ተጠቅሞ እርሱ የሚፈልገውን መንግሥት ለማቋቋም ካርድ መውሰድ አለበት። አንዳንድ ቦታ የምርጫ ጣቢያ መመዝገቢያ ቦታዎች ምቹ አይደሉም፤ ሌሎችም ምክንያቶች አሉ። ነገር ግን ችግሮቹን ተጋፍጦ ካርድ በመውሰድ የሚፈልገውን “ይመራኛል” የሚለውን ኃይል መምረጥ አለበት፡፡ “ይመራኛል” ብሎ በድምፅ የመረጠውን ደግሞ የምንወዳደር ኃይሎች ማክበር አለበን። እኛ ማክበር አለብን። ይሄ ትልቅ መሰረት ይጥላል።

ብልጽግና ሀሳብ ካለው፤ ብልጽግና አገር የሚያሻግር ራዕይ ካለው ያን ሐሳብና ራዕይ በትክክል ለህዝብ መሸጥ የሚችል ከሆነ በየቀኑ የሚያጋጥሙ ችግሮች አካል መሆን የለበትም፤ ማገዝ ነው ያለበት፡፡ ችግር የሚፈጥሩ ሐሳብ የሌላቸው ናቸው። የሚሳደቡ ሐሳብ የሌላቸው ናቸው። “ሐሳብ አለን” ብለን ካመንን ደግፌ አጋዥ ችግር የማንፈጥር መሆን አለብን። ሌላውን ከመክሰስ በፊት በእኛ በኩል ያሉ በየቀኑ የሚታዩ ስንክሳሮች፣ ድካሞች፣ ስንፈቶች ካላረምን በስተቀረ አሁን በሚባለው መንገድ የተሳካ ምርጫ ማድረግ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። የዚህ ሳምንት ውጤት ከሠራን እንደምንቀይር ያሳያል። ካልሠራን ግን ማንን ልንከስ ነው?

ምርጫ ላይ ጸጥታን በሚመለከት በየክልሎቹ ምርጫ የሚካሄድባቸው ቦታዎችን ‘ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ ብለን እንክፈላቸው። “ቀይ” ብለን የምንከፍላቸው የምርጫ ጣቢያዎች ወይንም ክልሎች ካሉ ምንም ዓይነት ችግር በመራጮችና በአስመራጮች እንዳያጋጥም የአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስና የክልል ፖሊስ ተቀናጅተው ይሰራሉ። “ቢጫ” በምንላቸው በመለስተኛ ደረጃ ክልከላ እና ችግር እንዳያጋጥም በክልል ደረጃ ምርጫ ጣቢያዎችን ለመጠበቅ የሚቸገር አይኖርም። እኛ የቸገረን ተደብቆ በሽንቁር እየገባ ዜጎች የሚገል ሽፍታ እንጂ በታወቀ ቦታ ላይ ጠብቀን የምናስበውን ምርጫ ለማካሄድ የሚያስቸግረው

አይደለም። ሪፖርቱም የሚያሳየው ይህንኑ ነው።

የክልሎች አመራር አባላት በሚቀጥለው ስብሰባ ሥራችንን ስንገመግም አሁን የተነሱትና ያልተጀመሩ፣ ያልተመዘገቡ ያልናቸውን ችግሮች ሙሉ በሙሉ ካልጨረስንና የተንጠባጠቡ ጣቢያዎች ካሉ እንደአዲስ አንጀምርም፤ ይሄ የመጨረሻ ሳምንታችን ነው፡፡ ምርጫ ጣቢያ ለመክፈትና ሁለተኛም በስፋት ምዝገባ ለማካሄድ በሚቀጥለው ሳምንት ስንገናኝ “በሆነ ምርጫ ክልል ውስጥ አንድ ጣቢያ አልተከፈተችም” የሚል ሪፖርትም ንግግርም አይኖርም። ያልተከፈተ ጣቢያ ይቀራል ማለት ነው፡፡ ጊዜ የለንም። በዚህ ሳምንት ግን በከፍተኛ ርብርብ ብንሠራ ብዙውን ችግር እናቃልላለን።

አሁን ከብዙዎቻችሁ የቀረበው ሪፖርት የሚያሳየው አበረታች ውጤት ነው። ነገር ግን እንዳትዘናጉ፤ በከፍተኛ ትጋት በየቀኑ እየገመገማችሁ ሥሩ። ሳምንት ስንገናኝ በወሳኝ መልኩ ምርጫውን ለማካሄድ የሚያስችል ሥራ ካከናወናችሁ ምርጫ ቦርድ ከእኛ የሚፈልገው ድጋፍ ነው፡፡ ያን ድጋፍ ለምሳሌ “ሎጀስቲክስ” ተብሏል፤ የምርጫ ቁሳቁስ በሚሰማራበት ወቅት ከዚህ ወደ ዋና ዋና የክልል ቦታዎች የክልል ዋና ከተሞች ሰፋ ያለ ክልል ደግሞ ካለ ዋና ዋና የሚባሉ ቀጣናዎች የፌዴራል መንግሥት ከምርጫ ቦርድ ጋር ሆኖ በአየር ኃይልም፤ በአየር መንገድም ያጓጉዛል። ወደ ዋና ዋና ክልል ቦታዎች ልክ አየር መንገድ ሲደርስ ምርጫ ቦርድ ካቀረበልን በዚያው ተዘጋጅተን ወደ ዋና ዋና ቦታ እኛ እናደርሳለን። በዚያው ዕለት ክልሎች በፖሊስ ተሽከርካሪ ወይም በእናንተ ተሽከርካሪ ሊሆን ይችላል ጥበቃ እያደረጋችሁ ከምርጫ ቦርድ ጋር በትብብር ወደ ዞን ካደረሳችሁ፤ እያንዳንዱ ዞን የክልል ድጋፍ ታክሎበት ወደ ወረዳዎች ካደረሰ ከሦስት ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ መሥራት ይቻላል። ዋናው ዕቅድ ነው። በትክክል በማቀድ፤ ሁላችንም ሥራችንን እንሥራ። ማድረስ ይቻላል፡፡ ግን ትብብር ይፈልጋል፡፡ በእኛ በኩል የሚሰራ ሥራ አለ፤ በእናንተ በኩል እንደዚሁ የሚሰራ ስራ አለ። ይሄን ማድረግ ብትችሉ ምርጫ ቦርድ የሚፈልገውን ማሳካት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው ምርጫ ጣቢያን በሚመለከት በዕለቱ ለሚደረገው ምርጫ እንደተባለው ድንኳን ወይንም ዳስ ለምስጢራዊ ቦታ ለብቻ ለሚታዘቡ ሰዎች በሚመች መንገድ በየጣቢያው ማዘጋጀት ከባድ ስራ አይመስለኝም፡፡ ከወር በላይ ጊዜ አለን፤ የሚያስፈልግ ቁሳቁስ ካለ

እናሟላለን። ባለፈው ክረምት በየክልሉ በሺህ የሚቆጠር መማሪያ ክፍል የሠራ ወጣት፣ የሠራ ህዝብ አሁን በትብብር ለእርሱ ምቹ በሆነ መንገድ ዝናብ ያለበት ቦታ ዝናብ እንዳያስገባ፣ ፀሃይ ያለበት ቦታ ፀሃይ እንዳይመታው በማድረግ፣ በሰልፍ ለሚጠብቁ ሰዎች የሚመች ጥላ አድርጎ መስራት ይችላል፡፡ ይሄን ከወዲሁ አስቦ ማሟላት የምርጫ ቦርድንም ስጋት እና ጭንቀት የሚቀንስ ይሆናል። ክልሎች በኃላፊነት ስሜት ሎጅስቲክስንና የምርጫ ጣቢያ የመምረጫ ቦታን ማዘጋጀት በተመለከተ ብትወስዱት ጥሩ ነው፡፡

ፀጥታን በሚመለከት የፀጥታ ኮሚቴው ግምገማ ሲያደርግ ቆይቷል። የደህንነት ምክር ቤትም ግምገማ ያደርጋል። የምናከናውናቸው አሠራሮች ይኖራሉ። በየክልሉ “ቀይ፣ ቀይ” ብለን የለየናቸው ቦታዎች የፌዴራልና የክልል ጸጥታ ኃይሎች በቅንጅት የሚሸፍኑት ይሆናል፡፡ ስለዚህ አብዛኛው የናንተ ፖሊስ ቢጫ እና አረንጓዴ ያላችሁት ጋር አድርጉ። የፌዴራል ፖሊስ እና መከላከያ ከእናንተ ጋር በመቀናጀት የሚያሰጉ ቦታዎችን ይሸፍናሉ፡፡ ሁለተኛ ረድፍ ያለውም እናንተ እንድትሸፍኑ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚያ የከፋ ነገር ደግሞ ካለ እንደተባለው አሰልጥኖ አዘጋጅቶ ሚሊሺያዎችንም መጠቀም ይቻላል፡፡ ለታዛቢ፣ ለመገናኛ ብዙኃንና ለሚፎካከር ሰው የማይመች፣ ምርጫ ቦርድ እንደፈለገ ሥራውን የማይሠራ ከሆነ ይሄን ሁሉ ቢሊዮን ብርና ጊዜ ማባከን አያስፈልግም። ይሄ ሁሉ ሀብት የሚጠፋው ለድራማ አይደለም። ዴሞክራሲ ለማምጣት ነው። ብዙ ሀብት አፍሰን ስናበቃ በትናንሽ ነገር ምርጫው እንዳይስተጓጎል ሁላችንም በከፍተኛ የሐላፊነት ስሜት ብንሰራ ጥሩ ይሆናል፡፡ ይሄንን ካደረግንና ከተደጋገፍን በቀረበው ሪፖርት መሰረት በሚቀጥለው ሳምንት አመርቂ ነገር ማየት እንችላለን የሚል ግምት አለኝ፡፡

ዩኒቨርሲቲን በሚመለከት የቀረበው ምክረ ሀሳብ የምርጫ ቦርድን እናየዋለን፤ ከሚመለከታችው አካላት ጋር ምን ማድረግ እንደሚቻል ተነጋግረን መልሱን እንነግራችኋለን፡፡ በእኛ በኩል በከፍተኛ ደረጃ የእናንተን ምክረ ሀሳብ ታሳቢ እናደርጋለን። በመንግሥት በኩል ምርጫ ቦርድን በማገዝ፣ በመደገፍ ኢትዮጵያን የሚያሻግር ዴሞክራሲን ለመጀመር የሚያስችል ህዝብ ወዶና ፈቅዶ የመረጠው ኃይል እንዲያስተዳድረው ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን፡፡ ይሄን ማድረግ ሥራችን ነው።

ዜጎች በሰላም የምርጫ ካርድ አውጥተው መብታቸውን የመጠቀም ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል። እያንዳንዱ ሰው ምርጫ ካርድ ወስዶ የራሱን ሀሳብና ፍላጎት ለመምረጥ መወሰን መቻል አለበት። እስካሁን ለሚፎካከሩ ፓርቲዎች አውድ ለማስፋት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ትናንሽ የማያሻግሩ ስልቶች ሲከተሉም አይተናል። በተለያየ መንገድ የጨረቃ ምርጫ ለማካሄድ፣ ለማሸበር የሞከሩ ኃይሎችም ሲጠፉ አይተናል። ለእነርሱ ያለኝ ምክር ወደ ስልጣን ኮርቻ የሚወስዳችሁ መንገድ ሰላማዊና ዴሞክራሲያው ምርጫ ብቻ ነው፡ ፡ ከዚያ ውጭ ያለው መንገድ የመንግሥት አካሄድ ይቀይር ይሆናል እንጂ እናንተን ወደ ስልጣን አያመጣችሁም። ያ እንዳይሆን ደጋግማችሁ በምክንያት አስቡ። በተቻለ መጠን ስሜታችሁን ተቆጣጥራችሁ በምክንያት አስቡ።

ይሔ ምርጫ ያስፈልገናል። በምርጫ፣ በሀሳብ አሸንፉ፤ የገባነውን ቃል እናሳያችኋለን። ከዚህ ውጪ ያሉ አማራጮች ግን ኢትዮጵያን ይጎዳሉ። እናንተንም በጣም እንደሚጎዳ ታሳቢ ብታደርጉ መልካም ነው፡፡ አንዳንድ በምርጫው አካባቢ በቀጥታ በመምረጥ ባለመምረጥ ተሳትፎ የሌላቸው ባለድርሻ አካላት ደግሞ ግጭትም ይሁን ድካሞች ሲኖሩ በምክንያት ቆሞ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ምንድን ነው የሆነው? እንዴት ነው የሆነው? መቼ ነው የሆነው? የሚሉ ጥያቄዎች ሳንጠይቅ እና በቂ ምላሽ ሳናገኝ እንዲሁ በደቦ የምናደርጋቸው ነገሮች ኪሳራ ናቸው፤ ጥፋት ያመጣሉ። በየክልሉ ፖሊስ እየሞተ፣ በየክልሉ መከላከያ እየሞተ፣ መንግሥት ያን ለመምራት ቀን ከሌት እየሰራ በቂ ድጋፍ ሳናደርግ ተጨማሪ ፍላጎት ብናቀርብ ያጠፉናል እንጂ ጥቅም የለውም፡፡ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ማየትና ማስተዋል ያስፈልጋል። ይሄን ጉዳይ ለአገራችን፣ ለልጆቻችን ያለውን ጠቀሜታ ማሰብ ከሁላችንም ይጠበቃል።

የክልሎች አመራር አባላት አልፎ አልፎ የሀሳብ ድህነት ሲያጋጥም ስድቦች፣ ርግማኖች፣ አላስፈላጊ ቃላት እዚህም እዚያም ሊታዩ ይችላሉ። ሰሞኑን ስንነጋገር እንደነበረው ማስተዋል ያለብን ነገር እኛ የተሸከምነው ኢትዮጵያን ነው፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ነው። ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊያንን ለማሻገር አይደለም ስድብ የሕይወት መስዋዕትነትም ቢጠይቅ ዝግጁ መሆን አለብን። ትንሽ ነገር ባየን ቁጥር አኩርፈን መጥፎ ነገር የምንከተል

ከሆነ ጥፋት ነው፡፡ መማር ከፈለግን ጥሩ ጥሩውን እንማር። ሌላ ቦታ መጥፎ ነገር ካየን "አይበጅም" ብለን መተው እንጂ በስሜት ያን መንገድ መከተልና ሌላ ጥፋት መሥራት አይጠቅመንም። ከስሜት እንውጣ፤ በምክንያት እናስብ። ኢትዮጵያዊያን መሸጋገር ይፈልጋሉ። ኢትዮጵያዊያን በህብረት መለወጥ ይፈልጋሉ። ኢትዮጵያዊያን ከድህነት መውጣት ይፈልጋሉ። ጥያቄ የለውም፡፡ ከጫፍ ጫፍ ኢትዮጵያን ከእኛ በተሻለ የሚያውቅ የለም። ኢትዮጵያን ሳያውቅ ሰፈሩ ተቀምጦ ነው የሚፎክረው። ከእኛ በተሻለ ከጫፍ ጫፍ የኢትዮጵያዊያንን ስሜት የሚያውቅ የለም። ተባብረን ይቺን አገር ማሻገር አለብን፡፡ ከዚህ ውጪ ያለውን በሕግ አግባብ ህጋዊ እርምጃ እየወሰድን ማስተካከል ከሁላችንም ይጠበቃል። ሽግግሩ የሚረጋገጠው ሁሉም ሰው በሕግና በዴሞክራሲ ብቻ ከሰራ ነው፡፡ ከዚያ ውጪ ያለውን በሕግ አግባብ እርምጃ እየወሰዱ ማስተካከል ያስፈልጋል።

ለክልሎች አመራር አባላት ዋናው መልዕክቴ ይህ ሳምንት ወሳኝ የሥራ ጊዜ ነው። ስሜትን፣ አላስፈላጊ ትምህርትን በመተው በምክንያት፣ በትብብር ሙሉ ኃይላችሁን ተጠቅማችሁ ምርጫ ቦርድን ብታግዙ በእርግጠኝነት በሚቀጥለው ሳምንት በወሳኝ መልኩ ምርጫ ለማካሄድ ብቻ ሳይሆን የተሻለ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችል የሥራ ሪፖርት እናደምጣለን፡፡ ከዛሬ ጀምሮ የጸጥታ ኮሚቴውም ሆነ የምርጫ ኮሚቴው በቅርበት ከምርጫ ቦርድ ጋር እየተነጋገረ አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

ስጋት እንዳይፈጠርብን የምፈልገው ከግራ ከቀኝ  በጣም ብዙ ፈታኝ ተግዳሮቶች አሉ። በየቀኑ የምንሰማው ክፉ ዜና ነው። በየቀኑ የምንሰማው እሳት ማብረድ ነው። በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ግን አሁን እየገጠመን ያለው ፈተና ከመጣንበት አኳያ ኢምንት መሆኑን ነው፡፡ የመጣንባቸው ፈተናዎች ከባድ ነበሩ። አሸንፈናቸዋል። ይሄንንም እናሸንፋለን፡፡ ሰላም እናረጋግጣለን፣ ብልጽግና እናመጣለን፤ ኢትዮጵያን እናስቀጥላለን። ከዚህ ቀደም እንደሆነው ይሄን የማይፈልጉ ኃይሎች ይቀበራሉ፤ ዋጋ እንከፍላለን። መስዋዕትነት እንከፍላለን። ከባድ ፈተና ይገጥመናል። ነገር ግን ኢትዮጵያ ትሻገራለች። ይሄን አስበን በከፍተኛ ኃላፊነት ስሜት ብንሰራ መልካም ውጤት ልናመጣ እንደምንችል ይሰማኛል። የተቀመጡትን ሶስቱን የምርጫ ቦርድ ሀሳቦችና አሁን የተቀመጠውን ወስዳችሁ መለስተኛ እቅድ አዘጋጅታችሁ

በየቀኑ እየገመገማችሁ ከሠራችሁ በኋላ የሚቀጥለው ሳምንት መጨረሻ ውጤቱን ዓይተን የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት የምንገባበት ይሆናል። በዚህ ሳምንት ስለተሠራው ሥራ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። በሚቀጥለው ሳምንትም እንደሚደገም ተስፋ አደርጋለሁ።

**መልካም የስራ ጊዜ ይሁንላችሁ!**

**ግንቦት፣ 2013 ዓ.ም**





## እንኳን ለ1442ኛው ዒድ አል ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

“ዒድ አል ፈጥር” በቅዱሱ ረመዳን ወር መጨረሻ እና በሻወል ወር የመጀመሪያ ቀን ላይ የሚውል የጾም ወር ማጠናቀቂያ ታላቅ በዓል ነው። ሕዝበ ሙስሊሙ ወሩን ሙሉ በጾምና በስግደት፣ እንዲሁም በመልካም ተግባራት አሳልፎ ከፈጣሪ የመጨረሻውን ምንዳዕ የሚቀበልበት ልዩ ቀን ነው። በዒድ ዕለት ሕዝበ ሙስሊሙ ሰብሰብ ብሎ የዒድ ሶላት ይሰግዳል። ይሄም የመሆኑ ምክንያት በመሰባሰብ ውስጥ አንድነት፣ በመሰባሰብ ውስጥ ኅብረት፣ በመሰባሰብ ውስጥ ጥንካሬ መኖሩን ለማመልከት ነው። ለብቻ ከሚሰገደው በላይ በጀምአ መስገድ ከአላህ ብዙ እጥፍ ምንዳዕ እንደሚያስገኝ በእስልምና ይታመናል። “የአላህ እጅ ሰብሰብ ባሉ ሰዎች መሐል ይገኛል” ሲል የእምነቱ አስተምህሮም ያስረዳል።

ሰብሰብ ብሎ ሶላት መስገድ የበዛ በረከት እንደሚያስገኝ ሁሉ፥ ተሰባስቦ ለአንድ ዓላማ መሥራትም በቃላት የማይገልጽ ተአምራዊ ውጤት አለው። በመሰባሰብ ውስጥ መደጋገፍ፣ በመሰባሰብ ውስጥ ብርታት፣ በመሰባሰብ ውስጥ አጋርነት አለና። አንዱ የሌላውን ክፍተት የመሸፈን ዕድል የሚገኘው በዚህ መሰባሰብ ውስጥ ነው። ለብቻ ሶላት ሲሰገድ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ትኩረት ተሰርቆ ለፈጣሪ የሚደርሰው ምስጋና ምሉዕ ስለማይሆን ጭምር ነው የእምነቱ አስተምሮ በመሰባሰብ፣ በጀምአ መስገድን የሚያበረታታው።
የዘንድሮውን ዒድ አል ፈጥር የምናከብረው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በላይ በርካታ ፈተናዎች እንደተደቀኑባት እያስታወስን ነው። መዋኛችን ድፍርስ፣ መንገዳችን እሾህ የበዛበት መሆኑን እናውቃለን። በመንገዳችን ላይ እንቅፋቶችን የሚያኖሩ፣ ወደኋላ የሚጎትቱ፣ ተስፋችንን ሳናይ በፊት ተሰብረን እንድንወድቅ መሠረታችንን የሚገዘግዙ ኃይሎች፣ ከውጭም ከሀገር ውስጥም በርትተው የመጡበት ፈታኝ ጊዜ ነው።

ነገር ግን ተገዳዳሪዎቻችን ያልተረዱት አንድ ሐቅ አለ። በፍቅር እንጂ በኃይል እንደማንንበረከክ፣ ለእውነትና ፍትሕ እንጂ ለመደለያ እንደማንገዛ እና ሀገራዊ ክብርና ጥቅምን አሳልፈን እንደማንሰጥ ታሪካችን ምስክር ነው። የማንንም ሐቅ የማንሻ ሕዝቦች፣ የፍቅር እጃችን ብሎ ለሚመጣው እንግዳ አክብረን ተቀባይ፣ ለሚሳደደው መሸሸጊያ ጥላ ስለመሆናችን ከነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) እና ተከታዮቻቸው የተነገረልን የምስክርነት ቃል ከበቂ በላይ ነው። በታሪካችን ውስጥ ያኖርነውን ደማቅ አሻራ ሁሌም ሲያንጸባርቅ ይኖራል። እኛ ሌላ ማንም አይደለንም። የእናት አባቶቻችን ልጆች ነን። ቀደምቶቻችን ያቆሙልንን መልካም ስምና ጀግንነት ለማጠንከር እንጂ ለመናድ አልመጣንም። ተገዳዳሪዎቻችን ምንም

ያህል ቢለፉ ጸንተን ለመቆም መወሰን አለብን። ክፉውን ጊዜ እንደ ዒድ ሶላት ሰብሰብ ብለን ልንጋፈጠው፣ የአንድነታችንን ልክ አሳይተን ልናልፍ ይገባል። በኅብረታችን የሚገጥሙንን ፈተናዎች እንደ ምንሻገራቸው ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያውያን እድል በእኛው እንጂ በሌላ በማንም እጅ እንዳልሆነ ለዓለም ማሳየት ይኖርብናል።

ውድ ወገኖቼ፣

የእስልምና አስተምህሮ እንደሚገልጸው አንድ ሰው ለራሱ ጥቅም ብቻ ቢኖር ሕይወቱ ትርጉም አይኖረውም። የሚኖርበት ማኅበረሰብ ተርቦ እሱ ጠግቦ ቢውል፤ ጎረቤቶቹ ተረብሸው እሱ ሰላም ቢሆን፣ ሀገሩ ተቸግራ እሱ ቢደላው፣ በዙሪያው ርኩስ ተግባራት በዝተው ስለእሱ ብቻ ቅድስና የሚያስብ ከሆነ ከአላህ ፈጽሞ እዝነትን አያገኝም። የእሱ ጻድቅ መሆን ሕዝብና ሀገርን ካላጸደቀ፣ የእሱ ከፍ ማለት ሀገርና ወገንን ከፍ ካላደረገ፣ የእሱ ስኬት ሀገርንና ማኅበረሰብን ስኬታማ ካላደረገ አላህን ማገልገሉ ብቻ ጽድቅ አያስገኝለትም። ይልቁኑም ለራሱ ብቻ የኖረ ሰው ቀድሞውን ባይወለድ እንደሚሻለው የእምነቱ ሊቃውንት ያስቀምጣሉ።

አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታም ለግላችን ሳይሆን ለጋራ ህልውናችን እንድናስብ የሚያስገድደን፣ ከግል ምቾታችን በላይ ለጋራ ደኅንነታችን እንድንተጋ በእጅጉ ግድ የሚልበት ጊዜ ነው። በሕዳሴ ግድብ እና ከፊታችን ባለው ምርጫ ምክንያት ሀገራችን ፈተናዎቿ በዝተው አይተናል። እነዚህ ሁለቱን ማሳካት ለእኛ ቀላል የማይባል የስኬት በሮችን እንደሚከፍቱልን እናውቃለን። ምርጫውን በስኬት ማከናወን አዲስ የዴሞክራሲ ምዕራፍ እንደሚከፍትልን ግልጽ ነው። የሕዳሴ ግድብ መጠናቀቅም ግዙፍ የብልጽግና ፋና እንደሚለኩስልን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያውቃል።

ሀገራችን ለዘመናት የተቆለሉባትን ችግሮች ፈቀቅ በማድረግ ከሌሎች ጥገኝነት ነጻ እንደሚያደርገን፣ ብሎም በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ያለንን ተቀባይነት በማሳደግ በኩል ሁለቱ ግዙፍ ፕሮጀክቶቻችን ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን እኛ ብቻ ሳይሆን የዘመናት ተገዳዳሪዎቻችንም ጠንቅቀው ያውቁታል። ተከታታይ ትንኮሳቸውም ከዚያ የመነጨ ነው።

እነዚህን ትንኮሳዎች በመመከት በኩል ጥቂት የማይባሉ አርቆ አስተዋይ ዜጎቻችን በሀገር ውስጥና በውጭ መድረኮች ትልልቅ ጀብዱዎችን እየፈጸሙ ይገኛሉ። ለጋራ ጥቅማችን ሳይሰስቱ ተሟግተዋል፣ ሐቃችንን ለዓለም ተናግረዋል። የእነሱ ትጋት በገንዘብ የማይተመን ጥቅም ለኢትዮጵያ ቢያስገኝም፣ የእነሱ ጥረት ብቻውን ፍሬ እንዲያፈራ ዐውቀን በጉዳዩ ላይ

ሌሎቻችንም እንድንረባረብ ይጠበቃል። "ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ" እንደሚባለው፣ በሕዳሴ ግድብና በሌሎች ሀገራዊ ጥቅሞቻችን ላይ እንደ ችሎታችን የበኩላችንን ብንታገል ለዘመናት የሀገራችን ችግሮች ፈውስ የሚሆን አቅም መፍጠር እንችላለን።

በቅዱስ ቁርዐን ላይ፣ «ሁላችሁም በአንድነት ሳትከፋፈሉ እመኑ! አላህ ያደረገላችሁን አስታውሱ፣ ልቦቻችሁን የሰበሩ ጠላቶቻችሁ ቢሆኑም እንኳ በአላህ ፈቃድ ወንድም ሊሆኑዋችሁ ይችላሉ» በማለት በአማኞች መካከል አንድነትንና ፍቅርን፣ የእርስ በርስ መረዳዳትን እና መደጋገፍን አስፈላጊነት በደማቁ ሠፍሯል። እያንዳንዳችን የተለያየ የፖለቲካ እምነት ሊኖረን ይችላል። ያለችን ግን አንድ ሀገር ናት። የተለያየ አመለካከት እናራምድ ይሆናል። ያለን ግን፣ አንድ ሕዝብ ነው። ችግራችንም አንድ ነው - ድህነት እና ኋላ ቀርነት! ምንም ትልቅ ታሪክ ቢኖረን፣ ምንም ትልቅ ሕዝብ ቢኖረን በኢኮኖሚ፣ በዴሞክራሲ፣ በቴክኖሎጂና ጥቂት በማይባሉ ሌሎች የሥልጣኔ ዘርፎች ከኋላ ተከታዮች መካከል የምንመደብ ነን። ይሄንን ኋላ ቀርነታችንን ለማሸነፍ መጀመሪያ እርስ በእርሳችን እንዋደድ፣ ሀገራችንንም እናስቀድም። እርስ በእርስ ስንተሳሰብና ሀገራችንን መውደድ ስንጀምር እምነታችንም የበለጠ ሙሉ ይሆናል።

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) በአንድ ሐዲሳቸው፣ "ለሀገርህ ያለህ ፍቅር፣ የእምነትህ አንድ አካል ነው" ብለው እንደ ነበረ ማስታወስ ተገቢ ነው። በሌላም ጊዜ፣ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) "ድንበር ላይ እያሉ፣ በእንቅልፍ ሳይሸነፉ ሀገርን አላህ በሚወደው መንገድ መጠበቅ፣ ከሁሉም ምድራዊ ጸጋዎች የላቀ ጸጋ ነው" ስለማለታቸውም፣ የእምነቱ ሊቆች ያስተምራሉ።

በዒድ አል ፈጥር በዓል ዋዜማ ላይ ሆነን ስለ ምሕረት፣ ስለ ይቅርታ እና ስለ ፍቅር እንጂ፣ ስለ ጠብና ጥላቻ ማሰብ ያስቸግራል። ቀጣይ ጊዜያትም ስለ አንድነት እንጂ፣ ስለ መለያየት የምንዘምርባቸው ጊዜያት እንደማይሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ። በተቀደሰው የረመዳኑ ወር ለሀገራችሁ ጸጋና በረከት፣ ሰላምና ፍቅር እንደ ጾማችሁና እንደ ጸለያችሁ ሁሉ፥ በክብረ በዓሉም፣ ከዚያ ወዲያ ባሉት ቀናትም ለሀገራችንና ለሕዝባችን ዱዐ ማድረጋችሁን እንድትቀጥሉ በትሕትና እጠይቃለሁ። በዚህ ጊዜ ክፋትን አርቀን መልካምነትን፣ ጠብና ጥላቻን ንቀን በምትኩ እርቅና እዝነትን በሀገራችን ብናነግሥ ምድራዊ ረድኤቶች ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ምንዳዎች በዝተው እንደሚጠብቁን አልጠራጠርም።

ጠብን ለሚዘሩ፣ ከሌሎች ወንድም እኅቶቻችን ጋር ግጭት ለሚጠነስሱ፣ ቁስላችንን በማከክ ለሚያደሙ ዕድል አንስጣቸው። እኛ ከፍቅር እነርሱ ከጠብ፣ እኛ ከአንድነት እነርሱ ግን ከመለያየት፣ እኛ ከድልድይ እነርሱ ግን ከአጥር፣ እኛ ከሀገር እነርሱ ግን ከመንደር

እንደምናተርፍ አንርሳ። ለዛሬ ብለን ነገን ከምናበላሽ፣ ለነገ ስንል ዛሬን እንሠዋ። የሰላም፣ የደስታ፣ የተስፋና የበረከት ዒድ እንዲሆን ተመኘሁ።

**ዒድ ሙባረክ!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና**
**ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**

ግንቦት 4፣ 2013 ዓ.ም

# የሰመራ ኢንዱስትሪ ፓርክ ፊር ቀዳጅነት የተንጸባረቀበት ሥራ

በኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነት ላይ እንኳን ህዝቡ ግመሎቿ በማይደራደሩባት፣ የሉሲ፣ የበርካታ ሀብት መገኛ ምንጭ እና የበረሃ ፈርጥ በሆነችው ከተማ ላይ እንደዚህ ዓይነት ፕሮጀክት ጀምረን በመጨረስ በጋራ ለማየት በመቻላችን ከፍተኛ ደስታ የተሰማኝ መሆኑን እገልጻለሁ፤ "እንኳን ደስ አላችሁ" እላለሁ።

ልማት አፋርንና ሌሎች ክልሎችን፣ ኢትዮጵያንና ጎረቤት አገሮችን የሚያገናኝ መሆኑ ግልጽ ነው። ዘመናዊ ልማቶች፣ ኢንዱስትሪዎችና ፋብሪካዎች ወደ አፋር በማምጣት የኢትዮጵያ ምስራቅ በር ድልድይ የሆነችውን ክልል መቀየር አስፈላጊ ነው። ይህ ደግሞ የእኛም የመላው አፋር ህዝብ ቀዳሚ መሻትና ዓላማ መሆኑን እንገነዘባለን።

ዛሬ ያየነው ድንቅ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መላው የአፋር ህዝብና የክልሉ አመራር አባላት ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመተባበር መሰል ፕሮጀክቶችን ጀምሮ ሪቫን በመቁረጥ ለህዝባችን ተስፋና ስንቅ መሰነቅ እንድትችሉ በታላቅ ትህትና አደራ እላችኋለሁ።

አፋር ውስጥ ያለውን እጅግ ምቹ የሆነና የተንጣለለ መሬትን በዘመናዊ የመስኖ እርሻ ብናለማ ለአፋር ብቻ ሳይሆን የተቀረውን የአገራችንን ክፍል መመገብ እንችላለን። በጨው ምርት፣ በፖታሽ እንዲሁም በሌሎች ማዕድናት እጅግ የበለጸገ፣ ታታሪ፣ ትጉህ ሠራተኛና አገር ወዳድ ዜጎች ያሉበት ክልል ነው። ለኢትዮጵያ ተጨማሪ ገቢ ከምናስገባባቸውና በፍጥነት ብልጽግናችንን ከምናረጋግጥባቸው ምቹ የልማት ክልሎች አንዱ ነው። ይህንን በመገንዘብ የክልሉ አመራር አባላትና ወጣቶች "ሁሉም ነገር ወደ ልማት፤ ሁሉም ነገር ወደ ብልጽግና" እንዲሆን ይበልጥ ቀበቷችሁን ጠበቅ አድርጋችሁ ወደ ስራ እንድትሰማሩ፣ ወደ እናንተ የሚመጡ ኢንቬስተሮችን በደስታ እንድትቀበሉና እንድታስተናግዱ አደራዬ ጥብቅ ነው።

ሁላችሁም እንደምታስታውሱት የዛሬ ዓመት ገደማ የተጀመረው ይህ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሁሉንም አዲሶቹን መመዘኛዎች (standard) አሟልቷል። እጅግ ያማረ ግቢ እንዲሁም ዛፎችና አበባዎች አሉት። ፓርኩ ቢሰራበት የሚያምር፣ ይበልጥ ዛፎች እየተከልንና እያሳመርን ከሄድን ለኑሮ ምቹ የሆነ አዳዲስ የኢንዱስትሪ መንደሮችን ለመፍጠር የሚያስችል ፈር ቀዳጅ ተግባር እንደሆነም አይተናል። በዚህም እኔም፣ የፌዴራል መንግሥት ካቢኔ አባላትም እጅግ ደስታና ኩራት ተሰምቶናል። ከሁሉ በላይ ይሄንን ሥራ አቅደው የሠሩትና ለምርቃት ያበቁት የአዲሱ ትውልድና የነገይቱ ኢትዮጵያ መሪዎች የሆኑት ሁለቱ ቁልፍ አመራር አባላት ሳንዶቃን ደበበ እና ለሊሴ ነሜ - እንኳን ደስ አላችሁ!

በአሁኑ ወቅት ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት ታሪክ የሌላቸውና በንዋይ ብዛት የሚያስቡ አንዳንድ አገሮች ኢትዮጵያ ጠዋት ቁርሷን ምን መብላትና ማታ ምን ለብሳ መተኛት እንዳለባት "ካልነገርናት፤ ካላስተማርናት" እያሉ ነው። እናንተ የኢትዮጵያ ፈርጥ፣ የኢትዮጵያዊነት ምስጢር ናችሁ። እኛ ታሪክ ያለን ታሪካችን ደግሞ በአባቶቻችን የተሠራ ዛሬ፣ በህብረት፣ በትብብር ያማረ ነገን የምንፈጥር፣ ያልተገዛንና የማንገዛ፣ ያልተንበረከክንና የማንንበረከክ ነን። የእኛ ልማትም ጥፋትም በመሰረታዊነት የሚወሰነው በኢትዮጵያዊያን ብቻ መሆኑን ያልተገነዘቡ፣ በምግብ ራሳችንን ለመቻልና ከወረቀት፣ ከሃሳብና ከስንዴ ልመናዎች ለመገላገል የምንጥር መሆናችንን ያልተገነዘቡ አገሮች ምን ማድረግ እንዳለብን ሊነግሩን ይዳዳቸዋል።

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ በበቂ ደረጃ በልቶ የሚደፋው፣ ለሌላ የሚረዳው ምግብ የሌለው ሊሆን ይችላል። በበቂ ደረጃ የሚተረክ ታሪክና ክብር፣ የሚያኮራ ማንነትና ነጻነት ያለው ህዝብ ነን። ከዚህ በላይ ግን ዘመናዊ ቅኝ ግዛት ሊያመጡብን የሚፈልጉና ምን ማድረግ እንዳለብን እንኳን እንደማናውቅ የሚያስቡ አገሮች መኖራቸውን መገንዘብ ይገባል። በፖለቲካ፣ በሃይማኖት፣ በብሄር ሳንከፋፈል ኢትዮጵያዊያን ነጻ የነበርንና ነጻ በመሆን የምንቀጥል፣ በልጽገን ለዓለም ምሳሌ እንደምንሆንም የምናውቅ ህዝብ ነን።

ዴሞክራሲን የምናውቅ በተገቢው ያልተናገርን፣ ህብረት ትብብርን የምንረዳ በተገቢው መንገድ ያልገለጽን ነን። በሃይማኖት በጋራ መኖር ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሃይማኖት

የመጀመሪያው ወራት ተቀባዮችና አሸጋጋሪዎች መሆናችን የሚታወቅም ነው። በመንግሥት ሥርዓት ከብዙዎች ቀድመን የነበርንና ለዘመናት የኖርን ነን። ኢትዮጵያዊያን ለመልማት ያለን ቁርጠኝነት በሌሎች በጎ ፈቃድ ላይ የተወሰነ ሳይሆን፤ በራሳችን ትብብርና ውሳኔ ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆኑን በተግባር የምናሳይበት ወሳኝ ጊዜ አሁን ነው። አሁን ባሉ ፕሮፖጋንዳዎች፣ የመገናኛ ብዙኃን ዘመቻዎች ማስፈራራት ሳንንበረከክ፣ ተስፋ ሳንቆርጥ በሁሉም ሜጋ ፕሮጀክቶቻችን ሪቫን እየቆረጥን ኢትዮጵያዊነትን ለዓለም በድጋሚ የምናሳይበት ጊዜ ነው። ኢትዮጵያዊያን እንድትበረቱ፣ አንድ እንድትሆኑ ለዓለም "ኢትዮጵያዊነት" ማለት "ነጻነት እና ክብር" መሆኑን እንድታሳዩ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ።

ይህ ፕሮጀክት ኮሮናን የሚያክል ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሞን፤ በአገር ውስጥ እዚህም እዚያም ከፍተኛ ግጭቶች ባሉበት ወቅት ሳንቆም በገባነው ቃል መሰረት ያሳካነው ነው። ይሄንን ፕሮጀክት ብቻ ሳይሆን በአገር ደረጃ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ቃል ገብተን "እንሰራለን፤ እንፈጽማለን" ብለን ያስቀመጥናቸው ፕሮጀክቶች በጊዜና በጥራት ሳይዛነፉ የመጨረስ ልምምድን ኢትዮጵያ ውስጥ አስተዋውቀናል። በቀጣዩ ዓመታትም ያለ ምንም ጥርጥር የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና እና ሰላም ለማረጋገጥ በቂ ልምድ፣ ብቃት አካብተን ወደፊት እንገሰግሳለን። ይሄን ለማስቆም የሚችል ምንም ምድራዊ ኃይል እንደሌለ አረጋግጥላችኋለሁ።

እኛ አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት፣ ከእስካሁኑ በተሻለ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማድረግ ባለን ቁርጠኝነት የወሰነውን ውሳኔ የማንም ፍቃድ የማያስፈልገን፣ የኢትዮጵያን መንግሥትና ምርጫ የሚወስኑት ኢትዮጵያዊያን ብቻ መሆናቸውን በድጋሚ አረጋግጣለሁ።

በመጨረሻም ወሳኝ የልማት ድልድዮች የሚገነቡበትና ሪቫን እየቆረጥን ተስፋ የምንሰንቅበት፣ ጠላቶቻችንን ተስፋ የምናስቆርጥበት ወራት ከፊታችን መኖሩን መገንዘብ ይኖርብናል። ስለዚህ ከምንም በላይ ለጠላት ፕሮፖጋንዳ፣ ለጠላት ማስፈራሪያና መደለያ ጆሮ ሳንሰጥና ልባችን ሳይከፈት በትብብር፣ በአንድነት ስሜት ይቺን ታላቅ አገር ወደነበረችበት ክብርና ብልጽግና ለመውሰድ በትብብር መንፈስ መስራት አለብን።

የኢትዮጵያ መንግሥት ኮንትራቱን እስኪጨርስ ድረስ በኢትዮጵያ ክብርና ነጻነት ላይ ከማንም ኃይል ጋር አይደራደርም። መንግስት ኢትዮጵያን ከነክብሯ ከነነጻነቷ ወደ ብልጽግና ለማሸጋገር ቁርጠኛ ነው። በዛሬው አስደሳች የኢንዱስትሪ ምርቃት የተገኛችሁ በሙሉ “እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ አለን” ተመሳሳይ ድሎች ይቀጥላሉ።

**ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች!**

**በጋራ እንሻገራለን!**

**ሌሎችንም እናሻግራለን!**

**ግንቦት፣ 2013 ዓ.ም**

# የኢትዮጵያን ክብር እና ዝናዋን የምናጎናጽፍበት - ሳምንት

በዚህ የኢትዮጵያ ሳምንት ለኢትዮጵያ ድምቀት፣ ለኢትዮጵያ ክብር እንኳን አደረሳችሁ።ኢትዮጵያን ለማልበስ፣ ከኢትዮጵያም ለመልበስ "እንኳን አደረሳችሁ! እንኳን ደስ አላችሁ!"።

ቀደም ሲል ከጎንደሬዋ ሂሩት "ኢትዮጵያ" የሚለው ድምጽ ሲንቆረቆር፣ ከሱማሌዋ ፊልሰን "ኢትዮጵያ" ሲንቆረቆር፣ ከአፋሯ አይሻ "ኢትዮጵያ" ሲንቆረቆር ሰምተናል። ኢትዮጵያ እንደዚህ ነች። ከሁላችን አፍና ልብ ልትወሰድ የማትችል፣ ሁላችንም የምንኮራባት፣ የሁላችንም የኩራት ምንጭ ነች።

ኢትዮጵያዊያን በአገራችን የምንኮራ ብቻ ሳይሆን ለብዙ አገሮች የኩራት፣ የጀግንነትና የብልጽግና ምሳሌ መሆን የምንችል ነን። በአህጉራችን ያለውን ችግር ለማቃለል ዛሬም እንደ ትናንቱ አገራችን ፈር ቀዳጅ ሆና ሥራዋን እንደምትጀምር እና መፈጸም እንደምትችል የምናሳይበት በር መክፈቻ ንግግር ስለሆነ በድጋሚ - እንኳን ደህና መጣችሁ!

እንግዲህ ሚኒስትሮቹ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሳምንት ብዙ ኢትዮጵያዊያን ኢትዮጵያን አያውቋትም፤ ኢትዮጵያ በየአንዳንዱ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊ ማንነት የተገመዱ፣ በሚያስደንቅ ባህል፣ በተፈጥሮና ሠው ሰራሽ ሀብት የተሳሰሩ ዜጎች ያሉባት ናት። አንዱ ለአንዱ ግብዓት የተሟላ ጸጋ ይታይባታል። ይህን ዛሬ በዚህ ስፍራ የተገኘን ሰዎች በድጋሚ ያረጋገጥን ይመስለኛል። በእያንዳንዱ ክልል የሚታየው ባህል፣ ቅርስና ጠንካራ መስተጋብር የማፅድን ብዛት፣ የእርሻ ምርት ኢትዮጵያን ለምንወድ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ሳያውቁ ለጠሏትም ጭምር ጥሩ ትምህርት የሚገኝበትም ነው።

በዚህ ሳምንት ሁላችሁም በመምጣት ከኢትዮጵያ ጋር በመተዋወቅ፣ ኢትዮጵያን በመልበስ፣

ክብር እና ዝናዋን መልሰን ለሚያውቁም ለማያውቁም የምናጎናጽፍበት ሳምንት ነው። በተለይም ተማሪዎች እና ታዳጊዎች ወደዚህ ስፍራ በመምጣት አገራችሁን ለማወቅ ጊዜ እንድትሰዉ ይሁን። በዚህ ስፍራ ቀን ብቻ ሳይሆን ምሽትም ዘለግ ያለ ጊዜ እንደሚኖር ተስፋ አደርጋለሁ። እያንዳንዱ በታሪክ ኢትዮጵያን ለማወቅ ፍላጎት ያለው የመገናኛ ብዙኃን እዚህ በመምጣት የሁላችንንም ባህል፣ የሁላችንንም ታሪክ በእያንዳንዳችን ክልል ውስጥ ያለውን ሃብት ለማበልጸግ በጋራ እንድንሰራ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም እነዚህ ሶስት እንስት ሚኒስትሮች ይሄንን ሃሳብ ጀምረው ስለጨረሱ፤ እንደዚህ ባለ ሁኔታም ስላሰባሰቡን በኢፌዴሪ መንግሥት እና በራሴ ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

መልካም የኢትዮጵያ ሳምንት ይሁንልን!

ሁላችሁም እንደምታዩት “አገራችን” ከሚለው ቃል ወጥተን “ኢትዮጵያ” የሚለውን ቃል መጥራት ከጀመርን በኋላ የጥቁር ህዝቦች ሁሉ የኩራት እና የነጻነት ምንጭ የሆነው ስም በእያንዳንዳችን አፍ ውስጥ ተለምዷል። ሰው በሰማው እና በተመለከተው ስለሚቀረጽ “ኢትዮጵያ” ማለት እንዲህ እንደምታዩት አበባ የምታምር፣ ኢትዮጵያ ማለት ለነጻነት እና ለክብሯ የማትደራደር አገር መሆኗን ለማየት፣ ለማሳየት፣ ለመማር፣ ለማስተማር በእጅጉ የሚያግዝ ጊዜ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ምንአልባት ኢትዮጵያን ሳታውቁ የምትሞካከሩን አንዳንድ ያልገባችሁ ሰዎች ካላችሁ የኩራት እና የድፍረታችን ምንጭ ራሷ ኢትዮጵያ ናት።

**አመሰግናለሁ !**

**ግንቦት 11፣ 2013 ዓ.ም**

# የአማራ ልማት ማህበር ወቅት የተደረገ ንግግር

እንድነት ፓርክ እንደዚህ ግርማ ሞገሱ የሚወጣው በጋራ አንድ ላይ ቆመን ደማቅ በሆነ መልክ ኢትዮጵያዊነትን እያገነንንና ባህሎቻችንን እያወደስን በጋራ ስንቆም ነው። ይህ ባህል እንዲጠናከር ደጋግማችሁ እንድትመጡ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ስማችሁ እንደ ግብራችሁ ልማትንና ህብረትን ያሳያል። የዚህ ስብስብ ዋነኛ ዓላማ ድህነትን ከመጠየፍና ካለመፈለግ የተነሳ ነው። ህብረት ደግሞ ብቻችንን ለማልማትና ለመልማት ስለምንቸገር መሰብሰብ፣ መተጋገዝ፣ መሰናሰል፣ መደመር ዘላቂ የሆነ ልማት ለማምጣት ወሳኝ በመሆኑ መጀመሪያ የልማት ማህበሩን ስምና ግብር አመስግኜ እንድጀምር ይፈቀድልኝ።

በድሮ ጊዜ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሁለት ቤተሰቦች ነበሩ። እነዚህ ቤተሰቦች በቤታቸው ሁሉም ዓይነት ምግቦችና ሙዝ፣ አቮካዶ፣ ፓፓያ የተለያዩ ፍራፍሬዎች ጠረጴዛቸው ላይ ይገኛል። አንደኛው ቤተሰብ እጅግ ደስተኛ ሆኖ ይኖራል። ሌላኛው ቤተሰብ ደግሞ ምግቡን እያየው ምግቡም ርሱን እያየው ይኖራል። እነዚህ ቤተሰቦች በጠረጴዛ ላይ የተደረደረ ምግብ ቢኖራቸውም አንስቶ ለመብላት ዋነኛ ችግር የሆነባቸው እጃቸው አለመታጠፉ ነበር። መያዝ ይችላሉ፤ አንስተው መብላት ግን አይችሉም። አንደኛው ቤተሰብ "አንስቼ ልበላው አልችልም" ብሎ ምግቡን እያየ እያዘነ ሲኖር፤ ሌላኛው ግን ከምግቡ እያነሳ ወንድሙን ያጎርሳል፤ ያኛውም እርሱን ያጎርሰዋል። በመጎራረሳቸውና በህብረታቸው ምክንያት አንደኛው ቤት ፌሽታ ደስታ ሲኖር፤ ሌላኛው ቤት ደግሞ መጎራረስን ባለማወቅ፣ መተባበርን ባለማወቅ በሃዘን፣ በረሃብ ይኖራሉ። የእኛን ሁኔታ ስንመለከት ተመሳሳይ ይመስላል። በተለይ የኢትዮጵያን ሳምንት ያያችሁ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም የሚያስደንቁ የማዕድን ክምችቶች አሉ። እነሱም ያዩናል፤ እኛም እናያቸዋለን።

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያስደንቅ ባህል፣ የምግብ ብዛትና ዓይነት አለ። እዚሁ ወንድማማችነት ፓርክ ውስጥ ብትሄዱ ይታያል። ነገር ግን እኛም እናየዋለን፣ እርሱም ያየናል። ለምንድን ነው

ያ የሆነው? የትብብር፣ የመነጋገር፣ አብሮ የመሆን፣ የመደጋገፍ ሁኔታ ከልባችን ካልሰራንበት በስተቀረ አሁን ባለንበት ሁኔታ እንዲሁ እየተያየን እያዘንን ከመኖር ያለፈ ለውጥ ልናመጣ አንችልም። ይህ እንዲሆን ደግሞ በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጪም የሚሰሩ ሃይሎች አሉ።

በአገራችን "የሀብታም ልጅ ሁሌም በደሃ እናት ጀርባ ላይ ነው የሚያድገው" ይባላል። ሀብታሞች ይወልዳሉ እንጂ አያዝሉም። ከወለዱ በኋላ ደሃ አሳዝለው፣ የታጠበ ንጹህ የለበሰ ልጅ እየሳሙ ያሳድጋሉ። ኢትዮጵያ እንደ ደሃ እናት ጀርባ ብዙዎች ተፈናጠውባት ሊያድጉ ይፈልጋሉ። ሁሉንም ስታናግሩ "ትልቅ ህዝብ ያለበት፣ ለአፍሪካ ቀንድ ወሳኝ የሆነ፣ አብረን ልንሰራ የምንፈልገው አገር ነው" ይላሉ። ነገር ግን ሃምሳ በመቶ "በጨለማ ቢኖር ችግር የለውም፤ እንዲሁ ትልቅ እንዳልናችሁ ኑሩ እንጂ ትልቅ መሆን እምብዛም አያስፈልጋችሁም" ይላሉ። "ለምን?" ያላችሁ እንደሆነ እኛ የእነርሱን ልጆች አዝለን ማሳደግ ግዴታችን እንደሆነ ስለሚያምኑ ነው። እኛ "በህብረት እንልማ፣ እንበልጽግ" እያልን ነው። የሀብታም ልጆችን እያዘልን ማሳደግ ሳይሆን፤ እርስ በእርስ ተደጋግፈን በህብረት ማደግ፣ መለወጥና ሲተርፈን መደገፍ የምንችልበትን ቁመና "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ሊፈጥሩ ይችላሉ" የሚል እምነት ስላለ ነው።

የኢትዮጵያ ሳምንት ያልነው ለምንድን ነው? ከስማችን እንነሳ። የእናንተ ስም ግብራችሁን እንደሚገልጸው ሁሉ የ'ኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር' ሲባል ኢትዮጵያዊ "ህዝብ አይደለም" ማለት ነው። ህዝቦች ናቸው። "ኦች" የሚለው ቃል በአማረኛ አብዝ ነው፤ በግዕዝ "አት" የሚለው አብዝ እንደሆነው ማለት ነው። ህዝቦች ካልን ብዙዎች ነን ማለት ነው። ብዙ ማለት በአንድ ሊጠሩ የማይችሉ የአፍሪካ ህዝቦች፣ "የኢትዮጵያ ህዝብ" ሊባል ሲገባው "የኢትዮጵያ ህዝቦች" ተብለን እንደ ዋዛ እንደ በቀቀን ይሄንኑ ቃል እየደገምን ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ እውነት መስሎት 'ህዝቦች' በጋራ በትብብር መቆም እስኪሳናቸው አድርሷቸዋል። ስለሆነም አንደኛው ለሌላኛው ጋሻ መሆን ሲገባው እንቅፋት እንዲሆን ስላደረገው ነው ስሙንም፣ ግብሩንም፣ ሳቢውንም ፈንቅለን ጥለን "የኢትዮጵያ ህዝብ ብልጽግና ይገባዋል" ያልነው።

ነገር ግን እናንተም በዚህ የልማት ማህበር እንደምታውቁት የብልጽግና ጉዞ ፈታኝ ነው። የብልጽግና ጉዞ ቀላል አይደለም። ልጆቻችን ከዚህ ቀደም ለማወዳደሪያ ዋቢ የሚያደርጉት አልነበራቸውም። አሁን እዚህ ግቢ የመጣ ሰው “ለምንድን ነው እንደዚህ ዓይነት ግቢ እኛ ሰፈር የማይኖረው?” ብሎ ይጠይቃል። ብልጽግና ማለት መጓጓት፣ መሻት፣ ተባብሮ መሥራት ማለት ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ብርቅዬ ልጆች! ከተባበርን እንበለጽጋለን፣ ከተባበርን እንለወጣለን፣ ከተባበርን እንደ አባቶቻችን ጀግንነት ማንም አይደፍረንም። ነጻነታችንና ክብራችንን ጠብቀን ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ማማ እንደንወስድ ዛሬም እንደ ትናንቱ ያለኝ መልዕክት በፍቅር፣ በይቅርታ፣ በመተሳሰብ፣ በመደመር መንፈስ አንድ ሆነን ኢትዮጵያን በማበልጸግ ለአፍሪካ ምሳሌ እንድናደርጋት አደራ እላለሁ!!

**እንኳን ደህና መጣችሁ! አመሰግናለሁ!**

**ግንቦት 15 ቀን 2013 ዓ.ም**

# ኢትዮጵያን እናልብስ!

የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክታችን ሶስተኛ ዓመቱን ጀምረናል። ባለፉት ሁለት ዓመታት መላው ህዝባችንን በማነቃነቅ ከዘጠኝ ቢሊዮን በላይ ችግኞች ለመትከል ችለናል፡፡ በዚህ ዓመት በአገራችን ስድስት ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል አቅደናል። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ቢሊዮን ችግኝ ለጎረቤት አገሮች በማደል ሀሳቡ ከአገራችን አልፎ ወንድም ህዝቦችን መንካት እንዲችል ዓልሞ የተጀመረ መርሀ ግብር ነው፡፡ የአረንጓዴ አሻራ ዓላማ፣ ፍላጎትና ሀሳብ በተደጋጋሚ በቃል ስንገልጽ የነበረ ሲሆን፤ ዛሬ ደግሞ በተግባር ለማሳየት ሞክረናል፡፡

አረንጓዴ አሻራ ለኢትዮጵያ ቤታችን፣ ቢሯችን፣ አካባቢያችን፣ ከተሞቻችን እንዲሁም "አገራችን ይህን መምሰል አለባት" የሚል እሳቤ አለው፡፡ ቢሯችንንና ከተሞቻችንን ለመቀየር አንድም ከውጪ ያስገባነው የዛፍ ወይንም የአትክልት ዓይነት የለም፡፡ የተለየ እውቀትም ገንዘብም ከውጭ አላስመጣንም። ከውጭ የጠራነው ሰው የለም። ሙሉ በሙሉ የተሠራው በውስጥ አቅም ነው። ይሄንን በአጭር ጊዜ መፈጸም ከቻልን መላ አገራችንን አረንጓዴ ለማልበስና ለማሳመር የሚቻል መሆኑን ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
ኢትዮጵያዊያን አስበው ለትውልድ የሚሸጋገር ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ምን አልባት የሚጠራጠሩ ኃይሎች ካሉ እግረ መንገድ ትምህርት እንዲወስዱ ያደርጋል። እኛ የምናስብ፤ ያሰብነውን መሬት ማስነካት የምንችል ነን።

የኢትዮጵያ ብልጽግና የመላ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ህልም ነው። ይሄንን ከማንም በላይ ኢትዮጵያዊያን ወንድና ሴት ልጆቻችን እጅ ለእጅ ተያይዘው ጠንክረው ከሰሩ ማሳካት የሚችሉት ህልም ነው። ያን ለማሳካት ማለም፣ ህልማችን የሚተገበርበት ሕግ ማዘጋጀት፣ ያንን ለመፈፀምም ቁርጠኛ አቋምና ፍላጎት እንዲኖረን ማድረግ ነው። ዛሬ የተጀመረው ሙሉ በሙሉ በቀጣይ ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በምንሰራቸው የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክቶች ዐይኖቻችን አይተው የሚረኩበትና የሚመገቡት አካባቢን ማብዛት ነው፡፡ ሰው በሚሰማውና በሚያየው ልክ እሳቤውና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ይወሰናል።

ሰውን ከሚሰማውና ከሚያየው ውጪ ማንነቱን መቅረጽ አይቻልም። ሰው የሚያየው እና የሚሰማው ነገር መልካም ከሆነ አእምሮው የሚያሰላስለው በመስማትና በማየት የወሰደውን ነገር ነው። መልካምን ነገር ማሰላሰልና በዚያው ልክ ማድረግ የሚያስችል ብቃት ይፈጠራል።

በአንዳንድ ዝናብ ቀድመው በሚያገኙ አካባቢዎች ችግኝ መትከል በቅርቡ ይጀመራል። ዝናብ በቅርቡ የማያገኙ አካባቢዎች ደግሞ ጉድጓድ እየቆፈሩ የመዘጋጀቱን ተግባር በማካሄድ በየደረጃው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ መጀመሩን ለህዝብ የምናስተዋውቅበት ጊዜ ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ተደምረን እንዳሳካነው በዚህ ዓመትም ተደምረን የላቀ ውጤት ልናመጣ እንደምንችል ይታመናል፡፡ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በእምነት፣ በዘር፣ በክልል፣ በጾታ በሌሎችም የልዩነት ምክንያቶች ሳይለያይ እንደ አንድ ሰው በትብብር መንፈስ ቆሞ እንዲያሳካው በታላቅ ትህትና ጥሪ አቀርባለሁ፡፡
ይህ ፕሮጀክት ከምርጫ ጋር ትስስር የለውም፡፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት አሁን የምንተክለው ችግኝ ለሚቀጥለው ምርጫ ካልሆነ በስተቀረ ለዚህኛውም አይደርስም፡፡ አገርን ታሳቢ ያደረገ እንጂ ምርጫን ታሳቢ ያደረገ ባለመሆኑ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ በተለያየ የሥራ መስክ ያሉ ዜጎችና አገር ወዳድ የሆኑ ሰዎች በሙሉ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። ይህንን ህልም እንዲያሳኩ ትናንት ኢትዮጵያ መልኳ የነበር፣ ነገም ኢትዮጵያ መልኳ እንዲሆን ነው፡፡

ስለዚህ ሁላችሁም በግልጽ እንደምትገነዘቡት እኛ እና ዛፍ ያለን ቁርኘት ባለ ብዙ ገጽ ነው። በተለይ ኢትዮጵያዊያን ከዛፎች ጋር ያላቸው ቁርኘት በብዙ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ስንጣላ እንደ ከላሽ የምንጠቀመው በዱላ ነው። በፀብ ጊዜ እንጠቀምባቸዋለን። ስናርስ ሞፈር ቀንበር የምናዘጋጀው ከእንጨት ነው። ለእርሻ እንጠቀምበታለን። በብዙ የኢትዮጵያ ገጠሮች ሰዎች ሲታመሙ ሕመምተኛውን ተሸክመው ከቀበሌ ቀበሌ የሚወስዱትን በአምቡላንስ ሳይሆን በምታውቁት መንገድ ነው። ስንተኛ አልጋችን ነው፤ ለቤት መስሪያ ማገርና ምሰሷችን ነው። በአብዛኛው ለቤተ ዕምነት መስሪያዎቻችን እንገለገልበታለን። ስንቀመጥ በርጩማችን ነው። ስናረጅና ስንደክም ምርኩዛችን ነው። ለጨለማም እንደ ብርሃን የምንጠቀመውም እንጨት ነው። ስንጓዝ ሲደክመን የምናርፍበት ጥላም ነው። በውጩ ዓለም እንደተሰሩ ካፊቴሪያዎችና ምግብ ቤቶች ስንቃችንን ይዘን የምናርፈው ዛፍ ስር ነው፡፡ በየዕለቱ በምናደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ኢትዮጵያዊያን እና ዛፍ ከፍተኛ የሆነ ትስስር አለን፡፡ ለሁሉም ለምንጠቀምበት ነገር ለመቁረጥ እንደበረታነው ሁሉ በመትከል ካልተጋን በጊዜ ብዛት እድሜያችን እየገፋ ሲሄድ ብዙዎቻችን ምርኩዝ ሲያስፈልገን እንቸገራለን። መቀመጫም፣ መኖሪያም፣ ብርሃን የሚሆነውም ነገር እያነሰ ከሄደ የኑሮ ዋስትና እናጣለን። ከሕይወታችን ጋር በከፍተኛ ደረጃ የተሳሰረ ጉዳይ ነው።

ሁለተኛ ከግጭት አኳያም ሲታይ በዓለም ላይ ያሉ ግጭቶች አብዛኛው ሊባል በሚችል ደረጃ ከተፈጥሮ ሃብት ቅርምት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ግጭት እና መፈናቀል እንኳን አብዛኛውን ከተፈጥሮ ሀብት ጋር ይገናኛል። የግጦሽ እና የእርሻ መሬት፣

የመኖሪያ ቦታ የተሻለ መልከዓ ምድር ለመያዝ የሚደረግ ግብግብ በዓለም ደረጃ፣ በቀጣናችን እንዲሁም በአገራችን በአብዛኛው የግጭት መንስኤ ነው። አብዛኛውን ቦታ መቀየር ማሳመር ከቻልን ግጭት ለመከላከል በአንድ በኩል ጠቀሜታ አለው። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ አገር ብዙዎች ዘለው እንዳይደፍሩን ያግዛል፡፡

ለዛሬው ትውልድ የኑሮ ዋስትና ነው። እኛ ዛፍ ካልተከልን እርሻ፣ መጠጥ ውሃ እና ብዙ ነገሮች ስለሚበላሹ ለመኖር ዋስትና እናጣለን፤ ለመሰደድ እንገደዳለን። ለትውልድ ግን የህልውና ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ አሁን በጀመረችው መንገድ ዛፍ እየቆረጠች ገላጣ በረሀ እየሆነች የምትሄድ ከሆነ ልጆቻችን የሚኖሩበት አገር አይኖራቸውም። እንደእኛ የኑሮ ዋስትና ብቻ ሳይሆን፤ የመኖር ያለመኖር ህልውና ጉዳይም ነው። ስለዚህ ለእኛ እና ለልጆቻችን ስንል የምንፈጽመው ሥራ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያን የወደፊት እጣ ፈንታ የልጆቻችን የኑሮ ዘዬ ምን መምሰል እንዳለበት የምንወስንበት ነው፡፡ ልጆቻችን ምን ዓይነት የኑሮ ስልት ይከተሉ? የሚለውን ከወዲሁ የምንቀርጽበት፣ አቅጣጫ የምናስቀምጥበትና መሰረት የምንጥልበት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በዓለም ደረጃ የአካባቢን መታመምና መቀያየር የማይገነዘብ አካባቢውን በአስተውሎ ለማየት የሚቸገር ሰው ብቻ ነው፡፡ አካባቢውን በጥሞና ማየት የሚችል ማንኛውም ሰው በዓለምም ሆነ በአገር ደረጃ አካባቢው እየታመመ መሆኑን ይረዳል። ከጊዜ ወደ ጊዜ የዝናብና የሙቀት መጠን በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣት የሰው ልጆች በሰላም የመኖር ሕልውና እያወኩ መሆናቸውን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡ ፡ ለዚህ ሕክምና መስጠት የሚችሉ ዜጎች ናቸው፡፡ በብዙ ዓለማት ያለው ችግር አካባቢ መታመሙን ለመናገር በጣም ብዙ ገንዘብ ማውጣት ነው። አካባቢ ችግር እንዳለበት የአየር ንብረት ላይ መሥራት እንደሚያስፈልግ የሚጠቁሙ በጣም ታላላቅ ጉባዔዎች ይካሄዳሉ። ብዙ ቦታ ያለው ችግር እነዚያን ጉባዔዎች ከሰማንና ከተመለከትን በኋላ በተግባር ችግኝ ማዘጋጀትና መትከል ላይ የሚደረግ እንቅስቃሴ አናሳ መሆኑ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ከብዙ ዓለማት በርካታ የተዋስናቸው ሀሳቦች እንዳሉ ይታወቃል።

ኢትዮጵያ ችግኝ መትከል ከጀመረች ከሁለት ዓመት በኋላ በርከት ያሉ አገሮች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች ቀርጸው “ችግኝ እንተከል” እያሉ ነው። ይህ በጎ ተፅዕኖ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን በጎ ተፅዕኖ ዘላቂና መሰረት የያዘ እንዲሆን ደግሞ በአገር ውስጥ ለውጡን በተግባር ማየት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም መጀመር ብቻ ሳይሆን መጨረስ፣ ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግና የልህቀትና ያማረ ውጤት ማየት በየመሀሉ የሚኖሩ ድካሞችን በከፍተኛ ትጋት መቋቋም ይኖርብናል፡፡ ችግኝ በዋዛ አይበቅልም። መቆፈር፣ መትከል፣ መንከባከብ

ይፈልጋል። ውበቱንና ጠቀሜታውን የምንገነዘበው ከዓመታት በኋላ ነው፡፡ ለዚያ ዘለግ ያለ ጥረትና ትጋት ማድረግ ከሁላችንም ይጠበቃል።

ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ችግኝ ፖለቲካ አይደለም። ምክንያቱም ፖለቲካ ለምሳሌ ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ምርጫ የሚያካሂድ አገር ቅስቀሳ የሚያደርገው ለአንድ ወር የሚበጅ ነው። አሁን የምንጀምረው የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክታችን ከዛሬ ጀምሮ አንዳንድ ቦታ እስከ መስከረም እና ጥቅምት ይዘልቃል። ከምርጫውም በኋላ እንደመንግሥት ብቻ ሳይሆን እንደዜጋም ይቀጥላል። ከተመረጥን ብቻ የምንሰራም ሳይሆን ባንመረጥም የምንተገብረው ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት ሁላችንም ለትውልድ በማሰብ ከምርጫና ከፖለቲካ ንትርክ ባሻገር ይህንን ሥራ ብናሳካ መፃኢ የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ ለመወሰን የተሰጠንን እድል በከፍተኛ ደረጃ እንጠቀምበታለን። ልጆቻችንም ከስደት ተገላግለው እዚሁ የመስራት እድል አግኝተው ምቹና በአማረች አገር ውስጥ ለመኖር እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ያግዛል። ይህንን ነገር በአንክሮ መገንዘብ በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡

የታላቅነት መገለጫ ለትውልድ አሻራ ማስቀመጥ እንጂ በፌስቡክ አቧራ ማስነሳት አይደለም። አሻራ ማስቀመጥ ዘላቂ ነገር ይጠይቃል። የዕለት ጉዳይ አይደለም። አቧራ የዕለት ጉዳይ ነው። ለአጭር ጊዜ የሚደረግ ጥረትም፣ ውጤትም ወዲያው የሚረሳና የሚዘነጋ ጉዳይ ነው፡፡ ዘላቂ ነገር በማስቀመጥ ለትውልድ መሰረት መጣል እንድንችል ርብርቡ ከሁላችንም የሚጠበቅ መሆኑን ከአደራ ጭምር ለማንሳት ነው፡፡

ለዘንድሮ ይዘን የቀረብነው ሁለት መሪ ሀሳብ ነው። ቀደም ሲል የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን ያቀረቡት መሪ ሀሳብ በጣም ጥሩ ነው። እንዳለ ልንቀበለው እንችላለን። በእኔ በኩል ግን ያሰበኩትና ቤቱ እንዲወስን የፈለኩት መሪ ሀሳብ "ኢትዮጵያን እናልብሳት" የሚል ነው፡፡ ኢትዮጵያ ተራቁታለች፤ አንሶላዋ የነበረው ነፋሻማ አየር ጠፍቷል። አንሶላዋን አጥታለች፤ ብርድ ልብሷ የነበረው ዝናብ በከፍተኛ ደረጃ በቴክኖሎጂ ለማገዝ ሙከራ የተደረገ ቢሆንም ችግር አለበት። ብርድ ልብሷ ከሌለ፤ አንሶላዋ ከሌለ ብርድ አለ ማለት ነው። ካፖርቷ የነበሩትን አረንጓዴ መስኮች፣ አረንጓዴ ተራሮች ማየት ብርቅ እየሆነ መጥቷል። ይህችን ራቁቷን ቀርታ፣ የድህነት ምሳሌ ተደርጋ የምትወሰድ አገር ብዙዎች በቀላሉ ለመድፈር የሚዳዳቸውን አገር ብናለብስ ከብርድ መከላከል ብቻ ሳይሆን ክብሯን ለመመለስም በእጅጉ የሚያግዝ ይሆናል። "ተራቁታለችና እራቁቷን ከምትሆን እናልብሳት" የሚል ሀሳብ ነው ያለኝ፡፡ ሁለቱንም አማርጠን መወሰን እንችላለን።

ኢትዮጵያን በማልበስ ጉዳይ ከክልል ባሻገር ማየት ካልቻልን፤ ኢትዮጵያን በማልበስ ጉዳይ

ከህይማኖት ባሻገር ማየት ካልቻልን፤ ኢትዮጵያን በማልበስና በማስከበር ጉዳይ ከፆታ ባሻገር ማየት ካልቻልን፤ አገር አልባ የሆነ ፖለቲካ፣ አገር አልባ የሆነ ዘር፣ አገር አልባ የሆነ ክልል በዘላቂነት መኖር አይችልም። በዚህ ጉዳይ ኢትዮጵያዊያን በአንድ መንፈስ፣ በአንድ ልብ ሆነው የተገለጠችውንና ሊያዋርዷት ብዙዎች የሚታገሏትን ኢትዮጵያን በማልበስና በማስከበር ግርማዋን መመለስ እንችላለን፡፡ በዚያ ውስጥ ኢኮኖሚ ጠቀሜታዎች ማሳደግ፣ ግጭት ለመቀነስ፣ ለመበልፀግ፣ ለመልማት ማቀድና ማሰብ ብቻ ሳይሆን መተግበር የምትችልና በነ ተጽዕኖ የምታመጣ አገር መሆንዋን ማረጋገጥ ከሁላችን ይጠበቃል፡፡

ለጎረቤት ሀገር የምናደርገው ተጨማሪ ሙከራ ኢትዮጵያ ብቻዋን አረንጓዴ መሆን አትችልም፤ ኢትዮጵያ ብቻዋን መበልጸግ አትችልም። እኛ የምንከተለው የሽሚያ እሳቤን ሳይሆን የትብብር ነው። በጋራ ማደግና በጋራ ሰላም ማምጣት የምናስብ ህዝብ ነን። እንደምናስበው ኢትዮጵያ በልጽጋና ተለውጣ ሁሉም የእኛ ጎረቤቶች ማደግ ካልቻሉ መቼም በደሃ አገር መኖር ማንም ስለማይሻ፣ በቀላሉም በእግር ተጉዞ መምጣት ስለሚችል ከቁጥጥራችን ውጪ የሆነ ሰው ሊመጣብን ይችላል፡፡ ብልጽግና በተሟላ ደረጃ እውን የሚሆነው ሁሉም ባለበት መልማትና ማደግ እንደሚችል ሲያዩ ነው። አሁን አንዳንድ አገሮች ስደተኛ እንዳይመጣባቸው የሚያደርጉትን ጥረት እየተመለከትን ነው። እንደዚህ ዓይነቱ ነገር ነገ የእኛም ልጆች እንዳይገጥማቸው ከወዲሁ አብረን የማደግ እሳቤን ማስፋት ያስፈልጋል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ በጀት ከእያንዳንዱ ዜጋ ጉልበትና ፍላጎት የሚወጣ ነው። እያንዳንዱ ዜጋ ጉልበቱን ጊዜውን ካልሰዋ በስተቀረ በጥቂት ወራት ውስጥ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ መትከል አይቻልም። አንድ ችግኝ ለማዘጋጀት ወራት ይፈልጋል። ከተዘጋጀበት ወደሚተከልበት ለመውሰድ ዋጋ ይፈልጋል። ጉድጓድ ለመቆፈር እንዲሁ ገንዘብ ይፈልጋል። ለመትከልና ከተከልን በኋላ ውሃ ለማጠጣት ለመንከባከብ ገንዘብ ይጠይቃል። ለእያንዳንዱ ችግኝ ጀምረን እስከምንጨርስ አንድ ዶላር አወጣን ብለን ብናስብ አንድ ዶላር ማለት አርባ ብር ቢሆን፤ ችግኝ የሚዘጋጅበት፣ የሚንቀሳቀስበት፣ የሚቆፈርበት፣ የሚተከልበትና እንክብካቤ የሚደረግበት የወጪ መጠን ከአርባ ብር ይልቅ እንደሆን እንጂ አያንስም፡፡ የአንድ ቀን ሥራ አይደለም። ለአንድ ቀን ሥራም ሰው ከዚህ ያነሰ ገንዘብ ስለማይቀበል ስድስት ቢሊዮን ዶላር ኢንቨስት እያደረግን ነው ማለት ነው፡፡ ስድስት ቢሊዮን  ዶላር ኢንቨስት ስናደርግ በጥሬ ገንዘብ መልክ አይታይም። በዓይነት፣ በጊዜ ብዛት በብዙ እጥፍ በልጦ ይታያል፡፡

ዘንድሮ የምንተክለው ባህር ዛፍ እና ጥድ ብቻ አይደለም። ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ፓፓዬ እና ቡና እንተክላለን። ይህ የተከልነው በብዙ እጥፍ ተባዝቶ ሀብት ይሆናል። ለዚህም ዋናው የበጀት

ምንጭ “ህዝባችን ይሆናል” ተብሎ ነው የታሰበው፡፡ ወዳጅ አገሮችም “ያግዙናል” ተብሎ ታሳቢ ይደረጋሉ። በጣም ጠቃሚ ኢንቨስትመንት ነው። እዚህ ላይ የሚጎድለውን የክልል እና የፌዴራል መንግሥታት በትብብር ይሞሉታል፡፡ ስለዚህ በጀት የንግግር አጀንዳችን አይሆንም። ከዚህ ባሻገር በፍላጎት ላይ ተመስርቶ ጊዜና ጉልበት በመስጠት የምናሳካው ይሆናል። ከጎደለን እንደአስፈላጊነቱ ከተለያዩ ምንጮች አሟልተን ሥራውን በተሟላ ደረጃ ለመስራት መንግሥት ዝግጁነት አለው። እናንተ አምናና ካቻምና እንዳደረጋችሁት ከተባበርን ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን እጅግ የሚያኮራ ለሌሎች ደግሞ በብዙ የሚያስተምር ስራ እናከናውናለን።

ስለጦርነት ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ተወርቷል። ትልልቆቹ መገናኛ ብዙኃን ስለእኛ ጦርነት በከፍተኛ ደረጃ ሰብከዋል። ስለእኛ ግጭት፣ ስለእኛ ድህነት፣ ስለእኛ አለመግባባት በብዙ ሰብከዋል። ከዚያም በላይ ስለእኛ ምርጫ “ይካሄድ አይካሄድ” በሚል በብዙ ዘግበዋል፡፡ እነዚህ መገናኛ ብዙኃን እውነተኛ የኢትዮጵያ ወዳጅ ከሆኑ አሁን ይታያሉ፡፡ ስለ አረንጓዴ አሻራ በዚያ ልክ በየቀኑ ተጨንቀው ከሰበኩ መልካሙንም ክፉውንም በጋራ የሚያሳዩ፤ አሊያም እምብዛም መልካም መልካሙን የማይደግፉ መሆናቸውን እናያለን፡፡ ስለአረንጓዴ አሻራ ግድ የማይላቸውና ስለእኛ መጋደል ብቻ የሚናገሩ ከሆነ ግን ማንነታቸውና ፍላጎታቸውን ምንጥር አድርጎ የሚያሳይ መድረክ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያዊያን መትከል ብቻ ሳይሆን እነዚህ ኃይሎች እንዴት እንደሚዘግቡም ጭምር ስንከታተል ሌሎች ስለእኛ የሚያስቡት ምን እንደሆነ በገሀድ ለመገንዘብ ያግዘናል። የእኛ መገናኛ ብዙኃን አምናም ሠርተዋል፤ ዘንድሮም ይሠራሉ።

ኢትዮጵያዊያን አምናም ተክለዋል፤ ዘንድሮም ይተክላሉ። ወዳጆቻችን አምናም ደስ ብሏቸዋል፤ ዘንድሮም ደስ ይላቸዋል። የእኛን መባላትና መበተን የሚፈልጉ ኃይሎች ግን “አልሰማንም አላየንም” ስለሚሉ ይሄንን በማየት ብቻ ሌሎች ፍላጎቶቻቸውም እንዳይሳኩ ለማድረግ ትምህርት መቅሰም ያስፈልጋል፡፡ በድምሩ የዘንድሮ አረንጓዴ አሻራ ከምንሠራቸው ዋና ዋና ሥራዎች እንደአንዱ የሚወሰድ፤ በሌሎች የማይተካ ራሱን ችሎ የሚቆም አንድ ምሰሶ ነው። ይህም በየዓመቱ በቀጣይነት ሲሠራ ብቻ ሙሉ እንደሚሆን በመገንዘብ እንደአምናው እንደ ካቻምናው ሁሉም መሪዎች የስራቸው አካል፣ የዕለት ዕለት ዕቅዳቸው አድርገው መፈጸም አለባቸው። እንግዳ ስትቀበሉና ስትሸኙ፣ ስብሰባ ስትጀምሩ፣ ስትጨርሱ፣ ወደ ቤት ስትገቡ ሁሉ ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት እንደዋና ሥራችሁ እንድትሠሩት አደራ እላለሁ።

የዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ከተስማማን “ኢትዮጵያን እናልብስ” የሚለውን ወይም “ለጋራ ልማት አረንጓዴ አሻራ” ያሉትን የአቶ ዑመርን አማርጠን በመውሰድ በዚህ የመሪ ሀሳብ መንፈስ መሥራት አለብን። ለዚህ ምርጫ በጣም ብዙ ፎቶ በጣም ብዙ ማስታወቂያዎች አይተናል። ከዚህ ምርጫ ያልተናነሰ ዋጋ ላለው ለአረንጓዴ አሻራ በየከተማው ምን ያህል

ፎቶዎችና ማስታወቂያዎች እንደሚለጠፉ እናያለን። ያን በማድረግ ለልማትም ለምርጫም እኩል ግምት የምንሰጥ መሆናችንን ማረጋገጥ ይጠበቅብናል፡፡

በአስር ክልሎችና ሁለት ከተማዎች ሁለት የተሳካ መርሀ ግብሮች ይኖሩናል። አንደኛው እያንዳንዱ ክልል በክልል ደረጃ የተከላ ቀን አለው። ለምሳሌ ዛሬ የአማራ ክልል የተከላ ቀን ከሆነ ሌሎች ክልሎች እና የፌዴራል የሥራ ኃላፊዎች የአማራ ክልል በሚያደርግላቸው ጥሪና ግብዣ መሰረት ከክልሉ ጎን በመቆም የአንድ ቀን ችግኝ ተከላ ያካሄዳሉ። ሌላ ቀን የቤንሻንጉል ጉምዝ የክልል ችግኝ ተከላ ቀን ካለው እንዲሁ ይደረጋል፡፡ እያንዳንዱ ክልል የራሱ የዕለት ችግኝ ተከላ ቀን ይኖረዋል። አስር ክልሎች ሁለት ከተማ አስራ ሁለት ቀን ማለት ነው፡፡ ይሄንን ካጠናቀቅን በኋላ በሐምሌ አጋማሽ ገደማ አንድ አገር አቀፍ የተከላ ቀን እናደርጋለን። ይሄ ጠቀሜታው ምንድን ነው? ክልሎች ውስጥ እኛም ለመሳተፍ እድል እናገኛለን፡፡ ሁለተኛ ዘንድሮ ከኦሮሚያ፣ ከአማራ እና ከደቡብ ክልሎች ክብረ ወሰን የሚሰብረው "የትኛው ክልል ነው?" ለሚለው የተግባር ምላሽ እንጠብቃለን። ክብረ ወሰን ለመስበር መርሀ ግብር ይኖራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚሁ አግባብም ምናልባት ሽልማቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እያንዳንዱ ክልል በሰፊው አቅዶ በክልል ደረጃ የተከላ ቀን ይወስናል፤ ይፈጽማል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃም እንደዚሁ ይወሰናል፤ ይፈጸማል፡፡ ይሄንን መርሀ ግብር ክልሎች ቀደም ብላችሁ ብታሳውቁን እኛም እንድንሳተፍ እድል እናገኛለን፤ እንደየአመቺነቱ፡፡

እንግዲህ ሁላችንም ባልነው መሰረት ቃላችንን እንጠብቅ፤ የምንታወቀው ቃላችንን ጠብቀን በመፈጸም ነው። ቃላችንን እየፈፀምን፤ ያቀድነውን እያሳካን፤ ሪቫን እየቆረጥን፤ ለትውልድ ተስፋ እየሰነቅን፤ ጠላቶቻችን እኛን ለመበተን፣ ለማባላት፣ ይበልጥ ለማደህየት ያላቸውን ተስፋ እያስቆረጥን የምንቀጥልበት ጊዜ ይሆናል፡፡

በተግባባነው መሰረት ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊያንን በተለይም የሁላችንም የመጨረሻ መጠለያና ማረፊያ የሆነች ድንቅ አገራችንን ክብሯን፣ ሞገሷን፣ ውበቷንና አንድነቷን በጋራ እናልብስ፡፡ "እናልብስ" ሲባል ካፖርት ብቻ አይደለም፤ "ጃኬት" ብቻ አይደለም፤ ብርድ ልብስ ብቻ አይደለም 'ሞገስ ነው' የምትለብሰው፤ 'ክብር ነው' የምትለብሰው፤ አንድነቷን ነው የምትለብሰው። ውበቷ ነው። ይሄን ለማድረግ በጋራ እንድንቆም በድጋሚ ጥሪ አቀርባለሁ። በእኛ ግቢ ውስጥ ለሁለት ዓመት ችግኝ ተክላችኋል። ግቢያችን ተጨማሪ ችግኝ ለመትከል የሚያስችል ቦታ ስለሌለው ለሁላችሁም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በስጦታ መልክ ችግኝ አዘጋጅቶላችኋል። ቤታችሁ ወስዳችሁ እንድትተክሉና በእርሱ እንድታስታውሱን አደራ እንላለን፡፡ ከዛሬ ጀምሮ የሚያገናኘን መድረክ አብዛኛው ችግኝ መትከልና መንከባከብ ይሆናል።

**እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!**

ግንቦት፣ 2013 ዓ.ም





አረንጓዴ አሻራ
#greenlegacy

# ኢትዮጵያን የማልበስ የአርጓዴ አሻራ መርሃ ግብር - በደብረ ማርቆስ

ኢትዮጵያን የማልበስ የአርጓዴ አሻራ መርሃ ግብር - በደብረ ማርቆስ እጅግ በምታምረውና 168ኛ ዓመትዋን ዛሬ የምታከብረው፣ እንደገነት የምትታየው የጥንታዊቷ ከተማ ደብረ ማርቆስ ስለሰበሰበችን፣ ስላሰባሰበችን መዳረሻችን ስለሆነች እንኳን በሰላም መጣችሁ። እንኳን ተገናኘን።

ወጣቶች ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ ሁላችሁም ለመልካም ነገር መጥታችኋል። መልካም ዘር ልትዘሩ ነውና - እንኳን ደስ ያላችሁ፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት አቶ በላይነህ ክንዴ በቡሬ ባሰራው እጅግ ውብ ድንቅ የዘይት ፋብሪካ ምርቃት ላይ ስንገኝ ጎጃም መጥተን ችግኝ እንደምናስተክል ቃል መግባታችን ይታወሳል። ዛሬ ደግሞ ከሁሉ በላይ ለየት ያደረገው የአቶ በላይነህ ክንዴ ወንድምና የቅርብ ጓደኛ አቶ ወርቁ አይተነው የገነባነውን ፋብሪካ ሲያስመርቅ በዚህ መልካም ግጥምጥሞሽ ጎጃም ላይ የአማራ ክልል ኢትዮጵያን የማልበስ፤ የአረንጋዴ አሻራን ማሳረፊያ መርሀ ግብርን የማስጀመር እድል እኔም ጓደኞቼም አግኝተናል። በዚህም እጅግ ደስ ያለንና ፈጣሪን የምናመሰግን መሆኑን በድጋሚ እገልጽላችኋለሁ።

ኢትዮጵያን የማልበስና የአረንጓዴ አሻራ ጉዳይ ከምናስበው በላይ ውጤታማ እንደሆነ ትናንት ጎንደር በነበረንበት ቆይታ መመልከት ችለናል፡፡ ጎንደር ለረጅም ጊዜ የምናውቀው፣ ብዙ ጊዜ የተመላለስንበት፣ የኖርንበት ከተማ ቢሆንም፤ ጎንደር በከፊልም ቢሆን ለብሳ ያላት ውበትን፣ ያላት መለወጥን፣ ያላት ሳቢነትን ስንመለከት "የኢትዮጵያን የማልበስ" ነገር ቢቀጥል ተስፋ አለው" በማለት ይበልጥ እንድናምን አድርጎናል፡፡ በዚህ አጋጣሚ እዚህ ያላችሁ እንግዶች በሙሉ ዛሬ ይህ መርሀ ግብር ሲያልቅ በዚሁ ወደ ጎንደር አቅንታችሁ በጎህና በጎንደር ሂል ሪዞርቶች አርፋችሁ፤ የጎንደርን ውበት የትናንትና ግርማዋ እንዴት እየተመለሰ እንደሆነ ብታዩ፣ ብትደግፉ፣ መልካም ነው። ጎንደርን ዓይታችሁ እንደእኛ ደስ ቢላችሁ፣ ውስጣችሁም ቢነቃቃ መልካም ስለሚሆን በዚሁ ተጋብዛችኋል። ወጪውን ግን ማን እንደሚሸፍን አላውቅም። ነገር ግን ሄዳችሁ እንድታዩ አደራ እላችኋለሁ፡፡

እዚህ ቦታ ያሰባሰበን ነገር ሰው መሆን ነው፡፡ አንድ ሰው ወደ ትልቅ ሰው ዘንድ ሄዶ "አሁን ጎርምሻለሁ፤ ደርሻለሁ በምን የሥራ መስክ ብሰማራ ይበልጥ አዋጪ ሊሆን ይችላል? ይምከሩኝ" ብሎ ጠየቀ። እኚህም ትልቅ ሰው አሁን ለጊዜው እጅግ በጣም አዋጭና ብዙ ተፎካካሪዎች የሌሉበት የሥራ መስክ "ሰው መሆን ነው" ይሉታል፡፡ ሰው መሆን ሰዎች እንደዋዛ ቢያዩትም ሰው መሆን ባለመቻል እንገፋፋለን፣ ሰው መሆን ባለመቻል

እንገዳደላለን፤ ሰው መሆን ባለመቻል ያለንን አካፍለን በጋራ መኖር ሲገባን አንዳንዶቻችን ቀማኞች እንሆናለን። ሰው መሆን ባለመቻላችን ይህቺን ድንቅ አገርና ድንቅ ስጦታ ጠብቀን ለልጆች ማሻገር ፈተና ይሆንብናል። እያንዳንዳችን ሰው መሆንን ብቻ አጥብቀን ብንይዝ፤ ችግኝ መትከል፣ ወንድምን መውደድ፣ አገርን ማበልጸግ፣ ነፃ ሆና የተሰጠችንን አገር ነፃ አርጎ ማስቀጠል ለሁላችንም ምስጢር አይሆንም፡፡

የዛሬው ኢትዮጵያን የማልበስ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ደብረ ማርቆስ ላይ ስንጀምር እያንዳንዳችን አዋጭ እና ይበልጥ ጠቃሚ ወደሆነው ሰው መጧጋት ወስነን ችግኝ እንድንተክል "አደራ!" እላችኋለሁ።

ከአርማጭሆ ጀምረን ጎንደር ለመድረስ በሄሊኮፕተር ሄደን ልንጨርሰው አልቻልንም፡፡ ዛሬ ጠዋት ከጎንደር ተነስተን እዚህ ለመምጣት አንድ ሰዓት ነው የፈጀብን። እጅግ ትልቅ፣ ውብና ሳቢ አገር ነው ያለን፡፡ እኛ ሰው እንሁን፤ አገራችንን እንውደድ፤ እንተባበር እንጂ ለሌሎች የምንተርፍ ከሌሎች የማንሻ መሆናችንን ተፈጥሮ መስክራ ሰጥታናለች። ሰው ሆነን እንድንጠብቃት በድጋሚ አደራ እላችኋለሁ።

ብዙ ሰዎች የኢትዮጵያን ገላጣ ቦታዎች ተመልክተው "ኢትዮጵያን እናልብሳት" የሚለውን መሪ ሀሳብ በመጠራጠር መንፈስ ሲመለከቱት ይስተዋላል። ነገር ግን በዚህ ስፍራ ያለ እያንዳንዱ ሰው ከጥቂት ዓመታት በፊት የነበረውን ፎቶ መለስ ብሎ ቢያይና የዛሬው ማንነቱን ቢያስተውል ኢትዮጵያ ላይ ችግኝ እየተከልን ኢትዮጵያን የማልበሱን ጉዳይ ሊሳካ እንደሚችል ራሱን በማየት ብቻ ይገነዘባል። ዛሬ እያንዳንዳችሁ የሰው ልጅ እጅ ሥራ መስሎ እጅግ የሚያምረው ጥርሳችሁ ከጥቂት ዓመታት በፊት ተነቅሎ እንደነበረ አትዘነጉም። የያኔ ፎቷችሁን መለስ ብላችሁ ብታዩ በጣም አስደንጋጭ ድድ ብቻ እንደነበር ታስተውላላችሁ፡፡ ዛሬ እንዲህ ያማረ ጥርስ በብዙዎቻችሁ ላይ የሚታየው ያኔ ተነቅሎና በቅሎ ነው። ጥርስ ሲነቀል አይበቅልም ወይም አይተከልም ማለት አይደለም። ሰባት ዓመት ሲደረስ ጥርስ መንቀል ወጉ ነው፡፡ ደግሞ ከፍ ስንል በቅሎና አድጎ ማየት እንዲሁ የተፈጥሮ ፀጋ ነው፡፡ ስንፈጠር አረንጓዴና ያማረ መልክዓ ምድር ነበረን። በእኛ ስህተት በተፈጥሮም ሁኔታ ተነቃቅሎ ገላጣ ሆኖ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አሁን ከተከልን ልክ እንደጥርሳችን በሆነ ወቅት ጊዜውን ጠብቆ ያማረ ይሆናል። ችግኝ እየተከልን አገራችንን ውብ ማድረግ ከሁላችንም ይጠበቃል። ደግሞም እጅግ ማራኪ ሥራ ነው፡፡ ዛሬ እንጀምረዋለን፤ በሚቀጥሉት ወራት ሁላችንም ደጋግመን በመትከል ለነፍሳችን ሀሴት፤ ለልጆቻችን ደግሞ እጅግ ጠቃሚ ነገር ማስተላለፍ ይኖርብናል፡፡

በመጨረሻ ከአማራ ክልል ቅድም በቀረበው ሪፖርት የዚህ ዓመት እቅዳቸው ከአንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ከፍ ያለ ነው፡፡ ይህ ለአቶ መለስ እና ለአማራ ክልል አይመጥንም። እንደምንም ተረባርበን ሁለት ቢሊዮን መሙላት አለብን። ለሪፖርትም ስለማይመች ተረባርበን ሁለት ቢሊዮን ብንሞላው አቶ መለስን የመሰለ ወጣት የግብርና ቢሮ ኃላፊ

ይዘን አቶ ደመቀን የመሰለ ደጋግሞ መትከል የሚያስደስተው መሪ ይዘን የቀረችውን መቶ መሙላት አንቸገርም። መስከረም ላይ መስማት የምንፈልገው “ሁለት ቢሊዮን ችግኝ ተተክሏል” የሚል ይሆናል፡፡ ስለመጣችሁ፤ ኢትዮጵያን ለማልበስ ስለፈቀዳችሁ እጅግ አድርጌ እያመሰገንኩ፤ በዚሁ መርሀ ግብሩን ሳናራዝም ችግኝ እንድንተክል እጋብዛችኋለሁ።

**አመሰግናለሁ !**

ግንቦት 30፣ 2013 ዓ.ም

# መሃል አርማጭሆ ጀግናን አድናቂ

ፕሬዝደንት ደስታ ሌዳሞ ከሲዳማ ክልል አርማጭሆን እንደእኔ ናፍቀው ለማየት ስለመጡ እርሳቸውንም እንዲሁ በክብር "እንኳን ደህና መጡ" እላለሁ። እጅግ የተከበራችሁ፣ የተወደዳችሁ፣ በብዙ የተናፈቃችሁ የአርማጭሆ ህዝብ፣ ዓይን ለዓይን ስለተያየን፣ ስላገኘኋችሁ ምድራችሁን ስለረገጥኩ እጅግ ከፍተኛ ኲራትና ክብር እንደተሰማኝ እገልጽላችኋለሁ፡፡

ከብዙ ወዳጆቼ ስለአርማጭሆ ታሪኩን፣ ክብሩንና ጀግንነቱን ስሰማ ኖሬያለሁ። ዛሬ በአካል ተገኝቼ ጀግንነት ብቻ ሳይሆን ውበቱን ማየት በመቻሌ እድለኝነት ተሰምቶኛል፡፡ አርማጭሆ የብዙ ጀግኖች አገር ነው። በጀግንነታቸው የሚታወቁ፣ የነራስ አሞራው ውብነህ፣ የነደጃች ብሬ ዘገየ፣ የነደጃች ሀጎስ ተሰማ፣ የጃኖራ ቆላ ወጋራ ጀግና ናቸው፣ የነቢተወደድ አዳነ መኮንን ወይንም አባ ደፋር፣ የነደጃች ደስታ ማሩ የጠገዴ ጀግና፣ የፊታውራሪ መስፍን ረዳ፣ የጠለሎ ጀግና ደጃች አያና፣ የቸኮል የአውራ ጀግኖች ብዙ ናቸው። የአርማጭሆ ጀግኖች፣ አርበኞች፣ የነፃነት ታጋዮች ስማቸው ከምድር በላይ ገኖ የሚነገር፣ ለልጅ ልጆቻቸው አልፎ ዛሬ ዝናሽ ታያቸው ብሬ የእነዚህ ሰዎች ምክንያት ሆና በዚህ ቦታ ትምህርት ቤት ለማሠራት እኛን ለማሰባሰብ በመብቃቷ አርማጭሆ "እንኳን ደስ አላችሁ" ለማለት እወዳለሁ።

አርማጭሆ ጀግና ማፍራት ብቻ ሳይሆን ጀግና ማድነቅ ይችልበታል።

"አይቆረጠም የድንጋይ ቆሎ፣
አይወረወር የእሳት አሎሎ፣
ፍቅሩን ነው እንጂ ጠቡን ማን ችሎ" ያለው አርማጭሆ ለጀግኖቹ ነው። እነቢትወደድ አዳነ መኮንን በእንደዚህ ዓይነት ግጥም ሲሞካሹ በብዙ ድርሳናት ተጽፎ የሚገኝ ማጀገን ብቻ ሳይሆን ጀግናን የሚያወድስ ህዝብ መሆኑን ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል፡፡ ዛሬ በዚህ ስፍራ በስማቸው ትምህርት ቤት የተገነባላቸው አርበኛ ጀግና አያት ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ በጀግንነታቸው በአርማጭሆ በኢትዮጵያ እናንተ ባታውቁት እንጂ በእንግሊዝም ጭምር የሚታወቁ ጀግና ናቸው። ደጃች ብሬ ዘገየ "ያለእዳው ዘማች ብሬ ደጃዝማች" የተባለላቸው፤ በተለይ በሳንጃ ምሽግ አንዳንድ ለጣሊያን ያደሩ ወገኖቻችንን ምሽግ አፍርሰው ከጣሊያን በመውሰድ በእንግሊዝ መንግሥት ጭምር ታላቅ ክብር ያገኙ ጀግና ናቸው። በስማቸው ከፍተኛ ትምህርት ቤት ቢሰራ ያንስባቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይሆንም፡፡ የደጃች ብሬ ዘገየ ዘመዶች ብቻ ሳንሆን፤ እኛ ሁላችን የአርማጭሆ ህዝብ ጀግኖቻችንን በማጀገንና

በማውሳት፤ ለልጆቻችን ታሪክ በማውረስ ረገድ ይህ ትምህርት ቤት ትልቅ ትርጉም አለው። ከአርማጭሆ አንድ ሳይሆን ሺህ ጀግኖች ለማውጣት የተተከለ መሰረት ነው። ሁላችሁም ተንከባክባችሁ ለአርማጭሆ ብሎም ለኢትዮጵያ ሚሊዮን ጀግኖች እንድትፈጥሩ ከአደራ ጭምር አሳስባችኋለሁ።
አርማጭሆ ሲባል ተዋጊ ብቻ አይደለም። አርማጭሆ የሚታወቀውና የሚታወሰው በሞፈርና በምንሽር ነው። አርማጭሆ በሰላም ጊዜ ከንጋት እስከ ምሽት ጠምዶ የሚያርሥ ስራ ወዳድ ህዝብ ነው። ለዚህም ነው፤
"ሰሜን አርማጭሆ የጀግኖች አገር፣
እርፍ ያገላብጣል እንደ ዲሞፍተር፣" የተባለው።
የአርማጭሆ ሕዝብ በሰላም ጊዜ ቀን ከሌት በማረስ፣ በመሥራት ራሱን ማኖር፣ ማሳደር፣ ቤተሰቦቹን ማሸጋገር የሚችል ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን አምስት ዓመት የመሸጉ አርበኞችንም በስንቅ መደገፍ የቻለው በመሥራቱና ሥራ ወዳድ ህዝብ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ ነገር ግን አርማጭሆ በቀኝ እጁ እያረሰ በግራ እጁ አገሩን ይጠብቃል።
ችግር ሲገጥም ደግሞ ፦
"ሰሜን አርማጭሆ ወልቃይት ጠገዴ፣
ማረሻው ዲሞፍተር መተኮሻው ጓንዴ'' ይላል።
ችግር ሲገጥመውም ጀግንነትና አገር መጠበቅ የሚያውቅ፣ በልማትም በጦርነትም የማያሳፍር የጀግኖች ሰፈር በመገኘታችን ታላቅ ክብርና ኩራት የሚሰማን መሆኑን በድጋሚ እገልጻለሁ። አርማጭሆ ማጀገን ብቻ ሳይሆን ሥራ ወዳድ ወጣቶችንም መፍጠር ስለሚወድ የማይሠሩ ሰዎችን በግጥምና በእንጉርጉሮ ጎሸም ያደርጋል፤ መትጋት መስራት እንደሚያስፈልግ ስለሚያምን፤
"እርጉለት ጎመን ከመሶቡ ላይ፣
ያላረሰ ጎበዝ ወጥ ይበላል ወይ" ይላል አርማጭሆ፤ ሥሩ ማለት ነው፤ 'ሳንሰራ መለወጥ የለም' የሚል ትምህርት ለልጆቹ ያስተምራል። መዋጋት ያስተምራል፤ መሥራት ያስተምራል፤ ሰነፎችን ደግሞ በግጥም በእንጉርጉሮ ይኮንናል። በአርማጭሆ ምድር ስንፍና ሊታይ የማይገባው ያልወረሰው እውነት ስለሆነ ነው፡፡
የአርማጭሆ ህዝብ አገርና መንግሥት ለየቶ የሚያውቅ የአገርንና የመንግሥትን ልዩነት በአንክሮ የሚገነዘብ ህዝብ ነው፡፡ በሸዋ ደጃች ባልቻ አባነፍሶ ከንጉሱ ጋር በነበራቸው ቅራኔ በግዞት የተቀመጡ ቢሆንም፤ ጣልያን ሲመጣ "ፀቤ ከንጉሱ እንጂ ከአገሬ አይደለም" ብለው ከጣልያን ጋር መግጠማቸው ይታወቃል። የዚህ ዓይነቱ ታሪክ በሸዋ ብቻ ሳይሆን በአርማጭሆም ይታወቃል። እንደምታውቁት ደጃዝማች አያሌው ከመንግሥት ጋር የሚስማሙ አልነበሩም። በወቅቱ ከነበሩት ንጉስ ጋር የማያግባባ ጉዳይ ነበራቸው። ነገር ግን "ከንጉስ ጋር ብጣላ ከኢትዮጵያ ጋር አልተጣላሁም። የእኛ ይደርሳል። ለመኳረፍም

አገር ያስፈልጋል” ብለው ከነደጃች ብሬ፣ ከነራስ አሞራው ጋር በመሆን ጠላትን ያርበደበዱ ንግስናንና አገርን የለዩ፤ መንግሥትንና አገርን የለዩ “ከመንግሥት ተጣላሁ” ብለው ለወራሪ ጠላት ያላደሩ ጀግኖች የፈለቁበት ነው። አርማጭሆ የዛሬው ትውልድ የመንግሥት አስተዳደር ባይመቸው ኢትዮጵያ በምቾት በድሎት የማትመነዘርና የማትቀየር እናት መሆኑን በመገንዘብ አገሩን ከውስጥም ከውጭም ጠላቶች የመከላከል የጀግንነት ታሪኩን ዛሬም እንደትናንቱ እንዲደግም አደራ እላለሁኝ፡፡

“ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው” እንደሚባለው በዚህ ዘመን ጀግኖችን በጀግና ሰፈር እንዳይውሉ የሚያደርጋቸው ወሬ ነው። ይህን ደግሞ አርማጭሆ ጠንቅቆ ያውቃል፤ በዚያ በመከራ በችግር ጊዜ ለወረኞች አርማጭሆ፤

“መረረኝ እንደሬት በላኝ እንደሳማ፣

የማይረባ ነገር ጆሮዬ እየሰማ።” ያለው ወሬ ጀግናን የሚከፋፍል፣ ጀግንነትን የሚያኮላሽ መሆኑን በመገንዘብ “አልባሌ ነገር ጆሮዬ አይስማ” በሚል ልጆቹን ያስተማረ ነው። የአርማጭሆ ህዝብ አሁንም የኢትዮጵያ ህዝብ ከማይረባ ወሬ ተጠብቆ በአንድነት፣ በመሰብሰብ፣ በመተጋገዝ፣ በፍቅርና በይቅርታ አገሩን ማሻገር ይችላል። ይህ ህዝብ እንደትናንቱ ዛሬም እንዲያስተምር በታላቅ አክብሮት በድጋሚ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ክቡር ፕሬዚዳንት በአጋጣሚ ሆኖ አርማጭሆ አካባቢ እንዳስተዳደሩ ቅድም አንስተውልናል። ከርሳቸውም ቀድሞ የተናገረው ወንድሜ አንዳንድ ነገር አንስቷል። ነገር ግን ለእነዚህ ሰዎች ያለኝ ምላሽ አርማጭሆን ሁኑ ነው፡፡ አርማጭሆ ጀግንነት ብቻ ሳይሆን ትዕግስት ያውቃል። ይሄንንም በግጥሙ ሲገልጽ፡-

“ኧረ! ድመቲቱን አይጢቱ መታቻት፣

ህምም ብላ ቀረች ጊዜ ባይመቻት።” ያለው የአርማጭሆ ህዝብ ጀግንነት ብቻ ሳይሆን ጊዜ መምረጥን የሚያውቅ ነው። ከአርማጭሆ ህዝብ ትዕግስት፣ ብልሃት፣ ማስተዋልና መሰብሰብ ተምረን ጠላትን የማንገጠም ከገጠምን ደግሞ የማንሸነፍና የማንመለስ መሆናችንን በድጋሚ አረጋግጥላችኋለሁ።

አንድ ወዳጄ “አሁን ያለውን ሁኔታ ግራ አጋቢና ለመግለጥ የማይቻል የሚያስቸግር ነው” ብሏል። “አሁን ያለውን ሁኔታ በአንድ ምሳሌ ልንገርህ” አለኝ፤ ይህ ወዳጄ ንግግር አዋቂ ነውና “ሁለት ጎረምሶች በመንገድ ሲጓዙ ከሌላ ሰው ጋር ይገናኙና የተለመደ የጎረምሳ ግጭት ይገጥማቸዋል። ከተጋጩ በኋላ አንደኛው ጎረምሳ አንደኛውን በጩቤ ይወጋዋል። ጎረምሳ ደሙ እንዳይፈስ የተወጋውን ቦታ በእጁ ይዞ እየጮኸ ‘ወየው! ድረሱልኝ ተወጋሁ’ እያለ ይሮጣል። ከኋላውም የወጋው ሰውዬ እየጮኸ ተከትሎት ይሮጣል። በመሃል ሽማግሌዎች መጥተው ሁለቱንም ይዘው ‘ምን ሆነህ ነው የምትሮጠው?’ ቢሉት ይሄኛው ‘በጩቤው

ወጋኝ ደሜን ተመልከቱ' ብሎ ያሳያቸዋል። 'አንተኛውስ ምን ሆነክ ነው ምትሮጠው?' ሲሉት 'ጩቤዬን ይዞብኝ ሔደ' ብሎ መለሰ። ጩቤውን ከሰካበት በኋላ መሰካቱ ሳያንስ 'ይዞብኝ ሄደና መልሱልኝ' እያለ ተከትሎ ሮጠ።" አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ነገር እንዲህ ነው፡፡ የተወጋን እኛ፤ ተወቃሽ እኛ። ይሁን እንጂ እውነት ከጀግኖች ጋር ስላለች፣ እውነት ከኢትዮጵያ ጋር ስላለች፣ የእውነት አምላክ ትናንት በታሪካችን በተደጋጋሚ እንዳሳየው ነገም አሸናፊ እንደሚያደርግ ቅንጣት ታክል ጥርጥር የለንም፡፡ አርማጭሆች ጀግንነት ብቻ ሳይሆን ደጋጎች፣ አቃፊዎች፣ አኩራሾች፣ ትብብርን የምታውቁ ስለሆናችሁ፣ በትዕግስት፣ በማስተዋል፣ በመደማመጥ የተቸገረ ምርኮኛም ሆነ ጠላትም በማኩረስ ኢትዮጵያዊነትን ደግማችሁ እንድታሳዩ በታላቅ አክብሮት አደራ እላለሁ።

በመጨረሻ ዛሬ በዚህ በሚያምር ስፍራ ጀግንነት ብቻ ሳይሆን ለእርሻ ምቹ የሆነ ሲያዩት እጅግ የሚያስጎመጅ አካባቢን ለማየት እድል ያገኘንበት ዋንኛው ምክንያት እህታችን ዝናሽ ታያቸው ብሬ ብትሆንም ላለፉት ወራት ለረዥም ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን እዚህ ቦታ እንድንመጣ አብረን እንድንጎበኝ በተደጋጋሚ ያነሱ ነበር። እርሳቸው፣ እህታችሁና ልጃችሁ ይህንን ስፍራ ለማየት ከጀግኖች ጋር ለመገናኘት የእናንተን ውሎ ገብ የእናንተን አካባቢ ለማየት እድል ስለሰጡኝ በአርማጭሆ ህዝብ ስም እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

አብዝቼ እወዳችኋለሁ፤ አከብራችኋለሁ። ስለተገናኘን በጣም ደስ ብሎኛል። ደጋግመን እንደምንተያይ ተስፋ አደርጋለሁ። እንግዲህ የዛሬው እንደጥሎሽ ይወሰድ።

**አመሰግናለሁ!**

ሰኔ 1፣ 2013 ዓ.ም

# ጉራጌ የህብረት ተምሳሌት

እንዴት አረፈዳችሁ? ክቡር አቶ ርስቱ ይርዳው ለዛሬው መርሃ ግብር አልጋበዙኝም። ነገር ግን ከቢሮዬ ሆኜ የተንቢ "በላለዴንጣ" የሚለው ድምጽ አላስቀምጥ ስላለኝ "ሰላም" ብያችሁ ብሄድ ብዬ ነው፤ ከረበሽኩ በጣም በጣም ይቅርታ፡፡

መቼም ድምጻችሁ፣ ህብረታችሁ፣ ጣዕመ ዜማዎቻችሁ ቢሮ አላስቀምጥ ያሉኝ የነንጉስ ዳርዜሞ ጌሮ የጌታ ካቹ፣ የአጋዝ ደቀመ የበርደ ፈርጣሶ፣ የነባንቺዬ የነአጋ ሸበታ፣ የባሻ ይገኑ ልጆች ስለሆናችሁ በአንድነት በሚያምር መንገድ ድምጻችሁ ዛሬ ለአዲስ አበባ የሚያምር ጣዕም ያለው እጣን ሆናችኋልና የተንቢ፡፡

እንኳን ደህና መጣችሁ!

ከአባቶቻችሁ እንደተማራችሁት "እንምጊ የማትንህነ" ይላል ጉራጌ፤ "እንምጊ የማትንህነ" የሚለው የአንድነት፣ የመሰባሰብ፣ የመደመርን ጣዕምና ትርጉም በደምብ ስለሚያውቅና ከዚያም በላይ "ንቅነት፤ ቅማትነት" ስለሆነ ነው፡፡

አንድነታችሁ ከአባቶቻችሁ የወረሳችሁት ባህላችሁ፣ ታሪካችሁ የኢትየጵያ ጣዕምና ጣፋጭ ሆኖ እንዲቀጥል እንዲሁ እንዳማረባችሁ እንድትቀጥሉ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርብላችኋለሁ። ዘንድሮ ያሰብነው ወልቂጤ ላይ ነበር። አንዳንዶች ስላኮረፉ ወደ አጋሮ ገፋ አድርገነዋል። የወልቂጤዎቹ ፈርተው ማለት ነው። ለማንኛውም በጉራጌ ባህል ኩርፊያ፣ ግጭት ይኖራል። ነገር ግን ከአባቶቻችን የተማርነው አንድ ቁም ነገር አለ። "በአብ አፈር ይትዋኬ ባዶ ጠፈር ይድችፋጉቺ" ይላል። ኩሪፍያም ቢኖር የሚያምርብን እንዳስተማሩን በፍቅር በአንድነት በመደመር ለብልጽግና ቁልፉ ነገር የጉራጌ ባህል ነው። ኢትዮጵያ እንድትበለጽግ እንድትለማ ዛሬም እንደትናንቱ ሥራ እያሳያችሁ፣ እያስተማራችሁ፣ እቁብ እየጣላችሁ፣ ሀብት እየተጋራችሁ፣ ኢትዮጵያን እንድታስቀጥሉ፣ እንድታሻግሩ አደራ እላችኋለሁ።

የዛሬን አያርገውና በዓለም ደረጃ እነሮዛ ፓርክ ሳይታወቁ ጉራጌዎች እነቃቄን እነ አዴሾን እነዳነቦሊዲያትን እነአጀት ውቅሬትን እነአጀት ማርቴት የመሳሰሉ ለሴት ልጆች እኩልነት ነፃነት የታገሉ ጀግኖች ያሉበት ሕዝብ ነው። ጉራጌ ሥራ እና ንግድ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ ሲሆን ትግልም ያውቃል። ይህንን ባህልና ቁምነገር ደግሞ ዛሬ ኢትዮጵያ አብዝታ ስለምትፈልግ ልክ እንደእናቶቻችሁ፣ እንደአባቶቻችሁ በቀኝ እጃችሁ እየሠራችሁ በግራ እጃችሁ አገራችሁን እንድትጠብቁ፤ ሰላማችሁንና የኢትዮጵያን ሰላም እንድታረጋግጡ አደራ እላለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ ሰዎች ጉራጌን በክትፎ ያነሳሉ። እኛ ጉራጌን በቅርበት የምናውቀው ግን ክትፎ ብቻ ሳይሆን ዝማሞጃት፣ ዱኩቸር፣ ብራብራት፣ ቄሳን የመሳሰሉ ጣፋጭ ምግቦችን ለኢትዮጵያ ያስተዋወቀ የኢትዮጵያ ኩራት ነው። ከዚህ ህዝብ ጋር ተባብረን ታሪኩን ልማቱን ማፋጠን እንድንችል በጉራጌ አካባቢ እጅግ ማራኪ የሆኑ ታሪካዊ ቦታዎች መኖራቸው ማወቅ ተገቢ ነው። እነዚህን ለማያውቁ ለማሳሰብ ጭምር ጢያ ላይ ታሪካዊ ትክል ድንጋይ በሶዶ አካባቢ እንዳለን፤ ከኦርቶዶክስ እምነት አኳያ በጣም ጥንታዊ ገዳማት እንደምድረ ከብድ አቦ ያሉ ሌሎችም ገዳማት ያሉን መሆኑን፤ ከሙስሊም አኳያ አብሬት እና ቃጥባሬ የመሳሰሉ መስጊዶች ታሪካዊ ማዕከላት አሉን። ከዚህም በተጨማሪ እጅግ ማራኪ የሆኑት የኮሩት ዘብይደርና የሞን ተራራ ልክ እንደእንጦጦ ቢለሙ ለብዙዎች መስህብ መሆን የሚችሉ ናቸው።

የጉራጌ ሕዝብ ታሪክ ጀግንነት፣ አገር ወዳድነት በኢኮኖሚውም በባህሉም አዳዲስ ነገር በማስተዋወቅ የሚታወቅ ነው። የአዲስ አበባ ጣዕም፣ የኢኮኖሚያችን ጣዕም፣ የኢትዮጵያ ጣዕምና የመደመር ምሰሶ ናችሁ፡፡ መደመር ማለት ጉራጌ ከወልቂጤ፣ ከኩምሪ፣ ከወርበጨ ሳይቸገር፣ አጋሮ፣ መቀሌ፣ ባህርዳር፣ መርካቶ ላይ በነፃነት እንዲሰራ ማስቻል ነው። በዚሁ አግባብ በፍቅር በአንድነት አገራችንን እንድናስቀጥል፣ ባህል ታሪካችንን እንድንጠብቅ፣ ታላቆቻችንን እንድናከብር፣ ትናንትናችንን እንዳንረሳ፣ ኢትዮጵያን እንደጣፈጠች እንደበለጸገች ለአፍሪካ ጨው እንድናደርግ በታላቅ ትህትና አደራ እላችኋለሁ። የጀመርነውን ሁሉ እንጨርሳለን፤ ኢትዮጵያን እናበለጽጋለን። ሰላማችንን እናረጋግጣለን። ዛሬም እንደትናንቱ የአፍሪካ ፈርጥ ሆነን እንቀጥላለን። መልካም በዓል ይሁንላችሁ!
ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር!

**አመሰግናለሁ!**

ሰኔ 2፣ 2013 ዓ.ም

# አሻራ መጽሐፍ የ“አሻራ ማንጸሪያ”

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የብዙ ማጣቀሻዎች፣ የብዙ መረጃዎች ምንጭ ነው። አሁን ባለው ደረጃ ደግሞ የብዙ ዜናዎች ምንጭ ሆኖ እያገለገለ ነው። በዚህ ሁኔታ 80ኛ ዓመት በዓሉን ስናከብርና አሻራን ስናስመርቅ በበኩሌ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል።
ዶክተር ብርሃኑ ሌንጂሶ፣ ዶክተር ፍጹም አሰፋ፣ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው መጽሐፉን በሚመለከት ጊዜ ወስደው አብራርተዋል። እኔም አየት አየት አድርጌዋለሁ። እንደ አንባቢ ደስ ብሎኛል። እንደ ተናጋሪ መናገርና እንደ አንባቢ መናገር ስለሚለያይ ማለት ነው። እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምንታዘበውና የምንማረው ነገር አለ። ሰዎች ሁሉ ሃሳብ አላቸው። ሃሳቦቻቸውን በቃል ለሌሎች ያጋራሉ፣ ቃሎች ተሸክነውና ታቅደው ተግባር ይሆናሉ። ተግባር አሻራ ይሆናል። በአሻራ እና በቃል መካከል ድልድይ የሚሆነው መጽሐፍ ነው። ሃሳብን ከቃል ወስዶና መሃል ላይ ተግባር እንዳለ ታሳቢ በማድረግ አሻራን ያሳየ መጽሐፍ ለትውልድ እጅግ ይጠቅማል። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጊዜ ወስዶ ይሄንን መጽሐፍ ስላዘጋጀ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

እየሠራን ሥራዎቻችንን እየዘከርን ለትውልድ አሻራ እየተውን መሄድ ያስፈልጋል። እየሠራን ካልሆነ ከአሻራ ጋር ልንገናኝ አንችልም። አሻራ ሥራ ስለሚፈልግ በየዕለቱ እየሠራን ሥራዎቻችን ደግሞ ለትውልድ የሚተላለፍበትን መንገድ ከፈጠርን በእርግጠኝነት ኢትዮጵያ ብልጽግናን ማረጋገጥ ትችላለች። ቀደም ሲል ዶክተር ብርሃኑ ሌንጂሶ ስለአንዳንድ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ሲያነሱ ትውስታ ስለፈጠሩብኝ አንዳንድ ማስታወሻ ለመያዝ ሞክሬያለሁ።

በርካታ ሰዎች ባለፉት ሦስት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ “መፈናቀል፣ ግጭት፣ ጦርነት፣ ኮሮና፣ አንበጣ፣ ጎርፍና አለመረጋጋት በዝቷል” ብለው ይናገራሉ። በትክክልም መናገር ብቻ ሳይሆን ችግሮቹና ፈተናዎቹ ነበሩ። ነገር ግን እነዚህ ‘በብዙ ችግር ያለፍንባቸው’ ብለን በተደጋጋሚ የምናነሳቸው ሦስት ዓመታት ካለፉት አስር ዓመታት ጋር በንጽጽር ብናወዳድር ቢያንስ ከጂዮ ፖለቲካ አኳያ አሁን ያለብንን ጫና ያህል ከስድስት እና ሰባት ዓመት በፊት አልነበረም።

አሁን በሰሜን የተፈጠረውን ሁኔታ አንዳንዶች ከኤርትራ ግጭት፣ አንዳንዶቹም ከካራማራ

ጋር ሊያወዳደሩ ይሞክራሉ። ነገር ግን ወታደርም ስለሆንኩ ችግሩ ከሁሉም የከፋ ነው። ምክንያቱም ከጣሊያን ጋር ስንዋጋ በጦር በጎራዴ ቢሆንም፤ እኛ ጎራዴያችንን እነርሱ መሳሪያቸውን ይዘው ፊት ለፊት ተዋግተናል። ከኤርትራም ጋር እኛ ባለን እነርሱም ባላቸው ነው የተዋጋነው። ካራማራም እንደዚሁ ነበር። አሁን ግን ከእኛ ጋር የገጠመን ውጊያ በመጀመሪያ የእኛን ክላሽ፣ ትጥቅ፣ መድፍ በመያዝና መከላከያን በማፍረስ ነው። እኛ ኃይል ይዘን፣ ጠላትም ኃይል ይዞ አይደለም። የእኛ ኮር ክፍል በጠላት ቁጥጥር ሥር ሆኖ ነው ውጊያ የተጀመረው። እንደዚህ ዓይነት ውጊያ አልጠበቅንም። ውጊያው ከእስከ አሁኑ ይለያል።
በሦስት ዓመት ውስጥ በመከራ፣ በችግሮች፣ በግጭቶች ውስጥ አልፈናል። እነዚያ በንጽጽር በተሻለ ደረጃ "ሰላም ናቸው" በምንላቸው ጊዜያት የነበሩ ጉዳዮችን ብቻ ጥቂት ለማሳያነት መመልከት ጠቃሚ ይሆናል። የዛሬ ሰባት፣ ስምንት፣ አስር ዓመት ተጀምረው ሊጠናቀቁ ያልቻሉ አስር የስኳር ፋብሪካዎች ነበሩ። በሰላሙ ጊዜ ማዕቀብ የሚባል በማይወራበት፣ የጂዮ ፖለቲካ ጫና በሌለበት፣ በምስራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ግጭት ባልተፈጠረበት ጊዜ አስር ስኳር ፋብሪካዎችን ጀምረን መጨረስ ተቸግረን ነበር። ነገር ግን መከራ የበዛባቸው በምንላቸው ጊዜያት ሰባቱን አጠናቀናል። እንዴት ነው አንጻራዊ መረጋጋትና ሰላም በነበረበት ወቅት ፕሮጀክት ጀምረን ሳንጨርስ "ችግር" አለ በተባለበት ወቅት ከ92 ቢሊዮን ብር በላይ በማውጣት ሰባቱን ፕሮጀክቶች መጨረስ የቻልነው? በነገራችን ላይ ስምንተኛው የወልቃይት ስኳር ፋብሪካ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፤ ለሥራ ዝግጁ ነው። ትልቁ ችግር አገዳ ነው። አገዳውን ለማምረት ትልቅ ግድብ መሥራት ይጠበቅብናል። በዚያ ምክንያት እርሱን ባንጨምረውም ሰባቱ ግን ማምረት ጀምረዋል። እንደ አገር አራት አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጀምረናል። ከአራቱ ሶስቱ ተጠናቀው ስራ ጀምረዋል። የተጀመሩትና የተጓተቱት በንጽጽር የተሻለ ወቅት በምንለው ሲሆን፣ የተጠናቀቁት ደግሞ በንጽጽር የከፋ ወቅት በምንለው ነው።

የኢንዱስትሪ ፓርክን ብንወስድ ከኮምቦልቻ፣ መቀሌና ሃዋሳ ውጪ ስምንት ፓርኮች ተጀምረው ያላለቁትንና ተጨማሪ ወጪና ጊዜ የጠየቁትን በዚህ ሦስት ዓመት አጠናቀናል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ጅማ፣ አዳማ፣ ሰመራ፣ ድሬዳዋ፣ ባህር ዳር፣ ደብረ ብርሃን፣ ቦሌ ለሚ አንድ እና ሁለት አጠናቀናል። እንደ መከላከያ፣ እንደ ኢመደአ ያሉ በርካታ ህንጻዎች ተጀምረው አስር ዓመት ገደማ የወሰዱ ቢሆንም ግንባታቸውን ያጠናቀቅነው በዚህ ጊዜ ውስጥ ነው። ይሄ ብቻ ሳይሆን ታላቁ ህዳሴ እንደተጠናቀቀ ሆኖ፣ ነገሌ ዳዋ ከሦስት ዓመት በፊት ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ግድቡ ውሃ መያዝ ስላልቻለ የኤሌክትሪክ ኃይል አያመርትም። ከለውጥ በኋላ ውሃ ይዘን የኤሌክትሪክ ኃይል አምርተናል። ኮይሻ ተጀምሮ ቆሞ ነበር። ታላቁ ህዳሴ ግድብንና ጣና በለስን ለየት የሚያደርገው ነገር ጣና በለስ ችግሩን ከለየን በኋላ በአዲስ መልክ ገንዘብም፣ ሰውም መድበን ስራ ስንጀምር አምስት ወር የፈጀብን ቀድሞ ካለ አግባብ

የተከማቹ ፋብሪካ ሳይሆኑ ፋብሪካ የሚመስሉ እቃዎችን ማንሳት ነው፡፡ ታላቁ ህዳሴም እንደዚሁ ጊዜ የወሰደው በሙቶኛ ከፍ ብሎ ይነገር የነበረው የኤሌክትሮ ሜካኒካል ክፍሉን በማንሳት ነበር፡፡ ይህ ከለውጥ በኋላ የመጡ ጉዳዮችን ሳላነሳ በንጽጽር ሰላም ባልናቸው ወቅቶች ሊጠናቀቁ ያልቻሉና በከፋ ጊዜ ውስጥ የተጠናቀቁ ስራዎችን ያመላክታል፡፡
ይህ የህልምና ላቅ ያለ ትኩረት የመስጠት የቁርጠኝነት ውጤት ነው፡፡ ሃሳቦቻችን፣ ቃሎቻችን፣ የምናከብራቸው ጉዳዮችን በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብንሆን ማሳካት እንደምንችል ያመላክታል፡፡ ይሄንን ነገር ለመካድ እንዳልነበረ አድርጎ ለማየት መሞከር አግባብ አይደለም፡፡

ከሶስት ሰዓት በፊት ወደዚህ ስፍራ ስትመጡ ፀሐይ ነበረች፡፡ ፀሐይን መካድ አይቻልም፡፡ የሚቻለው ነገር ዓይንን መጨፈን ብቻ ነው፡፡ ዓይንን ጨፍኖ ራስን ማጨለም ይቻል ይሆናል እንጂ ለዓለም የምትበራን ብርሃን "የለችም" ብሎ መሞገት አይቻልም፡፡ አሁን ብዙ ሰዎች እየመጣ ያለውን ተጨባጭ ለውጥ ማመንና መቀበል የሚቸገሩት ውስጣቸውን ስለሚያሳውሩ ነው፡፡ ይህ ነገር ለኢትዮጵያ ብልጽግና አይጠቅምም፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ በመንግሥት ሥራ ላይ ያላችሁ የሥራ ሐላፊዎች በጣም እድለኛ መሆናችሁን ተገንዝባችሁ በሠራችሁት ሥራ የምትኩራሩ እና ድል ብቻ የምትዘክሩ ሳትሆኑ ይበልጥ ለመስራት መትጋት ከሁላችንም የሚጠበቅ መሆኑን ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ባለው ፍጥነት አስር የስኳር ፋብሪካ ቆሞ ሰባት እያጠናቀቅን፤ አራት አግሮ ኢንዱስትሪ ጀምረን ሶስት እያጠናቀቅን ከሄድን ብልጽግናን ማረጋገጥ አንችልም፡፡ የኢትዮጵያ ብልጽግና የሚረጋገጠው አስራ አምስት ወይም ሃያ የስኳር ፋብሪካዎች ስንጨርስ ብቻ ነው ፡፡ እንደ ድል የምንናገረው ብቻ ሳይሆን ገና ብዙ ልናከናውን የሚገባን ሥራ እንዳለ አሁንም ሰዓት እንደምንቆጥር፣ ብዙ መሮጥ እንዳለብን ማሰብ በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡

ናይጄሪያዊያን አንድ አባባል አላቸው፡፡ ሁልጊዜ የአዳኞች ታሪክ በጀግንነት የሚነገረው ሃምሳ አዳኝ ለአደን ወጥቶ አስር አዳኞች አንበሳ ገድለው ከተመለሱ ከሆነ ጊዜ በኋላ ይገጠማል፣ ይዘመራል፣ ይዘፈናል፣ ይጻፋል፡፡ አስሩ ጀግኖች ስለሚወደሱ የአዳኞች ጀግንነት ይነገራል፡፡ ነገር ግን ከሃምሳው አርባው በአንበሳ ተበልተው ቢሆን፤ አንበሶች ታሪካቸውን መጻፍ ስለማይችሉ የአንበሶች ጀግንነት አይነገርም፡፡ ታሪክ የአሸናፊዎች ብቻ ሳይሆን የእውነት ጠበቃ መሆን አለበት፡፡ ታሪክን ያሸነፈው ኃይል ሳይጽፈው ሲቀር የሚረሱና የሚዘነጉ ከሆነ በሙሉ አስተማሪ አይሆንም፡፡ ብዙ ጊዜ የሚጻፍላቸው ጀግኖች እያሉ ሳይጻፍላቸው፣ ሳይዘመርላቸው ይቀራል፡፡ በዚህም ከበርካታ ጀግኖች ታሪክ ልንማር፣ ልንቀስም የሚገባንን እውቀት ሳንቀስም እንቀራለን፡፡ ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በእኔ እምነት አንጋፋ

በራሱም አሻራ ነው። ስለዚህ የእኔን ንግግሮች ብቻ ሳይሆን የሌሎች ከእኔ የላቀ ጥበብ፣ እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን በተለያየ ቦታ የሚናገሯቸውን ቁምነገሮች በደንብ በዚህ መንገድ ተጽፈው ለትውልድ እንዲሸጋገሩ ማድረግ ከተቻለ አሁን ያለው 'በታሪክ ላይ ተንተርሰን የምንጣላው፣ የምንነጋገረው ይቀንሳል' ማለት ነው።
ታሪክ የዛሬ ዜና ውጤት ነው። የዛሬ ዜና እና የነገ ዜና ተሰናስለው፣ ተደምረው ታሪክ ይሆናሉ። ሰዎች ዜናን ዋሽተው፣ በሀሰት ዜና የሚጽፉ ከሆነ ታሪክ ይሆናል። የዚያ ዜና ድምር ውጤት ደግሞ ሀሰተኛ ታሪክ ለትውልድ እንዲሸጋገር ያደርጋል። በዚህ መንፈስ የምንጽፍ ሰዎች ደግሞ በተቻለ መጠን ለዛሬ ስሜታችን ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችን በጎንዮሽና በቀጥታም እያሰብን መሥራት አለብን። መጻፍ፣ ማንበብ፣ የጻፉ ሰዎችን ማመስገን፣ የጻፉ ሰዎችን ማክበር እና ጽሑፍ በእውቀት መልኩም እንዲሸጋገር ማድረግ ይገባል፤ ለዚህም "አደራ" ማለት እወዳለሁ።

ኢትዮጵያዊያን ስለጽሑፍ ስናነሳ በጋዜጣ ለሰዎች የተሰራጩ ጽሁፍን በመቶ ዓመት መገደብ የለብንም። ለሺ ዓመታት መጀመሪያ በስዕል በኋላም በቅርጽ፣ በኋላም በጽሑፍ ኢትዮጵያዊያን እምነትን አሸጋግረዋል። በአፍሪካ ሕብረት ውስጥ አረብኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ፖርቱጋል፣ ፈረንሳይ የሚሰራበት ሲሆን፤ አንድም የአፍሪካ ቋንቋ የለበትም። የሁሉም የአፍሪካ ህብረት የሥራ ቋንቋዎች ከሌላ የዓለም ክፍል የመጡ ናቸው። ከአፍሪካ የመጡ አይደሉም። ነገር ግን የራሳችን ፊደል ኖሮን መጽሐፍ ቅዱስን እና ቅዱስ ቁርአንን በብራና ላይ ጽፎ ያሸጋገረ ህዝብ ታሪክ ወደ መቶ ዓመት መሰብሰብ የለብንም። በሺ ዓመት የሚቆጠር በጽሑፍ በግዕዝም ይሁን በአማርኛ በሌሎች ቋንቋዎች የተጻፈ ታሪክ ያለን ህዝብ ነን። ይህንን ነገር እኛ ካላልነው ልክ እንደ አንበሳው ታሪክ ይሆናል። የራሱ ፊደል ያለው አንድም የአፍሪካ አገር የለም ሳይሆን፤ በአፍሪካ ህብረት ውስጥ አንድ የአፍሪካ ቋንቋ የስራ ቋንቋ እንዲሆን ለመፍቀድም ትንሽ ጊዜ ይፈልጋል። ይሄ የሆነበት አንደኛው ምክንያት የገደሉ ይጽፋሉ፣ አንበሶቹ አይጽፉም። "እባካችሁ አንበሶች ብትነቁ ይሻላችኋል" ለማለት ነው። የኢትዮጵያ ሰላም፣ ብልጽግና፣ የወደፊት ጉዞ ብንፈልግም ባንፈልግም ይረጋገጣል። ዋናው የዚህ ታሪክ አካል ለመሆን እንደምናስበው፣ እንደምንናገረው ሁሉ በተለይ ችግኝ እየተከልን ለትውልድ መልካም ነገር እንድናኖር አደራ።

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንኳን ደስ አላችሁ!**
**በጣም አመሰግናለሁ!**
ሰኔ 2፣ 2013 ዓ.ም

# አሻራ መጽሐፍ የ"አሻራ ማንጸሪያ"

መስቀል አደባባይ ብዙ ያየ ብዙ ያሳለፈ የማንነታችን ክፋይ፣ የመሰብሰቢያችን ሲሳይ ነው። የብዙ አገሮች መሪዎችን ተቀብሎ አስተናግዷል፤ በህልፈተ ህይወት የተሰናበቱ መሪዎች ሸኝቷል። በመስቀል ደመራ በዓል ደምቋል፣ ታላላቅ የህዝብ በዓላትን አስተናግዷል። የድጋፍና የተቃውሞ ሰልፎችን አይቷል። በየማለዳው የአካል ብቃት ሯጮችንና ስፖርተኞችን አደግድጎ ተቀብሏል። ስሙ ተቀይሮ "የአብዮት አደባባይ" ተብሏል፤ የምርጫ 97 እና የሰኔ 16 የገነፈለ የህዝብ ስሜት በሰፊ ሆዱ ተሸክሞ አሳልፏል።

የኢትዮጵያ ብቸኛ ትልቅ አደባባይ በመሆኑ የመጣውን ታላቅ ኹነት ሁሉ ለብቻው እንደ አመጣጡ ተቀብሏል። ከመቀሌ እስከ ሞያሌ፣ ከሐረር እስከ ጎንደር፣ ከኮንሶ እስከ ገለምሶ፣ ከሁመራ እስከ ሰመራ፣ ከደገሃቡር እስከ ባህር ዳር፣ ከድሬደዋ እስከ አድዋ፣ ከአክሱም እስከ ይርጋለም፣ ከላሊበላ እስከ ጋምቤላ፣ ከአሶሳ እስከ አዋሳ፣ ከጅማ እስከ መተማ፣ ከጅጅጋ እስከ ቦንጋ፣ ከቢያራ እስከ ጌራ፣ ከሽሬ እስከ ቡሬ፣ ከቤጊ እስከ ቴፒ፣ ከቡታጅራ እስከ ጎርጎራ፣ ከአዲስ አበባ እስከ አላባ፣ ከሻሸመኔ እስከ ገዋኔ፣ ከደሴ እስከ ነቀምቴ፣ ከሞጆ እስከ ነጆ፣ ከመቱ እስከ ቢሾፍቱ፣ ከእንደርታ እስከ ወላይታ፣ ከጨንቻ እስከ ኮምቦልቻ፣ ከበሻሻ እስከ መናገሻ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከሁሉም ጫፍ "መዲናዬ" ብሎ በሚሰበሰብባት ከተማችን አንድ የሚመጥናትን አደባባይ ለሁላችንም የሚበቃ ለሁላችንም የሚያረካ ሆኖ በመገንባቱ "እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን" እላለሁ።

ልማት እንደ ማጥፋት፣ ማደስ እንደ ማፍረስ ቀላል አይደለም። መቶ ዓመት የቆመ ዛፍ በጥቂት ደቂቃ ተቆርጦ ሊወድቅ ይችላል። በብዙ ድካምና ጥረት የተገነባ ቤት በቅጽበት ማፍረስ ቀላል ነው። መጽሐፍ ጽፎ ለማሳተም ወራት እና ዓመታት ይፈጃል። ለማጣጣልና ለማቃጠል ግን ክብሪት እና ክፋት በቂ ነው። ለዘመናት ተከባብሮ እና ተሳስሮ የኖረን ህዝብ አቃቅሮ ለማፋጀት ምሁርነት ወይንም ጀግንነት ሳይሆን ክፋትና ተንኮለኝነት ይበቃል። ማጥፋት ሥራ አይደለም፤ ማፍረስም ሥራ ሊባል አይችልም። እውቀት፣ ክህሎትና በጎ ልቦና ከትጋት እና ጽናት ጋር የሚጠይቀው መስራት እና መለወጥ ነው። አገራችንን የማልማትና የማጥፋት፣ የመካብ እና የመናድ ምርጫ ከፊታችን ተቀምጧል። ኢትዮጵያዊያን ቅራኔ መሰልጠን፣ መገፋፋትም ምርጫ እንዳልሆነ ጠንቅቀን እናውቃለን። ጠንክረን አገራችንን እንድንጠብቅ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

የትናንት ጠባሳ የነገ አበሳ እንዳይሆን መትጋት ከሁላችንም ይጠበቃል። ታሪክ ትናንት በዛሬ ላይ ጥሎ ያለፈው አሻራ ወይንም ጠባሳ ነው። ራዕይ ደግሞ በዛሬ ላይ ያነጣጠረ ተስፋ ወይንም አበሳ ነው። የትናንት አሻራን በማጥናት፣ የነገን ተስፋ በመሰነቅ፣ የዛሬን ዕድል መጠቀም ከዜጎች ሁሉ የሚጠበቅ ኢትዮጵያን የምትሻገርበት ብቸኛ መንገድ ስለሆነ ነው። ይህ ካልሆነ የትናንት ጠባሳ የነገን አበሳ ይወልዳል። ለዚህም ነው በትናንት ጥፋትና ውድቀት ተተብትበን ያለፈውን ትውልድ ከመርገም ይልቅ ብሩህ ተስፋና ተዝቆ የማያልቅ እድል ላይ አነጣጥረን የመጪውን ትውልድ ብልጽግና እውን ለማድረግ ዛሬ ላይ ሳንታክትና ሳናሰልስ መትጋት ይኖርብናል የምንለው። ተሰናስለን ከተጋን ያማረች ኢትዮጵያን መፍጠር እንችላለን።

ወገኖቼ ሰላም እንደ ጤና ነው። የመኖሩ ዋጋ አይታወቅም። ሲጠፋና ሲረበሽ ደግሞ ከጤና በላይ ውድ፣ ከሰላም በላይም መሰረታዊ ነገር አለመኖሩን እንረዳለን። በአሁኑ ወቅት ኮቪድ 19 የተባለ ህመም መነሻው ባልታወቀ ጦስ ተከስቶ ከአንድ ዓመት በላይ ዓለምን እያመሰ ይገኛል። በኮቪድ ምክንያት የጠፋውን የሰው ህይወትና ጤና፣ ሀብትና ጊዜ ለመለካትና ለመገመትም ይከብዳል። ለክትባት እና ሕክምና፣ ለመደጎም እና ለማቋቋሚያ የፈሰሰው ጥሪት በትሪሊዮን ዶላሮች ይቆጠራል። በየዓመቱ ለጦር መሳሪያና ከሌላው ብርቱ ሆኖ ለመገኘት የሚፈሰው ሀብት እጅግ ከቁጥር በላይ ነው። ለዚህ ነው የአንድ ጦርነት ዋጋ ከአንድ መቶ ዓመት ሰላም ወጪ ይበልጣል የሚባለው። ጤናማ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ከሌሉ ጤናማ ማህበረሰብና አገር አይኖርም። ሰላምም ከግል የሚጀምር ነው። ሰላማዊ ንግግር ሰላማዊ ግብር ይፈጥራል። ስለሆነም እያንዳንዳችን ሰላምን አጥብቀን የምንሻና የምንኖራት እንድንሆን በታላቅ ትህትና ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ተፈጥሮ የብዙ ነገሮች ብዛት፣ የብዙ ነገሮችም ጥራት መሸከም ትችላለች። አስደማሚ ደን ብዙ ዛፎችን መያዝ ይችላል። ጥሩ ለመሆን ጥቂት፣ ብዙ ለመሆን ደግሞ ብዙ ኮተታም መሆን ግዴታ አይደለም። ህዝባችን ብዙ ስለሆነ ጥሩ ኑሮ ለጥቂቶች ብቻ የተገባ አድርጎ መውሰድ ስህተት ነው። ትልቅ አገር ስላለን "ጥሩ ነገር በጥቂት ቦታ ብቻ ሊኖር ይገባል" ብሎ ማሰብም ተገቢ አይደለም። ጥሩ ነገርን ፍለጋ የተንከራተትነው እዚህ ያለው ስለማይበቃን አይደለም። የምንሰራው ጥሩውን ለማብዛትና ብዙውን ጥሩ ለማድረግ ነው። የአንድነት ፍሬ ዛሬ ብንተክል፣ የብልጽግና መሰረት ዛሬ ብንጥል ለልጆቻችን የተሳለች፣ የምታጓጓ፣ ነጻ ኢትዮጵያን መፍጠርና ማሻገር እንችላለን።

"ተሃድሶ እንዲኖር ሊታደስ የሚገባውና የሚችል የቀደመ ስልጣኔ ሊኖር ይገባል" የሚል መከራከሪያ ሲነሳ ይሰማል። አፍሪካ የቀደመም የአሁንም ስልጣኔ የሌላት በመሆኑ "የአፍሪካ

ተሃድሶ" የሚለው እንደ ተራ ኩረጃ ሊያጣጥሉት የሚሞክሩ ብዙዎች ናቸው። በእርግጥ አፍሪካ የነገ ህልሟን የሚሸከም የኋላ ታሪክ የሌላት ጨለማ አህጉር ናትን? የኢትዮጵያ ቀደምት ወርቃማ ዘመንስ? በማሊ፣ በዚምባቡዌ የነበሩ ያልተዘመረላቸው ታላላቅ ስልጣኔዎችስ? የኑቢያ እና የካርቴጅ ስልጣኔስ? የግብጽ ስልጣኔስ? እነዚህ ሁሉ የአፍሪካ ስልጣኔ አይደሉምን? በአፍሪካ ከእስያና አውሮፓ ያልተናነሱ ስልጣኔዎች ነበሩ። ለዚህ ግንባር ቀደም ከነበሩት ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ነች። የሚታደስም አዲስ የሚፈጠርም ስልጣኔ መፍጠር እንችላለን፤ የኋላ ታሪካችንና የወደፊት ህልማችንን ማገናኘት ከቻልን የዛሬ ማንነታችን የተደላደለ መሰረት ላይ ይቆማል። ስለሆነም ጊዜው አላለፈም።

የጋራ ህልማችንን እውን ለማድረግ ዛሬ መሰረት በመጣል ኢትዮጵያን ወደ ነበራት ገናና ማንነት በመመለስ ብቻ ሳይሆን፤ ለትውልድ ማሸጋገር እንችል ዘንድ ዛሬ በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራር አባላት የነገዪቱን ኢትዮጵያን በመገንባትም በጋራ እንድንቆም በታላቅ ትህትና ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ኢትዮጵያን በአፍሪካ ቀንድ የአፍሪካ ክንድ እናደርጋታለን። ከጎረቤት አገሮች ጋር ድንበር ብቻ ሳይሆን፤ ህዝብ፣ ህልምና ህልውና እንጋራለን። በደምና በአጥንት የተዛመድን፣ በቋንቋና በባህል የተዋሃድን፣ በህልምና በህልውና የተጋመድን ከመሆናችን በላይ ወደ ሩብ ቢሊዮን የሚጠጉ ህዝቦቻችን ሰፊና ውብ፣ ለምለም መልከዓ ምድራችን ከቀይ ባህር እስከ ህንድ ውቅያኖስ የሚዘልቅ የባህር ድንበራችን፣ በከርሰ ምድራችን ያሉ ሀብቶቻችን ቢደመሩ ሊፈጥሩ የሚችሉት የብልጽግና ልክ መገመት ከሚቻለው በላይ ነው። ከጥላቻና ጥርጣሬ መር ግንኙነት ወጥተን የቅርብና የሩቅ ሸራቢዎችን የከፋፍለህ ግዛ ወጥመድ አምልጠን በመከባበርና በመተባበር የጋራ ጥረትና ትስስር ብንፈጥር በአጭር ጊዜ ውስጥ የአፍሪካ ክንድ መሆን ይቻላል። ለዚህ ደግሞ የቀጣናውን ግማሽ ህዝብ ይዛ ሁሉንም በዝምድና እና በጉርብትና የምታስተሳስረው ኢትዮጵያ ልዩ ታሪካዊ ሃላፊነትና እድል በእጇ ይገኛል።

የአፍሪካ ቀንድ ተባብሮ የአፍሪካ ክንድ መሆን ከቻለ መላው አፍሪካ ከቀኝ ገዢዎች ነጻ እንዲሆኑ ያለፈው ምዕተ ዓመት አብሪ ኮከብ የሆነችው ኢትዮጵያ የአፍሪካ የድህነት መቃብርና የብልጽግና ምሳሌ መሆን ትችላለች። የአፍሪካ ቀንድ የድህነትና የረሃብ ቀጣና መሆኑ ቀርቶ የቤተሰብነትና የአንድነት ተምሳሌት ከሆነ የአፍሪካ የብልጽግና ፀሃይ ከምስራቅ ወጣች ማለት ነው። ለዚህ ሁሉ መሰረትና መነሻው የኢትዮጵያዊያን ቀድሞ መንቃት፣ ነቅቶ መትጋት፣ ተግቶ መስራት እና ሰርቶ ማሳየት ነው። ጥላቻና መከፋፈልን ካሸነፍን ውስጣዊ ሰላም ካረጋገጥን፣ በዙሪያችን የሰላም ምንጭ መሆን አይከብደንም። ዙሪያችን ሰላም ከሆነ ደግሞ የቅርብ ሩቅ፣ ትንሽ ትልቁ በራችንን ማንኳኳቱና መክፈቱ አይቀሬ ነው።

ወገኖቼ፣ ዛሬን እንንቃ፣ እንትጋ። የኢትዮጵያ ብልጽግና የሚወለደው በልጆቿ ትጋትና አንድነት ብቻ መሆኑን አንዘንጋ። የኢትዮጵያ ብልጽግና በብልጽግና ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በጋራ የፓርቲዎች ትብብር መሆኑን ከወዲሁ መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል። አባቶቻችን ለልጆቻቸው ሲሰሩ ብዙ ፈተና ገጥሟቸዋል። ዛሬ ልንኮራባቸው፣ ልናስጎበኛቸው፣ ልንንከባከባቸውና ልንጠብቃቸው የሚገባ ቅርሶች የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጎንደር አብያተ መንግስታት፣ የጂማ የአባ ጅፋር ቤተ መንግስት በየስፍራው ያሉ ቅርሶቻችን ሲሰሩ መሪዎቻችን ተፈትነው ነበር። ሳይነቃነቅ የሚያበጥር ሰፌድ የለም። ገለባን ከእህል ለመለየት መነቅነቅ የግድ ይላል። አሁን መነቅነቃችን ገለባን አራግፈን ኢትዮጵያን የአፍሪካ ፈርጥ ለማድረግ ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ ኩራት እንጂ ፍርሃት የማይነካካን መሆኑን በድጋሚ አረጋግጣለሁ።

እኛ ስንሠራ የሚረዱ፣ የሚርዱ፣ የሚያርዱ አሉ። ስንሠራ የሚረዱ ባያግዙም ይገባቸዋል። የሚረዱን ደግሞ በጊዜ፣ በገንዘብና በእውቀት የሚያግዙን ናቸው። የሚርዱት ብልጽግናችን የሚያስጨንቃቸው ነው። የሚያርዱት ግን “እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል” የሚለውን የኢትዮጵያ አባባል “ውሸትና ምሽት እያደር ይነግሳል” ብለው ለመተካት የሚጥሩ ብቻ ናቸው። እኛ ግን የሚረዱንን አስከትለን፣ ለሚረዱን ታምነንና ሳንሰርቅ በንጹህ ልብ እያገለገልን፣ የሚርዱትን አጽናንተን፣ የሚያርዱትን ደግሞ አስታግሰን፣ ሥራችንን እንቀጥላለን።
ኢትዮጵያ እንደ ቅኔ ነች፤ እኛ እንደ ገጣሚ ነን። አሁን የምንጽፈው ታሪክ ዛሬ ሳይሆን በልጆቻችን ሲተረክ ይኖራል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዛሬ ቢነቃና አሻራ ላይ ቢያተኩር አዲስ ሥራ ቢሠራ ቢተባበር፣ ቢቀናጅ ኢትዮጵያ እውነትም የአፍሪካ ፈርጥ መሆን ትችላለች።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ኢትዮጵያ በቁጥር ስድስተኛውንና በዓይነቱ የመጀመሪያውን ምርጫ ታካሂዳለች። በዚህ ምርጫ መንግሥት ከምንጊዜውም በላይ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሁሉም ፓርቲዎች በእኩል የሚሳተፉበት፣ በሕግ አውጪው ምክር ቤት ብዙ ድምጾች የሚሰሙበት፣ ሁሉም ፓርቲ በወሳኝ ወሳኝ ጉዳይ እየተባበረ የኢትዮጵያን ጥቅም እያስቀደመ፣ የከፋፍለህ ግዛ ሃሳቦች ባንዳ ሳይሆን ታጋይ ሆኖ እየታገለ በጋራ የሚቆም መንግሥት እንዲኖራት እንፈልጋለን። ነገር ግን ምርጫን ተውሰናል። አንድ ነገር ዓለምን እንድናስተምር በታላቅ ትህትና የኢትዮጵያን ህዝብ እጠይቃለሁ። እየመረጥን አሻራችንን እናስቀምጥ፤ በዕለቱ አርባ ሚሊዮን ገደማ ህዝብ ይወጣል። አርባ ሚሊዮን ወይም ሰማኒያ ሚሊዮን ችግኝ አሊያም መቶ ሃያ ሚሊዮን ችግኝ ብንተክል አሻራ እያኖርን እንደምንመርጥ በማሳየት ዓለምን ማስተማር እንችላለን። ሁልጊዜ ከእነርሱ የምንቀበል ሳይሆን አንዳንድ

ጊዜ የምናስተምር እንድንሆን በጋራና በትብብር እንድንቆም ጥሪዬን አቀርባለሁ።
በመጨረሻም ዛሬ የምናስመርቀው ይህ ድንቅ ስራ በዚህ ቦታ ጀምረው ለቀጣዩ አመራር ያሻገሩት የቀድሞ ምክትል ከንቲባ ታከለ ኡማና ከእርሳቸው ጋር የነበሩ ባለሙያዎችን በሙሉ እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። ክብርት ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለአዲስ አበባ አንድ አደባባይ አይመጥናትም። በርከት ያለ፣ ያማረ፣ የላቀ አደባባይ በመስራት ዳግም እንደምንገናኝ ተስፋዬ የላቀ ነው።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ እና ተከብራ**
**ለዘላለም ትኑር! ትኖራለችም!**
**አመሰግናለሁ!**
ሰኔ 7፣ 2013 ዓ.ም

# አሻራ መጽሐፍ የ"አሻራ ማንጸሪያ"

የተፎካካሪ ፓርቲዎች አመራር አባላትና ተወካዮች በዚህ ስፍራ ወንድማማችነትን፣ ህብረትን፣ የኢትዮጵያን አሸናፊነት የሚያረጋግጠውን መሰረት ለመጣል ፍቃደኛ ሆናችሁ የተገኛችሁ ወንድም እና እህቶቼ በሙሉ እንኳን ለዚህ ቀን አበቃን።

ሁላችሁም እንደምታውቁት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ በዚህ መልክ በህብረት ቆመን ለምርጫ የምንዘጋጅበት ብዙም ታይቶ አይታወቅም። የምርጫ ቦርድ ነጻ ተቋም ሆኖ መጪውን ምርጫ በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ እንዲቻል በገባነው ቃል መሰረት በፋይናንስ ላለፉት አምስት ምርጫዎች ከወጣው ወጪ የበለጠ ሀብት መድበናል። ሕግ አሻሽለናል። እንዲሁም ሁላችሁም በምታውቁት መንገድ የምርጫ ቦርድ አመራር አባላት ነጻ ሆነው እንዲሰየሙ ለማድረግ ጥረት አድርገናል።

ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ገደማ ምርጫ ቦርድ ያቀረበው ማንኛውም የድጋፍ ጥያቄ መንግሥት አቅም በፈቀደ መልኩ ሙሉ በሙሉ ለመመለስ ጥረት አድርጓል። ነገር ግን እስካሁን ምርጫ ቦርድ በወሰናቸው በምንቀበላቸውም በማንቀበላቸው፣ ትክክል ነው ብለን በምናምንባቸውም በማናምንባቸውም ጉዳዮች ጣልቃ ሳንገባ የምርጫ ቦርድ ነጻና ገለልተኛነትን አምነን ውሳኔዎቹን ለማስፈጸም ሥንሰራ ቆይተናል። በዚህም የገባነውን ቃል ለመፈጸም ባደረግነው ጥረት ለራሳችን እንደ ፖለቲካ ፓርቲ እንዲሁም እንደ መንግሥት ትልቅ ክብር የሚሰማን እና ትክክለኛ፣ መራር ቢሆንም ጠቃሚ ውሳኔዎች እንደወሰንን አድርገን እንወስዳለን። ይህንን አቋማችንን በምርጫው ማግስት ምርጫ ቦርድ "በዚህ ውድድር አሸንፈዋል" ብሎ የሚገልጻቸውን ፓርቲዎች እና ግለሰቦች ሙሉ በሙሉ በመቀበል እንደግመዋለን። ከዚህ ቀደም እንደነበረው ምርጫ ኮሮጆ አንሰርቅም። ማንኛውም ተፎካካሪ ፓርቲዎችና ግለሰቦችን በታላቅ አክብሮት እንቀበላለን። በጋራ የሚያሠራ ሁኔታም ካለ ከምንጊዜውም በላይ ከእናንተ ጋር ለመስራት ዝግጁ መሆናችንን ደግሜ አረጋግጣለሁ።

ይህንን ባህል ማስቀጠል ከቻልን በሕግ አውጪው ምክር ቤት ውስጥ በምናወጣቸው ህጎች፣ ስትራቴጂዎች ፖሊሲዎች ጠቃሚ የውይይት መድረኮች በመፍጠር አስቀድመን መንግስታችንን ማጠናከር እንችላለን። ከዚያም ባሻገር በምርጫ ሙሉ በሙሉ ያሸነፉ ወይም የተወሰነ ድምጽ አግኝተው ለማሸነፍ የማይችሉ ተፎካካሪ ግለሰቦችና ፓርቲዎች

በሚያገኙት ድምጽ ልክ መንግሥት አስፈላጊውን አክብሮት በመስጠት በጋራ ለመስራት በስድስተኛው ምርጫ እንደሚጀምር እምነት አለኝ። ቢያንስ ቢያንስ በብልጽግና ፓርቲ በኩል ከእያንዳንዱ ፓርቲዎች አገር ወዳድ ግለሰቦች እንዳሉና ከእነርሱ ጋር ተቀራርበን ብንሰራ ኢትዮጵያ ዳግም አሸናፊ ብትሆን እንጂ ዳግም እንደማትጎዳ በጽኑ እናምናለን። ለእናንተ ያለኝ መልዕክት በህብረት ከቆምን በጥንቃቄ ከያዝናት ኢትዮጵያ አለት ናት፤ አትሰባበርም፣ አትደፈርም ማንም አይሸራርፋትም። ነገር ግን በህብረት ካልሰራን ደግሞ እንደ ብርጭቆ ናት። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ብርጭቆ የሆነች ኢትዮጵያን ማየት አይመኝም። ጠንካራ አለት የሆነች ኢትዮጵያን ለማየት በእኛ በኩል ከተሸነፍን በተደጋጋሚ እንዳልኩት አቅፈን ስልጣን እናስረክባለን። ምናልባት የተወሰነ ወንበር የምንጋራ ከሆነም ባልተለመደ ሁኔታ በትብብር እንሰራለን። በተለያዩ አጀንዳዎችም በተደጋጋሚ እንወያያለን። አደራ ልላችሁ የምፈልገው እንደ መንግሥት በእኛ በኩል ማድረግ የሚገባንን ሁሉ ለማከናወን ዝግጁ ብንሆንም ከሰላማዊ መንገድ ውጪ የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚያስቡትን አንዳንድ ሰላም የማናጋት ሁኔታዎች በእናንተ በኩል ከመንግሥት ጎን በመቆም አንዳች ኮሽታ ሳይሰማ ህጋዊና ሰላማዊ ምርጭ እንድናደርግ በትህትና እጠይቃችኋለሁ።

እዚህ ካለነው ፓርቲዎች ፍላጎትና ምርጫ ውጪ አዲስ አበባ ላይ የተወሰኑ ሰዎች ከሌላ ቦታ ለማስገባት በጎጃምና በምዕራብ አካባቢ ትንሽ ሁከት ለመፍጠር የሚደረገውን ሙከራና ዝግጅት ሙሉ በሙሉ መንግሥት የሚያውቀው፣ የሚቆጣጠረው፣ የሚያመክነው ይሆናል። ሰላማዊ ምርጫ በኢትዮጵያ የሚደረግና ያሸነፈ ወይም ያሸነፉ ፓርቲዎች በጋራ ኢትዮጵያን የሚያልቅ መንግሥት እንደሚመሰርቱ፣ ካላሸነፍን ልናስረክባችሁ፣ በጋራ የሚያሰራ ሁኔታ ካለ ልንሰራ፤ ካሸነፍን ኢትዮጵያን ልናሻግር ቃላችንን ልንጠብቅና ላናጥፍ ዝግጁ መሆናችንን አረጋግጣለሁ።

በምርጫው ሂደት የሚፈጠር ማንኛውም ስህተት ካለ ከእናንተ ሰምተን ከእናንተ ጋር ተባብረን ልንፈታው ዝግጁ መሆናችንን እንድትገነዘቡ እፈልጋለሁ። በተለይ ከሩቅ "አይስማሙም፣ አይግባቡም፣ እንደፈለግን እናባላቸዋለን" ለሚሉ ሰዎች ኢትዮጵያን ሲሳይ እንዳናደርግ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊያንን ከሁሉ በላይ ልጆቻችን የሚኮሩበት ታሪካዊ ክስተት እንዲሆን በታላቅ ትህትና ሁላችሁም በአንድ ልብ እና መንፈስ "አደራ" እላለሁ። ለሁላችሁም መልካም ምኞቴን እየተመኘሁ፣ በዚህ ፓርላማ ብዙ ድምጾች፣ ብዙ ሰዎች እንዲታዩ በግል ያለኝን ፍላጎት እገልጻለሁ።

**አመሰግናለሁ!**

ሰኔ፣ 2013 ዓ.ም

# መስቀል አደባባይ
# የድንቅ ሥራ ማሳያ

መስቀል አደባባይ ብዙ ያየ ብዙ ያሳለፈ የማንነታችን ክፋይ፣ የመሰብሰቢያችን ሲሳይ ነው። የብዙ አገሮች መሪዎችን ተቀብሎ አስተናግዷል፤ በህልፈተ ህይወት የተሰናበቱ መሪዎች ሸኝቷል። በመስቀል ደመራ በዓል ደምቋል፣ ታላላቅ የህዝብ በዓላትን አስተናግዷል። የድጋፍና የተቃውሞ ሰልፎችን አይቷል። በየማለዳው የአካል ብቃት ሯጮችንና ስፖርተኞችን አደግድጎ ተቀብሏል። ስሙ ተቀይሮ "የአብዮት አደባባይ" ተብሏል፤ የምርጫ 97 እና የሰኔ 16 የገነፈለ የህዝብ ስሜት በሰፊ ሆዱ ተሸክሞ አሳልፏል። የኢትዮጵያ ብቸኛ ትልቅ አደባባይ በመሆኑ የመጣውን ታላቅ ኹነት ሁሉ ለብቻው እንደ አመጣጡ ተቀብሏል። ከመቀሌ እስከ ሞያሌ፣ ከሐረር እስከ ጎንደር፣ ከኮንሶ እስከ ገለምሶ፣ ከሁመራ እስከ ሰመራ፣ ከደገሃቡር እስከ ባህር ዳር፣ ከድሬደዋ እስከ አድዋ፣ ከአክሱም እስከ ይርጋለም፣ ከላሊበላ እስከ ጋምቤላ፣ ከአሶሳ እስከ አዋሳ፣ ከጅማ እስከ መተማ፣ ከጅጅጋ እስከ ቦንጋ፣ ከቢያራ እስከ ጌራ፣ ከሸሬ እስከ ቡሬ፣ ከቤጊ እስከ ቴፒ፣ ከቡታጅራ እስከ ጎርጎራ፣ ከአዲስ አበባ እስከ አላባ፣ ከሻሸመኔ እስከ ገዋኔ፣ ከደሴ እስከ ነቀምቴ፣ ከሞጆ እስከ ነጆ፣ ከመቱ እስከ ቢሾፍቱ፣ ከእንደርታ እስከ ወላይታ፣ ከጨንቻ እስከ ኮምቦልቻ፣ ከበሻሻ እስከ መናገሻ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከሁሉም ጫፍ "መዲናዬ" ብሎ በሚሰበሰብባት ከተማችን አንድ የሚመጥናትን አደባባይ ለሁላችንም የሚበቃ ለሁላችንም የሚያረካ ሆኖ በመገንባቱ "እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን" እላለሁ።

ልማት እንደ ማጥፋት፣ ማደስ እንደ ማፍረስ ቀላል አይደለም። መቶ ዓመት የቆመ ዛፍ በጥቂት ደቂቃ ተቆርጦ ሊወድቅ ይችላል። በብዙ ድካምና ጥረት የተገነባ ቤት በቅጽበት ማፍረስ ቀላል ነው። መጽሐፍ ጽፎ ለማሳተም ወራት እና ዓመታት ይፈጃል። ለማጣጣልና ለማቃጠል ግን ክብሪት እና ክፋት በቂ ነው። ለዘመናት ተከባብሮ እና ተሳስሮ የኖረን ህዝብ አቃቅሮ ለማፋጀት ምሁርነት ወይንም ጀግንነት ሳይሆን ክፋትና ተንኮለኝነት ይበቃል። ማጥፋት ሥራ አይደለም፤ ማፍረስም ሥራ ሊባል አይችልም። እውቀት፣ ክህሎትና በጎ ልቦና ከትጋት እና ጽናት ጋር የሚጠይቀው መስራት እና መለወጥ ነው። አገራችንን የማልማትና የማጥፋት፣ የመካብ እና የመናድ ምርጫ ከፊታችን ተቀምጧል። ኢትዮጵያዊያን ቅራኔ መሰልጠን፣ መገፋፋትም ምርጫ እንዳልሆነ ጠንቅቀን እናውቃለን። ጠንክረን አገራችንን እንድንጠብቅ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

የትናንት ጠባሳ የነገ አበሳ እንዳይሆን መትጋት ከሁላችንም ይጠበቃል። ታሪክ ትናንት በዛሬ ላይ ጥሎ ያለፈው አሻራ ወይንም ጠባሳ ነው። ራዕይ ደግሞ በዛሬ ላይ ያነጣጠረ ተስፋ ወይንም አበሳ ነው። የትናንት አሻራን በማጥናት፣ የነገን ተስፋ በመሰነቅ፣ የዛሬን

ዕድል መጠቀም ከዜጎች ሁሉ የሚጠበቅ ኢትዮጵያን የምትሻገርበት ብቸኛ መንገድ ስለሆነ ነው። ይህ ካልሆነ የትናንት ጠባሳ የነገን አበሳ ይወልዳል። ለዚህም ነው በትናንት ጥፋትና ውድቀት ተተብትበን ያለፈውን ትውልድ ከመርገም ይልቅ ብሩህ ተስፋና ተዝቆ የማያልቅ እድል ላይ አነጣጥረን የመጪውን ትውልድ ብልጽግና እውን ለማድረግ ዛሬ ላይ ሳንታክትና ሳናሰልስ መትጋት ይኖርብናል የምንለው። ተሰናስለን ከተጋን ያማረች ኢትዮጵያን መፍጠር እንችላለን።

ወገኖቼ ሰላም እንደ ጤና ነው። የመኖሩ ዋጋ አይታወቅም። ሲጠፋና ሲረበሽ ደግሞ ከጤና በላይ ውድ፣ ከሰላም በላይም መሰረታዊ ነገር አለመኖሩን እንረዳለን። በአሁኑ ወቅት ኮቪድ 19 የተባለ ህመም መነሻው ባልታወቀ ጦስ ተከስቶ ከአንድ ዓመት በላይ ዓለምን እያመሰ ይገኛል። በኮቪድ ምክንያት የጠፋውን የሰው ህይወትና ጤና፣ ሀብትና ጊዜ ለመለካትና ለመገመትም ይከብዳል። ለክትባት እና ሕክምና፣ ለመደጎም እና ለማቋቋሚያ የፈሰሰው ጥሪት በትሪሊዮን ዶላሮች ይቆጠራል። በየዓመቱ ለጦር መሳሪያና ከሌላው ብርቱ ሆኖ ለመገኘት የሚፈሰው ሀብት እጅግ ከቁጥር በላይ ነው። ለዚህ ነው የአንድ ጦርነት ዋጋ ከአንድ መቶ ዓመት ሰላም ወጪ ይበልጣል የሚባለው። ጤናማ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ከሌሉ ጤናማ ማህበረሰብና አገር አይኖርም። ሰላምም ከግል የሚጀምር ነው። ሰላማዊ ንግግር ሰላማዊ ግብር ይፈጥራል። ስለሆነም እያንዳንዳችን ሰላምን አጥብቀን የምንሻና የምንኖራት እንድንሆን በታላቅ ትህትና ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ተፈጥሮ የብዙ ነገሮች ብዛት፣ የብዙ ነገሮችም ጥራት መሸከም ትችላለች። አስደማሚ ደን ብዙ ዛፎችን መያዝ ይችላል። ጥሩ ለመሆን ጥቂት፣ ብዙ ለመሆን ደግሞ ብዙ ኮተታም መሆን ግዴታ አይደለም። ህዝባችን ብዙ ስለሆነ ጥሩ ኑሮ ለጥቂቶች ብቻ የተገባ አድርጎ መውሰድ ስህተት ነው። ትልቅ አገር ስላለን "ጥሩ ነገር በጥቂት ቦታ ብቻ ሊኖር ይገባል" ብሎ ማሰብም ተገቢ አይደለም። ጥሩ ነገርን ፍለጋ የተንከራተትነው እዚህ ያለው ስለማይበቃን አይደለም። የምንሰራው ጥሩውን ለማብዛትና ብዙውን ጥሩ ለማድረግ ነው። የአንድነት ፍሬ ዛሬ ብንተክል፣ የብልጽግና መሰረት ዛሬ ብንጥል ለልጆቻችን የተሳለች፣ የምታጓጓ፣ ነጻ ኢትዮጵያን መፍጠርና ማሻገር እንችላለን።

"ተሃድሶ እንዲኖር ሊታደስ የሚገባውና የሚችል የቀደመ ስልጣኔ ሊኖር ይገባል" የሚል መከራከሪያ ሲነሳ ይሰማል። አፍሪካ የቀደመም የአሁንም ስልጣኔ የሌላት በመሆኑ "የአፍሪካ ተሃድሶ" የሚለው እንደ ተራ ኩረጃ ሊያጣጥሉት የሚሞክሩ ብዙዎች ናቸው። በእርግጥ አፍሪካ የነገ ህልሟን የሚሸከም የኋላ ታሪክ የሌላት ጨለማ አህጉር ናትን? የኢትዮጵያ ቀደምት ወርቃማ ዘመንስ? በማሊ፣ በዚምባቡዌ የነበሩ ያልተዘመረላቸው ታላላቅ ስልጣኔዎችስ? የኑቢያ እና የካርቴጅ ስልጣኔስ? የግብጽ ስልጣኔስ? እነዚህ ሁሉ የአፍሪካ ስልጣኔ አይደሉምን? በአፍሪካ ከእስያና አውሮፓ ያልተናነሱ ስልጣኔዎች ነበሩ። ለዚህ ግንባር ቀደም ከነበሩት ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ነች። የሚታደስም አዲስ የሚፈጠርም

ስልጣኔ መፍጠር እንችላለን፤ የኋላ ታሪካችንና የወደፊት ህልማችንን ማገናኘት ከቻልን የዛሬ ማንነታችን የተደላደለ መሰረት ላይ ይቆማል። ስለሆነም ጊዜው አላለፈም።

የጋራ ህልማችንን እውን ለማድረግ ዛሬ መሰረት በመጣል ኢትዮጵያን ወደ ነበራት ገናና ማንነት በመመለስ ብቻ ሳይሆን፤ ለትውልድ ማሸጋገር እንችል ዘንድ ዛሬ በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራር አባላት የነገዪቱን ኢትዮጵያን በመገንባትም በጋራ እንድንቆም በታላቅ ትህትና ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ኢትዮጵያን በአፍሪካ ቀንድ የአፍሪካ ክንድ እናደርጋታለን። ከጎረቤት አገሮች ጋር ድንበር ብቻ ሳይሆን፤ ህዝብ፣ ህልምና ህልውና እንጋራለን። በደምና በአጥንት የተዛመድን፣ በቋንቋና በባህል የተዋሃድን፣ በህልምና በህልውና የተጋመድን ከመሆናችን በላይ ወደ ሩብ ቢሊዮን የሚጠጉ ህዝቦቻችን ሰፊና ውብ፣ ለምለም መልከዓ ምድራችን ከቀይ ባህር እስከ ህንድ ውቅያኖስ የሚዘልቅ የባህር ድንበራችን፣ በከርሰ ምድራችን ያሉ ሀብቶቻችን ቢደመሩ ሊፈጥሩ የሚችሉት የብልጽግና ልክ መገመት ከሚቻለው በላይ ነው። ከጥላቻና ጥርጣሬ መር ግንኙነት ወጥተን የቅርብና የሩቅ ሽራቢዎችን የከፋፍለህ ግዛ ወጥመድ አምልጠን በመከባበርና በመተባበር የጋራ ጥረትና ትስስር ብንፈጥር በአጭር ጊዜ ውስጥ የአፍሪካ ክንድ መሆን ይቻላል። ለዚህ ደግሞ የቀጣናውን ግማሽ ህዝብ ይዛ ሁሉንም በዝምድና እና በጉርብትና የምታስተሳስረው ኢትዮጵያ ልዩ ታሪካዊ ሃላፊነትና እድል በእጇ ይገኛል።

የአፍሪካ ቀንድ ተባብሮ የአፍሪካ ክንድ መሆን ከቻለ መላው አፍሪካ ከቀኝ ገዢዎች ነጻ እንዲሆኑ ያለፈው ምዕተ ዓመት አብሪ ኮከብ የሆነችው ኢትዮጵያ የአፍሪካ የድህነት መቃብርና የብልጽግና ምሳሌ መሆን ትችላለች። የአፍሪካ ቀንድ የድህነትና የረሃብ ቀጣና መሆኑ ቀርቶ የቤተሰብነትና የአንድነት ተምሳሌት ከሆነ የአፍሪካ የብልጽግና ፀሃይ ከምስራቅ ወጣች ማለት ነው። ለዚህ ሁሉ መሰረትና መነሻው የኢትዮጵያዊያን ቀድሞ መንቃት፣ ነቅቶ መትጋት፣ ተግቶ መስራት እና ሰርቶ ማሳየት ነው። ጥላቻና መከፋፈልን ካሸነፍን ውስጣዊ ሰላም ካረጋገጥን፣ በዙሪያችን የሰላም ምንጭ መሆን አይከብደንም። ዙሪያችን ሰላም ከሆነ ደግሞ የቅርብ ሩቅ፣ ትንሽ ትልቁ በራችንን ማንኳኳቱና መክፈቱ አይቀሬ ነው።

ወገኖቼ፣ ዛሬን እንንቃ፣ እንትጋ። የኢትዮጵያ ብልጽግና የሚወለደው በልጆቿ ትጋትና አንድነት ብቻ መሆኑን አንዘንጋ። የኢትዮጵያ ብልጽግና በብልጽግና ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በጋራ የፓርቲዎች ትብብር መሆኑን ከወዲሁ መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል። አባቶቻችን ለልጆቻቸው ሲሰሩ ብዙ ፈተና ገጥሟቸዋል። ዛሬ ልንኮራባቸው፣ ልናስጎበኛቸው፣ ልንንከባከባቸውና ልንጠብቃቸው የሚገባ ቅርሶች የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጎንደር አብያተ መንግስታት፣ የጂማ የአባ ጅፋር ቤተ መንግስት በየስፍራው ያሉ ቅርሶቻችን ሲሰሩ መሪዎቻችን ተፈትነው ነበር። ሳይነቃነቅ የሚያበጥር ሰፌድ የለም። ገለባን ከእህል ለመለየት መነቅነቅ የግድ ይላል። አሁን መነቅነቃችን ገለባን አራግፈን ኢትዮጵያን የአፍሪካ ፈርጥ ለማድረግ ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ ኩራት እንጂ ፍርሃት የማይነካካን መሆኑን በድጋሚ

አረጋግጣለሁ።

እኛ ስንሠራ የሚረዱ፣ የሚርዱ፣ የሚያርዱ አሉ። ስንሠራ የሚረዱ ባያግዙም ይገባቸዋል። የሚረዱን ደግሞ በጊዜ፣ በገንዘብና በእውቀት የሚያግዙን ናቸው። የሚርዱት ብልጽግናችን የሚያስጨንቃቸው ነው። የሚያርዱት ግን "እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል" የሚለውን የኢትዮጵያ አባባል "ውሸትና ምሽት እያደር ይነግሳል" ብለው ለመተካት የሚጥሩ ብቻ ናቸው። እኛ ግን የሚረዱንን አስከትለን፣ ለሚረዱን ታምነንና ሳንሰርቅ በንጹህ ልብ እያገለገልን፣ የሚርዱትን አጽናንተን፣ የሚያርዱትን ደግሞ አስታግሰን፣ ሥራችንን እንቀጥላለን።

ኢትዮጵያ እንደ ቅኔ ነች፤ እኛ እንደ ገጣሚ ነን። አሁን የምንጽፈው ታሪክ ዛሬ ሳይሆን በልጆቻችን ሲተረክ ይኖራል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዛሬ ቢነቃና አሻራ ላይ ቢያተኩር አዲስ ሥራ ቢሠራ ቢተባበር፣ ቢቀናጅ ኢትዮጵያ እውነትም የአፍሪካ ፈርጥ መሆን ትችላለች።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ኢትዮጵያ በቁጥር ስድስተኛውንና በዓይነቱ የመጀመሪያውን ምርጫ ታካሂዳለች። በዚህ ምርጫ መንግሥት ከምንጊዜውም በላይ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሁሉም ፓርቲዎች በእኩል የሚሳተፉበት፣ በሕግ አውጪው ምክር ቤት ብዙ ድምጾች የሚሰሙበት፣ ሁሉም ፓርቲ በወሳኝ ወሳኝ ጉዳይ እየተባበረ የኢትዮጵያን ጥቅም እያስቀደመ፣ የከፋፍለህ ግዛ ሃሳቦች ባንዳ ሳይሆን ታጋይ ሆኖ እየታገለ በጋራ የሚቆም መንግሥት እንዲኖራት እንፈልጋለን። ነገር ግን ምርጫን ተውሰናል። አንድ ነገር ዓለምን እንድናስተምር በታላቅ ትህትና የኢትዮጵያን ህዝብ እጠይቃለሁ። እየመረጥን አሻራችንን እናስቀምጥ፤ በዕለቱ አርባ ሚሊዮን ገደማ ህዝብ ይወጣል። አርባ ሚሊዮን ወይም ሰማኒያ ሚሊዮን ችግኝ አሊያም መቶ ሃያ ሚሊዮን ችግኝ ብንተክል አሻራ እያኖርን እንደምንመርጥ በማሳየት ዓለምን ማስተማር እንችላለን። ሁልጊዜ ከእነርሱ የምንቀበል ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ የምናስተምር እንድንሆን በጋራና በትብብር እንድንቆም ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም ዛሬ የምናስመርቀው ይህ ድንቅ ስራ በዚህ ቦታ ጀምረው ለቀጣዩ አመራር ያሻገሩት የቀድሞ ምክትል ከንቲባ ታከለ ኡማና ከእርሳቸው ጋር የነበሩ ባለሙያዎችን በሙሉ እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። ክብርት ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለአዲስ አበባ አንድ አደባባይ አይመጥናትም። በርከት ያለ፣ ያማረ፣ የላቀ አደባባይ በመስራት ዳግም እንደምንገናኝ ተስፋዬ የላቀ ነው።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ እና ተከብራ ለዘላለም ትኑር! ትኖራለችም!**

**አመሰግናለሁ!**

ሰኔ 7፣ 2013 ዓ.ም





# ኢትዮጵያ አሸንፈች - እንኳን ደስ አለን!

ዛሬ ለመላው ኢትዮጵያዊያን ታላቅ ቀን ነው። ለዘመናት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማከናወን ስንናፍቅ ኖረናል። እነሆ! ጊዜው ደርሶ ያለምነውን ዛሬ ፈጽመናል። ዴሞክራሲ ለአገራችን ምኞት ብቻ ሳይሆን የታሪካችን አካል መሆኑን በዓለም ሕዝብ ፊት በግልጽ አሳይተናል። ከየትኛውም ወገን ያልሆነ ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ተቋቁሞ፣ በአጭር ጊዜ ተዓማኒና ፍትሐዊ የሆነ ምርጫ አካሂደን በስኬት አጠናቀናል። ከእንግዲህ የምርጫው አሸናፊ ማንም ይሁን ማን፣ በዛሬው ዕለት ኢትዮጵያውያን ከጫፍ እስከ ጫፍ ወጥተው "ይወክሉናል" የሚሏቸውን ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ በመምረጣቸው ኢትዮጵያ አሸናፊ ሆናለች። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ብታልፍም በዚህ ታሪካዊ ቀን ኢትዮጵያችን አሸንፋለች። እንኳን ደስ አለን።

የኢትዮጵያ ታሪክ በሁለት ተቃራኒ የሉዓላዊነት እውነቶች የሚላጋ ነው። ቀዳሚው የአገራችንን ሉዓላዊነት ከማንኛውም የውጭ ኃይል ተከላክለን ለዘመናት አስከብረናል። በዚህም የተነሣ ነጻነቷን የጠበቀችና ታፍራና ተከብራ የኖረች አገር መሥርተናል። በተቃራኒው የሕዝብን የሥልጣን ሉዓላዊነት ማስከበር አልቻልንም። የሕዝብን ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤትነትን ማረጋገጥ ባለመቻላችን፤ እርሱን ተከትለው በሚመጡ ችግሮች አገራዊ ህልውናችን ለተደጋጋሚ አደጋ ተጋልጧል።

ይህን የታሪካችንን እውነታ የመቀየር አጋጣሚ በተደጋጋሚ አግኝተናል። ግን አልተጠቀምንበትም። ሕዝብን ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤት የሚያደርግ ዴሞክራሲያው ሥርዓት ውስጥ እንድንገባ ታሪክ ዛሬ ሌላ ዕድል ሰጥቶናል።

በማንኛውም ጊዜ ወደ ዲሞክራሲ የሚደረግ ሽግግር ወደኋላ የሚስብ ያለፈ ኢ-ዴሞክራሲያዊነትና ወደፊት በሚታይ አዲስ የዴሞክራሲ ብሩህ ተስፋ መካከል የሚገኝ ነው። ከሽግግሩ አልፎ ዴሞክራሲን በማይነቃነቅ መሠረት ላይ ማቆም የሚቻለው ወደኋላ የሚከበንን ኃይል ለመታገል በምንጨርሰው ጉልበት ሳይሆን አዲስ በምንገነባው ሥርዓት ላይ አተኩረን ጠንካራ የዴሞክራሲ ጡቦችን በማስቀመጥ ነው።

ውድ ኢትዮጵያውያን! እስካሁን በአገራችን የተደረጉ ዴሞክራሲን የመትከልና የማጽናት

ትግሎች ያለፈውንና የነበረውን በመታገል ስኬታማ ሆነው ነበር። “አያስፈልግም” የምንለውን ያለፈውን ሥርዓት ካስወገድን በኋላ ግን ለወደፊት የሚያስፈልገንን በሚገባ አንተክለውም፤ ተክለንም አናሳድገውም። በዚህም ምክንያት ከትግሉ መነሻ እንጂ ከመድረሻው ላይ መቆም አልተቻለም። ትግላችን ሁሌም በእንጥልጥሉ የሚቋጭ፣ ለፍሬ የማይበቃ፣ ያለፍንበትን መንገድ ዳግም እንድንመለስበት የሚያደርግ ነው። ለዴሞክራሲ ታግለን የዴሞክራሲን ችግኝ የመንከባከብ ፍላጎቱ አይኖረንም። በአንዲት ምሽት ዴሞክራሲ እውን ሆኖ የሚያድርበት አገር እንደሌለ አውቀን ለዴሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ የሆኑ ጡቦችን ችላ ሳንል፤ አንዱን በሌላው ጡብ ላይ እየደረደርን መጓዝ መማር አለብን። ከዚህ አንኳያ ሲታይ የዘንድሮው ምርጫ በብዙ መልኩ ለዴሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ ከሆኑ እርምጃዎች እንደ አንዱ ስለሆነ ልምዶቻችን ወደፊት ለምናደርጋቸው እልፍ ምርጫዎች ጥሩ መነሻ ተደርገው መወሰድ አለባቸው።

የተከበራችሁ ተፎካካሪ ፓርቲዎች!

ለዚህ ምርጫ መሳካትና ሰላማዊ ሆኖ መጠናቀቅ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጫናዎችን ሁሉ ተቋቁማችኋል። ስህተቶችን በማረምና በመታገሥ ከፍ ያለ ሚና ተጫውታችኋል። ለዚህም ያለኝን አክብሮት ሳልገልጽ አላልፍም። የአገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች ውስብስብና ተደራራቢ መሆናቸውን ተገንዝባችሁ፣ ምርጫም ችግሮቻችንን ለመፍታት አንዱ መንገድ እንጂ በራሱ ብቸኛ መፍትሔ አለመሆኑን አምናችሁ ለዴሞክራሲያዊ ልምምዳችን የመጀመሪያውን ጡብ በጋራ ስላስቀመጣችሁ ይህንን ተግባራችሁን ታሪክ ሲዘከረው ይኖራል።

**አመሰግናለሁ !**

ሰኔ፣ 2013 ዓ.ም





# በክረምት የአቅመ ደካሞችን ቤት የማደስ ተግባር

የእናቶችን የደከሙ ቤቶች በየዓመቱ የማደስ፣ የመጠገን፣ የመቀየር ሀሳብ ከጀመርን ውሎ አድሯል፡፡ አሁን ክረምቱ እየጀመረ ነው፡፡ እንደሚታየው እናቶች የሚተኙት እዚህ ውሃ ዳር ነው። ዝናብ በሚሆንበት ወቅት የሚመጣባቸው ነገር አይታወቅም። ከዚያም በላይ ብዙ ሰዎች ዝናብ ሲመጣ ይሳቀቃሉ፤ ይጨነቃሉ ይንጋ አይንጋ በብዙ ያስባሉ። እነርሱ የሚተኙት እኛ ተረጋግተን እንደምንተኛው አይደለም። አንዳንድ እናቶች አሮጊቶች ልጅ የሌላቸው፣ አንዳንዶች ደግሞ የወላድ መሀን የሆኑ ናቸው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚኖሩ ስላሉ የየአካባቢው ማህበረሰብ እየተጋገዘ አምስትም፣ አስርም፣ አስራ አምስትም ቤት ቢሰራ የብዙ ሰው ሕይወት እፎይታ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

በዚህ ክረምት ሪፐብሊካን ጋርድና እኛ ከአስር እስከ አስራ አምስት የሚጠጉ ቤቶች ለመሥራት በመወሰን ዛሬ ሰባት ቤቶች አፍርሰናል። ከዚህ ቀደም የተወሰኑ የፈረሱ ቤቶች አሉ። ሰሞኑን የዚህ ዓይነቱ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ሁሉም አካባቢ ያሉ ዜጎች ገንዘብ የሌላቸውን እድሜያቸው ትንሽ ከፍ ያሉ እናቶችን እየለዩ በትብብርና በጉልበት ቤታቸውን ቢሰሩላቸው በብዙ መንገድ ኢትዮጵያ ትጠቀማለች፡፡ አንደኛ እነዚህ እናቶች ዓመትም ሁለት ዓመትም "እፎይ" ብለው ተኝተው "ያሰባችሁት ይሳካ፤ ኢትዮጵያ ትለምልም፤ ትበልጽግ" ብለው ቢመርቁን ለሁላችንም ይጠቅማል፡፡
በሌላ መንገድ ደግሞ በየአካባቢያችን በዚህ ክረምት ወጣቱ በጉልበቱ፣ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ የከተማው አስተዳደር፣ ሚንስትሮች፣ የተለያዩ ተቋማት ከተባበርን መቶ፣ ሁለት መቶ፣ ሶስት መቶ ቤት እንሰራለን። ይሄ ቀላል ነገር አይደለም። በየዓመቱ እንዲህ ከቀጠልንና ልምዳችን ከሆነ የብዙ ደሃ ሕይወት ስለሚቀየር መተባበር ያስፈልጋል። ጊዜ የለንም። ክረምቱ መጥቷል።

መላው የአዲስ አበባ ህዝብ በየአካባቢው ያሉ ዜጎቻችን ችግኝ መትከል በጣም መልካም ነገር ነው። መሬት ጦም እንዳያድር ማረስ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ነገር ግን ደግሞ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ "ክረምት መጣ አልመጣ፤ ዝናብ ዘነበ አልዘነበ" ብሎ የሚሰቃዩ እናቶችን ሕይወት ማሻሻል መቀየር ግዴታ ነው። በትብብር መንፈስ ከዛሬ ጀምሮ እንድንሠራና ክረምቱ ሳይቀድመን እንድንቀድመው አደራ እላችኋለሁ።

እንግዲህ አዳዲስ ሥራዎች እያከናወንን አዳዲስ እድሎች እያመጣን ጊዜያችንን ሳናባክን የምንሠራ ከሆነ ባጠረ ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ሁኔታ ይቀየራል። የኢትዮጵያ ሁኔታ የሚቀየረው የእኔ እና የአንተ ብቻ ሲቀየር አይደለም። የእኔና የአንተ ቤት ስለማያፈስም አይሆንም። በርካታ እናቶች ቤታቸው እንዳያፈስባቸው ማድረግ ስንችል ነው፡፡ ዛሬ ቤቱ ነገ ደግሞ ጓዳቸው እንዳያፈስ መሸንጥ መደገፍ ስንችል ነገሮች ይቀየራሉ። ሁላችንም በትብብር መንፈስ እንድንሠራ አደራ።

የመገናኛ ብዙኃን ባለሞያዎችም መዘገብ ብቻ ሳይሆን ተሰባስባችሁ የተወሰነ ቤት ብትሰሩ ጥሩ ነው፡፡ ምርቃትም ይጠቅማችኋል። ተባብረን የእናቶች ቤት እንስራ፤ አቅመ ደካሞችን እንደግፍ፤ እናግዝ። ይሄ በፈጣሪም በምድርም በጣም ጠቃሚ ነገር ነው።

**አመሰግናለሁ!**

ሰኔ 16፣ 2013 ዓ.ም





# የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ - ለአፍሪካውያን

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ለመንግስት፣ ለንግዱ ማህበረሰብ አመራር አባላት፣ ለተተኪ ወጣቶች የእውቀት ብርሃን የሚያፈልቅ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡
የአፍሪካም ሆነ የኢትዮጵያ ችግር የእውቀት ብርሃን ማጣት ነው፡፡ እውቀት ከማጣት የተነሳ እርስ በእርስ የምንባላ፣ የማንተጋገዝ፣ በጋራ የማንቆምና ሁልጊዜ የሌሎች ሲሳይ የምንሆን ያደረገን በአብርሆት ያልተሞላን፤ አርቀን ማየትና አሻጋሪ ሀሳቦችን ማፍለቅ አለመቻላችን ነው። ይሄንን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከእንጦጦ ጋር መሳ ለመሳ የሚነካካና እስካሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የትምህርት ተቋማት እጅግ በተለየ መንገድ ሰፋ ባለ ቦታ አካዳሚው ዘመናዊ ሆኖ ተገንብቷል። ይህ አካዳሚ በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅግ ዘመናዊ እቃዎች ተሟልተውለት ለምርቃት በቅቷል። ይህ ከመሰረተ ልማት አኳያ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ መድረሳችንን የሚያሳይ ታላቅ ድል ነው፡፡

ይህ ህንፃና መሰረተ ልማት የተሻለ ብቃት ያላቸው የአገር ውስጥና የውጪ ምሁራንን አቅፎ የሚፈለገውን የአመራር እውቀት ብቻ ሳይሆን ጥበብ የሚፈልቅበትና የሚገኝበት ተቋም ሆኖ እንዲገነባ ተጨማሪ ሥራዎች ማከናወን ይኖርብናል።

አፍሪካችን የኋላ ቀርነት፣ የጨለማ፣ የድህነት፣ የግጭት ምሳሌ ነች፡፡ ለምንድን ነው አፍሪካ የህዝቧ ቁጥሩ ከፍተኛ ሆኖ ሳለ እንዲሁም በርካታ የማዕድን ሀብትና መልማት የሚችል ምድር ይዛ ድሃ እና የድሃ ምልክት የሆነችው? የሚል ጥያቄ በስፋት ይነሳል። ለዚህ ቀላሉ መልስ ተደርጎ የሚወሰደው "ቅኝ የተገዛች አህጉር ስለሆነች ነው" የሚል ነው፡፡ ነገር ግን በዓለም ላይ ከመቶ በላይ አገሮች ቅኝ ተገዝተዋል። አውሮፓን ሳይጨምር በጣም ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ አገሮች ካልሆኑ በስተቀረ በቅኝ ያልተገዛ የዓለም ክፍል የለም፡፡ በእስያ፣ በደቡብ አሜሪካ፣ በሰሜን አሜሪካ በአውስትራሊያ ሁሉም አህጉሮች የቅኝ ተገዥነት እጣ ፈንታ ደርሶባቸዋል፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ በጨለማ ውስጥ አይደሉም። አፍሪካ በቅኝ መገዛቷን እንደምክንያት ወስዳ ካለችበት ጨለማ መውጣትና መሻገር ተቸግራ ቆይታለች። ይህን ምክንያት እንደ አህጉር ብንቀበለው እንኳን እንደ አገር ኢትዮጵያ ስላልተገዛች ለምንድን ነው እንደተገዙ አገሮች የጨለማ ምልክት የሆነችው? የሚለው ጥያቄ ጠንካራ መከራከሪያ ይሆናል። በቅኝ መገዛት ብቻውን በቂ ምክንያት ያለመሆኑንም ያሳያል፡፡
ሌሎች ሲከራከሩ "በአካል የነበረው ቅኝ መግዛት የቀረ ቢሆንም አሁንም ስልታዊ በሆነ

መንገድ የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ አልወጡም"ይላሉ። ለዚህም አህጉራቸውን፣ አገራቸውንና ህዝባቸውን የሚጠቅም ነፃ ሀሳቦች አፍልቀው መጠቀም ያለመቻላቸውን በመጥቀስ ይከራከራሉ።

የዚህ ችግር መነሾና መታጠፊያ ነጥብ የሆነው አስራ ስምንተኛው እና አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ እስከዚያ ጊዜ ድረስ አፍሪካ በሌላው ዓለም ካሉት ህዝቦች ጋር እምብዛም ባልተራራቀ ሁኔታ  እጣንም፣ እንጨትም ማንኛውም ጥሬ እቃ ለዓለም ገበያ በመሸጥ መኖር የምትችል ነበረች። የኢንዱስትሪ አብዮት በጀመረበት ምዕተ ዓመት ውስጥ በሰፊው የሚጓጓዘው ጥሬ እቃና  አገር እንዲያቀና በባሪያነት የሚሸጠው የአፍሪካ ዜጋ በዓለም ደረጃ የኢንዱስትሪ አብዮት ሲፋፋም የሰው ኃይል ፍላጎት እየቀነሰ ሄደ። “ጥሬ እቃውን እንጂ ሰው አያስፈልግም” ብለው ያመኑ ኃይሎች “የባሪያ ስርዓትን የሚያስፈጽም አህጉር መኖር የለበትም፤ የባርያ ስርዓት አደገኛ በመሆኑ መቆም አለበት” የሚል አዲስ ትርክት ይዘው መጡ፡፡

ይህ “የባሪያ ስርዓት ንግድ ይቁም” የሚለው ሀሳብ ለአፍሪካውያን ዱብዳ ነበር። ለዚህ ምክንያቱ ሰዎችን እየሸጡ ልክ እንደጥሬ እቃ ይኖሩ ስለነበር ነው። ከዚህ በኋላ “የሚሸጥ እና የማይሸጥ አገር፤ ዘመናዊ የሆነና ዘመናዊ ያልሆነ መንግስት” የሚል ትርክት ከዚያው ከሽጭ ገዢዎች አካባቢ መጣ። የባሪያ ስርዓት እኛ እንዲቆም ፈልገን ሳይሆን በበቂ ሰዎቻችንን የወሰዱ እና “ተጨማሪ ኃይል አያስፈልግም” ብለው ያመኑት ኃይሎች “የባሪያ ስርዓት አላስፈላጊና ወንጀል ነው ይቁም” የሚል ዱብዳ በአፍሪካውያን ላይ ሲጥሉ ነው፡፡

ከዚያ በኋላ አፍሪካውያን በገፍ ሰው እየላክን የምናገኘው ገቢ ቀነሰ። አፍሪካ ውስጥ ነዳጅን ጨምሮ ውድ የከበሩ ድንጋዮችና ሀብቶች አብዛኛዎቹ ሳይለሙ በጥሬ እቃነት እንዲበረከት የሚፈልጉ ኃይሎች ተፈጠሩ። እነዚህ ኃይሎች ሀሳባቸውን በማደርጀት አፍሪካ እርስ በእርሷ በብሔር፣ በሃይማኖትና በድንበር ስም እየተጋጨች እነርሱ አስታራቂ እየሆኑ ሀብቷን ንብረቷን ለመውሰድ ሁኔታዎችን አመቻቹ።

አፍሪካውያን መጀመሪያ ሀሳብ ሲሰጠን ተሽቀዳድመን ወስደን ስንፈጽም የሰለጠንን፣ የበቃን፣ የተሻልን መሆናችን ይነገረናል። እኛም እየተቀበልን ሸያጩን ካፋፋምን በኋላ “በቃ” ሲሉ ፈጥኖ ያቆመው “ዘመናዊ” ሸያጩን ማስቀጠል የፈለገ ደግሞ “ትክክለኛ ያልሆነ መንግስት” እንደሆነ እየነገሩን፣ እያጣሉን፣ እያጋጩን ላለፉት ሁለት መቶ ዓመታት ገደማ የጨለማ፣ የድህነት፣ የግጭት ምሳሌ ሆነን ቆይተናል።
አሁንም እነዚህ ሀሳቦች መልካቸውን ቀይረው አፍሪካ ላይ ይሰነዘራሉ። ያልተመቹ

መንግስታትና አገሮች አዳዲስ ስም ይሰጣቸዋል። ምናልባት "ነቅተናል፤ እንለወጥ" የሚሉ አፍሪካ አገሮች እንዲኮረኮሙ፣ አንገታቸውን እንዲደፉ፣ በግለሰብም በመንግስትም ደረጃ እንዲንኮታኮቱ ይደረጋል። በርካታ የአፍሪካ አገሮች መንግስታትና ግለሰቦች እንደምሳሌ ሊነሱ ይችላሉ። ምርጫ ብለው በስፋት የሚናገሩና የሚያስተምሩ የዓለም መንግስታት ምንም ምርጫ ካላደረጉና በወታደራዊ ኃይል ፈንቅለው ስልጣን ከያዙ መንግስታት ጋር በቅርበት ሲሰሩ ይታያል።

በአፍሪካ ውስጥ ምርጫ የማይደረግባቸው ወይም ተደርጎ በኃይል የሚገዙ አካባቢዎች ከነዚህ ኃይሎች ጋር በሰላምና በስምምነት ሲሰሩ ይታያል። ዋናው መመዘኛው ልማት፣ ሰላም፣ ብልጽግናና ዴሞክራሲ ሳይሆን የእነሱ መመቸት ነው፡፡ ይህ ከፍተኛ ችግር እየሆነና የአፍሪካን ህዝብ ወደኋላ እየጎተተ ያለው ድንቁርና ነው። ይሄ አካዳሚ ይሄንን ችግር ከመፍታት አኳያ ከፍተኛ ሚና ለእኛም ለጎረቤቶቻችንም ሊወጣ እንደሚችል ሙሉ እምነት አለን፡፡

ሁላችሁም እንደምታውቁት ከአፍሪካ በላይ በማህበረሰባዊ እሴት፣ በእርቅ፣ በእድር፣ በሽምግልናና በባህላዊ ስርዓት የደረጀ አህጉር እምብዛም አይገኝም። ሽማግሌዎችን ማክበር፣ የሽማግሌዎችንና የሀይማኖት አባቶችን ቃል መስማት በብዙ አፍሪካ አገሮች የሚታወቅ ቢሆንም፤ ይህ ማህበረሰባዊ እሴት ተንዶና ፈርሶ አፍሪካውያን እንኳን ለሌላ የሚተርፉ ለራሳቸው የእርቅ ማዕድ ሊሆኑ አልቻሉም። እንደውም ራሳቸው መታረቅ መነጋገር የማይችሉ፣ የሚያጋጩን የእርቅ መድረክ የሚከፍቱበትና የሚያስታርቁበት ሁኔታ በስፋት እየተፈጠረ ነው። ከዚህ በመውጣት ማሰብ፣ ማሰላሰል፣ አገራችንን ማልማትና ማበልጸግ ወደ ሰላም መንገድ መንደርደር ማለቂያ ወደሌለው ግጭትና ጦርነት የሚወስዱንን ጉዞዎች ማስቀረት አለብን። ለዚህም ይህ የእውቀት ማዕከል ለእኛም ለጎረቤት አገሮችም ጭምር እንዲያገለግል ሆኖ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ተሠርቷል። ቀጣዩን ሥራ በበቂ ደረጃ ማከናወን ከቻልን ለኢትዮጵያዊያን የመንግስት ኃላፊዎች ብቻ ሳይሆን በቢዝነስ ዘርፍ ላሉና በተለያየ ሥራ መስክ ውስጥ ለሚሰማሩ ከሶስት እስከ ስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እየመጡ ዋና ዋና የሚባሉ እውቀቶችን የሚገበዩበት ልምድ የሚቀያየሩበት አካዳሚ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

ይህ ተቋም ስያሜውን በቅርቡ ቀይሯል፡፡ ስያሜውን ከመቀየሩ ጋር ተያይዞ ብዙዎች የኢፌዴሪ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን አቶ መለስ ዜናዊን ስም ለማንሳትና እሳቸውን ካለመፈለግ ጋር ያያይዙታል። በአንፃሩ ደግሞ የእርሳቸው ስም መነሳት እንደ ተገቢ የወሰዱ የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ። ነገር ግን እውነታው ከሁለቱም ሀሳብ ወጣ ይላል። ይህ አካዳሚ

የተሠራበት ዋና ዓላማ ኢህአዴግ ካድሬዎቹንና ከፍተኛ አመራር አባላቱን እንዲያሰለጥን ነው፡፡ አካዳሚው ያኔ የሚያሰለጥንበትም መሰረታዊ እሳቤ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነበር፡፡ ባለፉት ሁለትና ከዚያ በላይ ዓመታት አካዳሚው ያንን እሳቤ ማስተማር ስለማይችል ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ስልጠና እየሰጠ አልነበረም። በአዲስ መልክ መሰረተ ልማት ስንገነባ፣ ሥርዓተ ትምህርት ስንቀርጽ፣ ብቃት ያላቸው መሪዎችና መምህራን ስንለይ ቆይተናል። አሁን የአፍሪካ የልህቀት አካዳሚ የተባለበት ዋናው ምክንያት የምናስባቸውን እሳቤዎች በአገራችን ብቻ አጥረን ማስቀረት ስለማንችል "እየሰጠን እየተቀበልን፤ እያስተማርን እየተማማርን፤ በጋራ የምንወጣበትን ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል" የሚል እሳቤ ይዘናል።

አሁን አካዳሚው የተመሰረተው ለመንግስት ወይንም ለፓርቲ ካድሬዎች ብቻ አይደለም። ለግል ዘርፍ አመራር አባላት፣ ለጎረቤት አገሮች፣ ለወታደሮች፣ ለዲፕሎማቶች ለልዩ ልዩ ዘርፎች ሙያተኞች እንዲውል ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ስራውም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ገደማ ሲጠና ቆይቶ በቅርቡ የተወሰነ ነው። ስለሆነም የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ስም ካለመፈለግ ወይንም ከመፈለግ ጋር ትስስር የለውም። አሁን የተደራጀበትን ዋና ዓላማ፣ አቅምና የሥርዓተ ትምህርቱ ዝግጅት ማሸጋገር በሚችልበት ደረጃ እንዲቆም ብቻ ታስቦ የተሰራ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ።

ይሄ አካዳሚ የብዙዎቻችንን ያለማወቅና በጥበብ አለመሞላት ደረጃ በደረጃ እያቃለለ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ ኢጋዥ ሚና እንደሚጫወት ይገመታል፡፡
የዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቶች፣ ሚኒስትሮች፣ የክልሎች አመራር አባላት፣ የትላልቅ ኩባንያ ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች አጫጭር ኮርስ እንዲማሩበት ታሳቢ ያደርጋል። እዚህ የሚገኘው ትምህርት በመደበኛ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው ዓይነት ሳይሆን የተለየ መሆኑን ማወቅ አለብን። በዚህ ተቋም ሁላችንም በመማር የምናውቀው ደግሞ በማስተማር የአገራችንን ብልጽግና እንድናፋጥን "አደራ" እላችኋለሁ።
ቦታው እጅግ የሚያምር ነው። እንደተባለው ከእንጦጦ ጋር ይተሳሰራል። ይሄንን በማድረግ ልማታችን፣ ሰላማችንና ብልጽግናችን ወደምናረጋግጥበት፤ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ሰላም የሚያረጋግጡና ብልጽግናዋን የሚያፋጥኑ ወሳኝ ውሳኔዎች የምናሳልፍበት ምዕራፍ ከፊታችን እንዳለ እገልጻለሁ።

**መልካም የሥራ ጊዜ! መልካም የእውቀት መገብያ ጊዜ!**
**እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!**
ሰኔ 19፣ 2013 ዓ.ም

# የትግራይ ክልል ወቅታዊ ሁኔታ

የዛሬ ሁለት ዓመት “የውጭ ወራሪ ሊያጠቃን ያስባል፤ ይፈልጋል፤ ይዘጋጃል። የውጭ ወራሪን አስቀድመን መከላከል ስላለብን ትጥቃችንንና ወታደሮቻችንን እናውጣ” በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ምን ያክል እንደተወያየንበት ታስታውሳላችሁ፡፡ እነዚህን ነገሮች ልናወጣ ስንሞክር “አትችሉም” እየተባለ ወጣቶች እየተኙ “ትጥቁም፣ ሠራዊቱም የእኛ ነው አይወጣም” በማለት ለሁለት ዓመት ያህል ክርክር ነበር። ነገር ግን በኋላ ላይ አግጦ አፍጦ እስከመጣው ግጭት ድረስ የነበረው ሁኔታ “ትጥቆቻችንን እናውጣ፤ አታወጡም” የሚል ነው፡፡

ይህ ጉዳይ አሁን በተካሄደው ኦፕሬሽን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ተሳክቷል፡፡ የምንፈልገውን አውጥተናል፡፡ ሠራዊታችንንም አውጥተናል፡፡ ሌሎች ኃይሎች የሚያስቡት ነገር ካለ ለመዘጋጀት ሰፊ እድል አግኝተንበታል፡፡ ትናንት ካየኋቸው አንዳንድ ግብረ መልሶች በመነሳት ህዝቡን እንድታስተምሩ እናንተም እሳቤያችሁን እንድታስተካክሉ ጥቂት ነገር ማለት እፈልጋለሁ፡፡

ትናንት ወታደር ወጣ ሲባል “አማራ ጉድህ ፈላ ተካድክ ጠፋህ ምናምን” በማለት የሚገልጹ ስልክ ያላቸው የማህበረሰብ አንቂዎችና ጋዜጠኛ ነን የሚሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ ምን ማለት ነው? ይሄን ንግግር ቆም ብሎ ማየት ያስፈልጋል፡፡

አማራ ከትግራይም ከሱዳንም ከሌላ ክፍልም ከፍቅር ውጭ ሰው በጉልበት በኃይል ሊያንበረክከው ከፈለገ ራሱን መከላከል የሚችልና በዚያም የሚታወቅ ሕዝብን የካደ ሀሳብ ነው፡፡ መካድ ብቻ አይደለም “ጠፍተሃል ወድቀሃል፣ እኔን ካልሠማህና ካላየኸኝ ዋጋ የለህም” ዓይነት በውድቀትና በስንፍና ውስጥ ጎልቶ ለመታየት መሻት ነው፡፡ በነገራችን ላይ እዚያ አካባቢ ሄዳችሁ ዓይታችሁ ይሆናል፡፡ የአርማጭሆ፣ የወልቃይት እና የጠገዴ ሕዝብ እንኳን አሁን ባለው ሁኔታ ባለፉት 30 ዓመታት ያ ሁሉ ዱላ እየወረደበት፣ ኢትዮጵያዊነቱንም የቤጌምድር ሰው መሆኑንም እየተናገረ፣ እየሞተ፣ እየተሠደደ ዛሬም አለ። ዛሬም ሸብረክ ያለ አካባቢ አይደለም፡፡ በትንሹም የሚሄድ አካባቢ አይደለም፡፡ ይሄ ነገር ለእኛ ፖለቲካ ሊሆን ይችላል። ለእኛ ቁማር ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ለልጆቻችን ምን እያልናቸው ነው? አትችሉም። አንተ ከሌላ ቦታ ፀብ ሲፈጠር ፍራ እያልን ነው። ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል፡


በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

፡ የመገናኛ ብዙኃን ሰዎች እንደዚህ ዓይነት ትርክት አንድን አካባቢ አጐልቶና ራሱን አኮስሶ የሚመለከት ትውልድን የመፍጠር አንድ ጡብ እንደሆነ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡
የዛሬ ሁለት ዓመት ያለው የኃይል ሚዛን ኢኮኖሚያዊ ዝግጁነት፤ የመንግስታዊ መዋቅር ለምሳሌ ትግራይ ክልል የነበረውን ከሌሎች ክልል ስናወዳድረው አይመጣጠንም። አሁን በነበረው ሁኔታ ወይ ዝቅታ ወይ ደግሞ ምናልባት የተቀራረበ ነው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትናንት በነበረው ሁኔታ "ልጠቃ እችላለሁ" በሚል ፍርሃት የሚፈጠርበት ምንም ዓይነት መሠረትና እውነት የለውም፡፡ በነዚህ ምክንያቶች እንደነዚህ ዓይነት ትርክት የማሸነፍና የመሸነፍ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አንድን ሕዝብ እንደ ሕዝብ በስጋት በጭንቀት እንዲኖር የሚያደርጉ ናቸው። ጋዜጠኞች ይሄንን ነገር በከፍተኛ ጥንቃቄ ማየትና ማስተማር ይጠበቅባችኋል፡፡ እውነትም አይደለም፤ ድሎችንም የሚያራክስ ነው፡፡

ሌላው ትናንት መቀሌን መልቀቅ ስንጀምር ብዙ ሰዎች ተደናግጠዋል፡፡ እናንተም ተደናግጣችኋል፡፡ የዛሬ ስምንት ወር መቀሌ ስንሄድ የግጭት የስበት ማዕከል እንዲሁም የመንግስት፣ የምናውቀውና የማናውቀው ሀብት ማዕከል ነበር፡፡ ዛሬ ከመቀሌ ስንወጣ በውስጡ የተሰገሰጉ፣ ሰዎችን የሚዘርፉና የሚቀሙ ቁጥራቸው ከመጨመሩ ውጭ ከአብያ አዲ ወይም ከሽራሮ ወይም ከበሻሻ የሚለየው ነገር የለም፤ የስበት ማዕከልነቱን አጥቷል፡፡ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በተለየ መንገድ የምናየው ነገር አይደለም። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታም ሆነ በወታደራዊ እይታ መቀሌን ወይም አብያ አዲን ከሌላው የሚለያቸው ምንም ነገር የለም፡፡ በተለየ መልኩ የስበት ማዕከል የሚያረገውና እንደሄድንበት ጊዜ የሚያጓጓን ነገር የለውም፡፡

አንደኛ ዓላማችን አካባቢ መያዝ አይደለም። እኛ የሄድንበት ዓላማ "ትጥቃችን ተይዟል፣ አስተዳደራችን ተይዞብናል፤ ሰዎች ሕግ ጥሰዋል" የሚል ነው እንጂ "መቀሌን ነፃ እናውጣ" ብለን አይደለም። ይሄንን ታውቃላችሁ፤ ተሳትፋችሁበታል፡፡ አሁን ግን ለመውጣት የወሰንባቸውን ውሳኔዎች በተወሰነ ደረጃ አነሳላችኋለሁ። እነዚህ ትርክቶች እርማት ይፈልጋሉ።

ሁለተኛው ጠላት "አሸንፌ መትቼ ነው የያዝኩት" ይላል። ተሸንፈን ነው ወይ? በሚል ጭንቀት የያዛቸው ሰዎች ይታያሉ። በነገራችን ላይ እነርሱ በፌስቡክና በቲውተር ላይ ተሸንፈው አያውቁም። እኛ መቀሌ የገባነው 'አንድ ሳምንት እንድንዝናናበት ፈቅደው ነው እንጂ ተሸንፈው አይደለም፤ በየቀኑ ይደመስሱናል። በየቀኑ ያጠፉናል። በየቀኑ ይገሉናል። በየቀኑ እኮ ነው የምንሸነፈው' ይህ ለእናንተ ብዙ የሚያስደንቅ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም እያጠቃን ስንሄድ እንኳን እናንተ በቅርበት ሪፖርት እያደረጋችሁ የሚዘገበው ነገር "አሸነፍን

23ኛን ደመሰስን፤ 25ኛን ደመሰስን እንትናን ገደልን፤ አበባውን ገደልን ባጫን ማረክን" የሚል ነበር። ይህ ኃይል አሁንም ቢዋሽ መደነቅ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡
ነገር ግን ከመገናኛ ብዙኃን አኳያ ቅድም እንዳነሳሁት ትርክቱ አንድ አደገኛ ችግር አለው፡፡ የእኛ ጓደኞች ሳያውቁ ወይም ሳታውቁ ጥፋት ይፈጸማል፤ የጠላትን የተዛባ ዜና የማባዛት፣ የማድረስና የወገንን የማራከስ በሽታ እኛ ውስጥ ያለው ልክ እንደ ኮረና ነው፡፡ ጠላት አንድ ውሸት ሲዘራ ሁሉም ለመደበኛና ኢ መደበኛ መገናኛ ብዙሃን ጆሮ ይሰጣል፤ ያባዛል። ምን ማለት ነው? ጠላት ደጋግሞ የሚናገረው በውስጡ ያለውን መሻት፣ ድካም፣ ስንፍና ሲተነፍስ እርሱን ታስተጋባለታለህ ማለት ነው። አንዱ ከዚህ የሥነ ልቦና ጦርነት አኳያ አሁንም ትምህርት መውሰድ ያለብን ከየትኛውም ወገን ይሁን የራስን ድል ለማግዘፍና ሌላውን ለማኮሰስ የሚደረጉ ፕሮፖጋንዳ ዓይተን አላየንም፣ ሰምተን አልሰማንም በማለት ብቻ ልንቀጣው እንችላለን፡፡ ብዙ ባየን ቁጥር ግን "ተመልካች አለው" የሚል እሳቤ ስለሚፈጥር ውሸት የለመደ ሰው በየቀኑ እየዋሸ ይቀጥላል፡፡ ውሸቱ እንዲቀጥል ደግሞ እኛ ተባባሪዎች ነበርን ማለት ነው፡፡ አሁንም ይታያል። ይሄን ዝንባሌ የመገናኛ ብዙኃን ሙያተኞች ማወቅ፣ ማስተማርና መከላከል አለባችሁ፡፡ የምንፈልገውን ነው ደጋግመን የምንናገረው እንጂ የሚሰድበንን የሚቀጥፈንን የሚዋሸውን የምናስተጋባ ከሆነ የመገናኛ ብዙሃን ጉዳይ በታጠረ ቦታ የሚቀመጥ አይደለም። ከቁጥጥራችን ውጭ በጣም በርካታ ሰዎች የሚያዩት ነው፤ ለሕፃናትም ጭምር በዚያ ምክንያት የተሳሳተ ታሪክ ስለሚያስተላልፍ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

የህወሃት ዓላማ ማሸነፍ አይደለም፡፡ በተደጋጋሚ ሰሞኑን ሲናገሩ ሰምታችኋል፤ እንደከዚህ ቀደሙ መንግስት እንሁንም አይደለም። "አመድ ሆኛለሁና ተያይዘን አመድ እንሁን፤ አቧራ ለብሻለሁና ተያይዘን አቧራ እንልበስ፤ ተከስክሻለሁና ተያይዘን እንከስከስ፤ ፓራሹት የሚባል ነገር እንዳላይ" የሚል ታክቲክና ስትራቴጂ ነው። ዓላማቸው ይሄ ነው። ለዚህ በጣም ብዙ ነገር ለማሳያነት ላነሳላችሁ እችላለሁ፡፡

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ኮሮና አለ። እግዚአብሔር ይመስገን ኮሮናው በተባለው ልክ አይደለም። ሰዎች የኢትዮጵያ መንግስት "ኦክሲጂን በበቂ ማቅረብ አለበት" ብለው ይጠይቃሉ፡፡ ሙያችሁም ስለሆነ ትሰማላችሁ። በሌላ መንገድ የሁላችሁም የሕልውና መሻት የሆነው ሕዳሴ ግድብ የሚባል አለ። ሰዎች ሕዳሴ ግድብ አልቆ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያመነጭ ይፈልጋሉ፡፡ በሌላ በኩል ከሕዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ ባሉ አንዳንድ ጉዳዮች ከስደት 40ሺ እና 50ሺ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ይመለሳሉ። እነዚህን ሰዎች በትራንስፖርት መጓጓዝና ለተወሰነ ቀናትም ቢሆን መቀለብ የመንግስት እዳ ነው፡፡
በኢትዮጵያ የተፈጠረው ችግር የኮሮና፣ የሕዳሴ ግድብ፣ የስደት ተመላሽ ጉዳይ ብቻ

ሳይሆን፤ በዋጋ ግሽበት ምክንያት በከተሞች ገቢያቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች ምናልባትም እናንተን ጨምሮ በቀን ያማራቸውን ለመብላት ይቅርና የሚያውላቸውን ለመብላት የሚከፍሉት ነገር ከአቅም በላይ እየሆነ ሄዷል። ይህ ማለት የተወሰነ ስንዴ፣ ዘይትና ስኳር ብናስገባ እንኳ አሁን ያለውን የዋጋ ግሽበት በተወሰነ ደረጃ ሊያረጋጋው ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ ባለፉት ስምንት ወራት በወታደራዊ መስክ ካለው ወጪ ውጭ የሚታይ ነው። ጥይቱን ምግቡን ልብሱን አይመለከትም።

ትግራይ ውስጥ መንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ጤና፣ ትምህርትና ሌሎችም ግንባታዎች ቀለብን ጨምሮ ለመፈፀም ከመቶ ቢሊዬን ብር በላይ አውጥተናል፡፡ 100 ቢሊዮን ብር ማለት ዘንድሮ የምንይዘውን በጀት 20 በመቶ ማለት ነው፡፡ 100 ቢሊዬን ብር ማለት ለትግራይ ከምንመድበው ዓመታዊ በጀት ከአስራ ሦስት እስከ አስራ አራት በመቶ እጥፍ በላይ ከፍተኛ ማለት ነው፡፡ በጀት የምንይዘው ስምንት ቢሊዮን ነው፤ 100 ቢሊዮን ብዙ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ወጪና ድካም ካደረግን በኋላ ግን በዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ሆነ በማንም ኃይል ‘ጥሩ ስራ አከናወናችሁ’ አልተባለም። የኤሌትሪክ ሃይል ለመቀጠል ሰዎች እየሄዱ ሞተዋል፡፡ ስንዴ እየሰጡና ምግብ እያዳረሱ ተገድለዋል፡፡ ስልክ እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ለመገንባት ሄደው ብዙ አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡ አንድም ሰው “ጥሩ ሥራ እየሰራችሁ ነው ቀጥሉበት በርቱ” የሚል አልገጠመንም። ሁሉም ሰው በእናንተ ምክንያት “ረሃብ ሊመጣ ነው፤ ሕዝቡ ወደ ችግር እየገባ ነው” ይላሉ። መንገድና መገናኛ ከለከላችሁ፤ ውጊያ አላቆማችሁም፤ ለኤርትራ ሠራዊት ፈቀዳችሁ የሚሉ ዓይነት ክሶች ብቻ ናቸው የሚቀርቡት።

ይህም ሆኖ እኛ እዚያ የምንይዘውን ይዘን የምንመታውን መትተን ትጥቆቻችንን ወስደን መውጣት እንጂ የመቆየት ዓላማ አልነበረንም፡፡ ምክንያቱም ፍላጎታችን መጀመሪያም ወጥተን ወደ ሌሎች ግንባሮች መዞር ነበር፡፡ ሌላ የሚያሠጋን ኃይል ስላለ፤ ለዚያ ዝግጅት ያስፈልገን ነበር፡፡ ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ አለ። አንድ አገር ዛሬ ቅድሚያ የምትሰጠው ነገር፤ ነገ ቅድሚያ ከምትሰጠው ይለያል፡፡

አገርም ቅደም ተከተል አላት። ፍላጎቶቿን በቅደም ተከተል መሰረት ትይዛለች፤ ትተገብራለች። አምና እንደምንሠጋው ሥጋት አሁን በኢኮኖሚም በወታደርም በምንም የለም። አሁን ያለብን ሥጋት ትተን እዚያ ብንጋጋጥ ሁለቱንም ያጣ ከመሆን ያለፈ ጥቅም አይገኝበትም፡፡ ምክንያቱም ፋቲክ ውስጥ ገብተናል፡፡

መጀመሪያ የገጠመን እንደመንግስት የደንብ ልብስ የለበሰ፣ መስመር ያለው፣ የሚቆምበትን የሚያውቅ ጦር ነው። ለዚህ 15 ቀን ወይም 20 ቀን ነው የፈጀብን፡፡ እንደዚያ ላለ ውጊያ

እምብዛም አልተቸገርንም፡፡ ቀጥሎ የገጠመን በተወሰነ ደረጃ ቢቀንስም በሽፍታነት መልክ የተደበቀ ቡድን ነው። እርሱን እየፈለጉ መያዝ ከመልክዓ ምድር አኳያ የሚያስቸግር ቢሆንም፤ ቴክኖሎጂ መጠቀምም ስለሚያስችል የተወሰኑትን በቁጥጥር ስር ለማዋል አንዳንዶቹንም ለመደምሰስ ተችሎ ነበር፡፡ አሁን ያለው ውጊያ ግን ተቀይሯል፡፡ አሁን ያለው ውጊያ ወታደር የትኛውም መንደር ሲሄድ ምንም ጠላት አያይም፤ ሕዝብ ነው የሚያየው፡ ፡ እዚያ የገባው ወታደር ቁጥሩ አሃዱ ውስንነት ያነሰ ከሆነ 'ምንም ጠላት የለም' ብሎ አልፎ ሳይጨርስ ከጀርባው በርከት ያሉ ሰዎች ወረውት በክላሽም በገጀራም ይጨፈጭፉታል፡፡ ለምሳሌ አንድ መንደር የገጠመን ነገር ወታደሩ ሲሄድ "ጁንታው ሰው ይገላል፤ ይረሽናል፡ ፡ አልደገፉንም የሚላቸውን ሰዎች ከቤተሰብ አውጥቶ ሕዝብ እያየ ይረሽናል፡፡ እየረሸኑን ነው፤ ጥበቃ አታደርጉልንም" ብለው ወታደሩን ጠየቁ።

ትግራይ ያለው ወታደር ለምሳሌ 50ሺ ወይም 100 ሺ እንኳን ቢሆን ዝም ብሎ 20 ሺው መቀሌ 20 ሺው አዲግራት ካልተቀመጠ በስተቀረ ሁሉም ተራሮችን እንዲያካልል የግድ 100፣ 50፣ 200 ካልሆነ በስተቀር አይቻልም፡፡ በዚያ መንደር "ጠብቁን መጥተው ይገሉናል፡ ፡" ብለው መከላከያን ሲጠይቁ፤ መከላከያ አምኖ ተቀበላቸው። በዚህም ምክንያት በቁጥር ከ20 እምብዛም የማይበልጡ ሰዎች አስቀምጦ አሰሳውን ቀጠለ፡፡ ጠዋት "ጠብቁን እንዳትሄዱ" ያሉት ሰዎች ከሰዓት እነዚያን ጥቂት ወታደሮች በብዛት ወጥተው ፈጇቸው። ይሄ ነገር ከቦታ ቦታ እየበዛ ሄደ። በዚች 15፣ 20 ቀን የነበረው የውጊያ ሁኔታ (ዝርዝሩን ባላነሳላችሁም) አንድ የታጠቀ ሰው የሆነ የተከማቸ ኃይል ይመጣበታል ብዙ ሰው ገድሎ ጥይት ጨርሶ የሚሞትበት በጣም ብዙ የማትገምቷቸው ጀግኖችና ትላልቅ ኃላፊዎች ራሳቸውን የገደሉበት ሁኔታ አጋጥሟል፡፡

ለምሳሌ የብርጌድ ኮማንድ፣ የተፈጥሮ ኮማንድ የሚባል አካባቢ ጥቂት ሰው ነው የሚኖረው። ዋናው ኃይል በየተራራው ይሰማራል። አካባቢ ላይ እነዚያ ሰዎች ባልኳችሁ መንገድ ሲመጡባቸው "ሕዝብ ላይ አልተኩስም" ብለው ራሳቸውን የገደሉ አሉ፡፡ ብዙዎች ደግሞ ገድለውና ጥይት ጨርሰው የተያዙ አሉ፤ የሞቱ አሉ፡፡ ይሄ ጉዳይ አጋጣሚ ቢሆን ችግር የለውም፡፡ አንድ ሲያጋጥም ገምግሞ ይስተካከላል፡፡ በኋላ ግን እንደ ባህል ሆነ፤ በተለይ መቀሌ ላይ ግልጽ እንድትሆኑ እዚያ የነበረን ኃይል ትልቅ ነው፡፡ መቀሌ አካባቢ ያለን ከ20 ሽ በላይ ነው፡፡ እንኳን ጁንታውን ምንም ነገር ቢሆን ራሱን ለመከላከል ከፍተኛ ብቃት አለው፡፡ ነገር ግን ይህ ቅድም ያልኳችሁ ስሜት በከፍተኛ ደረጃ ወታደር ውስጥ ገብቷል፡ ፡ የሚያየውን ሰው ሁሉ "ጠላት ነው" ብሎ አስቧል፡፡ አንዳንድ አካባቢ ቄሶች ክላሽና ማይክራፎን ይዘው "ተነስ" ብለው ሲሰብኩ ሰምቷል፡፡

በኢትዮጵያ ባህል መሰረት ሰው ቤተክርስቲያን ወይም በሙስሊም መቃብር ስፍራ ሲቀበር ጉድጓድ መቆፈር ግድ ነው። በጣም በርካታ ቤተክርሲቲያን ሰዎች ሞተው ተቀበሩ የተባለበት ቦታ ላይ ግን ልክ እንደሰው ሬሳ የተቀበረው አብዛኛው ትጥቅ ነው፡፡ በየቦታው ሰው ሞተ እየተባለ ትጥቅ ይቀበራል። መቀሌ ያለ ጦር ምናልባት ሳምንት ብናቆየው የዚህ ቤት ድንጋጤ 100 በመቶ የተገላበጠ ይሆናል፡፡

ለአንድ ወገን ገብተህ የምትዋጋው ለምሳሌ ከሻዕቢያ ጋር መጀመሪያ ባድመ ላይ ተዋጋን፤ ቀጥለን አልፈን ተኮብያ፣ ባሬንቱ ስንደርስ እንድንመለስ የተወሰነበት አንዱ ምክንያት ከደጀን እየራቅን በመሄዳችን ነው። ባደመ እያለን ግን ከፊት ያለው ይዋጋል፤ ሲቆስል ችግር የለም ከኋላ ደጀን አለ፤ ተገን አለ። ውጊያ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ካልሆነ ፋቲክ ይሆናል፡፡ ድሮ እንደተዋጋነው አስራ ምናምን ዓመት ስንጋጋጥ ነው የምንውለው፡፡

እኛ የወሰንነው የአገር መከላከያ ሠራዊት አብዛኛውን ሕዝብ እንደ ጠላት ወስዶ በታሪክ ውስጥ ጥቁር ጠባሳ ጥሎ የሚሸማቀቅበት ዓለምም በብዙ ዱላ ኢትዮጵያ ላይ የሚነሳበት ነገር ከሚፈጠር ደጀን ወደምንለው ሕዝብ ጠጋ ብለን ከኋላችን ደጀን በማስቀመጥ በምርጫው የጥሞና ጊዜ እንደተባለው “ለሕዝቡ የጥሞና ጊዜ እንስጠው” ብለን ነው የወሰነው፡፡
የኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ የመከላከያ ሠራዊት ጥረትና ድካም በብዙ እጅ መገንዘብ ሲጀምር ሁኔታውን እናየዋለን። ለሞተውም ለተራበውም ለቆሰለውም ለያንዳንዱ ጉዳይ ወንጀለኛ የሆነው፣ የሌለውን ሀብት እያፈሰሰ “ወገኔ” ብሎ ጀርባውን ሰጥቶ የሚሄደው ኃይልም በየቀኑ ጥቃት እየደረሰበት ስለሆነ የእፎይታ ጊዜ ብንሰጥ የተሻለ መሆኑን አምነናል። አሁን እንደአምና የሚያሰጋን ነገር የለም፤ ዛሬ አያሰጋንም፡፡ ሚሳኤሉን አውጥተናል። መሳሪያችንን አውጥተናል። እንደትናንትናው የምንፈራው ጉዳይ የለም። በተጨማሪም አሁን ባለው ሁኔታ በዚህ ክረምት ቅድሚያ የምንሰጠው ሌላ ጉዳይ ስላለን ገንዘባችንን፣ ሰዎቻችንንና ትጥቃችንን ቆጥበን ወደ ዋናው ጉዳይ ብናተኩር ይሻላል፡፡

ወያኔ ከደርግ መንግስት ጋር በነበረው ውጊያ የማሸነፊያው አንዱና መሠረታዊ ነገር የደርግን ትጥቅ፣ ስልጠና እየወሰደና ቀለብ እየበላ ነበር፡፡ ወታደር ከማረከ በኋላ አሠልጥንልኝ ይለዋል። ያሰለጥናል። ትጥቁን ይወስዳል። ስንቁን ይወስዳል። እርሱን እየያዘ ነበር ወያኔ ወደ ተደራጀ አቅም ያደገው። አሁን የፋሺዝም መልክ ሲኖረው አንዱ ያየነው ነገር ልብስና ውሃ መስረቅ፤ ያገኘውን ነገር ጉማ ካለ ማስተንፈስ፣ ተሽከርካሪ የሚሄድ ከሆነ መንገድ ላይ ድንጋይ መደርደርና እንቅስቃሴ መግታት ነው። እየዋልን እያደርን በሄድን ቁጥር የምናስታጥቀው ይሆናል። ከምግብ አኳያ አንድ ቤተሰብ አምስት አባላት ካለው 7፣ 8፣ 10 ብሎ ያስመዘግባል። የአስር ሰው ምግብ ይወስዳል። የአምስቱን ይበላል። የአምስቱን

ለጁንታው ይሰጣል፡፡

የመከላከያ ሠራዊት አንዳንድ ቦታ አራትና አምስት ቀን በተከታታይ ውጊያ ሲኖር ውሃ እንዳያገኙ ይደረጋል። የጁንታው ኃይል ግን የታሸገ ውሃ ይጠጣል፡፡ ይህን “ማስተናገድ የለብንም” በሚል ለሳምንታት ስንወያይ ቆይተን ነው የተወሰነው። ትናንት ከመቀሌ ስንወጣ መቀሌ ተያዘ ተባለ። ቅድም እስከመጣሁበት ጊዜ ድረስ አንድም የጁንታው ኃይል መቀሌ የደረሰ የለም፡፡ ከመቀሌ እየወጣ የጨፈረው እዚያው ተከማችቶ የነበረ ክላሹን የደበቀና ጊዜ የሚጠብቀው ኃይል ነው። አዲግራት ላይ በቀደም ሆነ አሁንም ያያችሁት እኛ ስንዴ እየሰጠን፣ እኛ ዞር ስንል የሚጨፍር ከሆነ የጥሞና ጊዜ ያስፈልገዋል፡፡ መያዝ የሚገባንና እዚያ መቆየት ያስፈልገናል የምንላቸውን ቦታዎች እንይዛለን። በተደራጀ መንገድ የሚመጣ ኃይል ካለም በከፍተኛ ደስታ እናስተናግዳለን። ምክንያቱም የእኛ ችግር ያ አይደለም። የእኛ ችግር ሕዝባዊ የሆነው ምልከታ ነው፡፡

እንደዚህ ዓይነት ውሳኔ ሲወሰን ኢትዮጵያዊያን ቶሎ የማሸነፍ ፍላጐት እና እሳቤ ስላላቸው ለመቀበል ይቸገራሉ። ግን እኛ መሪ የሆነው በእንደዚህ ዓይነት ስሜት ልንነዳ ሳይሆን ቆም ብለን ኢትዮጵያን የሚያሻግራትን ነገር ለመወሰን ነው፡፡ ኤርትራን የምናስገነጥል ከሆነ ያ ሁሉ ውጊያ አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ኪሳራ ነው፡፡ ኢትዮጵያን፣ ኢትዮጵያዊነትን ማንም አያሸንፍም፡፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን አሸናፊ የሚያደርገው ፈጣሪን መፍራት፤ መፀለይ ነው። ኢትዮጵያን ኢትዮጵያዊነትን አሸናፊ የሚደርገው የአባቶች ብልሃትና ጥበብ መጠቀም ነው። ኢትዮጵያን አሸናፊ የሚያደርገው የጐረምሶችን ጉልበት መጠቀም፤ ኢትዮጵያን በአንድ ትርክት ማምጣትና ማስተባበር ነው። “አንዴ ገብቼበታለሁ” በሚል ዝም ብሎ ተላፍቶ መጋጋጥ አይደለም፡፡ አሁን ማስተዋል ያስፈልገናል። ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች። ሕዝቦቿም ተለውጠው እናያለን። አስደማሚ ድሎች አስመዝግበናል። ይህ ይቀጥላል። የእናንተ ሚና ግን ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ልባችሁም አእምሯችሁም ነገን አሻግሮ የሚያይ በዚያ ልክ የምትመላለሱ ጀግኖች እንድትሆኑ አደራ እላለሁ።

# የሲቪክ ማኅበራት ደርጅቶች ምክር ቤት የምስጋና ምሽት

እዚህ የተገኛችሁ እንግዶች በሙሉ እንኳን ለዚህ ወግ፣ ማዕረግ አበቃን። ከምርጫ በኋላ እየተገናኘን የሚቀጥለውን የኢትዮጵያን ቅርጽና ሁኔታ ለመነጋገር መብቃታችን ዶክተር ራሄል ባፌ ከጠየቁት ጥያቄ አንደኛው ምዕራፍ ስለሆነ "እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን" እላለሁ።

በእኛ በኩል ምርጫው ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ነጻ የሚባል እንዲሆን ፍላጎትና ቁርጠኝነት ነበረን። ለዚህም ትጋት አሳይተናል። ይህ ምርጫ በኢትዮጵያዊያን ዐይን ሲመዘን እስካሁን ከነበረው የተሻለ እንዲሆን አበክረን ሠርተናል። ህዝብም ይሄን እንደሚገነዘብ፣ እንደሚመሰክር ሙሉ እምነት አለኝ። ይህ ምርጫ የተሟላ የሆነው በጋራ "ኢትዮጵያ ትወስን" ብለን በመወሰናችን ነው። በዚህ ውሳኔ ውስጥ ምርጫ ቦርድ የሚባል በጅምር ያለ ተቋም አይተኬ ሚና ተጫውቷል፤ ምስጋና ይገባዋል። ፍርድ ቤት ብዙ ልንሰራው የሚገባን ሥራዎች እንዳሉና እንደተጠበቁ ሆኖ ገለልተኛ ለመሆን ጥረት አድርጓል። የበኩሉን ድርሻ ለመጫወትም ሞክሯል። ፍርድ ቤትም እንደዚሁ ሊመሰገን ይገባል። ባልተለመደ ሁኔታ መገናኛ ብዙኃን በርካታ ቦታ ላይ ከቅድመ ምርጫ ጀምሮ እስከ ቆጠራ ባለ ሂደት ውስጥ በቀጥታ ለማሰራጨት፣ የምርጫውን ሂደት ከያለንበት ስፍራ መከታተል በሚያስችለን ደረጃ ያልነበረና አይተኬ ሚና ተጫውተዋል። መገናኛ ብዙሃን መመስገን ይኖርባቸዋል።

ተፎካካሪ ፓርቲዎች ብዙ ግፊት እንደነበረባቸው እናውቃለን። ያን ሁሉ ተቋቁመው "ኢትዮጵያ ታሸንፍ" ብለው መንግስትንና ህዝብን የአሠራር ሥርዓቱን በመላ አምነው በመሳተፋቸው እነርሱም እንደዚሁ ምስጋና ይገባቸዋል። ከሁሉ በላይ ግን ብናነበው፣ አብረን ብንኖር፣ ብናየው ብናጤነው ተዝቆ የማያልቅ ጥበብ ያለውና በየጊዜው "እናውቅልሃለን" የምንለውን የፖለቲካ መሪዎችና ሰዎች በንግግር ሳይሆን በተግባር እያስተማረ የሚገኘው ድንቅ ሕዝብ ክብር ይገባዋል።

እኔ እስካሁን ባለኝ ልምድ ከእኩለ ለሊት በኋላ ምርጫ ጣቢያ ላይ ተሰልፎ የሚመርጥ ህዝብ በሰለጠነውም ሆነ ባልሰለጠነው ዓለም ሰምቼ አላውቅም። የኢትዮጵያ ህዝብ "ሳልመርጥ አልመለስም" ብሎ እኩለ ሌሊት እስኪያልፍ ድረስ የወሰነውን ውሳኔና 'ሪፈረንደም' እንደ ቀላል ማሸነፍ እና መሸነፍ የምንወስደው አይደለም። ህዝቡ እየቀደመን እኛ መከተል

ያልቻልን ፖለቲከኞች እንደሆንን ትምህርት የሚወሰድበት ነው።
በነገራችን ላይ ፓርቲዎች አላውቅም የኔን በሚመለከት ግን እንኳን የሚመርጠው ህዝብ ይቅርና የሚመረጠው ሰው ከእኩለ ለሊት በኋላ እዚያ አካባቢ አልነበረም። መራጩ የነበረው ቁርጠኝነት ተመራጩ አልነበረውም። ይህ የሚያሳየው ህዝቡ በብዙ ደረጃ ቀድሞን እኛ መከተል ያለመቻላችን ነው። እኛ እዚህም እዚያም የሰማናቸውን ነገሮች በከባድ ቃላት በመናገር የምንልቅ ለመምሰል እንሞክራለን። ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ ከኢትዮጵያ ፖለቲከኞች የሚልቅ መሆኑን ያሳየበት ምዕራፍ እንደሆነ መግባባት ያስፈልጋል።

በእኛ በኩል ያለው ውሳኔ ምርጫው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ያስቻለው ቅድም የጠራኋቸው ያደረጉት ሚና እንዳለ ሆኖ፤ በዚህ ምርጫ በተመለከተ ምርጫ ቦርድ የተሟላ ዜና አላወጣም። ምናልባት ምርጫ ቦርድ "ብልጽግና አሸንፏል" ቢል ሙሉ በሙሉ ምርጫውን እንዳሸነፈ አይወሰድም። የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳሸነፈ ስለሚወሰድ፤ ከታችኛው እርከን ጀምሮ እስከ ላይኛው የአስፈጻሚ እርከን ድረስ ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንደተፎካከሩበት፤ ክልል እና ሁኔታ እንደ አቅማቸው መጠን በመንግስት ውስጥ በማሳተፍ በጋራ ኢትዮጵያን ለማሸነፍ በእኛ በኩል ዝግጁነቱ አለ። እስከንወዳደር ይቆይ ያልንበት ዋነኛው ምክንያት ማን በምን ያክል እንደሚደገፍ፣ ማን የት እንደሚደገፍ ሳይታወቅ በስመ ፖለቲካ የመጣውን ሁሉ ወደ ስልጣን ድርድር ብናስገባ አሁን ባለንበት ሁኔታ ኢትዮጵያን ለመሻገር ስለሚያስቸግር እንጂ ከብልጽግና የማያንሱ ሰዎች በየፓርቲው እንዳሉ ባለማመን አይደለም።

ሁሉም ኢትዮጵያውያን ተባብረውና ተጋግዘው ኢትዮጵያን ማቅናትና ማሻገር እንዳለባቸው በጽኑ እናምናለን። ምን አልባት ምርጫ ቦርድ "ተሸንፋችኋል" ቢል በዚሁ ዓይነት መድረክ ተገኝቼ አመስግኜ ላሸነፈው ለመስጠት ሙሉ ዝግጁነት ነበረኝ፤ እንደ ፓርቲም ነበረን። ይሄንን የማያምኑ ሰዎች አሉ። እውነቱ ይሄ ነው። ይሄን የምናደርገው ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ ነው። አሁን ከእኛ የሚጠበቀው የተፎካከራችሁ ፓርቲዎች ምናልባት ምርጫ ቦርድ 'ብልጽግና ባሸነፈበት አስር፣ ሃያ፣ ሰላሳ ቦታ ላይ የማጣራው ቦታ አለኝ። እዚያ ስፍራ ላይ በተደረገ ምርጫ ሙሉ እምነት የለኝም ሰርዤዋለሁ' ቢል ብልጽግና መቀበል አለበት። ሌሎችም ፓርቲዎችም እንደዚሁ ቢሳሳትም ውሳኔዎቻቸውን እያከበርን ከሄድን በጊዜ ብዛት ወደምንፈልገው ሂደት ስለሚሄድ ሳንደናገጥ የሚሰረዝ ካለም ተቀብለን፣ ወደፊት በምናደረገው ምርጫ አሻሽለን የሚመሰረተው መንግስት እንደ አቅማችንና እንደ ሰፈራችን ተወጣጥቶ ኢትዮጵያን የሚያሻግር እንደሚሆን እምነት አለኝ።

በዚህ ጉዳይ ላይ አደራ ልላችሁ የምፈልገው በጥቂት ጊዜ ውስጥ የታዘብነው ነገር ብዙ

አገሮች ሁለት ሁለት ሰው ይመድባሉ። ሁለተኛው ሰው የሚያናግረው ፓርቲና ግለሰብ አለ። ለምሳሌ ከብልጽግና እኔን ከሆነ ከሌላ ፓርቲ ደግሞ ሌላ ሰው ይመርጣሉ። እኔ ጋር የመጣው "ፓርቲ እኮ እናንተ ብቻ ናችሁ ተፎካካሪ እኮ ዋጋ የለውም" ይለኛል። እናንተ ዘንድ የመጣው "መንግስት እኮ እንዲህ እያስቸገረ ነው፤ ያላችሁት እናንተ ናችሁ" ይላል። ማታ ግን ምን ነገርከው ምን? ይላሉ። እኛ ማድረግ ያለብን ስለምንነጋገረው ነገር ወሰን እናብጅ። ከሌሎች ጋር መነጋገር ጥሩ ነው። እንደፈለጉ እንዲጫወቱብን መፍቀድ ግን ትክክል አይደለም። የምንቀበለውና የማንቀበለው ነገር አብረናቸው የምናወራውንና የማናወራውን ነገር መለየት ይኖርብናል። ካለበዚያ ላለፉት ሰላሳ እና አርባ ዓመታት እንዳባሉን አሁንም ያባሉናል። መንቃት የሚያስፈልገው ስናነጋግራቸው እስከ ምን ድረስ ከፈት ብለን መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ይሄን በተደጋጋሚ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውም ጉዳይ መታዘብና መማር የቻልኩት ነው። ፖለቲከኞች መንቃት አለብን። ባልና ሚስት አብረው እየኖሩ ጠዋት ሚስት ቡና ብትጠጣ ባል ወደ ሥራ ቢሄድ ሚስት የሆነውን ነገር በሙሉ ዘርግፋ ለጎረቤት አትናገርም፤ ባልም እንደዚሁ። በዚህ ምክንያት ትዳር ይውላል፣ ያድራል፣ ይሰነብታል። አገርም የምትጸናው፣ የምትሰነብተው ምን ያክል ተከፍተን ለሌሎች መረጃ እንደምንሰጥና እንደምንከለክል ካወቅን ብቻ ነው። እነርሱ እንደፈለጉት እየከፋፈሉን ግማሾቻችንን እያወደሱ፤ ግማሾቻችንን እየነቀፉ የእኛን አንድነት የሚያናጉ ከሆነ ኢትዮጵያ ለዘለቄታው አሸናፊ ለመሆን ትቸገራለች። መንቃት ይኖርብናል። መስተካከል ያሉባቸው በጣም ብዙ ነገሮች አሉ። እየተወያየን፣ እየተነጋገርን፣ እየተደማመጥን ለሰላምና ኢትዮጵያን አሸናፊ በሚያደርጉ ጉዳዮች የጋራ አቋም እየያዝን እንደ ምርጫው በሌሎች ወሳኝ ጉዳዮችም አሸናፊ እናደርጋለን። በዚህ ሁሉ ውስጥ የተሳተፋችሁትን እንዳለ እናመሰግናለን።

ምንም ጥርጣሬ የሌለው ጉዳይ ኢትዮጵያ ትሻገራለች፣ ኢትዮጵያ ታሸንፋለች፣ ኢትዮጵያም ትፎካከራለች። አገራችን የምትሆነው ሌሎች ያሰቡላትን ሳይሆን እኛ ያለምንላት ብቻ ነው። ይህ ፈተና ይሆናል፤ ፈተናውንም በጋራ እንወጣለን።

**አመሰግናለሁ!**

ሰኔ 25፣ 2013 ዓ.ም

## በምርጫው ውጤት እንኳን ደስ አላችሁ!

### የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊያት

ላለፈው ግማሽ ክፍለ ዘመናት፣ የአገራችን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በነጻ ፈቃዱ የመረጠው መንግሥት እንዲኖረው ብዙ ሙከራዎች ሲደረጉ ቢቆዩም፤ በተለያዩ ምክንያቶች ሲሰናከሉ ነበር። በሂደቱ አያሌ ተማሪዎችና ወጣቶች፣ አርሶ አደሮችና የቤት እመቤቶች፣ ምሁራንና መለዮ ለባሾች፣ መላው የአገራችን ሕዝብ ከፍተኛ ዋጋ ከፍሏል። ካለፈ ልምዳችንና ባልተሳኩ ጉዞዎች ጠባሳ ሰበብ፣ የአሁኑም ምርጫ "ዴሞክራሲያዊነቱ ተጠብቆ ባይጠናቀቅስ?" በሚል ስጋት፣ ያለፉትን ወራት እንደ አገር በፍርሃት ተወጥረን መክረማችን ሊካድ አይችልም።

ኢትጵያዊያን ግን ጨዋ ብቻ ሳይሆኑ አርቆ አሳቢ መሆናቸውን ዛሬም አስመስክረዋል። የተሰጋውን ሳይሆን የሚፈልጉትን ማድረግ እንደሚችሉ በግብር አሳይተዋል። ዝናብና ፀሐይ ሳይገድባቸው፣ በረጃጅም ሰልፎች ሳይሰለቹ፣ እስከ እኩለ ሌሊት ታግሰው ፍላጎታቸውን በካርዳቸው ገልጸዋል። እንደ እኛ እምነትም በዚህ ምርጫ አሸናፊ የሆነው ሕዝባችን ነው። ከሕዝባችን በመቀጠል፣ በብዙ ውሱንነቶች ውስጥ አልፈው በዴሞክራሲና በሕዝብ ድምፅ ላይ ባላቸው ጽኑ እምነት፣ ሀሳብና ፖሊሲያቸውን ለሕዝብ አቅርበው ብርቱ ውድድር ያደረጉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች የዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ድል አድራጊዎች ናቸው።

ይህንን ምርጫ ልዩና ታሪካዊ የሚያደርጉት ብዙ ጉዳዮች አሉ። በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከተጽዕኖዎች በተላቀቀ የምርጫ ቦርድ ዳኝነት ያደረግነው ምርጫ መሆኑ አንደኛው ነው። የምርጫ ቦርድ ዳኝነት እንዲሳካ ደግሞ ቁጥራቸው የበዙ የግልና የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን፣ የሲቪል ተቋማት፣ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ፍርድ ቤቶችና ሌሎችም ተቋማት በግልጽ የተከታተሉት መሆኑ ሂደቱን ከመቼም ጊዜ በላይ ተአማኒና ዲሞክራሲያዊነቱ የተጠበቀ ምርጫ ያደርገዋል።

ምርጫው ዴሞክራሲን የመትከል ግባችንን አንድ እርምጃ ያስኬደ በመሆኑ፣ ፓርቲያችን ከምንም በላይ ቀዳሚ ድሉ አድርጎ ይቆጥረዋል። በታሪካዊው ምርጫ ተሳታፊ መሆን በራሱ የሚፈጥረው ደስታ እንዳለ ሆኖ፣ ፓርቲያችን በሕዝብ ይሁንታ አግኝቶ አገር ለማስተዳደር መመረጡ አስደስቶናል። በውጤቱም ከአሸናፊነት ይልቅ ኃላፊነት፣ ከድል አድራጊነት ይልቅ

ታላቅ የሆነ አገራዊ አደራ እንዲያድርብን አድርጎናል።

መንግሥት የሚመሠረተው በሕዝብ በተመረጡ ፓርቲዎች ቢሆንም፤ አገርን መምራትና ማስተዳደር ግን ለተመረጡ ፓርቲዎችና መሪዎች ብቻ የሚተው አይደለም። ተፎካካሪ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸውም እስከሚቀጥለው ምርጫ በመንግስት አስተዳደርና ሕዝብን በማገልገል ሂደት ውስጥ ሚናቸው ሰፊ ሊሆን እንደሚገባ ለማስታወስ እወዳለሁ። በቀጣይ ወራት ብልጽግና በሚመሠርተው መንግሥት ውስጥ በአስፈጻሚው አካልም ሆነ በፍርድ ቤቶች፣ በሌሎችም የፌዴራልና የክልል ተቋማት ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው፣ በዘንድሮው ምርጫ በኃላፊነትና በብቃት የተወዳደሩ የሕዝብ አለኝታዎችን ከዚህ በፊት ካደረግነው በእጅጉ ከፍ ባለና አዎንታዊ ለውጥ በሚፈጥር መልኩ እንደምናካትታቸው ለመግለጽ እወዳለሁ። በተጨማሪም እስከሚቀጥለው ምርጫ የበለጠ ተጠናክረውና ተቋማዊ አቅማቸው ደርጅቶ ብርቱ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ አንልም። በዚህ ምርጫ የፈጠርነው አሸናፊና ተሸናፊን ሳይሆን፣ ጠያቂና ተጠያቂ ያለበት የዴሞክራሲ ሥርዓትን ነው። በዚህ ደግሞ ያሸነፉት በምርጫው የተሳተፉት ሁሉም አካላት ናቸው።

**ውድ የኢትዮጵያ ልጆች !**

በምርጫ ካርዳችሁ ስትመርጡን በዕቅድና በፖሊሲ የያዝናቸውን የብልጽግና ግቦች እንድናሳካ የድፍረትና የጥንካሬ ስንቅ እንደሚያቀብለን ሁሉ፣ እኛና እናንተን ያስተሳሰረው ቃል ኪዳን ተጠብቆ እንዲቆይ ነገሮች አልጋ በአልጋ እንደማይሆኑ እንገነዘባለን። ቢሆንም ከመቼውም ጊዜ በላይ ትከሻችንን አስፍተን፣ ኢትዮጵያን ከሚወዱ አካላት ጋር ሁሉ በትብብር ዐቅማችንን አሟጠን ለመሥራት ቆርጠን እንደተነሣን ሳበስራችሁ ደስ እያለኝ ነው። በቀጣይ ዓመታት አገራችን በእውነትም በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ከፍ የምትልበት ዘመን ይሆናል። ይህ እንዲሳካ የሀሳብና የሞራል ስንቅ እንደምታቀብሉን፣ መንገድ ስንስት እንደምትመልሱን፣ ስናጠፋም እንደምታርሙን ተስፋ በማድረግ ነው።

በአገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን እንዲሆን በቀጣዩ አምስት ዓመት ፈር ጠራጊ እንሆናለን የምንለው፣ በዙሪያችን ባሉና ብልጽግና በሚቀላጠፍባቸው አራት ማዕዘኖች መሐል ቆመን ነው። የመጀመሪያው ማዕዘናችን የመሠረተ ልማት ግንባታ ሲሆን፤ አገራችን እንድትበለጽግ በኢኮኖሚውም ሆነ በማኅበራዊና ፖለቲካ ዘርፎች ዘላቂ መሠረት የሚሆኑ፣ በፍጥነት የሚጠናቀቁ፣ ጥራታቸውን የጠበቁ፣ ከብክነት ነጻ የሆኑና የምንፈጥራቸውን ተቋማት መሸከም የሚችሉ ትውልድ ተሻጋሪ መሠረተ ልማቶችን መገንባታችንን እንቀጥላለን። ጥቂትም ቢሆኑ ባለፉት ሦስት ዓመታት አመርቂ ሥራዎችን ለመሥራታችን ምስክሮቹ እናንተው ናችሁ።

ሁለተኛው ማዕዘናችን የተቋማት ግንባታ ሲሆን፣ በጥቂት ግለሰቦችና ነጠላ ተቋማት ላይ ከማተኮር ባለፈ አገራችንን በጽኑ መሠረት ላይ የሚያቆሙ ጠንካራ ተቋማት ያስፈልጉናል። ዘመን ተሻጋሪ ሥርዓት ለማጽናት የሚስችሉ ገለልተኛና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚያገለግሉ ተቋማትን መገንባት ላይ ትኩረት ይደረጋል። ይኼ ማዕቀፍ ከፌዴራል እስከ ክልል የሚገኙ ተቋማትን የሚያካትት ይሆናል።

በሦስተኛ ደረጃ እንደ አገር የሚያስተሳስሩን የጋራ አመለካከቶችና የጋራ ትርክቶች ላይ ትኩረት ሰጥተን ልንሠራባቸው ይገባል። እርስ በእርስ የሚቃረኑና የሚጠፋፉ ትርክቶች ምን ያህል ለጠላቶቻችን ተመችቷቸው እኛን ደካማ እንዳደረገን ያሳለፍናቸው ዓመታት ሕያው ምስክሮች ናቸው። ስለዚህ ክፍተቶቻችንን በሚደፍን መልኩ ብቻ ሳይሆን እንደ አገር አጠንክረው በሚያቆሙን እሴቶች ላይ የተመሰረተ፣ ገዢና ሁላችንንም አሸናፊ የሚያደርግ ትርክት ለመገንባት ጠንክረን እንሠራለን።

በአራተኛ ደረጃ የሞራል ልዕልናና ግብረገባዊነት ተመጣጣኝ ትኩረት አግኝተው እስካልተሠራባቸው ድረስ በአገራችን ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ቁጥር እየቀነሰ፣ በተቃራኒው ኢ-ሞራላዊ ድርጊቶች እየተስፋፉ እንዲመጡ በር ይከፍታል። ይኼንን ችግር የማቃለልና የማስወገድ ኃላፊነት መንግሥትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ላይ ብቻ የሚጣል ሳይሆን፣ ከግልና ከቤተሰብ ጀምሮ የሚከናወን ሥራ ነው። ሁሉም አካላት ተረባርበው አገርና ትውልዱን እያቆሸሹ ያሉ መጥፎ ተግባሮችን ጠርጎ ሊጥላቸው ይገባል። በቀጣይ ዓመታት በሞራል ንጽህና የተገነቡ ተቋማትንና መሪዎችን አንጥረን የምናወጣበት እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

**ውድ የአገሬ ዜጎች!**

ባለፉት ሦስት ዓመታት በከፍተኛ ጥንቃቄ የቀረጽነው የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለተግባራዊነቱ በጋራ ከተጋን ያለ ጥርጥር በቀጣዩቹ ዓመታት ለአገራችን ብልጽግና እንደ ወሳኝ የመታጠፊያ ኩርባ ይሆናል። ዕምቅ አቅሞቻችን ምንድን ናቸው? ምን ዓይነት የመበልጸግ ዕድል እጃችን ላይ አለ? ምን ብናደርግ ኢኮኖሚያችን መዋቅራዊ ለውጥ ያመጣል? የሚሉትን በሚገባ ፈትሸን ያረቀቅነው ዕቅድ ነው።

በአገራችን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው። በፍጥነት የምግብ ፍላጎታችንን በማሟላት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከውጭ የምግብ ድጎማ መላቀቅ አለብን። ምግብ ለእኛ ቅንጦት ሊሆን አይገባም። ጠግቦ መብላት ቅንጦት የሆነበት ሕዝባችንን

መርጦ መብላት እንዲጀምር ለማድረግ ቆርጠን መነሳት አለብን። በብዝኃ ዕጽዋትና በብዝኃ እንስሳት የምትታወቅ አገራችን የእንስሳት ተዋጽዖና ፍራፍሬዎች ለገበታችን ከቅንጦትነት ወደ አዘቦትነት መለወጥ አለባቸው። ዶሮና ዕንቁላል፣ ወተትና ቅቤ፣ ተርፎን ለገበያ የምናቀርባቸው እንጂ ለዓመት በዓል አይተናቸው የሚሰወሩ የሩቅ እንግዳ መሆናቸው ሊያከትም ይገባል።

እዚህ አንድ መታወቅ ያለበት ሀቅ አለ። መንግስትና ሕዝብ እጅና ጓንት ሆነው እስካልሠሩ ድረስ ሕልማችን ይሳካል ማለት ዘበት ነው። በቀጣይ አምስት ዓመታት ተባብረን በተለይ በግብርናው ዘርፍ ምርታማነትን ለማሳደግ ጠንክረን መስራት አለብን። ከዚህ ቀደም ጀምረናቸው ውጤት እያመጡ ያሉ ተግባራት አሉ። የበጋ ስብሎችና ፍራፍሬዎች ላይ ለውጥ ለማምጣት ከተጀመሩ አነስተኛ መስኖዎች ባለፈ፣ ዝናብ አጠርነትን ለመዋጋት በቴክኖሎጂ አማካኝነት ደመናን ወደ ዝናብ የመቀየር ልምምዳችን እያደገ ይገኛል። በቅርቡም ምርትን የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅመን ችግሮቻችንን ወደ ዕድል መቀየር ጀምረናል።

አየር ንብረታችንን የሚያስተካክለውና የብዝኃ ዕጽዋትና የብዝኃ እንስሳት ሀብታችንን በእጅጉ ያሳድጋል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብራችን እንዲሁ ተጠቃሽ ነው። በቁጥር ግንባር ቀደም ያደረጉን የቀንድ ከብቶቻችን ከመቀንጨር ወጥተው ምርታማ እንዲሆኑ ያደርጋል። ወደየጎረቤት አገሩ የሸሹ የዱር እንስሳትም ተመልሰው፣ ከታሪካዊና ባህላዊ መስህቦች ጋር የተዋደደ ተፈጥሯዊ መስህብ በመሆን የቱሪስት ፍስትን እንዲጨምርና ኢኮኖሚያችን መስፈንጠር እንዲችል መደላድል ይሆናል።

## የአገራችን ሕዝብ ሆይ!

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ትኩረታችንን ሰቅዘው ከያዙት ጉዳዮች መካከል የሕዳሴ ግድብ አንዱ ነው። የዴሞክራሲ ጥያቄን አንድ ምዕራፍ ለማሳደግ የምርጫችን መሳካት ወሳኝ እንደነበረው ሁሉ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ችግራችንን ለማቃለል የሕዳሴ ግድብ ተመሳሳይ ነበር። በተለይ ለዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች መቀላጠፍ ጉልህ አስተዋጽዖ ከሚያበረክቱ ፕሮጀክቶቻችን መካከል አንዱና ወሳኙ የሕዳሴ ግድብ ግንባታችን እንደሆነ ይታወቃል።

የሕዳሴ ግድብ አጀንዳ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ከግድብም፣ ከኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭነትም በላይ ነው። ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ባለፈ ዳግም የመነሣታችን ተምሳሌት ነው። በራስ አቅም የመቆም፣ በራስ ፍላጎት የመመራት፣ የሉዓላዊነታችን ምልክት፤ የአገራዊ አንድነታችን ገመድ

ነው። በሕዳሴ ጉዳይ ብዙ አይተናል፤ ብዙ ተፈትነንበታል። በራሳችን አቅም መቆማችን የሚያስደነግጣቸው፣ በፍላጎታችን መመራት መጀመራችን የሚቆጫቸው ብዙ ጋሬጣዎችን ሲጥሉብን ነበር። “ሚስማር አናቱን ሲመቱት ይበልጥ ይጠብቃል” እንዲሉ ሆኖ፤ በዓባይ ጉዳይ በገፉን ቁጥር እየቆምን፣ በተጫኑን ቁጥር እየበረታን፣ ባዋከቡን ቁጥር ይበልጥ እየጸናን አሁን የደረስንበት ቦታ ላይ ቆመናል። በቅርቡ ሁለተኛውን ዙር የውኃ ሙሌት አድርገን፣ በምርጫው ስኬት የተደሰትነውን ያህል፣ በሕዳሴያችንም ሐሴት እንደምናደርግ አልጠራጠርም።

በሕዳሴ ግድብ ላይ ፍትሐዊ ተጠቃሚነታችን እንዲጠበቅልን እንጂ መቼም ቢሆን ሌሎች አገሮችን የመጉዳት ፍላጎት ኖሮን አያውቅም። አሁንም ለታችኛው ተፋሰስ አገሮች ደግመን ማረጋገጥ የምንፈልገው ሐቅ፣ የዓባይ ወንዝ እንደሚያስተሳስራቸው ወንድም ሕዝቦች በእናንተ ላይ ምንም ዓይነት አሉታዊ ተጽዕኖ የመፍጠር ፍላጎት የለንም። ዛሬም ሆነ ወደፊት በጋራ ተጠቃሚነት ዙሪያ ለመመካከር በራችን ክፍት ነው። እኛንም ሆነ እናንተን ነጥሎ ተጎጂ ወይም ተጠቃሚ በሚያደርጉ አካሄዶች ላይ እንድንሳተፍ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን አይፈቅድም።

ከጎረቤት አገሮች ጋር ያለንም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከኢትዮጵያዊ ማንነታችን የሚቀዳ ነው። በጋራ ተጠቃሚነት ዙሪያ ለመሥራት ሁሌም ዝግጁዎች ነን። የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ሰላሙ እንዲጠበቅ፣ የጋራ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር፣ በትብብርና በመግባባት እንድናድግ ኢትዮጵያ ትፈልጋለች፤ ጥሪም ታቀርባለች።
የተከበራችሁ ተፎካካሪ ፓርቲዎች!

የአገራችንን መጻኢ ጊዜ ብሩህ ለማድረግ በተገቢው መወጣት ከሚገቡን የቤት ሥራዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ፖለቲካዊ ጉዳዮቻችንን በሠለጠነ መንገድ መምራት ነው። ከላይ በመግቢያዬ እንደገለጽኩት ይኼ ሓላፊነት በመንግሥትና በተመረጠው ፓርቲ ላይ ብቻ የሚጣል አይደለም። አንድ አካል ልሥራው ብሎ ቢነሣ እንኳን በአግባቡ የሚወጣው ጉዳይ እንዳልሆነ በተደጋጋሚ አይተናል። እንኳንስ የሠለጠነ የፖለቲካ ሥርዓት መገንባትን የሚያህል ነገር ይቅርና፣ አንድ ዙር ምርጫን ዴሞክራሲያዊ አድርጎ ለማጠናቀቅ ብዙ አካላት መረባረብ እንዳለባቸው ካለፍናቸው ምርጫዎች በሚገባ ተረድተናል። የዘንድሮውንም ምርጫ ካለ እናንተ ድጋፍና ትብብር ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ማከናወን ባልተቻለ ነበር።

በቀጣይ ዓመታት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደታችን መሬት እንዲረግጥ የተለመደ

ትብብራችሁና በየምዕራፉ ያላሰለሰ ድጋፋችሁ እንደሚያሻን ከወዲሁ ለመግለጽ እወዳለሁ። በአገራችን የብልጽግና ጉዞ ውስጥ የሚኖራችሁ ድርሻ ወሳኝ እንደሆነም እናምናለን። የፖለቲካ ልዩነቶቻችን እንዳሉ ሆነው፣ ለአገርና ለሕዝባችን በሚጠቅሙ ማናቸውም የፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች ላይ ከእናንተ ጋር በመግባባት ለመሥራት ዝግጁዎች ነን።

**ምርጫውን ስኬታማ ያደረጋችሁ ውድ የተቋማት አመራር አባላትና ሠራተኞች !**

ይህ ምርጫ የተሳካ እንዲሆን የምርጫ ቦርድ አመራር አባላትና ሠራተኞች፣ እንዲሁም የምርጫ አስፈጻሚዎችና ታዛቢዎች ሁሉ ከደም መስዋዕትነት በመለስ ያለ ከፍተኛ ዋጋ ከፍላችኋል። ከግራ ከቀኝ የሚመጡትን ጫናዎች ተቋቁማችሁ በውጣ ውረዶች ሳትበገሩ ለአገራችን የማይደበዝዝ የዴሞክራሲ አሻራ አትማችኋል፤ በዚህም ታሪክ ስማችሁን አድምቆ ይጽፈዋል።

የጸጥታ አካላት፤ ምርጫው ሰላማዊ እንደሆን ጉልህ ሚና ተጫውታችኋል። እናንተ እንቅልፍ አጥታችሁ ስጋቶቻችን ሁሉ እንደ ጉም እንዲተን ስላደረጋችሁ ክብር ይገባችኋል። በተመሳሳይ፣ ፈጣንና ሚዛናዊ መረጃን ወደ ሕዝቡ በማድረስ በኩል የግልና የመንግስት መገናኛ ብዙሃን፤ እንዲሁም አጭር የጽሑፍ መልዕክት ስርጭት በኩል የኢትዮ - ቴሌኮም ሠራተኞች፣ ላበረከታችሁት አስተዋጽዖ ኢትዮጵያ ታመሰግናችኋለች።

**ውድ የፓርቲያችን አመራር አባላትና አባላት !**

በዚህ ምርጫ ሕዝቡ ያስተላለፈውን መልዕክት በሚገባ መረዳት የወደፊቱን መንገዳችንን ቀና እንደሚያደርገው እናምናለን። ሕዝቡ እኛን በአብላጫ ድምጽ የመረጠው ፓርቲያችን እንከኖች ስለሌሉበት አይደለም፤ ከነስህተቶቻችን ዕድል ሰጠን እንጂ ድል አላደረግንም። ሕዝብ የመረጠን በአንድ በኩል ያጠፋናቸውን እንድናርም፣ በሌላ በኩል መልካም ጅምሮቻችንን እንድናስቀጥል፣ ከአገር ግንባታ አኳያ በወሳኝ ደረጃ ላይ ያሉ የለውጥ ሥራዎችን በቀጣይ ጊዜያት ፈጽመን እንድናስረክብ ነው።

ሕዝባችን ጉድለቶቻችንን በሚገባ ያውቃል። ከስርቆት ዓመል ያልተላቀቁ፣ ለሰው ነፍስ ግድ የሌላቸው፣ ሕግን የማያከብሩ፣ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ አመራር አባላት በመካከላችን መኖራቸውን ጠንቅቆ ያውቃል። ድምፁን ሲሰጠን ታረሙ፣ ውስጣችሁን አጥሩ እያለን ጭምር ነው። እኛም በተግባር ሆነን ማሳየት አለብን። ይኼን ማድረግ ካልቻልን ከአምስት ዓመት በኋላ በካርዱ እንደሚቀጣን እናውቃለን።

**በአሁኑ ምርጫ መምረጥ ያልቻላችሁ ወገኖቻችን በሙሉ!**

በልዩ ልዩ የፀጥታና የደኅንነት ምክንያቶች፣ እንዲሁም በሎጅስቲክና በተለያዩ ውሱንነቶች ምርጫው በተያዘለት ክፍለ ጊዜ መሠረት ከተቀረው ሕዝብ ጋር አብራችሁ ድምፅ ባለመስጠታችሁ ታላቅ የሆነ ቅሬታ ፈጥሮብናል። ይኼ የሆነው ባልተጠበቁ ምክንያቶች እንደሆነ "ግንዛቤ ትወስዳላችሁ" የሚል ግምት አለን። ሁኔታዎች ተስተካክለው የምርጫ ቦርድ በወሰነው ቀን ምርጫው እንደሚደረግ እምነቴ ነው።

ትግራይን በተመለከተ የትግራይ ሕዝብ በሚፈልገው መንገድ ከተደራራቢ ችግር የሚወጣበትን፣ ተያያዥ አገራዊ ችግሮች የሚፈቱበትን፣ ሰላምና ደኅንነት የሚረጋገጥበትን የመፍትሔ አቅጣጫዎች እንከተላለን።

በመጨረሻም ከለውጡ ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ ስለ አገር አንድነትና ስለ ሕዝባችን ተጠቃሚነት ቀና ቀናውን በማሰብ በመንገዳችን ሁሉ ድጋፍ ሲያደርጉልን የነበሩ አካላትን ከልብ ሳላመሰግን አላልፍም። ኢትዮጵያ በታሪክ ለውጥ ላይ ናት። በዚህ የለውጥ ሂደት ተሳፍረን የተሻለች አገር እንገነባለን። በዚህ ምርጫ "ኢትዮጵያችን አሸናፊ" መሆኗን በድጋሚ ለመግለጽ እወዳለሁ። ቀጣይ ዘመናችንን ብሩህ ያድርግልን፤ ሁላችንም እንኳን ደስ አለን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ሀምሌ፣ 2013 ዓ.ም

# ጁንታው የኢትዮጵያ ህልውና ቀንደኛ ጠላት

ለትግራይ ሕዝብ ያለንን ሀሳብ፤ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ያለንን ቦታ ለመጨረሻ ጊዜ አሳይተናል። ግጭት ላለማባባስ፣ ለሕዝቡ የእርሻ ወቅት ፋታ ለመስጠት እንዲሁም የእርዳታ አቅርቦቱ ያለ ሰበብ እንዲከናወን ስንል በሰብዓዊነት ላይ የተመሠረተ የተናጠል የተኩስ አቁም አድርገናል። ሰላም የተወሰነ ዋጋ እንደሚያስከፍለን ብናውቅም ይህ ግን የመጨረሻ ሰላማዊ ዕድል ነው።

"ድመት መንኩሳ ዓመሏን አትረሳ" እንደሚባለው፤ ጁንታው የሰላም መንገድ ሊዋጥለት አልቻለም። አሁን ባለው ቁመና ያለ ግጭት ውሎ ማደር አይችልም። ሕጻናትና ወጣቶችን በአደንዛዥ ዕጽ እያሳበደ ወደ ጦርነት እየማገደ ይገኛል። የመከላከያ ሠራዊት እነዚህን ሕጻናት ወታደሮች የመታደግ ሞራላዊ ግዴታ ወድቆበታል።

ለሕዝባችን ስንል የከፈልነው ዋጋ ባልገባቸው ደካሞች ምክንያት ውጤት አልመጣም። ጁንታው የኢትዮጵያ ህልውና ቀንደኛ ጠላት መሆኑን ዳግም እያስመሰከረ ነው። ይሄንንም መላ ሕዝባችንን አስተባብረን እንቀለብሰዋለን። በአንድ በኩል ሰብዓዊ እርዳታ እንዲቀላጠፍ እየሠራን፤ በሌላ በኩል የውጭና የውስጥ ጠላቶች ተናበው የከፈቱብንን ጥቃት መክተን እንቀለብሰዋለን።

ጁንታው ዋሻ ውስጥ ገብቶ "ሕዝቡ በረሀብ ሊያልቅ ነው" እያለ ሲያላዝን ነበር። ለሕዝቡ ሲባል ሰብዓዊ የተኩስ አቁም ሲደረግ ደግሞ የረሀቡን አጀንዳ ትቶ የጦርነት ነጋሪት መጎሰም ጀመረ። ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ስለ እርዳታና ረሀብ ሲናገር መቆየቱን ዘንግቶ ጁንታው ሕጻናትን ሲያሰልፍ እንኳን ዝምታን መርጧል። የእርዳታ መግቢያ ኮሪደሮችን የግጭት ቦታዎች ሲያደርጋቸው  አሁንም የእርዳታ ድርጅቶች መንግሥትን ለመውቀስ ይቃጣቸዋል። እነዚህን ሁሉ ከግምት በማስገባት መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ በተገቢው መንገድ ያደርጋል።

ሕዝባችን አሁንም ከሀሰተኛ መረጃዎችና ከጠላት ፕሮፓጋንዳ ራሱን እንዲጠብቅ ለማሳሰብ እንወዳለን። ጁንታውና አጋሮቹ ያላቸው አቅም ውሸት መፍጠር ብቻ ነው። የውስጥና የውጭ ኃይሎች ፕሮፓጋንዳቸውን አቀናጅተው ሕዝብን ለመከፋፈል እየሠሩ ነው። ለዚህ ደግሞ ሕዝባችን እንደ ከዚህ በፊቱ ሁሉ እንደ አንድ ሠራዊት ሆኖ ለአገሩ ህልውና በመቆም፣

የመከላከያ ሠራዊቱን በሁሉም ነገር በመደገፍ፣ የውጪውን ጫና እና የውስጡን ትንኮሳ እንዲመክትና እንዲቀለብስ ጥሪ እናቀርባለን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

ሐምሌ 7፣ 2013 ዓ.ም

# ዒድ ሙባረክ!

**እንኳን ለ1442ኛው ዓመተ ሒጅራ የዒድ አል-አድሐ ዐረፋ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን!**

የዒድ አል-አድሐ ዐረፋ በዓል የመታዘዝና የመስዋት በዓል ነው። ነቢዩ ኢብራሒም ለፈጣሪያቸው ያላቸውን መታዘዝ ያሳዩበት ነው። አላህ (ሱ.ወ.) "ልጅህን ሰዋልኝ" ብሎ ሲያዝዛቸው አንድያ ልጃቸውን እስማኤልን ለመሰዋት ቅንጣት ታህል አላመነቱም። ይኼን ማድረግ ቀላል አይደለም፤ ድፍረትና ጽናትን ይጠይቃልና በሙስሊሙ ዘንድ የነቢዩ ኢብራሒም ታሪክ ልዩ ትርጉም አለው።

መታዘዝ የበታችነት ስሜት አይደለም። ራስን በሥነ ሥርዓት የመግዛት ውጤት እንጂ። ዋናው ጉዳይ ለማን መታዘዝ እንዳለብን ማወቅ ነው። በየመሥሪያ ቤቶቻችን ውስጥ ለትክክለኛው መመሪያ፣ አሠራርና አቅጣጫ ታዝዞ ያለመሥራት አንዱ ፈተናችን ነው። ነቢዩ ኢብራሂም የታዘዙትን ለመፈጸም ያጋጠማቸውን ፈተና ሁሉ አልፈውታል። ምክንያትም ሆነ ሰበብም ላለመስጠት ከራሳቸው ጋር ታግለዋል። ዓላማቸው የታዘዙትን መፈጸም እንጂ ለምን እንደማይቻል ምክንያት መፈለግ አልነበረም። በአገር ጉዳይ ሁላችንም በየተሰማራንበት መስክ ይሄንን እሴት ልንላበሰው ይገባል።

የዘንድሮውን የዐረፋ በዓል የምናከብረው እንደ አገር በሁለት አቅጣጫዎች እየተፈተንን ነው። እስከ አሁንም እልህ አስጨራሽ ትግል አድርገናል፤ መስዋትነት ከፍለናል። በአንድ በኩል በሕዳሴ ግድባችን ዙሪያ የዘመናት ምኞታችን እውን እንዲሆን፣ የዓመታት ልፋታችን ፍሬ እንዲያፈራ የመጨረሻውን ተጋድሎ በማድረግ ላይ እንገኛለን። በሌላ በኩል አንድነታችንን ከሚሸረሽሩና አገራችንን ከጀርባ እየወጓት ከሚገኙ እኩይ ኃይሎች ጋር እየተፋለምን ነው። አሁን ለአገራችን ያለንን ጥልቅ ፍቅር በተግባር የምናሳይበት ወሳኝ ወቅት ነው። በአገር ጉዳይ እስከ ምን ድረስ ለመፈተን ዝግጁዎች መሆናችንን ልናስመሰክር ይገባል።

የመጨረሻዋ የመስዋት ሰዓት በደረሰች ጊዜ ነቢዩ ኢብራሒምና ልጃቸው እስማኤል የተሰማቸው ጭንቀት እጅግ ከባድ ነበር። ነገር ግን ፈተናው አላሸነፋቸውም፤ በድል ተወጥተውታል። እኛም በሕዳሴ ግድብ ዙሪያ አስጨናቂውን ጊዜ በድል እንደምንወጣው አልጠራጠርም። የሚገጥሙንን የዲፕሎማሲና ሁለንተናዊ ጫናዎች ተቋቁመን በጽናት እንጓዛለን። እስከ አሁን አንደኛውና ሁለተኛውን ዙር የውሃ ሙሌት በድል ማጠናቀቅ ችለናል። በዚህ መልኩ እውነትን ይዘን በትብብርና በመናበብ መጓዛችንን ከቀጠልን ያለጥርጥር ፍጻሜያችን ያምራል።

በዚህ አጋጣሚ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሆናችሁ በሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ስትፋለሙ ለነበራችሁ ሁሉ ያለኝን አክብሮት ለመግለጽ እወዳለሁ። አገር ፍቅራችሁን በምትሻበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ከጎኗ በመቆማችሁ፣ አስፈሪ የሚመስሉ ተገዳዳሪዎቿን በድፍረት በመጋፈጣችሁ፣ በኢትዮጵያ ስም ሳላመሰግናችሁ አላልፍም። ወደፊትም አይተኬ ሚናችሁን አጠንክራችሁ እንደምትገፉበት ተስፋ አለኝ።

የዛሬውን የመስዋት በዓል ከሙስሊም ወገኖቻችን ጋር ሆነን በምናከብርበት በዚህ ዕለት፣ አገራችንን አደጋ ላይ እየጣላት የሚገኘውን የጁንታ ኃይል ለመፋለም በዱር በገደሉ ዋጋ እየከፈሉ የሚገኙ ወገኖቻችን አሉ። ዐረፋን ስናከብር እነዚያን መስዋት የሚሆኑ ወንድሞቻችንን እያሰብንና ተገቢውን ክብር እየሰጠናቸው መሆን አለበት። ዛሬ እነሱ የሚቀበሉት መከራ ትናንት በጁንታው ፕሮፓጋንዳ ምክንያት ለዓመታት ተራርቀው የሚገኙ ወንድሞቻችንን ይመልሳል፤ ፍቅርና መተሳሰብን ያመጣል፤ ከምንም በላይ እንደ አገር በአንድነት ጠንክረን እንድንቆም ያደርጋል።

## የተከበራችሁ ሙስሊም ወንድም እህቶቼ!

የዐረፋ በዓል የመስዋት ብቻ ሳይሆን የመተጋገዝና የመደጋገፍ በዓል ጭምር ነው። ሕዝበ ሙስሊሙ ደስታና ሐዘኑን እየተጋራ በዓሉን በአንድነት ያከብራል። የዐረፋ ሰሞን አንድም ሰው ተርቦና ተጠምቶ፣ ታርዞና ተከፍቶ አያሳልፍም። በዐረፋ ከሚከናወነው እርድ አንድ ሦስተኛው ለምስኪኖች እንዲሰጥ የእስልምና አስተምህሮ ያዛል። በዓሉ በዓል የሚሆነው ምእመኑ ተረዳድቶና አንድ ሆኖ ሲያከብረው ነው። መረዳዳትና መተሳሰብ አገርን ከፈተና የሚያወጣና ወደምትፈልገው ደረጃ የሚያደርስ እሴት ነው። ኢትዮጵያውያን ያለንን ሁሉ አውጥተን፣ የተማሩ ላልተማሩ፣ ያላቸው ለሌላቸው፣ የሚችሉ ለማይችሉ፣ የተረዱ ላልተረዱ አካፍለው ይሄን ያለንበትን ፈታኝ ጊዜ ማለፍ እንዳለብን ዐረፋ ያስተምረናል።

የዐረፋ በዓል አዳምና ሔዋን የተገናኙበት የአንድነት በዓልም ነው። አንድነት የሰው ልጅ ዘመናትን ተሻግሮ፣ የገጠሙትንም ፈተናዎች አልፎ ዛሬ ለደረሰበት የሥልጣኔ ደረጃ ያበቃው ዕሴት ነው።

የሰው ልጅ የትራንስፖርትና የመገናኛ መሣሪያዎችን ሲፈለስፍ የኖረው፣ ዓለምን ለማሰስ ዋጋ የከፈለው፣ ከሌላው ጋር አንድ ካልሆነ በቀር ህልውናው ከአደጋ እንደማይጸዳ ስለተረዳ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን የዐረፋን በዓል ስናከብር አንድነታችንን አጥብቀን መቆም እንዳለብን እናስባለን። አንድነቱን ያጸና ሕዝብ በማንኛውም ፈተና ፊት ብርቱ ሆኖ ይቆማል። ማንኛውንም ተግዳሮት አሸንፎ ያልፋል። ማንኛውንም መሻቱን በጥረቱ ይደርስበታል። ጠላቶቻችን አንድ ሆነው እየመጡ ነው። ኢትዮጵያን የማፍረስ አንድ ግብ ይዘው እየመጡ ነው። ዐቅማችንን፣ ዕውቀታችንን፣ እሴቶቻችንንና ጉልበታችንን ካስተባበርን፣ አንድ ሆኖ የመጣን ጠላት አንድ ሆነን ድል ማድረግ እንችላለን።

መጭው ጊዜ ለአገራችን የደስታና የበረከት እንዲሆን ከዐረፋ በዓል ያገኘናቸውን እሴቶች በሁሉም ዘርፎች እንደምንተገብራቸው እተማመናለሁ። እንዲያ ስናደርግ የሚፈትኑን መከራዎች ሁሉ የሚታለፉ፣ ጠላቶቻችን ሁሉ በቀላሉ የሚሸነፉ፣ የምንመኘው ብልጽግና በፍጥነት የሚሳካ ይሆናል።

በድጋሚ መልካም የዐረፋ በዓል እንዲሆንላችሁ እየተመኘሁ፣ በእለቱ ድኾችን፣ በየመጠለያው ያሉ ወገኖችን፣ በየሕክምና ማዕከሉ ያሉትን ሕሙማን እንድናስባቸው አደራ እላለሁ፡፡

**ዒድ ሙባረክ!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ!**
ሀምሌ 12፣ 2013 ዓ.ም

# የውሸት ፀሐይ ሲጠልቅ የሤረኞች ወጥመድ ይበጠሳል!

ሁልጊዜም ከመንጋቱ በፊት ድቅድቅ ጨለማ ይሆናል። በምሽትና በንጋት ሽግግር ውስጥ ያላለፈ አገርና ትውልድ የለም፡፡ ብርቱው ጨለማ የንጋቱ ጸዳል አብሳሪ ስለሆነ፣ መቼም ቢሆን "ይኼ ምሽት እንደጨለመ ቢቀርስ? ወይም ንጋት ባይመጣስ?" ብለን አንሠጋም። ንጋቱ አይቀሬ ነውና አስደንጋጩ ጨለማ በማለዳው የብርሃን ጸዳል ይዋጣል፡፡
የአዲሱ ቀን ጎህ ሲቀድ አስፈሪዎቹ አውሬዎች ወደየጎሬያቸው መግባታቸው፣ የሌሊቱም ቁር ለቀኑ ሙቀት ሥፍራ መልቀቁ አይቀሬ ነው። በቀን የተሰወሩት ከዋክብትም ቢሆኑ ከመቼውም ይልቅ ደምቀውና ጎልተው የሚታዩት በሕይወት ጉዟችንም ከጠበቅነው የተስፋ ንጋት ቀድሞ ጨለማ የሚመስል ፈተና ከፊታችን እንደ ጅብራ ሊደነቀር ይችላል፡፡ ፈተናው አዲስ እየመሰለን የስሜት መረበሽ ያጋጥመናል፡፡ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በአስተዳደርና በሌሎች ማኅበራዊ ሂደቶች ሁሉ፣ ተግዳሮትና ፈተና ውስጥ ገብተን ራሳችንን እናገኛለን። ግለሰቦችና ቤተሰቦች፣ መንግሥታትና አገሮች በጥፉት ሥጋት የህልውና ጥያቄ ውስጥ በመግባት በአጣብቂኝ ውስጥ ያልፋሉ፡፡ ጥያቄው 'ይህ ጊዜ ያልፋል ወይስ አያልፍም?' ሳይሆን 'እንዴት ይታለፋል?' የሚል ነው። ይህ ችግርና ተግዳሮት በጨለማው ውስጥ ደምቀውና አሸናፊ ሆነው ብዙዎችን አስከትለው ለሚወጡ ከዋክብት የድምቀትና የጀግንነት እድልም ነው፡፡
አገራችን ኢትዮጵያ በቀደምት ታሪኳ ብዙ ክረምትና በጋዎችን፣ ጨለማና ብርሃንን ያፈራረቁ ውጣ ውረዶችንና እንቅፋቶችን አሳልፋለች። በገባችበት የክረምት አረንቋና የውድቅት ሌሊት የፈተና ሰዓት የቁርጥ ቀን ልጆችዋ "በከፉዎች ሤራ ተጠልፋ ትወድቅ ይሆን?" የሚል ሥጋት ቢገባቸውም፣ እጃቸውን አጣጥፈው ከመቀመጥ ይልቅ በተስፋ ጽናት በሕይወታቸው ተወራርደው ችግሯን ተጋፍጠውላታል። ጠላቶቿን ለማሳፈር አንገታቸውን ለሰይፍ፣ ደረታቸውን ለጥይት ሰጥተዋል፡፡ በዚህም እንደ ጨለማ የበረቱት ጠላቶችዋ ሲወድቁ፣ እርሷ አንገቷን ቀና አድርጋለች።
ብዙ የዓለም አገሮች እኛ ዛሬ የምናልፍበት በሤራ የመጠለፍ አደጋና የመበታተን ሥጋት፣ በአንድ ወይንም በሌላ ዘመን ገጥሟቸው ያውቃል። እንደ ዩጎዝላቪያና ሶሪያ፤ ሱማሊያና ሊቢያ ያሉ አገሮች በሥጋታቸው ተጠልፈው ወድቀዋል። እንደ ጀርመንና ጃፓን፣ ኮርያና ቬትናም ያሉት አገሮች ደግሞ በተመሳሳይ ቀውስ ውስጥ አልፈው፣ ፈተናቸውን ፊት ለፊት ተጋፍጠው፣ ሊጋራ ድል በአንድነት ሠርተው፣ ለስኬት ከበቁ አገሮች መካከል በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ዛሬ በኢኮኖሚ ዐቅማቸውና በዘመናዊ የፖለቲካ

አስተዳደራቸው፣ በቴክኖሎጂ ምጥቀታቸውና በማኅበራዊ ዕሴታቸው እጅግ ዘመናዊ ከሚባሉት አገሮች መካከል የሚመደቡ ሆነዋል። አስቀያሚና ፈታኙን ቀውስ አይተው ተሻግረውታል። የገጠሟቸውን እንቅፋቶች እንደ መስፈንጠሪያ ነጥብ እየተጠቀሙ አሁን ካሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

ለምሳሌ ጀርመን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት ወድቃና ተንኮታኩታ ነበር። ምሥራቅና ምዕራብ ጀርመን እየተባለች ለሁለት ተከፍላ ለመቆየት ተገድዳለች። ጊዜው ቢረዝምም በመጨረሻ ሕዝቦቿ ተባብረው የለያቸውን የድንጋይና የርዕዮተ ዓለም ግንብ አፍርሰውታል፡፡ በ1860 አካባቢ ደም አፋሳሽ በሆነው የርስ በርስ ጦርነት ገብታ ለሁለት ከመከፈል ለጥቂት የተረፈችው አሜሪካ ራሷ ከደረሰባት ጥፋትና የመበታተን አደጋ የዳነችው በሙቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ የልጆቿን ሕይወት ዋጋ ከፍላ ነው፡፡

በድህነት ላይ የእርስ በእርስ ጦርነትና የውጭ ጣልቃ ገብነት ክፉኛ ፈትኗት ሳትረታና ሳትፈታ በድል ያለፈችው የደቡብ ኮርያ ታሪክ ከአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በእጅጉ ተዛማጅ ነው። ዛሬ እኛ እያለፍን በምንገኝበት መንገድ ውስጥ ያለፉ፤ ችግርና እንቅፋት የሩቅ ሳይሆን የቅርብ ጊዜ ትዝታቸው የሆነ፣ ሌሎች አገሮችም ቁጥራቸው ጥቂት አይደሉም። ጨለማው የሚበረታው ሌሊቱ ከመንጋቱ በፊት ነው።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ያልገጠሟት ፈተናዎች፣ ያላለፈችበት ተግዳሮቶች የሉም። ሁሉንም የቀለበሰችውና ድል አድርጋ የወጣችው በአንድነት፣ በብልሐትና በመደመር ነው። ከውጭ የመጣ አደጋም ሆነ ከውስጥ የተነሳባት ፈተና የቱንም ያህል የበረታ ቢሆን፤ ልጆቿ በህብረት ሲቆሙ ከአቅማቸው በላይ ሆኖ አያውቅም።

በሌላ በኩል ደግሞ “እኔ ከሞትኩ” ባዮች፣ ለግል ጥቅም ሲሉ እናታቸውን በሚሸጡና አገራቸውን አሳልፈው በሚሰጡ፣ ጠላት እንደፈለገው በሚጋልባቸው ከንቱ ልጆችዋ ምክንያት ኢትዮጵያ ከአንዴም ብዙ ጊዜ ብርቱ ፈተና ውስጥ ገብታለች። ዛሬም ኢትዮጵያ በደጎናው ቀን እፍታዋን ያጎረሰችው፣ የማጀቷን ምርጥ በልቶ የጠገበው የጁንታው ኃይል፣ አገርን ለጠላት አሳልፎ ለመስጠት ዐይኑን የማያሽ ውስጥ አዋቂ ባንዳ በመሆኑ ፈተናው ጠንክሮብን ይሆናል። በአንድነት ከቆምንና ተደምረን ከተጋን ግን ይኽን ፈተና አሸንፈን፣ ችግሩን ወደ ዕድል፣ ዕድሉንም ወደ ታላቅ ድል ለውጠን፣ ለአገራችን ወደ አየንላት የሰላምና የብልጽግና ከፍታ ማማ ላይ እንደምናደርሳት ለአፍታም ልንጠራጠር አይገባም።

ለዘመናት ሕወሓት በአገራችን የሰራ አካላት ውስጥ ተሰግስጎ ራሱን እያፋፋ ኖሯል። በኢትዮጵያችን አንጀት - ደም ስር ስርጎ ሲጣባ ሲመርዛት ኖሯል፡፡ አሸባሪው ሕወሐት አሁን ተጠራርጎ ሊወጣ አፋፍ ደርሶና ጣዕረ ሞት ይዞት በመንፈራገጥ ላይ ይገኛል። እድሜውን ለማራዘም የመጨረሻ መፍጨርጨርና የሞት ሽረት ትግል ላይ ነው። የአልሞት ባይ አትርሱኝ መወራጨቱ በዝቷል። ከግብአተ መቃብሩ በፊት ልትወጣ ያለች ነፍሱ እስካለች

ድረስ መንፈራገጡና የሰላም ደንቃራ መሆኑ አይቀርም። ክፉ መርዙን ተክሎ ጥገኝነቱን ከመሠረተበት የሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተነቅሎና ተጠራርጎ እስኪወጣ ድረስ ደዌ ነውና ሕመሙን ችለን፣ የማሻሪያ መድኃኒት እየወሰድን እንቆያለን፡፡ "ኮሶ ሊያሽር ይመራል" እንደሚባለው፣ የማያዳግም ፀረ-ሽብር መድኃኒቱ የጎን ጉዳት የሆነውን ምሬትና ሕመም ታግሠን ከቆየን፣ ሕወሓትም ሆነ ማንኛውም እናቱን ለመሸጥ የሚደራደር ኃይል የአገራችን ክፉ ትዝታ ከመሆን የዘለለ ፋይዳ ላይኖረው በቅርቡ ለዘለዓለሙ ይሰናበታል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በብዙ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አሻጥሮች ውስጥ አልፈናል። ዛሬ በዲፕሎማሲያችን ላይ የሚታየው ከፍተኛ መንገራገጭ ከሦስትና ከአራት ዓመታት በፊት በሁሉም ዘርፎች ላይ የተስተዋለ የየዕለት ስቃያችን ነበረ። በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማኅበራዊው ዘርፍ፣ በአስተዳደር፣ በሕግ ሥርዓቱ፣ በጸጥታና ደኅንነት ሥርዓቱ፣ ከክልል እስከ ወረዳ በሁሉም ቦታ ይሄ ቀውስ ነበር። በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ ፈውስ እስኪገኝ ስቃይ ነበር፤ ሕመም ነበር። ስለዚህ አሁንም በዲፕሎማሲያችን ውስጥ ቀውስ ውስጥ ገባን ብለን መበርገግ አይገባም። ጠላት ሁሌም በማስፈራራትና በፕሮፓጋንዳ ቀድሞ ሊያሸንፈን ሲጥር ተሸንፈን አንጠብቀው።

የምንዋጋው ኃይል ዋነኛ ትጥቁ ውሸት ነው። የማኅበራዊ ትስስር ሚዲያን ጨምሮ በየመገናኛ ብዙሃኑ አንድ ውሸት በተኮሰ ቁጥር የምትበረግጉ ሰዎች ባለማወቅ የጁንታው ተባባሪዎች እየሆናችሁ እንደሆነ እወቁ፡፡ ሰው አንድና ሁለት ጊዜ ይሸወድ ይሆናል፤ ባለፉት ብዙ ዓመታት የተሸወዳችሁት ሳያንስ ዛሬም በፕሮፓጋንዳው በመደንበር፣ የአገራችሁን ጥቅም ከማሳጣት በዘለለ ምንም የሚፈይድላችሁ ነገር የለም። በተለይ ጥቃቅን ነጥቦችን በመገጣጠም የሤራ ትንታኔ ለመስጠት የምትነሡ ሰዎች ሤራ በመተንተን የምሁርነት ጊዜው አልፏል። አሁን የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር ተገቢው ቦታ ላይ መሰለፍ የሚጠይቅበት ጊዜ ላይ ነን። የኢትዮጵያ ጠላቶች ድሮ በድብቅ የሚያደርጉትን አሁን በግልጽ በሁለት ግንባሮች ላይ ጦርነት ከፍተዋል። በጦር ግንባር እና በዲፕሎማሲ ግንባር ጦርነት አውጀው እየሠሩ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ህልውና ግድ የሚለው ሁሉ ከሤራ ትንታኔና ከአጉል መበርገግ ወጥቶ ሁለቱን ግንባሮች በይፋ ይቀላቀል።

ጁንታው ቀሩኝ የሚላቸውን የክፋት ካርዶች ሁሉ ተጠቅሞ ሊያሸብረን፣ ሊያበጣብጠንና ሊለያየን የሚችለውን ድንጋይ ፈንቅሏል። በገንዘብ ኃይል ሕዝባችን ላይ እሳት እየለኮሰና እርስ በእርስ እያጋጨ እርሱ በምቾት እሳት ሲሞቅና ሕዝባችን ላይ ሲሳለቅ ነበር፡፡ የሽብር ነጋሪቱን እየጎሰመ ጀሌዎቹን አስከትሎ ዘምቷል፡፡ አሁን በተቃራኒው ተሳዳጅና የሞት ሽረት ሩጫ ውስጥ ነው። ጀንበሩ እየጠለቀች ነው። በሞት ሽረት ሩጫ ውስጥ የቀበረውንና

የቀረውን የመጨረሻ ጥይቶቹን እየተኮሰ ነው። ከመጨረሻዎቹ ምሽጎቹ የጣር ድምጹንና የተስፋ መቁረጥ ቀረርቶውን ስሙልኝ ብሎ ነጋ ጠባ ያላዝናል።
የአገራችንን እጅ ለመጠምዘዝ የሚፈልገው የምዕራቡ ዓለም ዲፕሎማሲና የመገናኛ ብዙሃን ጩኸትም የጁንታውን ድምጽ በማስተጋባት ደጀን ሊሆን ጥረቱን ቀጥሏል፡፡ ተባብረን ጫናውን ለመቋቋምና ለመመከት ከቆረጥን ይኼ ኃይል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያልቅለታል፡፡

ዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት “ሰጥቶ በመቀበል” መርሕ የሚመራ የፖለቲካ ዳንስ ነው። በትክክለኛ የግንኙነት መሥመር በተቃኘ ዲፕሎማሲ በዋናነት ተጠቃሚ የምትሆነው ሀገራችን ለመሆኗ ምንም ጥርጥር የለውም። በተቃራኒው የሀገራችንን ጥቅምና ሉዓላዊነታችንን አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ የሚቃኝ ግንኙነት ለጊዜው ፋታ የሚሰጥ ቢመስልም ዘላቂ ጉዳቱ አመዛኝ ነው። ይኼን ለማስተከለል መንግሥት የበኩሉን እያደረገ ነው፤ ወደፊትም አቋሙን አጽንቶ ይቀጥላል።

በዚህ አንጻር መታወቅ ያለበት አንድ ቁልፍ ሐቅ አለ፡፡ በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ላይ ዋነኛ ተጽዕኖ የሚፈጠረው በመደበኛው መንገድ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ የምዕራቡ ዓለም ጫና ሊያደርጉባቸው በሚፈልጓቸው ሀገራት ላይ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎችን በመጠቀም መጠነ ሰፊ ልዩ ልዩ ዘመቻዎችን እንደሚያደርጉ የአደባባይ እውነት ነው። ዛሬም ሆነ ትናንት የሚደርስብንን ጫና “አይሆንም” ማለትስንጀምር አፍራሽና ስም አጠልሺ የሆኑ የሚዲያና የመረጃ ዘመቻዎች ይከፈቱብናል። እነርሱ ትልልቅ ዐቅምና ሽፋን አላቸው፣ የዓለም ሕዝብ የተሳሳተ ምስል እንዲኖረው የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ የሚዲያ መሣሪያዎችና የዳበረ ኃይል በበቂ አላቸው። ስለዚህም በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተውን የሚዲያና የዲፕሎማሲ ጫና ለመመከት ሁሉም ሀገር ወዳድ ወገን መረባረብ ይጠበቅበታል። ተደምረን ያለንንየተጽዕኖ በርና ዕድል ሁሉ በመጠቀም የተከፈተብንን ዘመቻ መመከት አለብን። በማኅበራዊና በዋናው ሚዲያ፣ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር፣ በግልና በጋራ፣ በተናጠልና በመናበብ ሀገራችንን የሚጎዱ የውሸት ዜናዎች መቃወምና ማምከን ያስፈልጋል። እውነት በትክክልና በበቂ ከተነገረች ውሸትን ታሸንፋለች፤ እናም ሁሉም ዜጋ ለሀገሩ እውነት ዘብ በመሆን ሐቃችን እንዲያሸንፍ ማድረግ አለበት። በዚህ አስፈላጊ ወቅት ሁሉም ሀገር ወዳድ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኖ እንዲቆም እናት ሀገሩ ጥሪ ታቀርብለታለች።

እስካሁንም ጥቂት የማይባሉ የሀገር ልጆች ቀደም ብለው ትግሉን በመቀላቀል ለሀገራችን ብርቱ ፍልሚያ በማድረግ ላይ ናቸው። እነዚህ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ጀግኖች፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ እስከዛሬ አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ የቆየችው በልጆቿ ብርቱ ጥረትና

ትብብር እንጂ፣ እጅን አጣጥፎ በመቀመጥና ወሬ በመስለቅ እንዳልሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ወደ ሌላ ሰው ጣት ከመቀሰር ይልቅ "ሀገሬ የገጠማትን ችግር ለመመከት ከእኔ ምን ይጠበቃል?" በሚል መንፈስ ጠዋትና ማታ ሳይታክቱ ይፋለማሉ። በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ ቢኖሩ፣ የሀገራችንን ችግር በመጋፈጥ ያገኟትን ዕድል ወደ ድል ለመለወጥ ነጋ ጠባ በመዋደቅ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ከማበርከት አልቦዘኑም። ኢትዮጵያም ለሚያደርጉት ትግል ታመሰግናቸዋለች።

በተመሳሳይ ጥሪዋን ተቀብለው በዱር በገደሉ የሕይወት መሥዋዕትን በመክፈል የሀገራችንን ህልውና ለማስጠበቅ ተጋድሎ የሚያደርጉ ብርቅዬ ኢትዮጵያውያንንም ታሪክ ለዘላለም ይዘክራቸዋል። እነዚህ ሁሉ ሀገር በጨለመባት በዚህ ሌሊት የአንድነት ደማቅ ኮከቦቿና የነጻነት ፋና ወጊዎቿ ናቸው። የውሸት ፀሐይ ሲጠልቅ የሤረኞች ወጥመድ መበጠሱ፣ እውነትም አንገቷን ቀና አድርጋ መታየቷ አይቀርም። ጨለማው ይነጋል፤ ክረምቱም ያልፋል፤ ይኼም ፈተና ሰብሮን ሳይሆን አጠንክሮን በድል ይጠናቀቃል። ያለን አማራጭ ወደ ፊት፣ ወደ ብልጽግና፣ ወደ ነጻነትና ወደ ሰላም መገስገስ ነው። ካለፈው ትውልድ የተረከብናትን ሀገር የተሻለችና የተመረጠች አድርገን ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ በጋራ እንነሣ።

ጠላት ወደ ወጥመዳችን እየገባ ነው፡፡ የማሸነፍ ዐቅማችን ተደራጅቶና ተጠናክሮ እየወጣ ነው፡፡ ቃል እንደ ገባነው እጅን በአፍ የሚያስጭን ገድል መፈጸማችንን የምናበሥርበት ጊዜው ቅርብ ነው፡፡ የያዝነው የኢትዮጵያን አምላክ ነው፤ የምንታገለው ለኢትዮጵያ ነው፣ የሚዋጋው የኢትዮጵያ ጦር ነው፡፡ በመጨረሻም ታሪክ እንደሚነግረን አሸናፊዋ ኢትዮጵያ ናት፡፡
መሆን ይችላል፡፡

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ነሐሴ 9፣ 2013 ዓ.ም

# የአረንጓዴ አሻራ የስኬት ጉዞ ማሳያ

በአረንጓዴ አሻራ ኢትዮጵያን የማልበስ የዘንድሮ መርሃ ግብር በስኬት ተጠናቆ እንኳን በዚህ ስፍራ ለመገናኘት አበቃን ልላችሁ እወዳለሁ። የጀመርናቸው በርከት ያሉ ሥራዎች ተጀምረው የሚቀሩ ሳይሆን፤ ሁሉም ባስቀመጥንላቸው እቅድ መሰረት እየተጠናቀቁ ናቸው። የኢትዮጵያን ብልጽግና፣ የኢትዮጵያን መጽናት፣ የኢትዮጵያን መላቅ ሊያረጋግጡና ማሳያ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ የአረንጓዴ አሻራ ነው። ከnn ሁላችሁም እንደምታውቁት ክረምት ሲመጣ የአየር ሁኔታው ትንሽ ከበድ የሚል አካባቢ ይፈጠር ነበር። አሁን ክረምት የሚናፈቅ እየሆነ ነው። በአንድ በኩል የአቅመ ደካሞች ቤት ይገነባል፣ ዛፍ ይተከላል፣ ከተማ አካባቢ ይጸዳል፣ የእርሻ ስራ በስፋት ይሰራል። በዚህ ምክንያት ወጣቶቻችን አካባቢያቸውን፣ አገራቸውን ለመለወጥ ሰፊ እድል ያገኙበታል።
ዘንድሮ ይሄንን ቦታ የመረጥንበት ዋነኛው ምክንያት እዚህ የምታዩዋቸው ዛፎች ሁሉ አልነበሩም። አሁን ጫካ ሆነው የምናያቸው የአረንጓዴ አሻራ የመጀመሪያው ዓመት የተተከሉት ዛፎች ናቸው። አረንጓዴ አሻራ ሃሳብ አይደለም፤ የሚዳሰስ፣ የሚጨበጥ እና ለውጥ የሚያመጣ ነው። ይህ ቦታ እንደማሳያ የተወሰደበት ምክንያት በአጭር ጊዜ ጫካ ካደረግን ድፍን ኢትዮጵያን ማልበስ የሚቻል መሆኑን ስለሚያረጋግጥልን ነው። ስለዚህ ተስፋን እንድንሰንቅና ይበልጥ እንድንሰራ ያደርገናል። በአራት ዓመታት ውስጥ ሃያ ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል አስበን፤ በሶስት ዓመት ውስጥ ከአስራ ስምንት ቢሊዮን በላይ ችግኞች መትከል ችለናል። በሚቀጥለው ዓመት ሰባት ቢሊዮን እንኳን ብንተክል ሃያ አምስት ሆነ ማለት ነው። ሃያ አቅዶ ሃያ አምስት ማሳካት ማለት አምስት ከእቅድ በላይ ማከናወን ማለት ነው። ይሄንን በሁሉም እቅዳችን ማለት በግብርና፣ በወጪ ንግድ፣ በመሰረታዊ አገልግሎት ማሳካት ከቻልን መቶ አቅደን ከዚያ በላይ የምንከውን ከሆነ ብልጽግናችን በቅርብ ጊዜ ውስጥ እውን ሊሆን ይችላል። ዋናው የሚያስፈልገው በትክክል ማሰብ፣ ማቀድ፣ መጨረስ መቻልን መለማመድ ነው። እንዲህ ካደረግን የምናስበው ብልጽግና ሊመጣ እንደሚችል ጥሩ ማሳያ ነው።
ኢትዮጵያዊያን አብረን ስንቆም፣ ስንተባበር ምን ማድረግ እንደምንችል ዓለም እያየ መጥቷል። አሁንም የኢትዮጵያ የብልጽግና፣ የሰላም፣ የገናናነት መሰረት እውን የሚሆነው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በሁሉም ግንባር አብሮ መቆም ሲችል ነው። በግብርናውም፣ በንግዱም፣ በሰላሙም፣ በዲፕሎማሲውም በአንድ ልብ አብሮ መቆም የቻለ እንደሆነ ኢትዮጵያ በቀላሉ የማትነቃነቅ፣ የጀመረችውን የምታሳካ እንደሚባለውም ነጻ አገር መሆኗን ማረጋገጥ ይቻላል።

በአረንጓዴ አሻራ ያረጋገጥነውን ድል፣ ያሳየነውን ውጤት በሁሉም በገጠሙን ፈተናዎች እንደግማለን። ጦርነቱን እናሸንፋለን፤ ሰላም እናረጋግጣለን። የኢትዮጵያን ሰላም፣ አንድነትና ህልውና እውን ይሆናል። በእያንዳንዱ ፈተና ውስጥ እንማራለን፣ እንሰራበታለን፣ አገር እንገነባበታለን፣ እንታነጽበታለን። ፈተና ችግር ብቻ ሳይሆን በርካታ እድልም ይዞ ይመጣል። በዚህ ወቅት እድሎቹን ማየትና መጠቀም የሚያስችል ሁኔታ ከፈጠርን፣ አብረን ከቆምን የማንሻገረው ፈተና እንደሌለ ዘንድሮ ያለፍንበት ሁኔታ ብቻውን በቂ አመላካች ነው።
በኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር የታየውን መታዘዝ፣ ትጋትና ህብረት በሁሉም መንገድ መድገም ተገቢ ነው። ከመተባበር፣ አብሮ ከመቆም፣ በፍቅር ከመተሳሰርና ከመተዛዘን በላይ የኢትዮጵያን አሁናዊ ሁኔታ የሚቀይር ነገር የለም። በዚሁ መንገድ መስራት ከቻልን መጪው ዘመን ብሩህ ነው። መጪው ዘመን የምንሻገርበትና የማንቻል መሆናችንን ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

አረንጓዴ ዐሻራ እንዲሳካ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ሚኒስትሮችና የሥራ ባልደረቦቻቸው፣ እንዲሁም የደን ኮሚሽን እና የስራ ባልደረቦቻቸው እና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ባደረጉት ትጋትና የተሳካ ሥራ በኢፌዴሪ መንግስት ስም ምስጋና ላቀርብ እፈልጋለሁ። በሌሎችም መስኮች እንዲሁ ድል እያረጋገጥን የምንገናኝበት ጊዜ ከፊታችን እንዳለ ለመግለጽ እወዳለሁ። በመገናኘታችን እና በተሳካው ሥራ እጅግ ደስተኛ መሆኔን እገልጻለሁ። አሁን ያለነው በኦሮሚያ ክልል ስለሆን እና አባገዳዎችም ስላሉ ትንሽ ሰላምታ ማቅረብ እወዳለሁ።

Egaa, naannoo keenya keessatti waa'ee biqiltuu, waa'ee magariisaa dubbachuun barbaachisaa miti. Itti guddanne, hin beenna waan ta'eef. Magariisni waa baayyeetiif furmaata fida. Bishaan fida, misooma fida, qonna keenya fooyyessa, dargaggoonni keenya hojii akka baran, hojii keessa akka oolan godha. Bu'aan isaa baayyee waa ta'eef, akkuma jalqabne kanatti cimnee akka hojjennu, waliin akka dhaabbannu, ida'amuu fi jaalalaan biyya kana jijjiiruu, bilisummaa ishii eeguu, misooma ishii dagaagsuu akka dandeenyuuf waamicha koo dhiyeessa. Mootummaan Naannoo Oromiyaa bara kana, keessattuu Ganna kana keessatti waan baayyee milkeessee jira. Kana keessaa waan lama duwwaa kaasuun barbaada. Tokkoffaan, waa'ema Giriin Leegaasii (Ashaaraa Magariisa) kana. Karooraa ol hojiin guddaan hojjetamee jira. Lammaffaan, Pireezidaantiin keenya ji'a sadi keessatti yoo xiqqaate kiiloo diigdama gadi buusuu qabdu jedhamanii, Ganna kana

keessatti kiiloo diigdamii-sadi, karooraa ol jechuudha, [...kolfa ሳቅ] karooraa ol gadi buusanii loltuu (wattaaddara) gaarii fakkaatanii jiru. Dargaggoonni keenya kanarraa barumsa fudhachuu qabdu. [Ulfaatina] Dhagna keenya gadi buusuu, of cimsuu, hojii hundaaf of qopheessuu, nageenya naannoo keenyaa eeguu, waliin taa'anii hojii naannoo fi biyya jijjiiru hojjechuun murteessaa akka ta'e Pireezidaantiin keenya ofirraa jalqabanii agarsiisanii jiru. Isaan irraa barannee, hundumti keenya of jijjiiruudhaaf akka kaanu ergaa koo dabarsuun barbaada. As argamuu keenyatti, kanaan dura kan dhaabne guddatee akkaataa kanaan arguu danda'uu keenyatti baayyee gammadeen jira. Baga Gammaddan! Jabaadhaa! Tokkummaan keenya, bilisummaan keenya, caallee argamuun keenya, misoomni keenya kan dhaabbatu miti. Rakkoon garaa garaa jiraachuu danda'a. Rakkoo keessatti qaramaa, barachaa, of cimsaa, of ijaaraa, biyya ijaaraa deemna. Hin yaaddayinaa. Injifannoon kan Itiyoophiyaadha!
Dhumarratti, Obbo Dammaqa Mokonnin as nu wajjiin argamanii jiru. Gara naannoo keenyaa gaafa dhufan Oromiffa [Afaan Oromoo] kana shaakaluu waan baraniif, dhufanii jechuma lama...sadi..tokko dubbatanii, Abbootii Gadaan nagaa akka jedhaniif carraa kennuufii barbaada. Obbo Dammaqa, gara kanatti dhuftanii otoo xiqqoo ummata keenya dubbiftanii.

**አመሰግናለሁ!**

ነሃሴ 30፣ 2013 ዓ.ም

# አዲስ ዓመትን በማይፀብሪ

**እንኳን ለ2014 አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ!**

ይሄን አዲስ ዓመት የምናከብረው በወሳኝ አገራዊ ፈተናና ተስፋ መካከል ሆነን ነው። ኢትዮጵያ በፈተና እና ተስፋ መካከል ሆና አዲስ ዓመት ስታከብር ይህ የመጀመሪያዋ አይደለም። ምናልባትም የመጨረሻዋም አይሆንም። ኢትዮጵያዊያን ፈተና የማያስበረግገን፣ ድልም የማያስክረን ስለመሆናችን ዓለም ሁሉ ያውቃል። ፈተናን ወደ ዕድል በመቀየር ታሪክ ከሚዘክራቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ አቅሙም፤ አቋሙም አለን።

ኢትዮጵያን የሚፈትኗት እርሷነቷን የማያውቋት ናቸው። ኢትዮጵያ "ለሺህ ዓመታት በነጻነት ኖራለች" ሲባል ትርጉሙን አይረዱትም ማለት ነው። ሺህ ዘመን በነጻነት የኖረችው ጠላት አጥታ አይደለም። የነጻነት ቀንዲሏ ሳይጠፋ እስከ ዛሬ የቆየችው ፈተና ረስቷት አይደለም። ከከፍታዋ ያልወረደችው ኃያላን ራርተውላት አይደለም። ሁሉንም እንደ አመጣጣቸው አሸንፋ ብቻ ነው።

ታሪካችንን ሳያውቁ የሚገጥሙንን ታሪካችንን አውቀን እንጠብቃቸዋለን። ለወዳጃችን ወተት፣ ለጠላታችን እሬት መስጠት እንችልበታለን። ከቶም "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም ከማሸነፍ እንጂ ከመሸነፍ ጋራ ተጠርቶ አያውቅም። ከነጻነት እንጂ ከባርነት ጋራ ዝምድና የለውም። ኢትዮጵያ ተፈትና ታውቃለች። ተሸንፋ ግን አታውቅም። ቀጥና ታውቃለች፤ ተበጥሳ ግን አታውቅም። የዘመመች መስላ ታውቃለች፤ ወድቃ ግን አታውቅም።

ይህ አዲሱ ዓመት ለ30 ዓመታት ኢትዮጵያን የተጣባትን ፈተና የምንገላገልበት፣ አዲስ መንግሥት የምንመሠርትበት፣ ከደረሰብን ፈተና የምናገግምበትና ፊታችንን ወደ ኢትዮጵያ ብልጽግና የምናዞርበት እንደሚሆን እምነቴ ነው። አዲሱ ዓመት ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን የሚጸናበት፣ ዴሞክራሲያዊ እሴቶቻችን የሚጎለብቱበት፣ የጀመርነው ሪፎርም መልክ የሚይዝበት እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

ፈተናችን ከኋላ፣ ተስፋችን ከፊት ነው። በአገር ፍቅር የነደደ፣ በማንነቱ የሚኮራ፣ አካባቢያዊ ማንነቱ ከአገራዊ ማንነቱ ጋር የተስማማለት፤ አዳዲስ ፈጠራዎችን መሞከር የማይታክተው፤ ባልተሄደበት ለመጓዝ ድፍረትና ጽናት ያለው፣ ጋራ ሸንተረሩን በደንና በምርት ለመሸፈን የሚተጋ፣ አዲስ ትውልድ እየተፈጠረ ነው። ኢትዮጵያ በልጆቿ ተስፋዋን ሰንቃለች።

ለአገራችንም ሆነ ለግል ሕይወታችን አዲስ ዓመት አዲስ ነገር ይዞ የሚመጣው ለአዲስ ለውጥ ራሳችንን ባዘጋጀንበት ልክ፣ ለመለወጥ ባለን መሻትና እርሱን ለማሟላት በምናሳየው ትጋት መጠን ነው። ለውጥን ከራሳችን ሳንጀምር የአገራችንን መለወጥ የምንናፍቅ ከሆነ ዘመኑ

እንጂ እኛ አልተቀየርንም። በአገር ጉዳይ ጣት ከመጠቆም ይልቅ “ከእኔስ ምን ይጠበቃል?” ማለት ካልጀመርን ዘመኑ አዲስ ቢሆንም እኛ አሮጌው ላይ ቆመን ቀርተናል።

እንደ አገር ወደ አዲሱ ዘመን የምናደርገው ሽግግር የሚጎዱንን አሮጌ ማንነቶች በመጣልና በአዲስ ጠቃሚ ማንነቶች በመተካት መሆን አለበት። በየግላችን ከምናደርገው ሩጫ ይልቅ ለጋራ ራዕይ ከተጋን፣ እርስ በእርስ መጓተቱን ትተን ለመተባበር ከቆረጥን፣ ጥላቻን ንቀን ፍቅርን ካነገስን ያኔ ለአገራችን አዲስ ዘመን ይመጣል።

አዲስ ዓመት ተፈጥሯዊ ነው። አዲስ ዓመትን ሰዋዊ ማድረግ የሚቻለው እኛ በአዲስ ጎዳና ከተጓዝን ነው። ምንጊዜም ያለፈው መነሻችን ነው። የዛሬው መጓዣችን ነው። የነገው ደግሞ መድረሻችን። ትናንት የተጓዝንበትን መንገድ እንደ አዞ አናጠፋውም። እንደ ፍየል ቀንድም ትናንትን ብቻ እያየን አንኖርም። ዛሬ ትልቁ ሀብታችን ነው። ዓመትን አዲስ ማድረግ የሚቻለው ዛሬን በመጠቀም ነው። የ2013 ዓ.ም የመጨረሻው ገጽ ጳጉሜን 5 ቀን ተጠናቅቋል። መቼም አይመለስም። የ2014 ዓ.ም አዲሱ ገጽ መስከረም 1 ይገለጣል። ማንም ምንም አልጻፈበትም። አዲሱ ዓመት ሁለት ነገሮችን ለመቀበል ዝግጁ ነው። በባዶው ገጽ ላይ የሚጽፍ ጀግናና የሚጻፍበት ታሪክ ነው። እኛ ዝም ብንል፣ ሌሎች የእኛን ነገር በፈለጉት መንገድ ይጽፉበታል። በሌላ በኩል ደገሞ ባንጽፍም የእኛ ያልሆነ ነገር ይጻፍበታል።

አሁን ቁልፉ ጥያቄ አንድ ነው። በዚህ ለሁሉም ባዶ ሆኖ በቀረበው አዲሱ የዘመን መጽሐፍ ላይ እኛው ኢትዮጵያውያን የራሳችንን ዕጣ ፈንታ እንጽፋለን ወይስ ሌሎች እንዲጽፉልን አሳልፈን መጽሐፉን እንሰጣለን? አባቶቻችን የራሳችንን የዘመን አቆጣጠር ሲፈጥሩ የራሳችንን የዘመን መጽሐፍ እንድናዘጋጅና ዕጣ ፈንታችንን ራሳችን እንድንጽፍ ያሰቡ ይመስለኛል። እኛው አቅደን፣ እኛው ሠርተን፣ እኛው ችግሮቻችንን ፈትተን፣ እኛው ተነጋግረን፣ እኛው ተወያይተን፣ እኛው ዘምተን፣ እኛው አሸንፈን፣ እኛው አልምተን፣ እኛው ተጠቅመን፣ እኛው አምርተን፣ እኛው ረሐብን አሸንፈን - የእኛኑ ጉዳይ እኛው እንድንወስን ይመስለኛል። በአዲሱ መጽሐፍ ላይ መጻፍ ብቻ ሳይሆን መጽሐፉን ራሳችን እንድናዘጋጅ ያሰቡ ይመስለኛል። በራሳችን ቁሳቁስ፣ በራሳችን ፈጠራ፣ በራሳችን መንገድ የራሳችንን የዘመን መጽሐፍ፣ ለእኛው በሚስማማ መንገድ፣ እኛው እንድናዘጋጀው ያሰቡም ይመስለኛል።

የዘመን መጽሐፍ የፈጠርን ሰዎች በመጽሐፉ ላይ በራሳችን መንገድ የራሳችን ዕጣ ፈንታ በእጃችን ለማሳረፍ የሚያቅተን ነገር የለም። እንቅፋቶቻችን እየተወገዱ ነው፤ ወደረኞቻችን ሁሉ ድል እየሆኑ ነው። ዘመኑ የኢትዮጵያ ነው። አዲሱ ዓመት የአዲሲቱ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ በአዲሱ የዘመን መጽሐፍ ላይ አዲሱን የብልጽግና ጉዞዋን ትጽፍበታለች። ድሏንና አሸናፊነቷን ትጽፍበታለች። ክብሯንና ታላቅነቷን ትጽፍበታለች።

አገራችን ብልጽግናና ድሎቿን ለመጻፍ ስትነሳ መጻፊያ ብዕሯ እኛ ነን፡፡ ቀለሙም የሚቀዳው ከላብና ከደማችን ነው፡፡ ዜጎች ተደጋግፈው በጋራ ለማደግ ሲነሱ ኢትዮጵያ የጨበጠችው ብዕር በአግባቡ መሥራት ይጀምራል፡፡ ዜጎች እርስ በእርስ ሲተሳሰቡ ብዕሩ ትርጉም ያለው

ገድል ይጽፋል፡፡ የአገር ልጆች ልዩነታቸውን ጠብቀው በጋራ ጉዳይ አብረው መቆም ሲችሉ ያኔ ብዕሩ ድልን አድምቆ ይጽፋል።

በድጋሚ መልካም አዲስ ዓመት፣ ዘመኑ አዳዲስ ስኬቶችን የምናስመዘግብበት ይሁን!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
መስከረም 1፣ 2014 ዓ.ም

## የሤረኞች ምንቸት ወጥቶ፣ የኢትዮጵያዊነት ምንቸት እየገባ ነው

**እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ!**

ስለ መስቀል በዓል ስናነሣ አንድ መታሰብ ያለበት ጉዳይ አለ። ከፈተና በኋላ ድል፣ ከጨለማ በኋላ ብርሃን፣ ከመውደቅ በኋላ መነሣት እንደሚኖር የታወቀ እውነት ነው። የጠፋ ሁሉ ጠፍቶ እንደማይቀር፤ የመስቀሉ ታሪክ ያስተምረናል።

ባለፉት ሦስት አስርት ዓመታት የኢትዮጵያዊነት ስሜት ከልባችን ላይ እንዲፋቅና ስለ አገር ያለን ፍቅር ከውስጣችን እንዲጠፋ በብዙ መልኩ ሤራ ተሠርቷል። እርስ በእርስ በጥርጣሬ እንድንተያይ ብዙ ተንኮል ተጎንጉኗል። በደስታም ሆነ በሐዘናችን፣ በድልም ሆነ በችግራችን አንድነትና ኅብረታችንን እንዳናስቀድም ተደርገናል። ምኞትና ፍላጎታችን በክልልና በብሔር ዙሪያ ብቻ ታጥሮ ትልቁን አገራዊ ምስል እንዳናስተውል ተሞክሯል። ሳይወዷት የመሯት ጠላቶቿ፣ ኢትዮጵያ በትንሽ በትንሹ እየፈረሰች እንደሆነ እያሰቡ ይደሰቱ ነበር።

"አሁን ያለችው ኢትዮጵያ እኛ ብቻ እንድናስተዳድራት የተሠራች ናት፤ እኛ እስከፈቀድን ድረስ የምትኖር፣ በሌላ እጅ ከገባች በቀላሉ የምትፈርስ ናት" እያሉ በእብሪት አፋቸውን ሞልተው ይናገሩ ነበር። ሕዝባዊ አንድነታችን ላልቶ እንደተበጠሰና እነርሱ በፈለጉ ጊዜ አገራችንን በቀላሉ ሊያፈርሷት እንደሚችሉ ደጋግመው ዝተዋል። ዳሩ ግን ሁሉም ነገር እንደተናገሩት አልሆነም። ኢትዮጵያዊነት እንደ ክርስቲያኖች መስቀል የመለያየት አፈር የተጫነው ቢመስልም አልጠፋም። አንድነታችን የሰለለ ቢመስልም አልተበጠሰም። ለአገር ያለን ቀናዒነት የተዳፈነ ቢመስልም አልቀዘቀዘም።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በክርስቲያኖች ዘንድ የፈውስና የኃይል ምንጭ ተደርጎ ይታመናል። ለሕመማቸው ፈውስን፣ በመከራቸው ጊዜ ጽናትን፣ በተሰበሩ ጊዜ ብርታትን፣ በተበታተኑ ጊዜ ኅብረትን አምጥቶላቸዋል። ይኽ ሁኔታ ያላስደሰታቸው የዚያን ዘመን ጨቋኞች ሤራ ሲያስቡ ዋና ትኩረታቸውን ያደረጉት የመስቀሉን ደብዛ ለማጥፋት ነበር። ከሰው ደብቀው ቀበሩት። ቦታውንም የቆሻሻ መጣያ እንዲሆን አዘዙ። ለ300 ዓመታት ከየነዋሪው ቤትና ከየሰዉ ግቢ ተጠርጎ የሚወጣ ቆሻሻ እየተጣለበት ቆይቶ ግዙፍ ተራሮችን መሰለ። ነገር ግን ከፉዎች እንዲህ ለክፋት መትጋታቸው በመስቀሉ ቤዛነት የሚያምኑትን አላሸነፈም። ተራራ ንደው፣ ቁልሉን ደርምሰው፣ አፈራውን ጠርገው፣ መስቀሉን ከማግኘት አላገዳቸውም።

ባሳለፍነው ዓመት አሸባሪው ጁንታና የኢትዮጵያ ጠላቶች በሐሰት ፕሮፓጋንዳቸው የአገራችንን ስም ሊቀብሩ ተባብረው ሲሠሩ ነበር። በውሸት የተቀመሙ ዜናዎቻቸውን በሚያሠራጩባቸው በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ያልተፈጠረውን "ተፈጠረ"፣ ያልሆነውን "ሆነ" እያሉ፣ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያ ቀና ብላ እንዳትታይ አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ አድርገዋል። ዓላማቸው ግልጽ ነው። የእነርሱ ጥቅም የሚከበረው በእኛ መሸነፍ ውስጥ እንደሆነ ያውቃሉ። በውንጀላዎቻቸው ተሸንፈን ጉልበታችን ሲብረከረክ በቀላሉ እጅ እንሰጣለን፤ ለእኩይ ፍላጎታቸው ተገዥ እንሆናለን ብለው አስበዋል። በተሸናፊነት ሥነ ልቡና ውስጥ ገብተን ዳግም በእግራችን መቆም ካልቻልን፣ ያኔ እስከመጨረሻው የእነርሱ ጥቅም ባሪያዎች ሆነን እንደምንቀር ጠንቅቀው ያውቃሉ። ስለዚህም የቻሉትን ያህል የውሸት ቆሻሻ ሰብስበው፣ የእኛን እውነት የሚጋርድ ግዙፍ ተራራ መፍጠር ችለዋል። መስቀሉን አርቀው የቀበሩ ሰዎች መስቀሉ ለዘላለም እንደተቀበረ የሚቀር መስሏቸው ነበር። መስቀሉ አፈር ተጭኖት ስለተከለለ ትውስታው ከምድረ ገጽ እንደሚሰረዝ፣ እምነቱ ከክርስቲያኖች ልብ ተፍቆ እንደሚጠፋ አስበዋል። ነገር ግን ሀሳባቸው እውነት የመሰለው እንደ ንግሥት እሌኒ ያሉ ብርቱዎች መስቀሉን ለመፈለግ እስኪነሡ ድረስ ብቻ ነው። የእነርሱ ዓላማ ስኬት የተመሠረተው በሌሎች ስንፍና ላይ በመሆኑ፣ ብርቱ ፈላጊዎች ቆርጠው በተነሡ ጊዜ፣ የመስቀሉ መጥፋት ጉዳይ ያከትምለት ጀመር። "ጠፋ፤ጠፋ" የሚለው ዜና "ተገኘ" በሚለው ተተካ። እንደተተካም ቀረ።

ንግሥት እሌኒ መስቀሉን ለመፈለግ በተነሣች ጊዜ፣ ነገር ሁሉ አልጋ በአልጋ ሆኖ አልጠበቃትም። መስቀሉ ስለመቀበሩ እንጂ የት እንደተቀበረ እንኳን አታውቅም። በዙሪያዋ የነበሩ ሰዎችም መንገድ ከመጠቆም ይልቅ ተስፋ በማስቆረጥ የተጠመዱ ነበሩ። የመስቀሉ ጉዳይ ያበቃ ያከተመለት መሆኑን ነበር የሚነግሯት። እርሷ ግን እጇን አጣጥፋ ከመቀመጥ ይልቅ እምነትና ተስፋዋን ይዛ በመፈለጉ ጸናች። ተስፋ አስቆራጮች የሚናገሩትን ትታ እምነት የጣለችበትን የዕጣን ጢስ ተከተለች። ተከትላም አልቀረች። ጢሱም መስቀሉ የተቀበረበትን ትክክለኛ ቦታ መጠቆም ብቻ ሳይሆን፣ ከብዙ ድካምና ልፋት ታደጋት። የዕጣኑ ጢስ ወደ እውነተኛው ቦታ የሚያደርስ ምልክት ሆናት።

ለዘመናት በሤረኞች ተንኮል ደብዝዞ የጠፋ የመሰለው አንድነትና ኢትዮጵያዊነታችን ወደ ቦታው እየተመለሰ ነው። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ይህን የሚጠቁሙ ምልክቶች መታየት ጀምረዋል። እንደ እሌኒ ያሉ ጀግኖች፣ ሤረኞች የቀበሩት የመሰላቸውን ኢትዮጵያዊነት እያወጡት ነው። ከመላ ኢትዮጵያ፣ አያሌ እሌኒዎች መጥተው ታሪክ እየሠሩ ነው። ድሮ በክልሎች መካከል የነበሩ መሥመር የሳቱ ፉክክሮች አሁን በትብብር ተለውጠዋል። "አትምጣብኝ አልምጣብህ" የሚሉ ክፉ ንግግሮች "ለችግርህ ደራሽ እኔ ነኝ" በሚል

ተተክተዋል። በየጓዳችን ተወሽቀን ስለ ጓዳችን ብቻ አብዝተን መጨነቃችን ቀርቶ ዛሬ አገራዊ ጥቅማችንን ላለማስነካት በዓለም ፊት በአንድ ድምፅ መናገር ጀምረናል። አሁን ኢትዮጵያዊ ማንነታችን በእርግጥም በደማችን ውስጥ ስለመኖሩ በግልጽ ይታያል። ህብርነታችን መለያያችን ሳይሆን የአንድነት ጌጣችን መሆኑን እንደ መስቀሉ ከፍ አድርገን አሳይተናል። አሁን ኢትዮጵያ በየተሠማሩበት መስክ ሉዓላዊነቷን ላለማስደፈር የሚባትሉ ልጆቿ ጥቂቶች አለመሆናቸውን እያየች ነው። ከጠላት ጋር አብረው ከጀርባ የሚወጓት ክፉ ልጆችዋ ዕለት በዕለት ቀን ሲጨልምባቸው፣ ወደ አመድነት ሲለወጡ፤ በተቃራኒው ለክብሯ ለሚጨነቁ ደጋግ ልጆችዋ ፈተናው እየቀለለ፣ የድል ውጋጋን በመታየት ላይ ነው። የጨለማው ጊዜ ተወግዶ ብርሃኑን፣ የፈተና ጊዜ አልፎ ድሉን የምናይበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አልጠራጠርም። የሤረኞች ምንቸት ወጥቶ፣ የኢትዮጵያዊነት ምንቸት እየገባ ነው።

የመስቀልን በዓል ስናከብር ግዛታዊ አንድነታችንን ለማስጠበቅ በዱር በገደሉ የሚወድቁ እህቶቻችንንና ወንድሞቻችንን እያሰብን መሆን አለበት። እነርሱ እንደ ደመራው አንድ ሆነው ለኢትዮጵያ የሚሠዉ ህያዋን ችቦዎች ናቸው። ዛሬ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ተጠብቆ ያለው እነርሱ በሚከሰክሱት አጥንትና በሚያፈሱት ደም ነው። በተመሳሳይ በጁንታው ጥቃት የተጎዱ ዜጎቻችንን "አለሁ" ልንላቸው፣ ከጎናቸው ልንቆም ይገባል። የከፈሉት ዋጋ ለኢትዮጵያ የተከፈለ ዋጋ ነው። የታመሙት የሁላችንን ሕመም ነው። ከቤት ከቀያቸው የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን መልሶ የማቋቋም፣ የፈረሱ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመገንባት እንገደድ ይሆናል። ጥርሳችንን ነክሰንና አንጀታችንን አሥረን እንጋፈጥ፤ ቤቶችን የመገንባትና የወደሙ ጤና ተቋማትን በምትካቸው የመሥራት ኃላፊነት በእያንዳንዳችን ትከሻ ላይ የወደቀ ነው። ከአሁኑ ይሄንን አውቀን ወገባችንን አሥረን መነሣት አለብን። "ካላነበሳችሁ አንረዳችሁም" የሚሉ ወገኖች ይኖሩ ይሆናል። ለኢትዮጵያ ሲባል ሀሞትና ከርቤ እንጠጣለን። ተጋፍጠንም እናሸንፈዋለን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
መስከረም 15፣ 2014 ዓ.ም

# የኢሬቻ አስተምህሮት - በዕርቅ፣ በይቅርታና በሰላም መሻገር

**እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!**

የኦሮሞ ሕዝብ ፍቅር፣ ወንድማማችነትንና ዕርቅን በሚገነቡ ባህላዊ እሴቶች እጅጉን የበለጸገ ሕዝብ ነው፡፡ ከእነዚህ ድንቅ ባህላዊ እሴቶች መካከል አንዱ የኢሬቻ በዓል ነው፡፡ ይህን ትልቅ ባህላዊ ዕሴት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ለአገራችን ኢትዮጵያ ያበረከቱ ቀደምት አባቶቻችን ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ኢሬቻ - የምስጋና፣ የዕርቅና የሰላም በዓል ነው፡፡ የፍቅር፣ የይቅርታና የአንድነት በዓል ነው፡፡ ኢሬቻ መጪው ጊዜ ብሩህ እንዲሆን ቃል የምንገባበት በዓል ነው፡፡ ሁሉን አስተካክሎና ውብ አድርጎ የፈጠረ ፈጣሪ የሚመሰገንበት፣ ቀጣዩ ጊዜ ብሩህ እንዲሆን ዓመት አሳልፎ ለዚህ ያደረሰንን ፈጣሪ የማመስገኛ መልካም ምኞት የሚቀርብበት በዓል ነው፡፡

ኢሬቻ- ትናንትን የማመስገኛና ነገን ሰላም የማድረጊያ በዓል ነው፡፡ ያለፈውንና ቀጣዩን ዓመት በመልካም ምኞትና በመልካም ተግባር የመጀመሪያ በዓል ነው፡፡ ሰው በዋናነት የሚኖረው ከተፈጥሮ ጋርና በተፈጥሮ ውስጥ ነው፡፡ የተፈጥሮ ጤና መሆን የሰው ልጅን ጤና ይወስነዋል፡፡ የተፈጥሮ መበላሸትም የሰው ልጅን ሥጋት ይጨምረዋል፡፡ ለዚህ ነው ቀደምቶቻችን ለተፈጥሮ ዋጋ የሚሰጠውን የኢሬቻን በዓል እንድናከብረው የሠሩልን፡፡

የክረምቱ ወቅት የምግብ እጥረትና የመገናኛ ችግር የሚከሠትበት ወቅት ነው፡፡ ወባን የመሳሰሉ ወረርሽኞች የሚያይሉበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ የችግር ወቅት ተደርጎ፣ በጨለማ ተመስሎ ይወሰድ ነበር፡፡ ወንዞች በመሙላታቸው ምክንያት መገናኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ከላይ ዝናቡ፣ ከታች ጭቃው ኑሮን ከባድ ያደርገዋል፡፡ በጥር አካባቢ የተሰበሰበው ምርት በክረምት ወቅት ስለሚያልቅ፣ ክረምቱ በቂ ምግብ የሚገኝበት አይደለም፡፡

ይህ ወቅት የሚያልፈው ፈታኙን ጊዜ በጠንካራ ትግል በመገዳደር ነው፡፡ በአንድ በኩል ለወቅቱ የሚሆነውን ሰብል በማምረት፣ በሌላ በኩል ለዘለቄታው የሚበጀውን እህል በማረስ ነው - መከራው የሚሸነፈው፡፡ በቆሎ፣ ገብስና ድንችን የመሳሰሉ ሰብሎችን ለክረምቱ እንዲደርሱለት አድርጎ ገበሬው ይዘራል፡፡ ሌሎቹን ደግሞ ለዓመት ጉርስ እንዲሆኑት

ያመርታቸዋል፡፡ ጤናን አጥብቆ በመጠበቅ ነው ወረርሽኙን የሚቋቋመው፡፡
ኢሬቻ- በንጹሕ ሕሊናና አስተሳሰብ በፍጹም ደስታ የሚከበር በዓል ነው፡፡ በባህሉ መሠረት ወደ ኢሬቻ በዓል ከመገባቱ በፊት የተጣላ ታርቆ፣ ቂምና ጥላቻ በይቅርታና ፍቅር ታክሞ፣ ለሰው ልጆች ሁሉ መልካም ምኞትን በመግለጽ በታላቅ አንድነትና ህብረት ይከበራል፡፡ በዓሉ የምስጋናና የአንድነት በዓል በመሆኑ በኦሮሞ ሕዝብ ብቻ የሚከበር አይደለም፡፡ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የኢሬቻን መሠረታዊ ዕሴቶች የሚጋሩ በመሆናቸው በበዓሉ ላይ በባህላዊ አልባሶቻቸው ተውበው፣ እያዜሙና እየጨፈሩ የሚያደምቁት፣ ኢሬቻ የኢትዮጵያን አንድነት የሚያስተሣሥር አንዱ ጠንካራ ሐረግ መሆኑን በተግባር የሚያሳዩበት ዕለት ነው፡፡ ስለሆነም በዓሉ የመላው ኢትዮጵያውያን በዓል ነው፡፡

ኢሬቻ- የመሻገር በዓል ነው፡፡ በጨለማ ከሚመሰለው ክረምት ወደ ብርሃናማው መጸው፣ ከጥላቻ ወደ ፍቅር፣ ከጠላትነት ወደ ወንድማማችነት፣ ከጸብ ወደ ዕርቅ፣ ከቂም በቀል ወደ ይቅርታ ከክፋት ወደ መልካምነት ሽግግር የሚደረግበት በዓል ነው፡፡
